
# መንፈሳዊ



# ውጊያ

ከዶ/ር መለሰ ወጉ

# ማውጫ


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| | መግቢያ | 7 |
| ምዕራፍ 1 | ሰይጣንን ማሸነፊያ አቋራጭ መንገድ የለም | 9 |
| ምዕራፍ 2 | የሰይጣን ማንነቱና የአፈጣጠሩ ታሪክ | 25 |
| ምዕራፍ 3 | የሰይጣን እንቅስቃሴውና አሠራሩ | 36 |
| ምዕራፍ 4 | የአማኝ ጠላቶቹና የሚያደርሱበት ጥቃት | 50 |
| ምዕራፍ 5 | ርኩሳን መናፍስት በአማኞች ላይ ያላቸው ሥልጣንና ኃይል | 68 |
| ምዕራፍ 6 | የሰው አዕምሮ ማዕከላዊ የጦር ሜዳ ነው | 79 |
| ምዕራፍ 7 | ሰይጣንን የምናሸንፍበትን ዘዴ እንወቅ | 89 |
| ምዕራፍ 8 | ሰይጣንን ፊት ለፊት እንቃወመው እንጂ እንሸሸው | 109 |
| ምዕራፍ 9 | የጦር መሣሪያ ሳንለብስ ሰይጣንን መዋጋት አንችልም | 119 |

# መንፈሳዊ



# ውጊያ

ከዶ/ር መለሰ ወጉ

መንፈሳዊ ውጊያ
"Mënfësawi Wugia"
"SPIRITUAL WARFARE"

የመጀመሪያ እትም መስከረም ፲፱፻፹፱ ዓ.ም.
First Edition, September 1997

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከመጀመሪያውና ከሁለተኛው እትም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች ነው።

ይህን መጽሐፍ በከፊልም ይሁን በሙሉ በማንኛውም ዓይነት መንገድ ለማባዛት በቅድሚያ ከኢትዮያውያን የወንጌል አገልግሎትዋና ጽሕፈት ቤት የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።

Copyright 1997 © by Ethiopian Outreach Ministry

All rights reserved No part of this book may be reproduced in any manner without written permission from Ethioian outreach Ministry except in the case of brief quotations in critical articles and reviews

Produced by:

Ethiopian Outreach Ministry
P.O.BOX 2241
YORK, PA 17405
United States of America

Ethiopia Office address:
P.O.Box 7888, Addis Ababa, Ethiopia
Tel: 011 156 42 68
1999 E.C.

KALU PRINTING PRESS

ዲያብሎስን ተቃወሙ፥
ከእናንተም ይሸሻል።
ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ፥
ወደ እናንተም ይቀርባል።

ያዕቆብ 4:7-8

# ማውጫ


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| | መግቢያ | 7 |
| ምዕራፍ 1 | ሰይጣንን ማሸነፊያ አቋራጭ መንገድ የለም | 9 |
| ምዕራፍ 2 | የሰይጣን ማንነቱና የአፈጣጠሩ ታሪክ | 25 |
| ምዕራፍ 3 | የሰይጣን እንቅስቃሴውና አሠራሩ | 36 |
| ምዕራፍ 4 | የአማኝ ጠላቶቹና የሚያደርሱበት ጥቃት | 50 |
| ምዕራፍ 5 | ርኩሳን መናፍስት በአማኞች ላይ ያላቸው ሥልጣንና ኃይል | 68 |
| ምዕራፍ 6 | የሰው አዕምሮ ማዕከላዊ የጦር ሜዳ ነው | 79 |
| ምዕራፍ 7 | ሰይጣንን የምናሸንፍበትን ዘዴ እንወቅ | 89 |
| ምዕራፍ 8 | ሰይጣንን ፊት ለፊት እንቃወመው እንጂ አንሸሸው | 109 |
| ምዕራፍ 9 | የጦር መሣሪያ ሳንለብስ ሰይጣንን መዋጋት አንችልም | 119 |

# መግቢያ

መጠኑ ይለያይ እንጂ ሁሉም የራሱ የሆነ የሕይወት ትግል አለው። አንዳንዱ በገንዘብ እጥረት ምክንያት ከሚችለው በላይ በመወጠር፣ ሌላው ደግሞ መራራ የሆነ ትዳር አጋጥሞት ነፍሱ ከስጋው ልትለይ እስከትደርስ ድረስ በመጨነቅ ዘወትር በዕንባ ሸለቆ ውስጥ የሚያልፍ አለ። አንዳንዱ ደግሞ በዕለታዊ ሥራው ላይ የማይመች አለቃ አጋጥሞት በብስጭት ምክንያት ጨጓራው ተልጦ ዘወትር እየደማ የሚኖር አለ። ከላይ በገለጽናቸው ችግሮችና ዕንቅፋቶች ውስጥ የሚያልፍ አማኝ «መንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ነኝ» ማለት ይችል ይሆን? ስርቆት፣ ዝሙትና መዳራት በርኩሳን መናፍስት አማካኝነት ያለአማኙ ፈቃድና ፍላጎት ወደ ሕይወቱ ሊገቡ ይችላሉ? ከሆነስ፣ እነዚህን ኃጢአቶች ገስጾ ከውስጡ በማስወጣት አማኙን ከማንኛውም ትግል ፍጹም ነጻ ማድረግ ይቻላል? «መንፈሳዊ ውጊያ» ማለት ሁልጊዜ ከሰው ሕይወት አጋንንትን ገስጾ ማስወጣት ብቻ ይሆን? ለመሆኑ «መንፈሳዊ ውጊያ» ማለት ምን ማለት ነው? በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከላይ ለጠየቅናቸው ጥያቄዎች መልስ ይሆናሉ ብለን ያመንባቸውን የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት በማድረግ በመጠኑም ቢሆን አንዳንድ ጠቃሚ ሀሳቦችን ለመስጠት ሞክረናል።

መንፈሳዊ ውጊያ ተረት ሳይሆን፣ ማንኛውም ክርስቲያን በግል ሕይወቱ ሊደርስበት የሚችል ልምምድ ነው። አማኝ ከማይታየው ጠላቱ ጋር ፊት ለፊት የሚገጥመው ረቂቅ የሆነ መንፈሳዊ ውጊያ አለበት። ሁሉም የራሱ የሆነ «መንፈሳዊ ውጊያ» ይኑረው እንጂ፣ የውጊያው ውጤት የሁሉም አንድ ዓይነት አይደለም። አንዳንዱ ጦርነቱ ሲፋፋምበትና መንገዱ ሲጠብበት፣ እጆቹን ወደ ሰማይ ዘርግቶ ሰይጣንን «ተማርኬአለሁ! ተሸንፌአለሁ» ይለዋል። ሌላው ደግሞ ጦርነቱ ሲያይልበት እንደ ዳዊት *«ልቤ በላዬ ተናወጠብኝ፤ የሞት ድንጋጤም ወደቀብኝ፤ ፍርሃትና እንቅጥቅጥ መጡብኝ፤ ጨለማም ሸፈነኝ። በርሬ አርፍ ዘንድ እንደ ርግብ ክንፍን ማን በሰጠኝ»* (መዝሙር 55:4-6) በማለት ዕርዳታ በመፈለግ ወድ አምላኩ ይጮሃል።

የብዙዎቻችን ትልቁ ችግር፣ ጠላታችን ማን እንደሆነ ለይተን አለማወቃችን ነው። ጠላታችን ማን እንደሆነ በደንብ ካላወቅን፣ ብዙ ጊዜ ከእግዚአብሔር ወይንም ከሰው ጋር ያለአግባብ የምንጋጭ መሆናችን ብቻ ሳይሆን፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችንም ተሸናፊዎች እንጂ አሸናፊዎች ሆነን መቆም አንችልም። ጠላታችንን የማናውቅበትም ዋናው ምክንያት ሰይጣን ራሱን የመደበቅ ችሎታ ስላለው ነው። ጠላታቸው ሰይጣን መሆኑን የተረዱትም አንዳንድ አማኞች፣ የሰይጣን አሠራርና እንቅስቃሴው ምን እንደሆነና፣ እንዲሁም ከእርሱ ጋር በምን ዓይነት

ሁኔታ መዋጋት እንዳለባቸው በቂ መረዳት ስለሌላቸው፣ «የተሸነፈ» የክርስትና ሕይወት ሲኖሩ ይታያሉ። ይህ ጠላት ኃይለኛ በመሆኑ፣ አማኝ ብቻውን ሊያሸንፈው አይችልም። ይህንን ያልተረዱ አንዳንድ ክርስቲያኖች የሚያጋጥማቸውን «መንፈሳዊ ጦርነት» ብቻቸውን ተዋግተው ለማሸነፍ ሲሞክሩ፣ በጦር ሜዳ ብዙ መላላጥና ከፍተኛ ሽንፈት የደረሰባቸው እንዳሉ እናውቃለን። ጠላታችን ኃይለኛም ቢሆን፣ የምናሸንፈው፡ ፊት ለፊት ገጥመን በመዋጋት እንጂ በመሸሽ ብቻ እንዳልሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። "ሰይጣንን ተቋቋሙት፤ ከእናንተም ይሸሻል" (ያዕቆብ 4:7)።

«መንፈሳዊ ውጊያ» ለብዙዎች አዲስ አይደለም። ይሁን እንጂ ውጊያው የሚካሄደው በያንዳንዱ ሰው አዕምሮ ውስጥ መሆኑን ብዙዎች የተረዱት አይመስልም። በዚህ ምክንያት በቀላሉ ሲታለሉና በተደጋጋሚ ሲወድቁ ይታያሉ። ብዙዎች «አሸናፊ ሕይወት» ለመኖር፣ በየቀኑ በሚያጋጥማቸው «መንፈሳዊ ውጊያ» ላይ ጠላታቸውን ማሸነፍ እንዳለባቸው ቢረዱም፣ በምን ዓይነት ሁኔታ ተዋግተው ማሸነፍ እንዳለባቸው ግን አያውቁም። ይህን መጽሐፍ አዘጋጅተን ያቀረብነው፣ ስለ "መንፈሳዊ ውጊያ" ለሚነሱት ጥያቄዎች ሁሉ ሙሉ መልስ ይሰጣል ብለን ሳይሆን፣ አሸናፊ የክርስትና ሕይወት ለመኖር ከፍተኛ ጥረት ለሚያደርጉ አማኞች መጠነኛም ቢሆን፣ ጠቃሚ መንፈሳዊ መመሪያና ምክር ይሰጣል ብለን በማመን ነው።

# 1

# ሰይጣንን ማሸነፊያ አቋራጭ መንገድ የለም

በሕይወታቸው በብዙ ዓይነት ትግልና ፈተና ውስጥ የሚያልፉ አንዳንድ ሰዎች በየጊዜው ያጋጥሙናል። በቅርብ ሊያገኙን የሚችሉ ቀርበው የልባቸውን ያፈስሉናል። በርቀት ምክንያት የማይችሉት ደግሞ በስልክ፣ ሌሎች ደግሞ በደብዳቤ ለችግራቸው መፍትሄ እንዲሰን በማለት ችግራቸውንና ጭንቀታቸውን ሳይደብቁ ዘርዝረው ይጽፉልናል። አብዛኛዎቹ ቅድስና የጠማቸው፣ የእግዚአብሔር ክንድ በሕይወታቸው ሲሠራ ለማየት የሚጓጉ፣ በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ውስጥ ብቻ ሕይወታቸው እንዲመራ የሚወዱ፣ አሸናፊ የክርስትና ሕይወት ለመኖር ከፍተኛ ጥማት ያላቸው እውነተኛና የተለወጡ ክርስቲያኖች ናቸው። ይሁን እንጂ በሕይወታቸው ውስጥ ከፍተኛ ትርምስ፣ መጣት፣ ጦርነትና ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ያለማቋረጥ እየፈለቁ የሚጨነቁ ናቸው። ጭንቀት፣ ሽብርና ትግል ሊደርስባቸው የቻለው መንፈሳዊ ሕይወታቸው ቀዝቅዞ፣ ወይንም ከሌሎች ክርስቲያኖች ያነሰ ሕይወት በመኖራቸው አይደለም። የእግዚአብሔር ቃል እንደ ውሃ የሚጠማቸው፣ የክርስቲያኖች ሕብረት የሚናፍቃቸው፣ ጉልበቶቻቸው በጸሎት ምክንያት «ምልክት» ያወጡ ብርቱ የጸሎት አርበኞች ናቸው። ይሁን እንጂ በሕይወታቸው ከፍተኛ ውጊያ ውስጥ ያሉ፣ የማያቋርጥ ጦርነት ያለባቸው በመሆናቸው፣ የሌላውን ሰው ዕርዳታ እንዲፈልጉ አድርጓቸዋል። «ሕይወቴን እንደ እግዚአብሔር ቃልና እንደ ፈቃዱ ለመምራት ከፍተኛ ጥረት አደርጋለሁ፤ ግን አሸናፊ መሆን አላገኘሁ፤ ምክንያቱ ምን ይሆን?» የሚለው፣ ከብዙ ጥያቄዎቻቸው መካከል አንደኛው ነው።

አንዳንዶቹ ለዚህ ጥያቄያቸው ከተለያዩ መንፈሳዊ መሪዎችና አስ ተማሪዎች የሚበቃቸውን ያህል መልስ አግኝተው፥ «አድርጉ» የተባሉ ትን ሁሉ አድርገዋል። ይሁን እንጂ ራሳቸውን አሸናፊዎች ሆነው ባለ ማግኘታቸው፥ ምናልባት ሌላ ተጨማሪ መመሪያና ትምህርት እናገኝ ይሆን? በማለት ነው ጥያቄዎቻቸውን ወደ እኛ የሚልኩት። ይህም መጽሐፍ የተዘጋጀው አንዳንዶቹ ለሚያቀርቡት ጥያቄ ከሞላ ጎደል መልስ ይሰጣል ብለን በማሰብ ነው። ችግራቸውን ወዲያው ሊፈታላ ቸው የሚችል ቀላልና አቋራጭ መልስ ወይንም ሀሳብ መስጠት ብንችል ምን ያህል ደስ ባለን ነበር! ግን አጭርና ቀላል መልስ የለንም። ምናልባት አንዳንዶቹ የጠበቁት ያን ዓይነት መልስ ከሆነ፥ መልሳችን የበለጠ ቅር ሳያሰኛቸው እንዳማይቀር እንገምታለን።

# 1. ሰው ለድካሙ ምክንያት መስጠት ተፈጥሮው ነው

በሕይወታቸው «መልካም ያልሆነ ነገር» ባጋጠማቸው ቁጥር የችግሩ ምክንያት «አጋንንት ነው» ብለው የሚያስቡ አንዳንድ ሰዎች አሉ።

- መኪናቸው መንገድ ላይ ተበላሽቶ ቢቆም፣ ወይንም የመኪና ቸው ጎማ ቢተነፍስ፥ ከመኪናቸው ውስጥ አጋንንንት ለማስወ ጣት የሚሞክሩ አሉ።
- በአንዳንድ ሀሳብ ባለመስማማታቸው ምክንያት በመካከላቸው ግጭት ሲፈጠር፥ ያልተግባቡበትን ነገር ቁጭ ብለው በመወያ የት ለመፍታት በመሞከር ፋንታ፥ እርስ በርሳቸው በመካሰስ "የትዕቢት መንፈስ፣ የቁጣ መንፈስ፣ ራስን የማመጻደቅ መንፈስ" በማለት እየተዊዊሁ አንዱ ከሌላው አጋንንት ለማስወጣት፣ ለመገሰጽና ለማሠር የሚሞክሩም አጋጥመውናል።
- በስሜት ሲከንፉ፥ ሚዛን እንዲኖራቸው የሚመክራቸውን ወይ ንም አስተያየት የሚሰጣቸውን ሰው ደግሞ «እርኩስ መንፈስ በቀጥታ ዐይኑን አፍጥጦ ሲመለከተኝ በውስጤ ያለው መንፈስ ትዳስ ተረበሸና አንተ የትችት አጋንንት በጌታ በኢየሱስ ክርስ ቶስ ስም እሰርሃለሁ! ብዬ በመገሰጽ፥ በዚያ ሰው በኩል ከሚ ዋጋኝ አጋንንት ጌታ በደሙ እንዲሸፍነኝ በውስጤ ጸለይኩ» የሚሉ ሰዎችም አጋጥመውናል።
- የባህርይ ችግር ኖሮባቸው ወይንም በሌላ ምክንያት ከሰው ጋር ተስማምቶ መኖር የማይሆንላቸው አንዳንድ ሰዎች፥ በራሳቸው ሕይወት ያለውን ችግር መርምረው ለማስተካከል በመጣር ፋንታ ከሌላው ሰው ሕይወት አጋንንት ለማስወጣት የሚታገሉ

መናራቸው የታወቀ ነው። በጥላቻና በፍርሃት በመጥላታቸውና እንዲሁም በተዛባ እምነታቸው ምክንያት ግራ ተጋብተው የክርስቶስን ስም ያለአግባብ ሲጠቀሙበት ይታያሉ። በዚህ ዓይነት የክርስቶስ ስም ያለቦታው ሲጠራና ሲረከስ ደስ የሚለውን አጋንንት፣ ፍላጎቱን በማሟላት ደስ ያሰኙታል።

ሰይጣን በተፈጥሮው ተወዳዳሪ የሌለው ልዩ ኃይልና ሥልጣን እንዳለውና ያለምንም ገደብ የፈቀደውን መሥራት እንደሚችል አድርገው የሚያምኑ አሉ። ስለሆነም፣ በሕይወታቸው በአንዳንድ አቅጣጫ ስተው ከመሥመር ሲወጡ፣ «ይህን ያስደረገኝ ሰይጣን ነው» በማለት ምክንያት ይሰጣሉ። ይሄም እምነታቸውን እውነትነት በሌለው መሠረት ላይ የመሠረቱ መሆናቸውን ያሳያል። ውስጣቸው በጠብ ጫሪነት፣ በጥርጣሬና በፍርሃት የተሞላ በመሆኑ በሄዱበት ሥፍራ ሁሉ ከሰው ጋር በሰላም መኖር አይሆንላቸውም። የግል ሕይወታቸውን በመመርመር ፈንታ የችግራቸው ሁሉ ምክንያት ሌሎች ሰዎች ስለሚመስላቸው፣ በየጊዜው ቤተ ክርስቲያን ሲለዋውጡ ይታያሉ። እንዲሁም በሄዱበት ሥፍራ ሁሉ አንዳንድ ከመስመር የወጣ፣ ስሜታቸውን ብቻ ሊቀሰቅስ በሚችል እንግዳ ትምህርትና ልምምድ በቀላሉ ይሳባሉ። በመንፈሳዊ አቋሙ ከእነርሱ ይህን ያህል ያልተሻለ፣ ራሱን «አገልጋይ» ብሎ የሚጠራ፣ በሕይወታቸው ያለባቸውን አንዳንድ ችግር፣ ይኸውም መራራነት፣ ራስ ወዳድነትና እንዲሁም የበታችነትን ስሜት ሲያይ፣ እነዚህን ሁሉ ያመጣባቸው እርኩስ መንፈስ ነው ብሎ ስለሚያምን፣ ያንን መንፈስ ከውስጣቸው ለማስወጣት ሲታገል እናያለን።

## 2. የተሳሳተ የሰዎች እምነት

⇨ በዓለም ላይ ያለው ችግርና ዕንቅፋት ሁሉ የመጣው በእርኩሳን መናፍስት ዕንቅስቃሴ ምክንያት ብቻ ነው ብለው የሚያምኑ አሉ።

⇨ ልዩ ልዩ ችግሮችና ዕንቅፋቶች ይኸውም፣ ጤና ማጣት፣ በገንዘብ ዕጥረት ምክንያት የሚደርሰው የኑሮ ውጥረት፣ ተስማሚ ያልሆነ የሰዎች ጠባይ፣ ወዘተ. ርኩሳን መናፍስት የፈጠሩአቸው ችግሮች ብቻ ናቸው ብለው ያምናሉ።

⇨ የሰዎች የግል ችግር፣ ማለትም ቁጡነታቸው፣ በፍትወት መቃጠላቸው፣ ተስፋ መቁረጣቸው፣ ብቸኝነታቸው፣ እነዚህ ሁሉ በርኩሳን መናፍስት አማካኝነት ወደ ሰዎች ሕይወት የገቡ በመሆናቸው፣ እነዚህ መናፍስት ተገስጸው ከውስጣቸው መውጣት አለባቸው፤ እርኩሳን መናፍስቱ ከወጡ በኋላ ከላይ የዘረዘርናቸው ኃጢአቶች ተመልሰው አይታዩም ብለው ያምናሉ።

⇨ «መንፈሳዊ ውጊያ» ማለት ሁልጊዜ ከሰው ሕይወት አጋንንት ማስወጣት ብቻ የሚመስላቸው አሉ። «በስሜ አጋንንትን ታስወጣላችሁ» የሚለው ተስፋ ለአማኞች ሁሉ የተሰጠ መሆኑን ባለመረዳት፣ አጋንንት ለማስወጣት ልዩ ችሎታ ወይንም ተሰጥኦ የተሰጠው ለእኛ ብቻ ነው» ብለው የሚያምኑ አሉ። የክርስትና ሕይወት ምን እንደሆነና በውስጡ ያለውን ትግል በደንብ ያልተረዱ ክርስቲያኖች፣ አጋንንንት በማስወጣት ተሰጠ አላቸው ብለው ወደሚያምኗቸው ሰዎች ዘንድ ሄደው፤ «የንዴት፣ የፍትወት፣ የቅናት፣ የተስፋ መቁረጥ አጋንንትን» ከውስጣቸው እንዲያስወጡላቸው ይጠይቃሉ። አጋንንት በማስወጣት ተሰጠ አለው ብለው በሚያምኑት ሰው ከተጸለየላቸው በኋላ እነዚህ ከላይ ከዘረዘርናቸው ድክመቶች ሁሉ «ነጻ ወጣሁ» በማለት ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ። ከጥቂት ቀናት በኋላ እነዚህን ድክመቶች እንደ ገና በሕይወታቸው ወስጥ ሲታዩ፤ «እነዚህ ርኩሳን መናፍስት ተመልሰው ወደ ውስጤ ገብተዋል» በማለት እያዘኑ እንደገና ርኩሳን መናፍስቱን ዝስጸው ለማስወጣት ሲታገሉ ይታያሉ።

⇨ ሰይጣንን «በሁለተኛ ደረጃ ያለ፣ ወይንም ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ያለ አምላክ» አድርገው የሚያምኑ ሰዎች አሉ። እግዚአብሔር በሰይጣን ላይ ያለውን ኃይልና ሥልጣን በመርሳት (ባለማወቅ)፣ ሰይጣንን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ኃይል እንዳለው አድርገው የሚገምቱም ሰዎች አሉ። በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር ሰይጣንን ለራሱ ክብር ወይንም ለዓላማው እንደሚጠቀምበት የተረዱ አይመስሉም። ክርስቶስ አሸናፊ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቢያነቡም፣ በግል ሕይወታቸው ውስጥ ግን «ሰይጣንና እግዚአብሔር እኩል የሆነ ኃይል አላቸው» ብለው ስለሚያምኑ፣ ነፍሳቸውን በቁጥጥሩ ሥር እንዲያደርግ ለማን እንደሚሰጡ እርግጠኞች አይደሉም።

⇨ አንዳንድ ሰዎች በተኙበት ወቅት ርኩሳን መናፍስት እነርሱ ሳያውቁ ቀስ ብለው ወደ ሕይወታቸው ተደብቀው የሚገቡ የሚመስላቸው አሉ። በትክክል ካልጠበቁ፣ ኃይል ያለውን ትክክለኛ ቃል ካልተጠቀሙ፤ ትክክለኛውን ዓይነት ጸሎት ካልጸለዩ አጋንንት ወደ ሕይወታቸው ውስጥ የሚገቡና እንዲሁም ለደህንነታቸው ወሳኞቹ እርኩሳን መናፍስት የሆኑ ይመስላቸዋል። ሰይጣን በእግዚአብሔር የተፈጠረና «ደህንነትም» ከጌታ ብቻ የሚገኝ መሆኑን በደንብ የተገነዘቡ አይመስሉም።

⇨ «መንፈሳዊ ውጊያ» የማያስፈልግ፣ ጊዜ ያለፈበት ተረት ብቻ የሚመስላቸው ሰዎች አሉ። ሳይንስ፣ የዘመኑ ቴክኖሎጂ፣ እንዲሁም የሰዎች መልካም አስተሳሰብና ጥረት የዓለምን ሕዝብ በደስታና በሰላም ሊያኖሩት ስለሚችሉ «እግዚአብሔር አያስፈል

ገንም፤ ሰይጣንም ኃይል የለውም» በማለት ተዝናንተው ለመኖር የሚያስቡ አሉ። ይሁን እንጂ እንደ ጠበቁት መልካምና ያማረ፥ እንዲሁም በእውነት ላይ የተመሠረተ ሕብረተሰብ መፍጠር እንደማይቻል ከብዙዎቹ የተሠወረ አይደለም። በዓለም ላይ ያለው የሰው ሕይወት የማያቋርጥ የሞራል ትግል (ግጭት)፥ ይኸውም በክፉና በደግ፤ በእውነትና በሀሰት፤ ትክክል በሆነና ባልሆነ፤ በሕይወትና በሞት፤ በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል የሚካሄድ ጦርነት የበዛበት ዓለም ስለሆነ እንደሚገባው መንፈሳዊ ውጊያችንን መዋጋት ይገባናል።

## 3. መንፈሳዊው ውጊያችን ብርቱ ነው

- ሰይጣን ነፍሳችንን ሊያጠቃ የተነሳ የጋራ ጠላት መሆኑን፥ በረቀቀ ዘዴው በአማኞች መካከል ውሸትን በመንዛት መከፋፈል፥ እርስ በርስ አለመተማመን እንዲኖር የሚያደርግ ዓይነተኛ ጠላት መሆኑን ብዙዎች የተገነዘቡት አይመስልም።

- በዘመናችን ከምንጊዜውም የበለጠ ስለ እግዚአብሔር ግድ የሌላቸው ግለሰቦች ቁጥራቸው እየጨመረ ሲሄድ እናያለን። ሳይንስ የሰውን ልጆች ችግር ሁሉ መፍታት እንደማይችል የተረዱ፥ ወደ ልዩ ልዩ እንግዳ አምልኮት ፊታቸውን ሲመልሱ ይታያሉ። ኮከብ ቆጣሪዎች፤ ሰይጣን አምላኪዎች፤ «የኒው ኤጅ ሙቭመንት» ተከታዮች በተለይ በሰለጠኑ አገሮች ቁጥራቸው እየጨመረ ሲሄድ ይታያል። እነዚህን ሁሉ እግዚአብሔር ስለሚጠላ፥ አማኞች ከእዚህ ጋራ የሚኖራቸው መንፈሳዊ ጦርነት (ውጊያ) ብርቱ እንደሆነ ሊገነዘቡት ይገባል።

- የምንኖርባት ዓለም በልዩ ልዩ መጥፎ አመልና ልማድ የተያዙ ሰዎች በብዛት የሚገኙባት ዓለም ናት። በመጠጥ፤ በሀሺሽ፤ በሚያስጸይፍ የዝሙት ተግባር፤ በገንዘብ ፍቅር፤ በምድራዊ ዳንኪራና ጭፈራ የታሠሩ ሰዎች ቁጥራቸው በርከት ያለ ነው። ሰዎች «ደስታ እናገኝበታለን» በሚሉት ነገር ራሳቸውን በገዛ እጃቸው ሲያጠፉ በብዛት እናያለን። የብዙዎቻችን ጥያቄ «አንዳንድ ሰዎች የልዩ ልዩ ልማድና አመል ባሪያዎች ለምን ይሆናሉ?» የሚል ነው። እዚህ ላይ መረዳት የሚገባን፥ ባሪያዎች ባሉበት አካባቢ ሁሉ ገዢዎች መኖራቸውን ነው። ስለዚህ ባሪያዎች እንዳንሆን ተገዢ ሊያደርጉን ከሚፈልጉት ነገሮች ጋር የማያቋርጥ መንፈሳዊ ጦርነት ገጥመን አሸናፊዎች መሆን አለብን።

- እንግዳ የሆነ ባሕርይ በሚታይባቸው ሰዎች መካከል፣ አንዱ ሌላውን ያለአግባብ ሲያጠቃ (ሲገዳ) ይታያል፤ ይህን ዓይነቱ ባሕርይ ያላቸው ሰዎች ብዙ ጊዜ "ተለዋዋጭ ባሕርይ" (Multiple Personality) ያላቸው ሰዎች ናቸው። እነርሱም ከሰው የማይጠበቅና የማይገመት ጭካኔ የሞላበት ተግባር ሲፈጽሙ ይታያሉ። ለመሆኑ በቁጣ፣ በፍርሃት፣ ራስን በማታለልና በተምታታ ሕይወት ውስጥ የሚኖሩትን መርዳት እንዴት ይቻላል? ሕይወታቸው ይህን ዓይነት መልክ እንዲኖረው ያደረጉት ርኩሳን መናፍስት ይሆኑ ይሆን? ከሆነ ከባድ መንፈሳዊ ጦርነት (ውጊያ) አለብን ማለት ነው።

- በግልጽ በሕይወታቸው የርኩሳን መናፍስት ባህሪ የሚታይባቸው አንዳንድ ሰዎች አሉ። የተጠጋቸውን ሁሉ የሚያጠቁ፣ እግዚአብሔር የሌለውን ባህሪ እንዳለው አድርገው ክፉ ወሬ የሚረጩ፣ መጽሐፍ ቅዱስን አጣመው በመተርጎም ብዙዎችን የሚያሳስቱ፣ ብዙዎች አሉ። ጠጋ ብሎ የሚያያቸው ሁሉ የርኩሳን መናፍስት ባህሪ እንዳለባቸው ያያል። ታዲያ እንደነዚህ ዓይነቶቹን ልንቀርባቸውና ልንደግፋቸው ስንሞክር በውስጣቸው ካለው ርኩሳን መናፍስት ጋር የማያቋርጥ መንፈሳዊ ውጊያ እንዳለብን አስቀድመን ማወቅ ይኖርብናል።

የክርስትና ሕይወት ጦርነትና ትግል የበዛበት ሕይወት ነው። ይሁን እንጂ የክርስትና ሕይወት ጦርነት የበዛበት መሆኑን የሚያውቀው ጌታ በትግሎቻችን አሸናፊዎች የምንሆንበትን መመሪያ ሳይሰጠን በጨለማ ውስጥ ብቻችንን አልተወንም። መጽሐፍ ቅዱሳችን በዚህ መመሪያ የተሞላ ነው። የብዙዎቻችን ችግር ግን መጽሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ በመመርመር ፈንታ አቋራጭ መንገዶችን የምንፈልግ መሆናችን ነው። «አቋራጭ መልስ አላቸው» ብለን የምንወስዳቸው እርምጃዎች፣ የጠበቅነውን ዓይነት መፍትሄ መስጠት አቅቷቸው በተደጋጋሚ መሸነፍ ሲደርስብን፣ ተስፋ ወደ መቁረጥ ደረጃ እንደርሳለን። አንዳንድ ሰዎች ሊወጡበት ከማይችሉት የኃጢአት አዘቅት ውስጥ የሚገቡበት፣ ወይንም የኃጢአት እስረኞች የሚሆኑበት ምክንያት ምን ይሆን? ይህንን የበለጠ ለመረዳት አንዳንድ ሰዎች በሕይወታቸው ያለፉበትንና ያጋጠማቸውን የሕይወት ፈተናዎችን እንመለከታለን።

ከዚህ ቀጥሎ የማቀርብላችሁ ተረት ሳይሆን እውነተኛ የተፈጸመ ታሪክ ነው። ታሪኩም የተፈጸመው ለረጅም ዘመን በሽምግልና ካገለገልኩበት የአሜሪካኖች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው። የዚህን ሰው የሕይወት ታሪክ ያቀረብኩበት ምክንያት፣ ይህንን ሰው ካለበት መንፈሳዊ ችግር ነጻ እንዲሆን በጸሎት፣ በምክር ለመርዳት ከሞከሩት

ሰዎች መካከል አንዱ በመሆኑና እንዲሁም የሰውየውን ማንነት በቅርብ ስለማውቅ፥ ለሁላችንም ጠቃሚ ትምህርት አለበት ብዬ ስላመንኩ ነው።

ታሪኩ ለብዙዎች ትምህርት እንዲሆን ቢጠቀስ ቅር እንደማይለው ስላረጋገጥሁ እንጂ የዚህን ሰው ምስጢር ለማውጣት ፈልጌ እንዳልሆነ በቅድሚያ መግለጽ እወዳለሁ። ይህን መጽሐፍ እኔ ባለሁበት ከተማ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ቢያነቡትና የሰውየውን ማንነት ቢያውቁም፥ ታሪኩ በጋዜጣ ቀደም ሲል የወጣ በመሆኑ፥ እሁንም የሰውየውን ምስጢር አውጥቻለሁ በማለት ህሊናዬን አይቆረቁረኝም። ይህ ሰው የቅርብ ወዳጄና ልረዳው ብዙ ይታገልኩለት ሰው በመሆኑ፥ ለሌሎች ትምህርት እስከ ሰጠ ድረስ ታሪኩ ቢወራ ቅር እንደማይለው አውቃለሁ።

የታሪኩ ባለቤት የሆነው ጂን፥ በአርባና በሃምሣ ዓመት ዕድሜ ክልል ውስጥ ያለ ሰው ሲሆን፥ የሦስት ልጆች አባት ነው። ሁለቱ ወንዶች ሲሆኑ፥ ሦስተኛዋ ሴት ነች። ሴቷ ገና የሁለት ወር ህጻን ሆና ከመንግሥት ተቀብለው ያሳደጓት ነች እንጂ በሥጋ አልወለዷትም። ጂን የአንድ ኩባንያ የሽያጭ ክፍል ኃላፊ ሲሆን፥ ከፍተኛ የዓመት ገቢ ያለው ሰው ነው። ከደሞዙ ሌላ ከአንድ ሰው የዓመት ደሞዝ የሚበልጥ ጉርሻ (bonus) ስለሚያገኝ የገንዘብ እጥረት የሌለበትና ተመችቶት የሚኖር ሰው ነው። በሥራው ምክንያት በየሥፍራው ሲዘዋወር የሚያርፈው፥ ከፍተኛ ሆቴል ውስጥ ነው። ትልቅና ያማረ የመኖሪያ ቤት ከነመዋኛው ያለው ሰው ነው። ከዚህ ሰው ጋር በጣም ስለምንቀራረብ፥ ልጆቻችን አልፎ አልፎ እዚህ ሰው ቤት እየሄዱ የሚዋኙበት ጊዜ ነበር።

ጂን ገና ተማሪ ሆኖ አንዳንድ መጥፎ ጠባዮቹ ከተለያዩ ችግር ውስጥ ይከቱት ነበር። መጠጣትና ከሴቶች ጋር መዳራት ጠባዩ ነበር። ጂን ስላለፈው ሕይወቱ ሲናገር፥ «ችኮ በሆነ አጋጣሚ የተያዝኩት ያኔ ነው» ይላል። ጌታን እንደ ግል መድኃኒቱ አድርጎ ከተቀበለ በኋላ ግን፥ ሕይወቱ ተለውጦ ያ ሁሉ መጥፎ ተግባሩን ተወ። ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ ጌታን ከማወቁ በፊት ይመለከታቸው የነበሩት ቅድስና የጎደላቸው መጽሔቶች (pornographic materials) ወደ አዕምሮው ብቅ በማለት ያስጨንቁት ነበር። ጂን ትዳር ከያዘም በኋላ ከዝሙት ፍጹም ነጻ አልሆነም ነበር። ሚስቱ በዚህ ጸባዩ ምክንያት ያልፈታቺው፥ ስለወደደችው ወይንም ልትታገሰው ስለፈለገች ሳይሆን፥ ከዚህ በፊት የመጀመሪያ ባሏን የፈታች በመሆኗ ሁለተኛ ላለመፍታት፥ ጂንን ብትፈታ ራሷንና ልጆቿን ለማስተዳደር በቂ ገንዘብ ስለሌላት «ምን እሆናለሁ?» ብላ በመፍራት ብቻ ነው። ከጋብቻው ውጪ የሥጋ ፍትወት ችግር እንዳለበት ብታውቅም፥ ምክንያቱ ስላልገባት «እኔ ይህን ያህል ቆንጆ ባልሆን ነው» በማለት በራሷ ታዝናለች።

ብዙ ጊዜ ጂን በተለያየ ምክንያት ከሚስቱ ጋር ይጋጫል። በሥርዓቱ ንስሀ ገብቶ ይቅርታ በመጠየቅና በመታረቅ ፈንታ «አዝናለሁ፤ ሆን ብዬ አንቺን ልጎዳ አይደለም» ብቻ በማለት ህሊናውን ለማጽዳት ይሞክራል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተመልሶ ተመሳሳይ በደል ይፈጽማል። ከፍቺ አይድረሱ እንጂ ጋብቻቸው ጣዕም ካጣ ረጅም ጊዜ ሆኖታል። ጂን ጌታን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን አባል ነበር። በሥራ ምክንያት ከከተማ ውጪ ካልሄደ በስተቀር፥ ከቤተ ክርስቲያን የቀረበትን ጊዜ ፈጽሞ አላስታውስም። አሥራቱን በታማኝነት ይከፍላል። ጂን የልቡን ገልጾ የሚያጫውተው የቅርብ ወዳጅ የለውም። ነገር ግን ከሰው ሁሉ ጋር በቀላሉ መተዋወቅ የሚያስችል ጠባይ አለው። በጣም ተጫዋችና ከሰው ሁሉ ጋር ተግባቢ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት «በስሜት» ላይ ብቻ የተመሠረተ ይመስላል። በቤተ ክርስቲያን የአምልኮት ሰዓት እጁን ዘርግቶ ስለሚያመሰግንና ስለሚዘምር ከአምላኩ ጋር በጣም የተቀራረበ ግንኙነት ያለው ሰው ይመስላል። የሚያስደንቀው እጁን ዘርግቶ ያምልክ እንጂ፥ የሚኖርበት የኃጢአት ሕይወት ግን ፈጽሞ አይቆረቁረውም ነበር። አንድም ጊዜ ፊቱ አዝኖ፥ ተክዞና ቅር ብሎት አይቼው ስለማላውቅ፥ ፍጹም ደስተኛና ሁሉ ነገር የተሟላለት ሰው ይመስለኝ ነበር።

አንድ ቀን አጣዳፊ የሽማግሌዎች ስብሰባ ተደርጎ ተጠራሁ። የተሰበሰብንበት ዋና ዓላማ ከላይ ታሪኩን የጠቀስኩት ጂን «ፈጸመ» የተባለውን ኃጢአት ለመስማትና አስፈላጊውን ውሳኔ ለመስጠት ነበር። የሰማሁትን ማመን አቃተኝ፤ በሰውየው ላይ በመፍረድ ፈንታ ልቤ አዘነለት፤ በጌታ ፊትም አለቀስኩለት። ከላይ የሰውየውን ታሪክ ስገልጽ፥ ከሕጋዊ ድርጅት የሁለት ወር ሕፃን ሆና እንደ ልጃቸው የሚያሳደጓት ሴት ልጅ እንዳለችው ጠቅሼላችኋለሁ። ይህች ልጅ ጤነኛ ሳትሆን፥ በተፈጥሮ አዕምሮዋ ከዕድሜዋ ጋር ያልበሰለ (retarded) ነው። ዕድሜዋ 16 ዓመት ይሁን እንጂ በአስተሳሰቧ ልክ እንደ አምስት ዓመት ህጻን ልጅ ነበረች። ጂን ይህችን ልጁን በማስገደድ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት በድብቅ ለብዙ ጊዜ ይፈጽምባት ነበር። አንድ ቀን አንደኛው ልጁ ይህን ሲያደርግ አየውና ለእናቱ ነገራት። እናቱም ከዚህ በፊት ጥርጣሬ ቢኖራትም በሁኔታው ተደናግጣ ለቤተ ክርስትያኗ መጋቢ በስልክ ሁኔታውን ገልጣ ተናገረች። በዚህ ምክንያት ነው እኛም የተቀረነው የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ለስብሰባ የተጠራነው።

ከሁለት ቀን በኋላ እንደ ገና ሽማግሌዎች ተሰብስበን ጂንና ሚስቱን ጠራናቸው። ስለ ሁኔታው ብዙ ተወያየን። ይህን ሰው ይህን ዓይነት በደል በልጅቷ ላይ ከሁለት ዓመት በላይ እንደፈጸመባት ተናገረ። ከላይ እንደገለጽኩላችሁ ይህ ሰው ከቤተ ክርስቲያን ቀርቶ አያውቅም። ታዲያ በዚህ ዓይነት ሕይወት ውስጥ ሲኖር እንዴት

መንፈስ ቅዱስ በመልዕክቱ ወይንም በሌላ መልክ ሳይናገረውና ሳይገለጸው ቀረ በማለት ራሴን እጠይቅ ነበር። ይህንኑ ጥያቄ ራሱ መልስ እንዲሰጠኝ በስብሰባው ላይ ጠየቅሁት። የሰጠኝ መልስ «በዚያን ጊዜ መላእክት እንኳን መድረኩ ላይ ቆመው ቢሰብኩልኝ የሚሰማኝ አይመስለኝም» ሲል መልስ ሰጠኝ።

ኃጢአት ዋጋ ያስከፍላልና ይህ ሰው የኃጢአቱን ዋጋ መክፈል ጀመረ። ሁኔታው በወረዳው አስተዳደር ባለ ሥልጣኖች ዘንድ የታወቀ በመሆኑ በጋዜጣ ታሪኩ ወጣ። ፍርድ ቤት ቀርቦ በፈጸመው ወንጀል ተፈረደበት። በሙሉ እሥራት ፈንታ የመጀመሪያ ጥፋቱ ስለሆነ ከሥራው እንዳይባረር በማለት ቀን እንዲሠራና ማታ ከሥራው ሲወጣ ወህኒ ቤት እንዲያድር፣ እንዲሁም ቅዳሜና ዕሁድ ወህኒ ቤት እንዲውልና እንዲያድር ተፈረደበት። በቤተ ክርስቲያን ደረጃም የፈጸመው ኃጢአት ምን እንደሆነ ለምእመኑ በግልጽ ሳይዘረዝር፣ በአጠቃላይ በኃጢአት እንደወደቀና ቤተሰቡን፣ እግዚአብሔርንና እንዲሁም ቤተ ክርስቲያኑን እንደበደለ ቆሞ በንስሀ መልክ ከተናገረ በኋላ፣ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ድምጽ ጸለየችለት።

ጂን እሥራቱን ጨርሶ ከወህኒ ቤት ወጣ። የመሥሪያ ቤቱ አለቆች የፈጸመውን ወንጀል ተመልክተው ከዚህ በፊት ከነበረው ደረጃና ሥልጣን በሁለት ደረጃ ዝቅ እንዲል አደረጉት። የወር ደሞዙም በዚያው መጠን ተቀነሰ። ለተወሰነ ጊዜ የሥነ ልቦና ሀኪሞች የሚሰጡትን ዕርዳታ እንዲያገኝ ሆነ። በተጨማሪ ከቤተ ክርስቲያኒቷም መጋቢ ጋር በየሳምንቱ እየተገናኘ የምክርና የጸሎት እርዳታ እንዲያገኝ ሆነ። በዚህ ሁሉ አሳፋሪ ሁኔታ ውስጥ ጂን ሲያልፍ፣ በሚያውቁት ሰዎች መካከል ሲሆን የማፈርና የመሸማቀቅ ስሜት ታይቶበት አያውቅም። እንዲያውም ምንም ነገር የደረሰበት አይመስልም ነበር።

ለሦስት ዓመት ያህል ጂን ከውጪ በሚታየው ሕይወቱ፣ እንግዳ የሆነ ጠባይ ወይንም ባህሪ አልታየበትም። ሁሉም በጎና ሰላም ይመስላል። ይሁን እንጂ ጂን በውስጡ ካለው ትግልና ጦርነት ነጻ አልነበረም። ቀደም ሲል የደረሰበት የኃጢአቱ ውጤት ወደፊት ስለሚሆነው ነገር ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ ሊሆንለት አልቻለም። እንደተለመደው አዕምሮዋ ከዕድሜዋ ጋር ካልበሰለው እንደ ልጁ ካሳደጋት ወጣት ጋር እንደገና የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ሲፈጽም ተያዘ። በሁለተኛ ጊዜ ጥፋቱ ከፍተኛ ቅጣት በፍርድ ቤት እንዳይሰጠው የረዳው፣ ልጅቷ በዚህ ጊዜ ዕድሜዋ 19 ዓመት በመሆኑ፣ ይሄ ዕድሜዋ እንደ ሙሉ ሰው ስለሚያስቆጥራት ብቻ ነበር። ይሁን እንጂ ጂን ቀድሞ ከደረሰበት ጉዳትና ቅጣት የበለጠ ተሰጠው። የቤተ ክርስቲያን አባልነቱም እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ተወሰደበት። ሚስቱም ከሞቀና ካማረ ቤቱ አባረረችው። መጠለያ የሌላቸው ሰዎች ከሚኖሩበት ድርጅት ገብቶ በአንድ ክፍል ውስጥ ተወስኖ መኖር ጀመረ። በዚህ አሳዛኝ ፈተና ውስጥ

ለሁለተኛ ጊዜ ከወደቀ በኋላ፣ ጂን ቢሮዬ መጥቶ ብዙ ተነጋገርን፤ አብረንም ጸለይን። በዚህ ጊዜ ነው ካለበት መንፈሳዊ ጦርነት ነጻ መሆን የሚችልበትን መንገድ በመፈለግ የወሰደውን እርምጃና ያደረገውን ያጫወተኝ።

ጂን ሕይወቱን ጨምድዶ የያዘውን የሥጋ ፍትወቱን መስመር ለማስያዝ ይሞክር የነበረው፣ የዝሙትን መንፈስ ከውስጡ በመገሰጽ ነበር። በቅርቡ አንድ የፈውስ ስጦታ ያለው ሰው ከሚያካሂደው ትልቅ ስብሰባ ተገኝቶ ሰባኪው «የፍትወት አጋንንት በውስጥህ አለ» ብሎ አጋንንቱን ከውስጡ እንዳስወጣለትና፣ አጋንንቱ ተመልሶ ቢመጣ ራሱ ገስጾ ማስወጣት እንደሚችል እንደተነገረው አጫወተኝ። ጂን ሦስት ዓይነት አጋንንቶች፣ ይኸውም የፍትወት፣ የቁጣና እንዲሁም የኩራት አጋንንት በውስጡ እንደነበረበትና ያንንም የፈውስ ስጦታ ያለው ሰው እንዳስወጣለት ነገረኝ። የፍትወት አጋንንት የገባበት ሰዎች ሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ሲፈጽሙ የሚያሳየውን መጽሔት (pornographic magazine) በሚያይበት ጊዜ እንደሆነ ይናገራል። ያስገረመኝ፣ ጂን ይህንን ገለባ ትምህርት አምኖ መቀበሉ ሳይሆን፣ ይህንን ዓይነት ትምህርት የሚያስተምሩ ስንኩል ነጋዴዎች እየበረከቱና ተቀባይነትም እያገኙ መምጣታቸው ነው።

ጂን በተነገረው መሠረት በውስጡ ያለውን መንፈስ ያለማቋረጥ ይገስጻል። አልፎ አልፎም አጋንንትን በማባረር ሥልጣን አላቸው ብሎ ወደሚያምናቸው ሰባኪዎች ዘንድ እየሄደ «የፍትወት አጋንንቶችን» እንዲገስጹለት ይጠይቃል። ይህን መጽሐፍ የመጀመሪያውን ድራፍት ስጨርስ የጂን ታሪክ እዚህ ላይ ያበቃ ነበር። ግን በጥቂት ሳምንታት ውስጥ የጂን ታሪክ ተራዝሞ አገኘሁት። ራሱን እስኪያሻሽልና በሕይወቱ እውነተኛ ለውጥ ማድረጉን እስኪያረጋግጥ፣ ሚስቱ ወደ ቤቱ እንዲመለስ አልፈቀደችለትም ነበር። የቀድሞ የቤተሰቡ ገቢ በጂን የኃጢአት ሕይወት ምክንያት በመቀነሱ ሚስቱ ሥራ ጀምራ ስለነበረ፣ እርሷ ሥራ የምትሄድበትን ሰዓት እየጠበቀ ከዚያች የአዕምሮዋ ዕድገት ከዕድሜዋ ጋር ካልዳበረው ወጣት ጋር የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈጸሙን ቀጠለ። ከዚህ በፊት በዝሙት ምክንያት ሕይወቱ ምን ያህል እንደተንሳቀለና እንደተዋረደ ቢያውቅም፣ ጂን ያንን ሁሉ በመርሳት ለሦስተኛ ጊዜ በተመሳሳይ ኃጢአት ወደቀ። ኃጢአት ምን ጊዜም ቢሆን መገለጹ አይቀርምና ለሦስተኛ ጊዜ በኃጢአቱ ተያዘ። ታሪኩን ለማሳጠር፣ በአሁኑ ወቅት ይሄ ሰው ከፍተኛ ቅጣት ለመቀበል በመጠባበቅ ላይ ይገኛል።

ጂን «በፍትወት አጋንንት ተይዣለሁ» ብሎ እንዲያምን የሚያደርጉት ልዩ ልዩ ምክንያቶች ነበሩት። በህጻንነቱ ያደገው ሥነ ሥርዓት በጎደለው ቤተሰብ ውስጥ ተገፍቶና ተንገላትቶ በመሆኑ አሁን የሚታይበት የሥጋ ፍትወት፣ ቁጣና እንዲሁም ትዕቢት እርኩሳን

መናፍስት በልጅነቱ፡ ስለገዙበት እነርሱ ያመጡት ውጤት ነው ብሎ ያምናል። በዚህ ዓይነት ራሱን ከተጠያቂነትና ከኃላፊነት ነጻ ለማድረግ ይሞክር ነበር። ግራ መጋባቱና በመንፈሱ መታወኩ፣ በርኩሳን መናፍስት በመያዙ ምክንያት ይመስለዋል። ይሁን እንጂ ጂን በርኩስ መንፈስ የተያዘ አልነበረም። መጽሐፍ ቅዱሱን ያነብል፤ የሚያነበው ግን ሥርዓት ተከትሎ ሳይሆን እንዴ እዚህ፣ እንዴ እዚያ እያለ ቃሉን እየቆራረጠ ነው። አንድ ሙሉ ምዕራፍ ጨርሶ ያነበበት ጊዜ የለም። ከዚህም ከዚያም ጥቅሶችን ይጠቃቅሳል። ጥቅሶችን የሚወስዳቸው ጽሁፉ ከሚለው ሀሳብ ውጪ ልዩ ትርጉም እንዲኖራቸው በማድረግ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ መመርመር ቢችል የበለጠ ምኝነቱንና አላዋቂነቱን ይረዳ ነበር። ጂን ሞኝና በሕይወቱ ያልበሰለ፣ ፈቃዱን ለሰይጣን ያስገዛ ሰው እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ጂን ጌታን ካወቀ ከ 20 ዓመት በላይ ይሁነው እንጂ፣ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ስላላደገ፣ የሰጡትን ሁሉ አምኖ ይቀበላል። በስሜታዊ ነገርም በቀላሉ ይሳባል። ጂን ልዩ ልዩ ችግር ያለበት ሰው እንጂ በርኩስ መንፈስ የተሞላ አይደለም። መስመር የለቀቀ ትምህርት ስላገኘ፣ እምነቱ የተዛባ ነው። እውነተኛ መንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ እንዴት መዋጋት እንዳለበት ቢማር፣ በእግዚአብሔር ጸጋ ውስጥ በማደግ የበሰለ የእግዚአብሔር ሰው መሆን ይችል ነበር። ጂን ማድረግና ማወቅ የሚገባው አንዳንድ ነገር አለ። ከእነዚህ መካከል ጥቂቶቹን ለትምህርታችን እንዲሆን ከዚህ ቀጥሎ ለመጥቀስ እንሞክራለን።

① ጂን በሚገጥመው መንፈሳዊ ትግል ውስጥ በእግዚአብሔር ተስፋና በክርስቶስ ፍቅር በመታመን ፈንታ ለማሸነፍ የሚሞክረው በራሱ መንፈሳዊ ጥረትና ትግል እንደሆነ እንገነዘባለን። በመንፈሳዊ ትግሉ አሸናፊ ለመሆን ቢፈልግ፣ በክርስቶስ ውስጥ መሸሸግን መማር ይገባዋል። «ሥልጣን አለኝ» በማለት ትምክህታዊ ሆኖ ስሙንና ደሙን በመጥራት ፈንታ፣ የሚለውን ማመንና መቀበል አለበት።

② ጂን እውነተኛ ጥበብን ለማግኘት ቃሉን በሚገባ መመርመርና ማጥናት ይገባዋል። ቃሉን ማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ እንደ ቃሉ ለመኖር ራሱን ማለማመድ አለበት።

③ ጂን «መንፈሳዊ ጦርነቱን» ለብቻው ሆኖ መዋጋት ማቆም አለበት። በቅርቡ ሆኖ የሚያማክረው፣ የሚጸልይለት፣ ሲደክም «አይዞህ» የሚለው ሲስት የሚወቅሰውና ሁልጊዜ ከጎኑ ሊቆም የምችል የቅርብ መንፈሳዊ ጓደኛ ያስፈልገዋል።

④ ጂን «በመንፈሳዊ ጦርነቱ» ውስጥ አሸናፊ ለመሆን፥ ሰይጣን የአዕምሮውን ሀሳብ እንዴት ሊጠቀምበት እንደሚችል ማወቅ አለበት። የጠላቱን ዘዴ ለማወቅ የማይጥር ጦረኛ በቀላሉ ተሸናፊ ይሆናል። ሰይጣን በሥጋ ፍትወት አማኞችን ለመጣል የሚሞክረው መጀመሪያ በሰው አዕምሮ በመጫወት እንደሆነ መረዳት ይገባዋል።

⑤ ጂን «በመንፈሳዊ ትግሉ» አሸናፊ መሆን የሚችለው ለሥጋዊ ፍትወቱ «አልሸነፍም» ያለ እንደሆነ ነው። እርግጥ ነው የሥጋ ፍትወትና ንዴት ሰው በቀላሉ ሊያሸንፋቸው የማይችላቸው የሰው ድካሞች እንደሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ሥፍራ ይጠቅሳቸዋል። ከእነርሱ ሸሽተን ወደ ክርስቶስ በመጠጋት ሕይወታ ችንን እንዳ ይገዙም መከላከል ይገባናል።

ይህን ሀሳብ የበለጠ መረዳት እንድንችል ሌላ ምሳሌ እንመልከት። ሁሉ አገርሽ ገና ትዳር ያልያዘች የ30 ዓመት ወጣት ሴት ልጅ ነች። ጌታን ከተቀበለች ከአሥር ዓመት በላይ ሆኗታል። በመንፈሳዊ ሕይወቷ ለማደግ በጣም ስለምትፈልግ፥ የማትገኝበት ኮንፍረንስ ወይ ንም መንፈሳዊ ስብሰባ የለም። እምነቷን የሚያሳድጉላት የሚመስሏትን መጽሐፍት ማንበብ ትወዳለች። የስልክ ኦፕሬተር በመሆኗ በስልክ ከብዙ ክርስቲያኖች ጋር ትገናኛለች። ለብዙዎች ሀሳብና ምክር ትሰ ጣለች። ከሁሉም በላይ «አጋንንትን በመገሰጽ የማስወጣት ስጦታ አለኝ» ትላለች። እንዲሁም ጌታን ለማገልገል ከፍተኛ ጥማትና ፍላጎት አላት። ለብዙዎች ጸልያ ልዩ ልዩ ርኩሳን መናፍስትን እንዳስወጣች ትመሰክራለች። ስለ ግል ሕይወቷ ስትናገር «በግሌ ከፍተኛ ትግልና ጦርነት ከሰይጣን ጋር እገጥማለሁ። በሌሎች ሰዎች ስለሚሆነው አላ ውቅም፤ ስለ ራሴ ግን የምናገረው ብዙ ነገር አለኝ። ሀሰት የሆኑ፥ ከሰይጣን የመነጩ ልዩ ልዩ ስሜቶች ወደ ሕይወቴ ይመጣሉ። በዚህን ጊዜ ራሴን ለመከላከል ርኩሳን መናፍስትን ያለማቋረጥ እገስጻለሁ። ሕይወቴን ሲገዙ፣ ሲቆጣጠሩ፣ ሲፈትኑኝና ባሪያ ሲያደርጉኝ የሚሞ ክሩትን ርኩሳን መናፍስት እየገሰጽኩ አባርራቸዋለሁ» ትላለች።

ሁሉ አገርሽ በግል ሕይወቷ ስለሚከናወነው ጦርነት ስትገልጽ፥ ከእግዚአብሔር ያልሆኑ ሀሳቦች ሳትፈልጋቸውና ሳትጋብዛቸው ድንበር እየጣሱ ወደ አዕምሮዋ እንዴት እንደሚገቡ ትናገራለች። እነዚህ መጥፎ ሀሳቦች ከእርሷ ሕይወት ውስጥ ወጥተው ጥልቅ ወደ ሆነው ጉድጓድ እንዲገቡ እንደምታዛቸው ትገልጻለች። «ጌታን በጣም እወደዋለሁ። ይሁን እንጂ አንዳንዴ ቁጣ ወይንም ንዴት በውስጤ እንደ እሳተ ገሞራ ሲፈነዳ ይሰማኛል። ይሄ ንዴት ከእኔ እንዳልመጣ አውቃለሁ፤ ስለዚህ «የቁጣን አጋንንት» ከውስጤ እገስጻለሁ፤ የቆሙብትን ምድር አፈራርሳለሁ። የቁጣ አጋንንት ወደ ውስጤ ዘልቀው እንዲገቡ ስለማልፈልግ አስሬ አስወጣቸዋለሁ» ታላለች።

ሁሉ አገርሽ በመንፈሳዊ ሕይወቷ የሚያጋጥማትን ትግልና ፈተና ለመቋቋም የምትሞክረው «በውስጤ አሉ» የምትላቸውን ልዩ ልዩ ርኩሳን መናፍስትን በመገሰጽ ነው። ይሄንንም «መንፈሳዊ ጦርነት» ትለዋለች። ማንኛውም ኃጢአት ከሰይጣን ጋር የተያያዘ እንደሆነ ሁሉ «ቁጣ» ወይንም ንዴትም ከሰይጣን ጋር የተያያዘ ነው። ሰይጣንን በመገሰጽ ብቻ ራሷን በቅድስና መምራት እንደምትችል የሚገልጽ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አናገኝም። ሁሉ አገርሽ እንደምታስበው ቢሆን ኖሮ የክርስትና ሕይወት ቀላልና «ወዲያው» ድል የሚገኝበት ሕይወት ይሆን ነበር። ኢየሱስ ከተወለደበት ጀምሮ በመስቀል ላይ እስካረፈበት ጊዜ ድረስ ከሰይጣን ትግል ነጻ ሆኖ አያውቅም። ሁሉ አገርሽ እንደምታስበው ቢሆን ኖሮ፥ አንድ ጊዜ ገስጾ በማስወጣት ብቻ እረፍት አግኝቶ ይኖር ነበር። ሁሉ አገርሽ ስሜቷን ስትገልጽ፥ «እነዚህ መጥፎ ሀሳቦች ከከፉ ጠላት የመነጩ ሀሳቦች ናቸው፤ የሰይጣን እንጂ የእኔ ሀሳብ አይደሉም። እኔ እንደ እውነቱ «ቁጠኛ» ሰው አይደለሁም። ጌታን እወዳለሁ። እነዚህ ስሜቶች ያለኝን አቋም የሚቃረኑ ናቸው። እኔ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላሁ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ። ከዚህ «ከቁጣ አጋንንት» እግዚአብሔር እንዲያድነኝ የእርሱ ጥበቃ ያስፈልገኛል» ትላለች። ይህንን ማለት የቻለችው መንፈሳዊ ጦርነቷን ማካሄድ ያለባት ርኩሳን መናፍስትን በማባረር ብቻ እንደሆነ የተማረች በመሆኗ ነው። ይሁን እንጂ ልምምዱ መጽሐፍ ቅዱስ የሚደግፈው አይደለም።

«የቁጣን አጋንንት» ከውስጧ ለማስወጣት ከመሞከር ይልቅ ሁሉ አገርሽ ችግሯን መቋቋም የምትችልበት ሌላ መንገድ ይኖር ይሆን? ሁሉ አገርሽ ችግሯን ለማቃለል የምትችልባቸው ሌሎች መንገዶች አሉላት። ይኸውም፥

1. የምትቆጣው ያለአንዳች ምክንያት ይሆን? ማንም ያለአንዳች ምክንያት መቆጣት ስለማይችል፥ የቁጣዋ መነሻ ምክንያት ምን እንደሆነ ማወቅ ያስፈልጋታል። ምን ጊዜ እንደምትቆጣ፥ በተቆጣችበት ወቅት ምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እንደ ነበረች ራሷን መጠየቅ ይገባታል። ቆም ብላ የተቆጣችባቸውን ሁኔታዎች መመርመር ካልቻለች፥ እግዚአብሔር ምን እንድትሆን፥ ምን እንድታደርግ እንደሚፈልግ ተረድታ ለራሷ መልስ መስጠት አትችልም።

2. «ቁጣዋ» ምን ዓይነት መልክና አቋም እንደነበረው መመልከት አለባት። ሀሳቧ ምን እንደነበረ፥ በተቆጣችበት ጊዜ እንድታደርግ የተፈተነችው ምን እንደሆነ፥ ቁጣዋ ያተኮረው በማን ላይ እንደሆነና ምን ዓይነት ስሜት እንደተሰማት ማወቅ ይገባታል። ቁጣዋ በእግዚአብሔር ላይ፥ በራሷ ወይንም በሌላው ሰው እንደሆነ መለየት ይኖርባታል።

3. መጽሐፍ ቅዱስ «...እያንዳንዱ ሰው የሚፈተነው በገዛ ራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ነው...» ስለሚል (ያዕቆብ 1:14)፥ ቁጣዋ የተመኘችውን ባለማግኘቷ ሊሆን ይችላልና «ምን ተመኝታ እንደሆን» ራሷን መመርመር ያስፈልጋታል። ምን ትፈልጋለች? የምትፈልገው ነገር ምን ነበር? ቁጣዋን የሚቀሰቅስ የተሰወረ ፍላጎት ነበራት? አንድ ነገር ፈልጋ ወይንም ተመኝታ፥ ያንን የፈለገችውን ነገር ባለማግኘቷ ቁጣን በውስጧ ፈጥርባት ይሆን? «የቁጣ አጋንንት በውስጤ አለ» በማለት ያንን ዝስጾ ለማስወጣት ከመሞከር፥ በቁጣ እንድትሞላ የሚያደርጋት ሠይጣን ምን ዓይነት አቋም ወይንም እምነት እንዲኖራት ፈልጎ እንደሆን ራሷን መመርመር ይጠቅማታል።

4. እግዚአብሔር ማንነቱንና እንዲሁም የተናገረውን ማወቅ ይገባታል። በመንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ ስትሆን ከለላና ድጋፍ የሚሆናትን እውነተኛውን ጌታ ትመልከት። ሰይጣን ከባድ የሆነውን ፈተናውን በሚጥልበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር ሁሉን በቁጥጥሩ ሥር ማዋል እንደሚችል፥ ሰይጣን ከዘረጋው ፈተና ይልቅ እግዚአብሔር ያለው ኃይል እንደሚበልጥ መገንዘብ ይገባታል። እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ «ሁሉን ውደዱ» የሚለው ትዕዛዙ በውስጣችን የተሰወረውን «ቁጣችንንና» እንዲሁም «ምኞታችንን» ይገልጣል። ምንም ዓይነት ሁኔታ ቢያጋጥመን እውነተኛውና በፍቅር የተሞላው ኢየሱስ ይቅርታ መስጠት ብቻ ሳይሆን፥ እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ እንድንታመን ያስተምረናል። በውስጣችን ቁጣ እንደ እሳተ ገሞራ ሲፈነዳ፥ ከሕይወታችን ቆርጠ ለመጣል ያሰበው ምን ይሆን? ሙሉ ለውጥ አግኝተን በሕይወታችን ፍሬያማ መሆን እንድንችል የራሳችንንና የአምላካችንን ልብ መርምረን እንወቅ።

5. «የቁጣ አጋንንት» በማለት ከውስጧ ዝስጾ ለማስወጣት ከመሞከር ይልቅ፥ እግዚአብሔርን በአዲስ መልክ ማንነቱን መመልከትና ማሰብ በመንፈሳዊ ሕይወቷ ለማደግ ዕድል ይሰጣታል። «ቁጣ» በቀላሉ የምናሸንፈው ጠላት አይደለም። ይሄ ከመስመር የወጣ ቁጣ ጠላታችንን ዲያብሎስን እንድንመስል ያደርገናል። ይሁን እንጂ በዚህ ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ ለመግለጽ ይፈልጋል። እውነተኛውን ውጊያ እያወቅነውና እየተለማመድነው ስለሆነ፥ በማስተዋልና በጥበብ መራመድ ይገባናል።

እስቲ መለስ ብለን የሁሉ አገርሽን ችግር በጥንቃቄ ለመመርመር እንሞክር። «ቁጣዋን» የሚጭረው ዋናው ምክንያት ምን ይሆን? «የቁጣ አጋንንት» በማለት ዝስጾ ለማስወጣት ቢቻል ለሁላ

ችንም ቀላል መንገድ ይሆንልን ነበር። ሁሉ አገርሽ የመሥሪያ ቤት አለቃዋ የጠበቀችውን ዓይነት የደሞዝ ጭማሪ ስላልሰጣት በጣም ቅር ተሰኝታለች፤ «ሥራዬን ባይወደው ነው» በማለት በጣም አዝናበታለች። ይሁን እንጂ ክርስቲያን በመሆኗ አለቃዋን ምንም ዓይነት በደል ቢያደርስባትም ልትወደውና ይቅር ልትለው እንደሚገባት ታውቃለች። ቢሆንም ልቧ በጣም ስለተቀየመና ስላዘነ መውደድ አቃታት። በአለቃዋ ፊት ሥራዋን በተቀላጠፈ መንገድ ሠርታ ለማሳየት ብትሞክርም፥ ጥረቷን የሚያይላትና የሚቀበልላት አይመስላትም ነበር። ሁሉ አገርሽ ሌላም ችግር ነበረባት። አለቃዋ ያላገባ ሰው በመሆኑ፥ «ለጋብቻ ይጠይቀኝ ይሆናል» የሚልም ምኞትና ፍላጎትም ነበራት። አለቃዋ ከሌሎች ሴቶች ጋር ሲወጣ ስታይ ከውስጧ «ቁጣዋ» እንደ እሳተ ገሞራ ይፈነዳል። በዚህ ምክንያት እንጂ ሁሉ አገርሽ እንደ ምታምነው «የቁጣ አጋንንት» ውስጧ ዘሎ በመግባት እንዳልሆነ፥ ከዚያም ነጻ ለመውጣት «የቁጣ አጋንንቱን» መገሰጽ ብቻ እንደማ ይበቃ እናያለን። የግድ አስተሳሰቧንና አመለካከቷን ማስተካከል አለባት። ሁሉ አገርሽ «ቁጣዋ» የሚያይልበት ቀን ቀን አለው። ቅዳሜና ዕሁድ የማትወዳቸው ቀናቶች ናቸው። ብቸኝነት በጣም ያጠቃታል። በነዚህ ቀናት ከዚህ በፊት የነበራትን እጮኛ ታስታውሳለች። «ሳያገባኝ ጊዜዬን አጠፋብኝ» በማለት ከፍተኛ ንዴትና ቅሬታ በዚያ ሰው ላይ ነበራት። «ከእንግዲህ ወዲያ የማግባት ዕድሌ እየመነመነ ነው» ብላ በማሰብ ፍርሃትና ተስፋ መቁረጥ ይሰማታል። በዚህ ሁኔታ በውስጧ ልትቆጣጠረው የማትችለው «ንዴት» በውስጧ ሲሰማት፥ አቋራጭ የሆነ መፍትሄ ትፈልጋለች። ይሁን እንጂ የምትጠብቀውን ዓይነት መፍትሄ አላገኘችም።

ሁሉ አገርሽ በግልጽ አትናገረው እንጂ በእግዚአብሔርም የምትቆጣ ትመስላለች። የደሞዝ ጭማሪ ስትፈልግ፥ ባል አግብታ እንደ ጓደኞቿ ለመኖር ስትመኝ፥ ብቸኝነት ሲያንገላታት እግዚአብሔር እያወቀ በጎ የሆነውን ነገር የከለከላት ስለሚመስላት በእርሱም ላይ ከፍተኛ ቁጣ አላት። ሁሉ አገርሽ በውስጧ የሚነደው አግባብ ያልሆነ ቁጣ መፍትሄ ማጣቱ፥ ለራሷ ማዘኗና እንዲሁም ራሷን መክሰሷ ከምታምነው እምነት ጋር አብሮ አልሄድም አላት። እርሷ የተማረችውና የምታምነው በአጋንንት ሁሉ ላይ ሥልጣን እንዳላት ስለሆነ፥ እነዚህን ሕይወቷን ያዘበራረቁባትን ርኩሳን መናፍስት ገስጻ በማስወጣት ከዚህ ሁሉ ነጻ ሆና መኖር አለመቻሏ በውስጧ ትልቅ ጥያቄን ፈጥሮባታል።

ሁሉ አገርሽ «የቁጣ አጋንንት አለባት» ብሎ ከመደምደም፥ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ችግሯን በተሻለ መንገድ ማሳየትና ማየት እንችላለን። የሥጋ ምኞቷ (ፍላጎቷ) «ከሌላ ነገር» ጋር በመጋጨቱ፥ ማለት በወቅቱ ልታገኘው የማትችለውን ነገር በጣም በመፈለግና ያንንም ማግኘት ባለመቻሏ በውስጧ ኃይለኛ ቁጣን ሊያስነሳ ይችላል።

ሰይጣን ይህን ከፍተኛ ጥማቷን (ፍላጎቷን) በመያዝና ተንኮሉን በመ ጠቀም ተስፋ መቁረጥና ቁጣ እንዲሰማት ያደርጋል። ይሁን እንጂ ሰማያዊው አባቷ ይህንኑ ሁኔታ በመጠቀም፣ ማለትም ፍላጎቷንና ጥማ ቷን በመያዝ ግራ የተጋባውን ሕይወቷን ትክክለኛውን መስመር ያስ ይዘዋል።

ሁሉ አገርሽ ያለችበትን እውነተኛ መንፈሳዊ ጦርነት ከዚህ በፊት በምታስበውና በምታምነው መንገድ ማሸነፍ እንደማትችል መጨረሻ ላይ እየተረዳች መጣች። ስለ ራሷ፣ ስለ እግዚአብሔርና እንዲሁም ስለ መንፈሳዊ ውጊያ የተለየ አመለካከት እንዲኖራት ሆነች። ችግሯን ከምንጊዜውም የበለጠ በትክክለኛው ሁኔታ ለማየት ቻለች። እንዲህም በመሆኑ ትክክለኛና ተጨባጭ የሆነ ተስፋ በውስጧ ተፈጠረ። ለመንገዷ መመሪያ አገኘች፣ በመታዘዟም የአዕምሮ መታደስ ማግ ኘት እንደምትችል ተገነዘበች። ተግባሯ፣ ተስፋው፣ የስሜቷ አቅጣጫ፣ የምታደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ቅደም ተከተላቸው ተስተካከለ፣ ሀሊና ዋም ታደሰ። ርኩሳን መናፍስትም በዚህ አቅጣጫ ፈተናቸውን፣ ውሸ ታቸውንና ክሳቸውን፣ ጠቅልለው ሄዱ። የእግዚአብሔር እውነት ሁሉ አገርሽን ወደ ብስለት እንድትደርስ፣ እውነትን አጥርታ እንድታይና ከክርስቶስ ጋር የተቀራረበና የበሰለ ግንኙነት እንዲኖራት አደረገ። ሁሉ አገርሽ በመጨረሻ ከደረሰችበት መንፈሳዊ ደረጃ ላይ ለመድረ ስና «መንፈሳዊ ውጊያችንን» እንደሚገባ ለመዋጋት፣ ከዚህ የሚቀጥ ሉትን ምዕራፎች በጥንቃቄ እንመርምር።

# 2

# የሰይጣን ማንነቱና የአፈጣጠሩ ታሪክ

በ 1940 ዓ·ም. (እ.ኤ.አ.) በዓለም በጣም የታወቁት የአዲስ ኪዳን ሊቅ ዶክተር ሩዶልፍ በልትማን ሰይጣን በአሁኑ ጊዜ አለመኖሩን ሲያስረዱ፥ «አባቶቻችን በየዋህነት አጋንንት ወይንም ሰይጣን አለ ብለው ይመኑ እንጂ፥ እኛ ሳይንስ በረቀቀበት ዘመን የምንኖር ሰዎች፥ እንደ አባቶቻችን «አካላዊ ሰይጣን» (PERSONAL DEVIL) አለ ብለን በማመን አዲስ ኪዳንን አፈ ታሪክ እንዳናደርገው እንጠንቀቅ» አሉ። የዶክተር በልትማን አባባል በአዲስ ኪዳን ሊቃውንት መካከል ከፍተኛ ተቃውሞና ክርክርን አስነስቷል። እንዲሁም በ1970 ዓ·ም. የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትን የሚወክሉ ብዙ የሥነ መለኮት ሊቃውንት ተሰብስበው በአንድ ድምጽ «አካላዊ ሰይጣን በዚህ በሰለጠነው ዓለም የለም» የሚል መግለጫ አውጥተው ነበር። ይህም አባባል ያለተቃውሞ የታለፈ ሀሳብ አይደለም። «የሰይጣንን ሕያውነት» የተቃወሙት፥ ምናልባት «ሰይጣን ቀንድና ጅራት አለው» ብለው የሚያምኑትን ሰዎች ምክንያት .በማድረግ ይሆናል። እርግጥ ነው ሰይጣን «ቀንድና ጅራት ያለው ነው» ብሎ መጽሐፍ ቅዱስም አይናገርም። ይሁን እንጂ የሰይጣንን ሕያውነቱንና እንዲሁም አደገኛነቱን እንዳንዘነጋ መጽሐፍ ቅዱስ ያስጠነቅቀናል። ሦስቱ ጣምራ ጠላቶቻችን ማለትም፥ «ዓለም፣ ሥጋና ሰይጣን» ክርስቲያኖችን ሁልጊዜ የሚዋጉ መሆናቸውን የክርስትና ትምህርት ከመጀመሪያው ጀምሮ .ያስተምራል።

ስለ ሰይጣን ሕያውነትና እንዲሁም እንቅስቃሴው፥ ሁለት የተለያየ እምነትና አስተያየት ያላቸው ክፍሎች እንዳሉ ይታወቃል። አንደኛው ክፍል፥ ሰይጣን በተፈጥሮ ካለው ኃይል የበለጠ እንዳለው፥

ወይንም ከሆነው በላይ እንደሆነ አድርገው የሚመለከቱትና በተፈጥሮው ካለውና ከተሰጠው በላይ ከፍተኛ ግምት የሚሰጡት ናቸው። በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ክርስቲያኖች ክርስቶስ ሰይጣንን በጎልጎታ ላይ ድል ያደረገው መሆኑን እንኳን የሚያውቁ አይመስሉም። ይሄ ሰይጣንን በጣም ደስ እንደሚያሰኘው የታወቀ ነው።

ሌላው ክፍል ደግሞ «ሰይጣን ጨርሶ የለም» ብለው የሚክዱ ናቸው። «ሰይጣን የለም» ብለው ሲተውትና ችላ ሲሉት፥ በሰዎች ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ጥፋት ማድረስ እንደሚችል ስለሚያውቅ፥ ሁልጊዜ የሰዎች አዕምሮ በትክክለኛው እንዳያስብ፥ ልባቸው በጥርጣሬ እንዲሞላ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። የሚያስደንቀው፥ የሰይጣንን ሕያውነትና ኃይሉን የሚጠራጠሩ ወይም ክርስቲያን መሳዮች የሚበዙት፥ ክርስቲያኖች በብዛት በሚገኙበት አካባቢ መሆኑ ነው። ክርስቶስ በመስቀል ላይ ድል እንዳደረገውና ሰይጣን የተወሰነ ኃይል ብቻ እንዳለው በሚያውቁት ክርስቲያኖች መካከል፥ ስለ እርሱ ሕያውነትና ማንነት ጥርጣሬ መፈጠሩ ሰይጣንን እጅግ በጣም ደስ ያሰኘዋል። ማንነቱ በታወቀበት አካባቢ ሁሉ ከፍተኛ መጠላትና ተቃውሞ እንደሚደርስበት ሰይጣን ያውቃል። ሰዎች «ሰይጣን የለም» ብለው ከተጠራጠሩ ወይንም መኖሩን ከካዱ፥ «ጠላት የለብንም» ብለው ስለሚዝናኑ፥ ያኔ በቀላሉ ሰይጣን የሚፈልገውን ዓይነት ጥፋት በሕይወታቸው ማድረስ ስለሚችል ደስ ይለዋል።

ክርስቲያኖች በማይኖሩበት አካባቢ ግን የተለየ ነው። የተለያዩ የሃይማኖት እንቅስቃሴዎች ለምሳሌ እስልምና፣ ቡድሂዝምና እንዲሁም ልዩ ልዩ የጣዖት አምልኮ በሚበዛበት አካባቢ፥ የሰይጣን እንቅስቃሴ በግልጽ ሲሠራ ይታያል። የሚፈሩትና የሚያመልኩትም ብዙዎች ናቸው። የሰይጣን መኖር ይህን ያህል አጠራጣሪ ስላልሆነ፥ የእርሱን መኖር ለማረጋገጥና እንዲሁም የማያምኑትን ለማሳመን ጊዜ ማጥፋቱ አስፈላጊ መስሎ አይታየኝም።

ሰይጣን እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት መካከል አንደኛው ሲሆን፥ በነበረው ቁንጅናና ኃይል ታብዮ በእግዚአብሔር ላይ በማመጹ የነበረውን ከፍተኛ ደረጃ ያጣ፥ በጥላቻ ተሞልቶ በፈጠረው አምላክ ላይ በአመጽ መንፈስ የተነሳ ፍጡር መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል ያረጋግጥልናል። የሁሉ ነገር ፈጣሪ እግዚአብሔር ስለሆነ ሰይጣንም በእግዚአብሔር የተፈጠረ መሆኑ የሚያጠራጥረን አይመስለኝም። «ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ ያውቅ ዘንድ ነው፤ እኔ ጨለማንና ብርሃንን እፈጥራለሁ፤ በረከትንና ጥፋትን አመጣለሁ፤ እኔ እግዚአብሔር ይህን ሁሉ አደርጋለሁ» (ኢሳ. 45:6-7)። «...እግዚአብሔር ካልፈቀደ በቀር በከተማ ላይ ክፉ ነገር ይመጣልን?...» (አሞጽ 3:6)። ከላይ ባነበብነው ቃል መሠረት እግዚአብሔር በዓለም ላይ ያለውን ነገር የፈጠረ ብቻ ሳይሆን፥ እርሱ ሳይፈቅድና ሳያውቅ

በዚህ ዓለም ላይ አንድም ነገር መሆን እንደማይችል እንረዳለን። ከፉ የሆነውን ነገር እንኳን እግዚአብሔር «ይሁን» ብሎ እንደሚፈቅድ የምንገነዘበው፥ በኢዮብ ሕይወት ውስጥ የተፈጸመውን ስናይ ነው። አንድ ጊዜ የሰማይ መላእክት በእግዚአብሔር ፊት በቀረቡ ጊዜ ሰይጣንም አብሮአቸው ቀርቦ ኢዮብን እንደከሰሰና (ኢዮብ 1:6-10) እንዲሁም እግዚአብሔር «...አትግደለው እንጂ በእርሱ ላይ የፈለግ ኸውን ማድረግ ትችላለህ» (ኢዮብ 2:6) በማለት እንደ ፈቀደለት እና ያለን። ሰይጣን ከፍተኛ ኃይል ያለው ፍጡር ቢሆንም፥ ለእግዚአብ ሔር ኃይልና ፈቃድ ሁልጊዜ የተገዛ ነው።

## ➊ ሰይጣን ማን ነው?

ኢየሱስ ለሰዎች «የግል አዳኝ» እንደ ሆነው ሁሉ፥ ሰይጣንም ለሰው ልጅ «የግል ጠላት» ነው። የሚያጠቃውም በአጠቃላይ ብቻ ሳይሆን በነፍስ ወከፍም ጭምር ነው። የዘለዓለም ሕይወትን ለማግኘት የሚፈልግ ሁሉ ኢየሱስን የግል አዳኙ አድርጎ መቀበል እንደሚያስፈ ልገው ሁሉ፥ ከሰይጣን እጅ ለማምለጥም፥ በግል ሰይጣንን መቃወም አለበት። በአጠቃላይ «ሰይጣን አለ» ብሎ ማመንና መቀበል ባያስቸግ ረንም፥ «ግላዊ ጠላት» መሆኑን መቀበል ግን ብዙዎቻችንን ያቅተናል። ሰይጣን ማንነቱ በደንብ ካልታወቀበት ብዙ ጥፋት ማድረስ እንደሚችል ስለሚያውቅ፥ አለመታወቁ ደስ ያሰኘዋል።

ለመሆኑ ስለ ሰይጣን ያለን እውቀት ምን ያህል ይሆን? ሰይጣን መንፈሳዊ እድገታችንን ወደ ኋላ መጎተት እንደሚችል ምን ያህል ተገንዝበን ይሆን? ሰይጣን ተጨባጭ የሆነ ተፈጥሮ (personality) ያለው አደገኛ ፍጡር እንጂ፥ «የሃይማኖት ትምህርት» (Doctrine) ወይንም «ፍልስፍና» ብቻ እንዳልሆነ በደንብ ማወቅ ይገባናል። መጽሐፍ ቅዱስን አገላብጠን፥ ከዚህና ከዚያ ጥቅሶችን ጠቃቅሰን በቀላሉ ማንነ ቱና ተግባሩ «ይህንን ይመስላል» የምንለው ነገር አይደለም። እንዲ ሁም «በውስጣችሁ ያለው ከውጪ ካለው ይበልጣል» (1 ዮሐ. 4:4) የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በቃላችን አጥንተን መጠቃቀሳችን ብቻ ከአጠገባችን እንዳይደርስ አያደርገውም። ወይንም ኢየሱስ በው ስጣችን መኖሩን መረዳታችን ከሰይጣን ውጊያ ነጻ አያደርገንም።

ሰይጣን ህያው መሆኑን ማወቅ ብቻ ከጥቃት አያድነንም። ከጥ ቃት የሚያድነን ህያውነቱን ተገንዝበን መከላከልና ማጥቃት የቻልን እንደሆን ነው። የብዙዎች ችግር ህያውነቱን ቢያውቁም እንዴት አድ ርገው መከላከልና ማጥቃት እንደሚችሉ አለማወቃቸው ነው። ይህንን ኃይለኛ ጠላት ለመቋቋም ምን ማድረግ እንደሚገባን ትክክለኛ መመ ሪያ ወይንም ትምህርት ሊሰጠን የሚችለው፥ መንፈሳዊ ሕይወታችን

የተመሠረተበት የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። ይኸው የእግዚአብሔር ቃል የሚሰጠን የመጀመሪያው መመሪያ «ተጠንቀቀን እንድንጠብቀው» ነው። ይህንን ማስጠንቀቂያ ተቀብለን በሥራ ላይ ካላዋልነው፣ መመሪያውን ማወቁ ብቻ ከጥቃት አያድነንም።

ይሄ የሰው ሁሉ ጠላት የሆነው ሰይጣን፣ የሚጠራበት የተለያየ ስም እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። እነዚህም ስሞች ባህሪውንና ተግባሩን ይገልጻሉ። ከስሞቹ አንዳንዶቹ፣

- የብርሃን መልአክ (2ኛ ቆሮ. 11፥14)
- ተቃዋሚ (ጠላት) (1ኛ ጴጥ. 5፥8)
- ፈታኙ (1ኛ ተሰሎ. 3፥5)
- አታላይ (2ኛ ቆሮ. 11፥3)
- አደናቃፊ (1ኛ ተሰሎ. 2፥18)
- አውሬ (ራዕይ 19፥9)
- የሚያገሳ አንበሳ (1ኛ ጴጥ. 5፥8)
- የዚህ ዓለም አምላክ (2ኛ ቆሮ. 4፥4)
- የአየር ላይ ገዢ (ኤፌሶን 2፥2) ይለዋል።

ሰይጣን በሌላ ሰው ሕይወት ውስጥ እንዴት እንደሚሠራ ብናውቅም፣ በግል ሕይወታችን ግን እንዴት እንደሚሠራ ብዙዎቻችን አናውቅም። ሰይጣን ብዙ ጊዜ በሌሎች ሕይወት ውስጥ የሚሠራውን የተንኮል ሥራ ብናይም፣ በግል ሕይወታችን ሲሠራ ግን ማየት አንችልም። ሰይጣን የተንኮል ሥራውን ሲሠራ «እጅ ተፍንጅ» መያዝ ብንችል እንዴት ድንቅ ይሆን ነበር! ይሄ ቢሆን ኖሮ ምናልባት አሠራሩንና ብልሃቱን በቀላሉ ለይተን እናውቅ ነበር! አሠራሩን ካወቅን ደግሞ ተመልሶ ሊያጠቃን ሲመጣ በድፍረት የምንቃወምበት ወይንም የምናጠቃበት ዘዴ ይኖረን ነበር።

እውነተኛ ክርስቲያኖች ሁሉ «መጽሐፍ ቅዱስ ከስህተት ሁሉ ነጻ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ነው» ብለው ያምናሉ። ያለውንም ሥልጣንና ኃይል አይጠራጠሩም። ይሁን እንጂ፣ ሰይጣን የሰው ግላዊ ጠላት መሆኑን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በግልጽ ተጽፎ ቢያነቡም፣ ሰይጣን ስለሚያታልላቸው ያንን እንዳያስተውሉ ያደርጋቸዋል። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ «የሰይጣንን የተንኮል ሥራ ስለምናውቅ ሰይጣን እንዳያታልለን ብዬ ነው» ያለው (2 ቆሮ. 2:11)። የሰው ሁሉ የግል ጠላት ስለሆነው ሰይጣን ማንኛውም ክርስቲያን በደንብ ማወቅ ሲገባው፣ አንዳንድ ክርስቲያኖች ግን የሰይጣን ብልሃትና ዘዴ፣ እንዲሁም አሠራ

ሩን ማወቅ ቀርቶ፣ ማን እንደሆን እንኳን አጥርተው አያውቁም። ከማያ ውቁበት ምክንያት አንደኛው፣ በአብዛኛው ቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ ስለ ሰይጣን በግልጽ ስለማይሰበክ ነው።

የሰይጣንን ሕያውነትና እንቅስቃሴውን መቀበል የሚያቅታቸው አንዳንድ ክርስቲያኖች፣ ሃዋርያው ጳውሎስ «...ወደ እናንተ ለመም ጣት ደጋግሜ ሞክሬ ነበር፤ ነገር ግን ሰይጣን ከለከለኝ» (1ኛ ተሰ. 2:18)፤ እንዲሁም «የሥጋዬ መውጊያ እሾህ ተሰጠኝ...» (2ኛ ቆሮ. 12:7) የሚለውን አባባል፣ ትክክል ያልሆነውን የራሳቸውን ትርጉም ሲሰጡት ይታያሉ። የሰይጣንን እንቅስቃሴ ማመንና መቀበል አስቸ ጋሪ በሆነበት ዓለም፣ «ሰይጣን ህያው ነው» ብለው የሚያምኑትን «ያልተማሩ መሀይሞች ናቸው» የሚል አስተያየት እንደሚሰጣቸው ግልጽ ነው። በዚህ ምክንያት ብዙዎች በድፍረት የሰይጣንን ህልውናና አጥፊነቱን በግልጽ መናገር ሲፈሩ ይታያሉ።

ሰይጣን ሕያውነቱ የሚታወቀው በፍሬው ነው። ብዙውን የዓለም ሕዝብ በረከሰ የሥጋ ፍትወት ሲሞላ፣ የቤተሰብን አቋም ሲያናጋና ሲያፈርስ፤ በአልኮል መጠጥ ሕዝቡን እርስ በርሱ ሲያፋጅ፤ በሀሺሽ (ሱስ በሚያስይዝ ዕጽ) ወጣቶች ልጆችን ወደ አመጽ ሲከት፤ ቁጥር ስፍር የሌላቸውን ልጆች አመጸኛ አድርጎ ከወላጆቻቸው ቤት ሲያስኮ በልል፤ የወንጀለኛው ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ እንዲሄድ ሲያደርግ፤ የሰይጣንን ህያውነት በግልጽ ማየት ያስችለናል። ይህንን ሁሉ በማያ ጠራጥር ሁኔታ እያየን፣ «ሰይጣን የለም» ብንል ራሳችንን ማሞኘት፣ እንዲሁም እውነትን መካድ ይሆንብናል። ስለዚህ ሰይጣን ህያውነቱን ብቻ ሳይሆን፣

- ኃይሉንና ማድረስ የሚችለውን ጥፋት፣
- አሠራሩንና ብልሃቱን፣
- በሰው አዕምሮ ውስጥ እንዴት እንደሚሠራና
- ኃይሉን መቋቋም የምንችልበትን ዘዴ ማወቅ ይጠቅመናል።

## ለ ሰይጣን አፈጣጠሩ እንዴት ነበር?

ሰይጣን ከየት መጣ? እግዚአብሔር ሆን ብሎ የፈጠረው ይሆን? እግዚአብሔር ሆን ብሎ ከፈጠረው ሰይጣን ለሚያደርሰው ጥፋት ሁሉ፣ እግዚአብሔር ተጠያቂ ይሆናል ማለት ነውን? ቅዱስ የሆነው እግዚ አብሔር እንዴት ሰይጣንን የመሰለ አጥፊ ይፈጥራል? ለመሆኑ ለነዚህ

ጥያቄዎቻችን አጥጋቢ መልስ ሊሰጠን የሚችለው ማን ነው? የዓለም የፍልስፍና መጽሐፍት የሚያረካንን ዓይነት መልስ ሊሰጡን አይችሉም። የሃይማኖት ሊቃውንትም ቢሆኑ መልሳቸው ሊያረካን አይችልም። ትክ ክለኛና አጥጋቢ መልስ ሊሰጠን የሚችለው የእግዚአብሔር ቃል ወይ ንም መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው።

አንዳንዶቻችን ሰይጣን ከሰማይ ተወርውሮ የወደቀ ፍጡር እንደ ሆነ እንወቅ እንጂ እንዴት እንደወደቀ በደንብ አይገባንም። ኢየሱስ «ሰይጣን እንደ መብረቅ ተወርውሮ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ» ይላል (ሉቃስ 10:18)። እዚህ ላይ ኢየሱስ ምን ማለቱ ነው? ከታሪክ በፊት በሰማይ ስለተከናወነው ጦርነት መግለጹ ይሆን? ወይንስ ወደ ፊት ስለሚፈጸመው ሁኔታና ሰይጣን ስለሚደርስበት የመጨረሻ ሽንፈት ትንቢት መናገሩ ይሆን? የትኛው ልክ እንደሆነ በግልጽ ማወቅ ያስቸ ግራል። ይሁን እንጂ የኢየሱስ አነጋገር አንዳንድ ነገሮችን ግልጽ ያደርግልናል። ይኸውም ሰይጣን ከዚህ በፊት መልካም አቋም ኖሮት ከእግዚአብሔር ጋር በሰማይ ይኖር እንደነበረና፥ ከእግዚአብሔር ጋር ራሱ በፈጠረው ጦርነት ምክንያት ተወርውሮ እንደወደቀ መረዳት እንችላለን።

ሉሲፈር ዋና ዓላማው የእግዚአብሔርን ዕቅድ ማበላሸት ነው። በትንቢተ ሕዝቅኤል መጽሐፍ ውስጥ፥ ነቢዩ ሕዝቅኤል በእስራኤል ጠላ ቶች ወይንም እስራኤልን በሚያሳድዱ ሕዝቦች ላይ የሚደርስባቸው የእግዚአብሔር ፍርድ ምን እንደሆነ ይዘረዝራል። ትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 28:1-10፥ በጢሮስ ላይ ስለሚደርሰው ፍርድ ሲናገር፥ በዚሁ ምዕራፍ ከቁጥር 11-17 ደግሞ፥ ከምድራዊው ከጢሮስ ንጉሥ በላይ ስለሆነውና፥ የጢሮስን ንጉሥ ስለሚቆጣጠረው ሌላ ኃይል ይናገራል። ያም «ኃይል» ሰይጣን ነው። እንደምናውቀው ሰይጣን ተግባሩን ከሚያ ከናውንባቸው መንገዶች መካከል አንደኛው ፈቃዱን ሊፈጽሙለት በሚችሉት ሰዎች በመጠቀም ነው።

በእስራኤል አማካኝነት የሚጠበቀው መሲህ ወደ ምድር ከመጣ ሰይጣን ከፍተኛ መሸነፍ እንደሚደርስበት ስለሚያውቅ፥ ይህ መሲህ እንዳይመጣ አስቀድሞ እስራኤልን ለማጥፋት አረማውያንን ያስነሳባቸው ነበር። እስራኤልን የሚያሳድዱ ሕዝቦችም፥ የሰይጣን ብልሃቱና ምክ ንያቱ ሳይገባቸው የእርሱን ፕሮግራምና ዕቅድ ለማስፈጸም ይታገሉ ነበር። በዚህ ምክንያት ሕዝቅኤል፥ እስራኤልን በሚያሳድዱት ህዝቦች ላይ ስለሚደርሰው ፍርድ ተነበየ። ትንቢቱ እስራኤልን ለማጥፋት በተ ነሱ ሕዝቦች ላይ የሚደርሰውን ቅጣት የያዘ ብቻ ሳይሆን፥ የራሱን ፕሮግራም በእህዛብ አማካኝነት ለመፈጸም የሚጣደፈውም ሰይጣን፥ ስለሚጠብቀው ፍርድ ይናገራል።

ሕዝቅኤል በጢሮስ ላይ ስለሚደርሰው ፍርድ በሦስት ምዕራፎች (ከምዕራፍ 26-28) ውስጥ የተጻፈውን ይተነብያል። ጢሮስ ከእስራኤል በስተ ሰሜን የምትገኝ ደሴት ስትሆን፥ ከእስራኤል ጠላቶች መካከል

በጣም ኃይለኛ የሆኑት «ፎኒሽያንስ» እየተባሉ በሚጠሩ ሕዝቦች የተያዘች ነበረች። ጢሮስ በጣም ኃይለኛና ሀብታም ከመሆኗም ሌላ፣ ኃይሏንና ሥልጣኗን ያለአግባብ የምትጠቀም አምባገነን አገር ነበረች። ሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ ሲናገር፣ «እግዚአብሔር እንዲህ ሲል እንደገና ተናገረኝ፤ የሰው ልጅ ሆይ! የጢሮስ ንጉሥ ስለሚገጥመው መጥፎ ዕድል ሙሾ አውጣ፤ እኔ ልዑል እግዚአብሔር የምለውንም እንዲህ ብለህ ንገረው፤ በጥበብ የሞላህና እጅግ መልከ ቀና በመሆንህ የፍጹምነት ምሳሌ ነበርክ» ይለዋል (ሕዝ. 28:11-12)።

ምዕራፍ 28፣ መጀመሪያዎቹ አሥር ጥቅሶች ውስጥ ስለ ጢሮስ ንጉሥ፣ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ስለ ጢሮስ ገዢ (ስለ ሰይጣን) የተነገረውን ሙሾ ይዟል። መጀመሪያው ክፍል ላይ የተዘረዘረው ሥጋ ለባሹን ሰው የሚገልጽ ሲሆን፣ ሁለተኛው ክፍል ላይ የተጠቀሰው ግን ስለ «ሰው» የተጻፈ ነው ብሎ መገመት ትልቅ ስህተት ይሆናል። ይሁን እንጂ ሁለቱንም ይቆጣጠራቸው ወይንም ይመራቸው የነበረው መንፈስ አንድ ዓይነት ነበር። ሁለቱም ግሩም የሆነ ውበት፣ ጥበብና ኃይል ያላቸው ነበሩ። ሁለቱም በህያው እግዚአብሔር ላይ ያመጹ ነበሩ። ስለ ጢሮስ «ገዢና» ስለ ጢሮስ «ንጉሥ» በሁለት ክፍል የተጻፈውን ሙሾ በጥንቃቄ ብንመለከት ተመሳሳይነታቸውን እናያለን። ሰው የሆነው የጢሮስ ንጉሥ ከውበቱ፣ ከጥበበኛነቱና ከሀብታምነቱ የተነሳ ኩራት እንደተሰማውና በመጨረሻም እንደጠፋ እናያለን። ከጢሮስ ንጉሥ በስተኋላ ያለው ወይንም እርሱነቱን የሚቆጣጠረው መንፈስ ከጢሮስ ንጉሥ ጋር ተመሳሳይ ባህሪ እንዳለው እናያለን። «ሰይጣን» ብለን የምንጠራው የመጀመሪያ መታወቂያ ስሙ «ሉሲፈር» ሲሆን፣ ትርጉሙም «አንጸባራቂው» ማለት ነው። በዚህ ውስጥ ሕዝቅኤል የሰይጣንን አመጣጥ ትክክለኛ ብርሃን ይፈነጥቃል። አጻጻፉ የግጥም ሥርዓት የተከተለ ሲሆን ሀሳቡ ድብቅና ምስጢራዊ ነው።

ሉሲፈር ተፈጣሪ እንጂ ያለፈጣሪ በራሱ ኃይል እንዲሁ የመጣ አይደለም፤ «ጠባይህም ከተፈጠርህበት ጊዜ አንስቶ ክፉት ማድረግ እስከ ጀመርህበት ጊዜ ድረስ ፍጹም ነበር» (ሕዝ. 28:15) ሲል ተፈጣሪነቱን ያሳየናል። ፈጣሪ የሌለው ዘለዓለማዊ የሆነ እግዚአብሔር ብቻ ነው። በዓለም ላይ የሚታየው ነገር ሁሉ መኖር የቻለው እግዚአብሔር ስለ ፈጠረው ነው። ተፈጣሪ የሆነ ሁሉ፣ ፈጣሪ ከሆነው ከእግዚአብሔር ፍጹም የተለየ ነው። እግዚአብሔር በመፍጠር ተግባሩ ቁጥር ሥፍር የሌላቸውን የመላእክት ሠራዊትን ሲፈጥር ሉሲፈርም ከእዚያ መካከል አንደኛው ነበር። ተፈጣሪ እንደመሆኑ መጠን እግዚአብሔርን ማምለክ፣ ማገልገልና መታዘዝ ግዴታው ነበር። ሉሲፈር ግን በእግዚአብሔር ላይ አመጸ።

ሉሲፈር እግዚአብሔር ከፈጠራቸው መላዕክት ሁሉ፣ ለእግዚአብሔር በጣም የቀረበ ነበር። መኖሪያው በተቀደሰ ተራራ ላይ የነበረ ሲሆን፣ በጥበብ የተሞላና እጅግ መልከ ቀና በመሆኑ የፍጹምነት

ምሳሌ ነበር። የተለያዩ መላእክት የተለያየ ተግባር እንዳላቸው ሁሉ እግዚአብሔርን ብቻ እንዲያገለግሉ የተመደቡ መላእክትም አሉ። «ንጉሥ ዖዝያ በሞተበት ዓመት እግዚአብሔርን አየሁት፤ እርሱም ከፍ ባለና ልዕልና ባለው ዙፋን ላይ ተቀምጦ መንኮራኩሮቹም ቤተ መቅደሱን ሞልቶት ነበር። ሱራፌል ተብለው የሚጠሩ እሳታውያን መላእክትም በዙሪያው ነበሩ፤ እያንዳንዱ መልአክ ስድስት ክንፍ አለው፤ በሁለቱ ክንፎቹ ፊቱን ይሸፍናል፤ በሁለቱ ክንፎቹ እግሮቹን ሸፍና በሁለት ክንፎቹ ይበር ነበር፤ አንዱ መልአክ ከሌላው ጋር በመቀባበል ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፤ ክብሩም በዓለም ሁሉ የሞላ ነው» ይላል (ኢሳ. 6:1-3)። እነዚህ መላእክት በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ በመገኘት እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ሲሆኑ፥ ሉሲፈር የእግዚአብሔርን ዙፋን እንዲጋርድ የተቀባ ኪሩብ ነበር። ይሁን እንጂ «መልክ ቀና በመሆንህ እጅግ ታብየህ ነበር፤ ክብር በመፈለግህም ጥበብን አረከስህ፥ ከዚህም የተነሳ አምዘግዝጌ ወደ መሬት ጣልሁህ» (ሕዝ. 28:17) አለው።

በኤፌሶን 1:21 ላይ እንደምናነበው፥ «ባለ ሙሉ ሥልጣን፥ ኃያል... ገዢ...» በሚለው ጥቅስ ውስጥ መላእክት የተለያየ ተግባርና ሥልጣን እንዳላቸው መገንዘብ እንችላለን። አንዳንድ መላእክት ተግባራቸው ቅዱሳንን መጠበቅ ነው። ዕብ. 1:14 «መላእክት የሚድኑትን ለማገልገል የሚላኩ የእግዚአብሔር አገልጋዮች የሆኑ መንፈሶች አይደሉምን?» ይላል። ዓለምን የሚጠብቁና የሚከላከሉ መላእክት ባይኖሩ ኖሮ አጋንንት ዓለምን በእጃቸው ሥር በማስገባት ሰዎች ክርስቶስን እንዳይቀበሉ በተከላከሉ ነበር። ገና በእናታችን ማህጸን ሳለን ጀምሮ በሥጋ ከተወለድንና ክርስቶስን እንደ አዳኛችን አድርገን እስከምንቀበል ድረስ የሚጠብቁን፥ ከተቀበልንም በኋላ ጥበቃቸውን የማያቋርጡ መላእክት ስላሉን ለልባችን መጽናናትን ይሰጠናል።

ሕዝቅኤል 28:14 «አንተን እንደ ጠባቂ ኪሩብ አድርጌ በመሾም በዚያ መደብሁህ፤ በተቀደሰው ተራራዬ ላይ ትኖር ነበር፤ እጅግ በሚያብረቀርቁ የከበሩ ድንጋዮች መካከል ትመላለስ ነበር» ይለዋል። በዚህ ጥቅስ መሠረት ሉሲፈር የእግዚአብሔርን ዙፋን እንዲጠብቁ ከተቀቡት ኪሩቤሎች መካከል አንዱ ብቻ ሳይሆን በእነርሱ ላይ አለቃ ወይንም የበላይ እንዲሆን በእግዚአብሔር የተሾመ ነበር። ይህንን ሹመት በራሱ ጥረት ያገኘው ሳይሆን፥ ሲፈጠርም ለዚሁ አገልግሎት ታስቦ የተፈጠረ ነበር። እነዚህ ኪሩቤል ከሌሎች መላዕክት በሥልጣን የላቁና እንዲሁም በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ ሆነው የሚያገለግሉ መላእክት ናቸው። ስልጣን ሁሉ የእግዚአብሔር ቢሆንም፥ ሉሲፈር እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ በአስተዳደር ከሌሎች መላዕክት የበለጠ ኃይልና ሥልጣን የተሰጠው ነበር።

የእግዚአብሔር ቃል ሉሲፋርን «በጥበብ የተሞላህና እጅግ መልከ ቀና በመሆንህ የፍጹምነት ምሳሌ ነበርክ» ይለዋል። እግዚአብሔር

ሉሲፈር የእርሱን ክብር እንዲያንጸባርቅ ውብና ጠቢብ አድርጎ የፈጠረው፣ በኪሩቤሉ ሁሉ ላይ አለቃ እንዲሆንና የእግዚአብሔርን ዙፋን እንዲጠብቅ ነበር። ይሁን እንጂ ከሌሎች መላእክት ሁሉ ብልጫ እንዲኖረውና የተለየ እንዲሆን ያበቁት ነገሮች፣ ለመውደቂያው ምክንያት ሆኑበት።

## ለ ሉሲፈር ከነበረው ክብር የወደቀበት ምክንያት

በሉሲፈር ልብ ውስጥ ገብተው የመውደቂያ ምክንያት የሆኑበትን ነገሮች የእግዚአብሔር ቃል (ኢሳ. 14:12-14) ደረጃ በደረጃ ያቀርብልናል። በዚህ ቃል ውስጥ በእግዚአብሔር ፈቃድና በሉሲፈር ፈቃድ መካከል የተፈጠረውን ግጭት እናያለን። እግዚአብሔር ሉሲፈርን ሲፈጥረው የወደቀ ሰይጣን፣ በእግዚአብሔር ላይ የሚያምጽ እንዲሆን አድርጎ ሳይሆን፣ እንዲታዘዘውና እንዲሰግድለት ነበር። እግዚአብሔር «የመምረጥ» ችሎታና ነጻነት ሰጥቶት ስለነበር፤ የተሰጠውን የመምረጥ መብት ተጠቅሞ፣ ሉሲፈር ከእግዚአብሔር ፈቃድና ውጪ «አደርጋለሁ!» «እሆናለሁ!» በማለት የራሱን ፈቃድ ማስቀደምን መረጠ። ሰይጣን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ያስወጡት የራሱ ፍላጎቶቹ እንደ ሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

ሉሲፈር «ወደ ሰማይ እወጣለሁ» ሲል፣ ሥልጣን ሁሉ ካለው ኃያሉ እግዚአብሔር ከሚኖርበት፣ ኃይሉን ሁሉ ከሚገልጥበት ከዚያ ከከፍተኛ ሥፍራ እወጣለሁ ማለቱ ነበር። ሉሲፈር ከፍጥረታት ሁሉ ከፍ ያለ፣ ከእግዚአብሔር ግን ዝቅ ያለ ደረጃ የነበረው ነበር። ይሁን እንጂ ከተሰጠው ሥፍራ በላይ፣ ወይንም እግዚአብሔር ካለበት ደረጃ ከፍ ብሎ ለመገኘት ተመኘ። ወደ ሰማይ ከፍ ለማለት የተመኘው እግዚአብሔርን ለማምለክ ሳይሆን፣ እንደ እግዚአብሔር በዚያ ለመቆየት ነበር። የእግዚአብሔር ዙፋን ጠባቂ እንዲሆን የተሾመው ሉሲፈር የእግዚአብሔር እኩያ ለመሆን ምኞት አደረበት። የእግዚአብሔርንም ዙፋን ከእግዚአብሔር ነጥቆ ለመቀመጥ ሞከረ። በዚህ ምክንያት ነው እግዚአብሔር ወደ መሬት አምዘግዝጎ የወረወረው።

የእግዚአብሔር ከዋክብት፣ የእግዚአብሔርን ክብር ያንጸባርቃሉ እንጂ በውስጣቸው የራሳቸው የሆነ ሕይወት የላቸውም። ታዲያ «በእግዚአብሔር ከዋክብት ላይ ዙፋንህን ለመዘርጋት ወስነህ ነበር» (ኢሳ. 14:13) ሲል ምን ማለቱ ነው? «በዚያን ቀን ማለዳ ከዋክብት እንደዘመሩ የሰማይ መላእክትም ተደስተው እልል እንዳሉ ታውቃለህን» (ኢዮብ 38:7) በማለት እግዚአብሔር ኢዮብን ሲጠይቀው እንሰማለን። «የማለዳ ከዋክብት» የሚላቸው «የእግዚአብሔር ልጆችን» ሲሆን፣ የእግዚአብሔርን ክብር ሲያዩ በዕልልታ የዘመሩትን «የመላእክትን ሠራዊት» ማለቱ ነው። ስለዚህ ሰይጣን «በእግዚአብሔር ከዋክብት

ላይ ዙፋኔን እዘረጋለሁ» ሲል፥ እግዚአብሔር በመላዕክት ላይ ካለው ሥልጣን በላይ ስልጣኔን አደርጋለሁ» ማለቱ ነበር።

ከእግዚአብሔር ቃል እንደምንረዳው መላእክት «ተፈጣሪዎች» ስለሆኑ ራሳቸውን ለፈጠራቸው አምላክ ያስገዛሉ። ሉሲፈርም በእግዚ አብሔር ፈቃድ የመላእክት ሁሉ አለቃ (የበላይ) እንዲሆን ሙሉ ሥልጣን የተሰጠው ፍጡር እንደ ነበር እናውቃለን። ነገር ግን እግዚ አብሔር ሌሎች መላእክትን እንዲያስተዳድር ሥልጣን ቢሰጠውም እርሱ ራሱ በእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር ነበር። «በእግዚአብሔር ከዋክ ብት ላይ ዙፋኔን እዘረጋለሁ» ሲል ሰይጣን «ራሴን ለእግዚአብሔር ሳላስገዛ ሥልጣኑን ለብቻዬ እይዛለሁ» ማለቱ ነበር። የተቀሩት መላ እክት ወደ ሉሲፈር ሲመለከቱ፥ ትዕዛዙን የሚሰጠው ከእርሱ በላይ ሥልጣን ያለው እግዚአብሔር እንዳለ ያውቁ ነበር። አሁን ግን «ፍጹም ሥልጣን ይገባ ትዕዛዝን ከእግዚአብሔር በመቀበል ፈንታ እኔው ራሴ እየሰጠሁ እግዚአብሔርን ፍጹም እንዳይታይ እጋርደዋለሁ» ማለቱ ነበር። በዚህ ዓይነት ሰማይን መያዝ ብቻ ሳይሆን፥ የማስተዳ ደሩንም ሥልጣን መያዝ እንደ ፈለገ እናያለን።

ኢሳያስ «የዘመኑ ፍጻሜ ሲደርስ፥ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የተሠራበት ተራራ፥ ከሌሎች ተራራዎች ሁሉ በልጦ ይታያል፤ ከኮረብታዎች ሁሉ እጅግ ከፍ ይላል» አለ (ኢሳ. 2:2)። በዚህ ጥቅስ ላይ «ተራራና ኮረብታ» የሚያመለክተው መሲሁ በምድር ላይ የሚ ኖረውን ኃይልና ሥልጣን ነው። መሲሁ ዳግመኛ ሲመለስ ዙፋኑን ይመሠርታል። በሚመሠርተውም መንግሥቱ ላይ ይነግሣል። ስለዚህ ሉሲፈር «በስተሰሜን ዳርቻ አማልክት በሚሰበሰቡበት ተራራ ላይም እነግሣለሁ» ሲል በተፈጠረው ጠቅላላ ዓለም (ዩኒቨርስ) ላይ የበላይ ሆኜ አስተዳድራለሁ ማለቱ ነበር።

«አሮንም ለመላው ማኅበር በተናገረ ጊዜ ፊታቸውን ወደ በረሃው አዞሩ፤ የእግዚአብሔርን ክብር የሚገልጠው አንጸባራቂ ብርሃን በደመና ተገለጠ» ይላል (ዘጸ. 16:10)። እስራኤላውያን ከግብጽ ምድር ወጥተው በበረሃ ሲጓዙ እግዚአብሔር አብሮአቸው ይንቀሳቀስ ነበር። ደመናው ሲገለጥ እግዚአብሔር ከነርሱ ጋር መሆኑንና ከፊት ለፊታቸው መቅ ደሙን ያውቁ ነበር። በሌላ ጊዜ ደግሞ ሙሴ ድንኳኑን ሠርቶ ከጨ ረሰ በኋላ ድንኳኑ በደመና እንደተሸፈነና የእግዚአብሔርን ክብር የሚገልጠው አንጸባራቂ ብርሃን ድንኳኑን እንደሞላው እናነባለን (ዘጸ. 40:33)።

በአዲስ ኪዳንም ኢየሱስ በማቴ. 24:30 ላይ ስለ ዳግመኛ ምጽዐት ሲናገር «የሰው ልጅም በኃይልና በታላቅ ክብር በደመና ላይ ሆኖ ሲመጣ ያዩታል» ይላል። በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን «ደመና» የእግዚአብሔርን በክብር መገለጥ የሚያሳይ ነው። ስለዚህ

ሉሲፈር «ከደመናው በላይ እወጣለሁ» ሲል «እግዚአብሔር ካለው ክብርና ውበት ሁሉ የበለጠ ይኖረኛል» ማለቱ ነበር። ቀደም ሲል ሕዝቅኤል ሉሲፈር ያለውን አንጸባራቂ ውበት ገልጿል፤ ያ ውበት ግን ከእግዚአብሔር የተሰጠው እንጂ ከራሱ የመነጨ አልነበረም። በእግዚአብሔር ላይ የሚታየው አንጸባራቂ ክብር ግን ከራሱ ከእግዚአብሔር የሚወጣ ነው። የሉሲፈር ፍላጎትና ምኞት ዓለምን ሁሉ ለመግዛትና የእግዚአብሔር የሆነውን ክብር የራሱ አድርጎ ለመውሰድ ነበር። ወሰን የሌለውን የእግዚአብሔርን ክብር አገኛለሁ ብሎ ማሰብ ምን ያህል ትልቅ ሞኝነት ይሆን?

ሉሲፈር «ተፈጣሪ» መሆኑን የተገነዘበው አይመስልም። «ተፈጣሪ» እንዴት «ፈጣሪ» መሆን ይችላል? ሉሲፈር «ሁሉን እንደሚችል አምላክ እሆናለሁ» ሲል ፈጣሪ እሆናለሁ ማለቱ ነበር። ሉሲፈር እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረቶች ሁሉ በጥበብ የላቀ ነው፤ ይሆን እንጂ ሁሉን ማወቅና ሁሉን ማድረግ የሚችል አይደለም። ከአንድ ሥፍራ ወደ ሌላ ሥፍራ በፍጥነት መንቀሳቀስ ይችላል፤ «በአንድ ጊዜ ሁሉ ቦታ መገኘት» ግን አይችልም። ታዲያ በምን ዓይነት ሁኔታ ነው ሁሉን እንደሚችል አምላክ መሆን የሚችለው? የሉሲፈር ምኞት የእግዚአብሔርን ዙፋን ይዞ በሰማይ በሚኖሩት መላእክትና እንዲሁም በምድር በሚኖሩት ፍጥረታት ሁሉ ላይ የበላይ ሆኖ ለመኖር ነበር።

ሉሲፈር ለኃይልና ለክብር እንደዚህ እንዲጠማ ያደረገው ለመሆኑ ምን ይሆን? ባለው ኃይልና መልክ ቀናነት ስለታበየ ነበር። «መልክ ቀና በመሆንህ እጅግ ታብየህ ነበር፤ ክብር በመፈለግህም ጥበብን አረከስክ፤ ከዚህም የተነሳ አምዘግዝጌ ወደ መሬት ጣልሁህ» ይለዋል (ሕዝ. 28:17)። እንግዲህ ሰው በዚህ ዓይነት ራሱን ከእግዚአብሔር ውጪ አድርጎ ሲመለከትና በራሱ ፈቃድ ብቻ ሲመራ፣ ሉሲፈር የፈጸመውን ዓይነት አመጽ ወይንም መተላለፍ እየፈጸመ መሆኑን መርሳት የለበትም።

3

# የሰይጣን እንቅስቃሴውና አሠራሩ

አንዳንድ አማኞች «የተሸነፈ» የክርስትና ሕይወት የሚኖሩት የጠላታቸውን የሰይጣንን አሠራርና እንቅስቃሴ፣ እንዲሁም ከእርሱ ጋር የሚያኪያሂዱት ጦርነት ምን ዓይነት እንደሆነ በቂ ግንዛቤ ወይንም መረዳት ስለሌላቸው ነው። ይህ ጠላት ራሱን የመደበቅና ሌላ መልክ ይዞ የመቅረብ ከፍተኛ ችሎታ ስላለው፣ ብዙዎች ተንኮለኛ መሆኑን ብቻ ሳይሆን መኖሩንም እንኳን ይጠራጠራሉ። አማኝ የሚሳተፍበት ጦርነት ምን ዓይነት እንደሆነና እንዲሁም ውጊያው ከማን ጋር እንደ ሆነ በደንብ ካላወቀ፣ በመንፈሳዊ ሕይወቱ አሸናፊ ሆኖ መኖር አይ ችልም። ጳውሎስ የአማኞች ውጊያ ከማን ጋር እንደሆነ ሲገልጽ፣ «የእኛ ውጊያ ከሰዎች ጋር ሳይሆን በዚህ በጨለማ ዘመን ከሚሠሩት ገዥዎች፣ ከባለ ሥልጣኖችና ከዓለም ኃይሎች፣ ይህም ማለት በሰማይ ካሉት የርኩሳን መናፍስት ሠራዊት ጋር ነው» ይላል (ኤፌ. 6:12)። ይህ ጠላት፣ በሥጋዊ ዓይን የማይታይ ከመሆኑም በላይ፣ አማኝ ብቻ ውን ሊያሸንፈው የማይችለው ኃይለኛና የሚያስፈራ ባላጋራ መሆኑን ማንኛውም አማኝ ሊያውቀው የሚገባ እውነት ነው።

ሰይጣን ተፈጣሪ በመሆኑ «በሁሉ ሥፍራ በአንድ ጊዜ መገኘት» (Omnipresent) አይችልም። መላእክትም ቢሆኑ ተፈጣሪዎች በመሆናቸው በአንድ ጊዜ ሁሉ ቦታ የመገኘት ችሎታ የላቸውም። ሉሲፈር ያለው ኃይልና ችሎታ «ውስን» የሆነው በእግዚአብሔር ላይ አምጾ «ሰይጣን» ከሆነ በኋላ ሳይሆን፣ መጀመሪያ ሲፈጠርም የነበረው ኃይል «ውስን» ነው። ሰይጣን ተፈጣሪ በመሆኑ፣ ፈጣሪ

የሆነው እግዚአብሔር ብቻ ያለውን ዓይነት «ፍጹም ኃይል» እንዲኖረው ሆኖ አልተፈጠረም። ስለዚህ ሰይጣን በአንድ ጊዜ ሁሉ ሥፍራ መገኘት ስለማይችል፥ በእግዚአብሔርና እንዲሁም በዓለም ዙሪያ በሚገኙት በእግዚአብሔር ሕዝቦች ላይ የማያቋርጥ ጦርነት የሚያካሂደው ከእርሱ ጋር አምጸው በወደቁት እርኩሳን መናፍስት በመጠቀም ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ላይ ስላመጹት መላእክት ብዙ አይናገርም። የሚገልጸው ነገር ቢኖር፥ ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ባመጸበት ጊዜ አያሌ መላእክትም እንደ እርሱ አምጸው ስለነበረ፥ የእርሱን ዓላማና ፈቃድ የተከተሉት መላእክት ሁሉ ርኩሳን መናፍስት ተብለው መጠራታቸውን ነው። ሰይጣን አስመስሎ መሥራት (መኮረጅ) ከባህሪው አንደኛው ስለሆነ፥ እግዚአብሔር ለመላእክቱ የተለያየ ደረጃና ሹመት እንደሰጠ ሁሉ፥ ሰይጣንም ለርኩሳን መናፍስቱ ልዩ ልዩ ሥልጣንና ኃላፊነትን ሰጥቷል። የተሰጣቸው ልዩ ልዩ ኀላፊነት ምን እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ አይነግረንም። የምናውቀው ነገር ቢኖር ግን ሁሉም ለአንድ ዓላማ እንደሚሠሩ ነው። ዓላማቸውም፥ እግዚአብሔርን መቃወምና እንዲሁም እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያወጣውን ዕቅድ ማደናቀፍና ማበላሸት ነው።

ሰይጣን ከሚገለገልባቸው ዘዴዎች መካከል በጣም የተጠቀመበትና ውጤታማ ሆኖ ያገኘው፥ የሰዎችን ውስጣዊ ልቡና በማሳወር «ሰይጣን የለም» ብለው እንዲያምኑና እንዲቀበሉ ማድረግን ነው። «ሰይጣን የለም» ብለው ካመኑ፥ ከእርሱ ጋር ጦርነት አይገጥሙም። ጠላታቸውን ካልተዋጉና ካልተከላከሉ ደግሞ ራሳቸውን ለሰይጣን አጋልጠው ስለሚያቀርቡ፥ በቀላሉ ሊያጠፋቸው እንደሚችል ግልጽ ነው። የሚያሳዝነው ብዙዎች የመላእክትን መኖር ቢያምኑም፥ ሕይወታቸውን ሊያበላሹ የሚችሉ ርኩሳን መናፍስት መኖራቸውን ግን መቀበል የሚያስቸግራቸው መሆኑ ነው። በተለይ «ተምረናል» ከሚሉት መካከል «ርኩሳን መናፍስት አሉ» ብሎ ማመን በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የነበረውን «አፈ ታሪክ» (superstition) መቀበል መስሎ የሚታያቸውና የሚሰማቸው ብዙዎች ናቸው። ሰይጣን ሕያውነቱን በዚህ ዓይነት እየደበቀ፥ የአማኞችን የክርስትና ሕይወት ወደ ኋላ ሲጎትትና በብዙዎች ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ጥፋትን ሲያደርስ ይታያል።

ርኩሳን መናፍስት፥ በማይታየው ዓለም ውስጥ የሚኖሩ፥ እንደ ሰው «ቁስ-አካል» ወይንም ሥጋና ደም የሌላቸው፥ ይኸውም መንፈስ ብቻ የሆኑ ናቸው። ራሳቸውን ማሳየት ወይንም መግለጽ የሚችሉት የሰውን ወይንም የእንስሳትን አካል በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው ከያዙ በኋላ በዚያ ሰው ሕይወት ውስጥ በሚፈጥሩት ትርምስና ሁከት ብቻ ነው። «በምኩራባቸው ርኩስ መንፈስ ያደረበት ሰው ነበር፤ እርሱ እንዲህ ሲል ጮኸ፤ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ! እኛ ከአንተ

ጋር ምን ግንኙነት አለን? ልታጠፋን መጣህን? አንተ ማን እንደ ሆንህ እኔ አውቃለሁ፤ አንተ እኮ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነህ። ኢየሱስም ርኩሱን መንፈስ «ዝም በል! ከእርሱ ውጣ» ብሎ ገሠጸው። ርኩሱ መንፈስም ሰውየውን ጥሎ ካንፈራገጠው በኋላ በታላቅ ድምጽ እየ ጮኸ ከእርሱ ወጣ» ይላል (የማር. 1:23-26)። እዚህ ላይ የርኩሳን መናፍስት ተፈጥሯዊ ባህሪ ምን እንደሆነ በግልጽ ሊታይ የቻለው የሰ ውየውን ሥጋ ከያዙ በኋላ በውስጡ በሚፈጥሩት ሁከትና ትርምስ ነው። ለዚህ ነው ኢየሱስ ርኩሱን መንፈስ «ዝም በል! ከእርሱ ውጣ!» ብሎ ካዘዘው በኋላ የሰውየው ሕይወት በጸጥታና በሰላም እንደገና የተሞላው። ሰዎች የክርስቶስን አዳኝነት ሰምተው እንዳይቀበሉ ርኩሳን መናፍስት ምን ያህል ከፍተኛ ረብሻና ተቃውሞ እንደሚያደርጉ በዚህ ሰው ሕይወት ውስጥ ማየት እንችላለን።

ስለ ጠላታችን ስለ ሰይጣን ሕያውነትና ተንኮለኛነት የእግዚአብ ሔር ቃል የሚሰጠንን ምክርና ማስጠንቀቂያ ችላ በማለት ከትልቅ ስህተት ውስጥ እንዳንወድቅ መጠንቀቅ ይገባናል። እግዚአብሔር በቃሉ ለፈጠራቸው ለሰዎች ልጆች አንድ ዓላማ አለው፤ ያም ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን፣ በሰማይና በምድር ሥልጣን ሁሉ የእርሱ ብቻ የሆነውን ጌታ አምነው እንዲቀበሉ፣ እንዲሁም ጉልበት ሁሉ ለእርሱ እንዲንበረከክ፣ ምላስ ሁሉ እርሱን እንዲያመሰግን ነው። ይሁን እንጂ ይህንን ዕቅድ ሰይጣን ለማጨናገፍ ያለማቋረጥ ከፍተኛ ጦርነቱን በሰ ዎች ሕይወት ውስጥ ያካሂዳል።

## ሀ

## ሰይጣን ዓላማውን ለመፈጸም የሚጠቀምባቸው መንገዶች

1. ሰይጣን ፈቃዱን ለመፈጸም ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንደኛው መንግሥታትን በራሱ ቁጥጥር ሥር በማዋል፣ ከእግዚአብሔር ዓላ ማና እንዲሁም ፈቃድ ውጪ እንዲዋሩ በማድረግ ነው። ሰይጣን በርኩሳን መናፍስቱ አማካኝነት የአንድን አገር የፖለቲካ እንቅስ ቃሴ በመጠቀም፣ መንግሥታትን፣ ልዩ ልዩ ድርጅቶችንና እን ዲሁም እንቅስቃሴዎችን ለራሱ ዓላማ የሚያውልበትን መንገድ ይቀይሳል። በዘመናት «ኃይልን» የተጠሙ አንዳንድ የአገር መሪዎች በሺና በሚሊዮን የሚቆጠሩትን ሰዎች ደም እንዴት እንዳፈሰሱ ታሪካቸውን ስንመረምር፣ ሰይጣን የማጥፋት ዓላማውን ምን ያህል በሰዎች እንደተጠቀመና አሁንም ቢሆን እንደሚጠቀም መገንዘብ እንችላለን።

2. እርኩሳን መናፍስት የማጥፋት ዓላማቸውን በተግባር የሚገልጹት፣ የአንድን አገር የፖለቲካ እንቅስቃሴና እንዲሁም የመሪዎችን ፍልስፍና በማስቀልበስ ብቻ ሳይሆን፣ ልዩ ልዩ የሃይማኖት ሥርዓትና እምነቶችንም ጭምር በመጠቀም ነው። ይሄን ዓይነቱ፡ የርኩሳን መናፍስት አሠራር፣ በብሉይ ኪዳን ዘመን በእስራኤል ሕዝብ መካከል በግልጽ ይታይ እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። «እውነተኞች ላልሆኑ አማልክት መስዋዕት አቀረቡላቸው፤ እነርሱም እስራኤላውያን ከቶ ያልተከተሉአቸው የቀድሞ አባቶቻቸውም ከቶ የማያውቋቸው እንግዶች አማልክቶች ናቸው» ይላል (ዘዳ. 32:17)። ሰዎች ለእንግዳ አማልክት መስዋዕት ሲያቀርቡ ለሰይጣን መስገዳቸው እንደሆነ ግልጽ ነው። ጳውሎስም ስለዚሁ ሁኔታ ሲናገር፣ «በኋለኛው ዘመን አንዳንድ ሰዎች አሳሳች መናፍስትንና የአጋንንትን ትምህርት በመከተል ሃይማኖትን ይክዳሉ» ይላል (1 ጢሞ. 4:1)። ሰዎች ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ እንዳይሰጡና እውነትን እንዳያውቁ፣ ሰይጣን እውነት ያልሆኑ ሃይማኖቶችን በዓለም ዙሪያ እንዲስፋፉ ሲያደርግ ይታያል። ስለዚህ እውነትን በማጣመም ሀሰተኛ ትምህርትን የሚያሰራጩና የሚያስተምሩ፣ አጋንንት የሚጠቀምባቸው ሰዎች መሆናቸውን መረዳት አያዳግተንም።

3. ርኩሳን መናፍስት ሰዎችን የሚያጠቁበት ሌላ ዘዴና መንገዳቸው የሰውን ሥጋዊ አካል በበሽታ በመምታት ነው። «...ሌሎች ሰዎች ጋኔን ያደረበትን ድዳ ወደ ኢየሱስ አመጡ። ጋኔኑም ከወጣለት በኋላ ድዳው ሰው ተናገረ፤ ሕዝቡም እንዲህ ያለ ነገር በእስራኤል ከቶ ታይቶ አይታወቅም እያሉ ተደነቁ» ይላል (የማቴ. 9:32-33)። ያ ሰው ዲዳና ደንቆሮ የሆነው ርኩሳን መናፍስት ሕይወቱን አሥረው በመያዛቸው ምክንያት እንደሆነ ግልጽ ነው። ርኩሱ መንፈስ ሲወጣለት፣ ያ ሰው ወዲያው መናገርና መስማት እንደቻለ ታሪኩ ይመሰክራል። ይሁን እንጂ በሽታ በተለያየ ምክንያት በሰው ላይ ሊደርስ ስለሚችል፣ ሰው ሁሉ የሚታመመው ሁልጊዜ በእርኩስ መንፈስ ሲያዝ ነው ወደሚለው የተሳሳተ እምነት እንዳንገባ መጠንቀቅ ይኖርብናል።

4. ርኩሳን መናፍስት እንቅስቃሴያቸውንና ተግባራቸውን ሲፈጽሙ የሚታዩበት፣ የሰውን ሥጋዊ አካል በበሽታ በመምታት ብቻ ሳይሆን፣ አዕምሮውንም በመቆጣጠር ጭምር ነው። ክርስቶስ በምድር በነበረበት ዘመን አንድ ጊዜ አንድ አባት በርኩስ መንፈስ የተያዘውን ልጁን ወደ ኢየሱስ አምጥቶ «ጌታ ሆይ! እባክህ ለልጄ ራራለት፤ የሚጥል የጋኔን በሽታ ክፉኛ ያሠቃየዋል፤ በእሳት ላይና በውሃ ውስጥ ብዙ ጊዜ ይወድቃል» (የማቴ. 17:15) አለው።

ርኩሳን መናፍስት የዚያን ሰው አዕምሮ ምን ያህል በቁጥጥራቸው ውስጥ እንዳዋሉት መረዳት የምንችለው፥ ያ ሰው ከእስራቱ ከተፈታ በኋላ ያገኘውን ሰላም ስንመለከት ነው። ይህ ሰው ጉዳት ላይ ሊጥለው የሚችለውን ውሃና እሳት እንኳን ለይቶ ማወቅ ተስኖት እንደነበር ስናይ፥ ርኩሳን መናፍስት አዕምሮው በትክክል ማሰብ እንዳይችል አድርገውት እንደነበረ እንገነዘባለን። ከላይ እንደተመለከትነው ሰይጣን በርኩሳን መናፍስቱ አማካኝነት የሚያደርገውን ከፍተኛ እንቅስቃሴ ተረድተን፥ ይህንን ጠላታችንን በማጥቃትና በመከላከል መንፈሳዊ ውጊያችንንና ትግላችንን ማፋፋም ይገባናል።

በክርስቶስ አምኖ ያልዳነ ሰው፥ ከሰይጣን መንግሥትና ሥልጣን ሥር ራሱን አስገዝቶ የሚኖር ሰው በመሆኑ፥ ርኩሳን መናፍስት በፈለጉበት ጊዜ ወደ ውስጡ ሊገቡና በቁጥጥራቸው ሥር ሊያውሉት እንደሚችሉ የእግዚአብሔር ቃል ያረጋግጥልናል። የክርስቶስን አዳኝነት የተቀበለ አማኝ ግን፥ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነና እንዲሁም በክርስቶስ ኃይልና ሥልጣን ሥር ስለሚኖር፥ ርኩሳን መናፍስት ወደ ሕይወቱ በምንም ዓይነት የመግባት ኃይልና ችሎታ የላቸውም። ይሁን እንጂ አማኝ እያወቀ ራሱን ለርኩሳን መናፍስት ፈቅዶ ከሰጠና ካስገዛ፥ ርኩሳን መናፍስት ሕይወቱን ሊይዙና ሊቆጣጠሩ ይችላሉ። ርኩሳን መናፍስት ባይዙትም አማኝ የሥጋ ደዌ፣ የአዕምሮ ቀውስ፣ የመንፈስ መታወክ በተለያየ ምክንያት ሊደርስበት የሚችል መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ፈቅዶ ራሱን ለርኩሳን መናፍስት ከሰጠ ግን በርኩሳን መናፍስት አማካኝነት የሚመጡ ከላይ የገለጽናቸው ችግሮች ሁሉ በሕይወቱ ሊደርስበት ይችላል።

አንዳንድ አማኞች ከሚገባው በላይ ስለ ርኩሳን መናፍስት በማሰብ አዕምሮአቸውን እረፍት ይነሱታል። ትንሹንም ሆነ ትልቁን የሚያሳብቡት በርኩሳን መናፍስት ነው። ለምሳሌ፥ የመኪናቸው ጎማ ቢተነፍስ፥ የጣዱት ምግብ ሳያማስሉት ቀርቶ ቢያርባቸው፥ ወይንም ቢገነፍል፥ ልጃቸው ኩፍኝ ቢይዘው፥ የደሞዝ ጭማሪ ባያገኙ፥ «ሰይጣን እየተዋጋኝ ነው» በማለት ምክንያት ሲሰጡ ይሰማሉ። ከሚገባው በላይ ስለ «ርኩሳን መናፍስት» በማሰብ አዕምሮአችን ሲያዝ፥ ሰይጣን በሌለበት ሥፍራ ሁሉ እንዳለ ሆኖ እንዲታየን ይሆናል። ምናልባት ይሄ ይህን ያህል አሳሳቢ ላይሆን ይችላል። አሳሳቢ የሚሆነው ግን፥ ሰይጣን በሌለበት ሥፍራ ሁሉ «አለ» በማለት በየነፍሱ እየገባን ርኩሳን መናፍስትን ስናባርር፥ በግል ሕይወታችን ውስጥ ግን በስውር የሚያኪያሄዱትን እንቅስቃሴና እንዲሁም የሚፈጥሩትን ትርምስ ማየት የተሳነን እንደሆነ ብቻ ነው።

ክርስቶስ ርኩሳን መናፍስትን የመቆጣጠር፥ የማዘዝ ኃይልና ሥልጣን ስለነበረው፥ በሄደበት ሥፍራ ሁሉ በእርኩሳን መናፍስት የተያዘ ሰው ሲያጋጥመው፥ «ዝም ብለህ ከእርሱ ውጣ» በማለት ይገስጽ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (ሉቃስ 4:35)። ርኩሳን መናፍስትም ከእርሱ ትዕዛዝ ውጪ መሆን፥ ወይንም «እምቢ!» ማለት ስለማይችሉ «ልቀቁ» የተባሉትን ሰው ለቀው ይወጡ ነበር። አንድ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ጋኔን ያደረበትን ልጅ ለምን መፈወስ እንዳቃታቸው ክርስቶስ ከተራራው ሲወርድ ጠይቀውት፥ «እምነታችሁ ጎዶሎ ስለሆነ ነው፤ በእውነት እላችኋለሁ፥ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ ይህን ተራራ «ከዚህ ተነስተህ ወዲያ ሂድ!» ብትሉት ይሄዳል፤ የሚሳናችሁም ምንም ነገር አይኖርም» አላቸው (የማቴ. 17:20)። ኢየሱስ እዚህ ላይ ለደቀ መዛሙርቱ ለመግለጽ የሞከረው ሁለት ጠቃሚ ሀሳብ እንዳለ እናያለን። አንደኛው፥ «የሰናፍጭ ቅንጣት» የሚያህል እምነት ቢኖራቸው የሰይጣንን መንግሥት ወይንም ርኩሳን መናፍስትን ማባረር (ማስወጣት) እንደሚችሉ ነበር። ሁለተኛው፥ «ይህን ዓይነቱ እርኩስ መንፈስ በጸሎትና በጾም ካልሆነ በቀር ከቶ አይወጣም» ሲላቸው ደግሞ፥ ማሸነፍ የሚችሉት በራሳቸው ኃይል ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ፍጹም በመታመን ብቻ እንደሆነ ሲገልጽላቸው ነው። ዛሬም እኛ በርኩሳን መናፍስት ላይ ሥልጣን እንዳለንና እንዲሁም ያ ሥልጣን ከራሳችን የመነጨ ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው መሆኑን ብናምን፥ ከሰይጣን ጋር በምንገጥመው ጦርነት ሁሉ አሸናፊዎች እንደምንሆን እናውቃለን። የእግዚአብሔር ቃል «...በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ...» (የማር. 16:17) ስለሚል፥ ማንኛውም አማኝ እርኩሳን መናፍስትን ለመቋቋም ሙሉ ሥልጣን እንዳለውና እንዲሁም እርኩሳን መናፍስትን ከሰው ሕይወት ውስጥ ማስወጣት እንደሚችል እንረዳለን። ይህ ዓይነቱ ሥልጣን የሚሰጠው ለተወሰኑ ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆን፥ አምነው በስሙ ለሚጠቀሙ ሁሉ ነው።

ሰይጣን በሰው ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ጥፋት ማድረስ የሚችለው፥ የሚያደርገው እንቅስቃሴ በደንብ ያልታወቀበት እንደሆነ ብቻ ነው። ቀደም ሲል እንደገለጽነው ሰይጣን ራሱን የሚደብቅበት ዋና ዘዴው ሰዎች «የእርሱን ሕያውነት» እንዲጠራጠሩ ወይንም እንዳያምኑ በማድረግ ነው። በዚህ ዓይነት ራሱን መሰወር ከቻለ፥ «በእግዚአብሔር ሰዎች ዘንድ እንቅስቃሴዬ ይታወቅብኛል» ብሎ ስለማይፈራ፥ ከፍተኛ ጥፋት በሰዎች ሕይወት ላይ ማድረስ ይችላል። ከአዲስ ኪዳን ጸሀፊዎች መካከል የሰይጣንን ሕያውነት በግልጽ ከጻፉት መካከል ሐዋርያው ጳውሎስና ሐዋርያው ጴጥሮስ ይገኙበታል። ጳውሎስ ሰይጣንን ሲገልጸው

«የዚህ ዓለም ገዢ፣ ...በሰማይ ያለ ኃይል፣ የብርሃን መልአክ» ሲለው፣ ጴጥሮስ ደግሞ «የሚያገሳ አንበሳ» ብሎ ይጠራዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰይጣን ህያውነትና ማንነት በግልጽ ቢጻፍም፣ ለምንድነው ሰዎች እውነተኛ ኃይሉንና ባህሪውን መረዳት ያቃታቸው? መንፈስ ቅዱስ ወደ ሕይወታቸው መግባት እንደሚችለው ሁሉ፣ ርኩሳን መናፍስትም ወደ ውስጣዊ ሕይወታቸው መድረስ እንደሚችሉ መረዳት የተሳናቸው ለምን ይሆን? የእያንዳንዱ ሰው ድክመት ምን እንደሆነ ሰይጣን በደንብ ያውቃል። ማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ ያንን ደካማ ጎናቸውን በመጠቀም የራሱ ተገዢ ሊያደርጋቸው ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያደርጋል። ታዲያ ይህን ዓይነቱን አጥፊ የሆነውን ጠላታቸውን ብዙዎች ለምን አቃለው ያዩታል?

ሰይጣን ራሱን ፍጹም ደብቆና ሸፍኖ በማቅረብ፣ በአማኞች ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳይፈጸም ትልቅ እንቅፋትን እንደሚፈጥር የእግዚአብሔር ቃል ይገልጻል። ሰይጣን በሕይወታቸው የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ያልተገነዘቡ አማኞች፣ ብዙ ጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የደከሙበትን ምክንያት ማወቅ ስለሚያቅታቸው፣ «የክርስትና ሕይወቴ ለምን ዕድገት አይኖረውም?» በማለት ራሳቸውን ሲጠይቁ ይሰማሉ። አንዳንዴ «እንግዳ ሀሳብ» ወደ አዕምሮአቸው ሲመጣ ከራሳቸው ውስጥ የመነጨ፣ የራሳቸው ሀሳብ ይመስላቸውና ይደነግጣሉ። «እንዲህ ዓይነት ባህሪ እንዲኖረኝና እንዲሁም ይህን የመሰለ ውሳኔ እንዳደርግ የተገደድኩት ከእኔ በላይ በሆነ ክፉ ኃይል ተደግፎ ይሆን?» ብለው ግን በመጠራጠር ራሳቸውን አይጠይቁም። ኢየሱስ አንድ ጊዜ ስለ መከራውና ስለ መስቀል ሞቱ ሲናገር ጴጥሮስ ሰምቶ፣ «ይሄ በአንተ ፈጽሞ አይድረስ» አለው። ኢየሱስም ይሄ ክፉ ሀሳብ ከጴጥሮስ እንዳልመነጨ ስላወቀ፣ «አንተ ሰይጣን ወዲያ ሂድ» ብሎ እንደ ገሰጸው እናስታውሳለን። በዚህ ዓይነት ያልተቀደሰ ሀሳብ ወደ እኛም ሕይወት ውስጥ ሲገባ፣ ምንጩ ከየት እንደሆነ ለይተን ማወቅ ይገባናል። ደጋግመን እንደገለጽነው ሰይጣን ራሱን ደብቆ ወይንም ሌላ መልክ ይዞ ስለሚቀርብ፣ ከብዙ ሀሳቦቻችንና ውሳኔዎቻችን በስተኋላ የሰይጣን ተንኮል እንዳለበትና እንደሌለበት በጥንቃቄ ራሳችንን መመርመርና መጠየቅ ያስፈልገናል። ሰይጣን የእኛን የግል «ፈቃድ» ወይንም ምርጫ ምን ጊዜም ቢሆን መጣስ ስለማይችል፣ እኛነታችንን ወይንም የሕይወታችንን አቅጣጫ እኛ ሳናውቀውና ሳንፈቅድ መለወጥ የሚችል ኃይል ይኖራል ብለን አንፈራም።

## ለ

# ሰይጣን ራሱን የሚደብቅባቸው ስፍራዎች

### 1ኛ ሰይጣን «በራስ ወዳድነት» መንፈስ ውስጥ ይኖራል።

ሰይጣን ከመጠን ባለፈ የራስ ፍቅር የተሞላና የታሠረ፥ ሁልጊዜ ለራሱ ብቻ የሚኖር ፍጥረት ነው። ከነበረበት ከፍተኛ ደረጃ ወደ ታች ሊጥለው የቻለውም ይኸው ባህሪው ነው። ሰይጣን በራሱ ፍቅር መያዙንና እንዲሁም «እኔ! እኔ!...» የሚለውን ቃል በጣም የሚወደው መሆኑን፥ ኢሳ. 14:13-14 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ በግልጽ ማየት እንችላለን። ሰይጣን፥

- «...ወደ ሰማይ እወጣለሁ...»
- «...ዙፋኔን እዘረጋለሁ...»
- «...አማልክት በሚሰበሰቡበት ተራራ ላይ እቀመጣለሁ...»
- «...ሁሉን እንደሚችል አምላክ እሆናለሁ...» ሲል እንሰማዋለን።

ሰይጣን በነበረው ውበት፥ ጥበብና ኃይል ምክንያት በራሱ ፍቅር የሰከረ ነበር። ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ማድረግ ወይንም ሁሉን እንደሚችል አምላክ ለመሆን መመኘቱ፥ በእግዚአብሔር እጅ መሥራት መሆኑን አልተረዳውም ነበር። ሰይጣን «እንደ እግዚአብሔር ለመሆን» የነበረው ጥማት ከፍተኛ ስለነበረ፥ የእግዚአብሔርን ዙፋን ለመንጠቅ ኃይለኛ ተጋድሎ አደረገ። በዚህ ጊዜ ነው እግዚአብሔር ወደ ጥልቁ የሙታን ዓለም አምዘግዝጎ የጣለው። ዛሬም የሰው የግል ፈቃድ ባየለበት፥ ራሱን ለማተለቅና የግል ፍላጎቱን ብቻ ለማርካት በሚታገልበት ሥፍራ ሁሉ፥ የሰይጣን እንቅስቃሴ በዚያ አካባቢ መኖሩን እናውቃለን።

### 2ኛ በአሮጌው ሥጋችን ውስጥ ሰይጣን ይደበቃል

ሰይጣን ከመውደቁ በፊት «ፍጹም» እንደ ነበር የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል። «ጠባይም ከተፈጠርህበት ጊዜ አንስቶ ክፋት ማድረግ እስከ ጀመርህበት ጊዜ ድረስ ፍጹም ነበር» ይለዋል (ሕዝ. 28:15)። እንዲሁም አዳም በኃጢአት እስከ ወደቀበት ጊዜ ድረስ

ምንም ዓይነት እንከን የማይገኝበት ፍጡር እንደ ነበር እናውቃለን። በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ግን፣ ባህሪው ልዩ መልክ ያዘ፤ ምድርም የተረገመች ሆነች። ሰይጣን እንዳደረገው፣ ሰውም እያወቀ የራሱን ፍላጎትና ፈቃድ ከእግዚአብሔር ፍላጎትና ፈቃድ ማስቀደም ጀመረ። ሰይጣን በአመጸኛነቱ ምክንያት የነበረውን ፍጹምነት እንዳጣ ሁሉ፣ ሰውም በእግዚአብሔር ላይ ሲያምጽ፣ በሰይጣን ውስጥ ይታይ የነበረው መጥፎ መንፈስ በእርሱም ሕይወት መታየት ጀመረ።

ሰይጣን በአመጸኛነቱ ምክንያት እግዚአብሔር ወደ ምድር አምዘግዝጎ እንደጣለው ሁሉ፣ ሰውም በኃጢአቱ ምክንያት ከምድረ ገነት ተባረረ። በዚህ ዓይነት የመጀመሪያው ሰው ከእግዚአብሔር ጎን በመቆም ፈንታ፣ ራሱን የሰይጣን የቡድን አባል ወይንም ተባባሪ አደረገ። ቀድሞ ምድር ሁሉ ለእርሱ የተሰጠ ነበር፤ በራሱ ፈቃድ የሰይጣን ቡድን አባል ከሆነ በኋላ ግን፣ የበላይነቱን ለሰይጣን አስረከበ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰይጣን «የዚህ ዓለም ገዢ»፣ የማይታዘዙት ሰዎች ንጉሥ ሆነ። ከአዳም በኋላ የተፈጠሩትም ሰዎች ሁሉ ከአባቶቻቸው «ያለመታዘዝን (አመጽን)» ስለወረሱ ሁሉም ኃጢአተኞች ሆኑ። በአዳም አለመታዘዝ ምክንያት ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደሆኑ ሮሜ 5:12 ይናገራል።

ሰው በኃጢአቱ ምክንያት ከወደቀም በኋላ፣ የግል «ፈቃዱ» ወይንም ምርጫው አሁንም እንደተጠበቀ ነው። ሰይጣን ለሰው ሀሳብ ከማቅረብ በቀር ምንጊዜም ቢሆን ገፍቶ ማለፍ፣ የሰውን ሕይወት መቆጣጠርና እንዲሁም አስገድዶ የፈለገውን ማስፈጸም አይችልም። ይሁን እንጂ ኃጢአተኛ የሆነው የሰው አሮጌው ተፈጥሮው፣ ሰይጣን ወደ ሰው ፈቃድ ጠጋ የሚልበትን በር ይከፍትለታል። ሰይጣንም በተከፈተለት ቀዳዳ በመጠቀም የሰውን ፍላጎትና ምኞት መንካትና ማባበል ይጀምራል።

እያንዳንዱ አማኝ ባለመታዘዝ መንፈስ ምክንያት የመጣ፣ «የተሸነፈ ሥጋዊ ተፈጥሮ» በውስጡ ይኖራል። ደህንነትን በሚያገኝበት ወቅት፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ያ ሰው አዲስ ተፈጥሮን ይለብሳል። ይሁን እንጂ አሮጌው ተፈጥሮው ፈጽሞ አይጠፋም። አሮጌው ተፈጥሮ ፍጹም መጥፋት ቢችል፣ «የክርስትና ሕይወት» ሁልጊዜ ቀላል ይሆንልን ነበር። አማኝ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እያደገ የሚሄደው፣ በሁለቱ ተፈጥሮዎቹ ማለትም በአሮጌውና በአዲሱ ተፈጥሮው መካከል ሆኖ ነው።

ሰይጣን ሁልጊዜ በእኛ ሕይወት ውስጥ ሥራውን ለማካሄድ እጁን የሚያስገባበት ቀዳዳ አለው። አሮጌው ተፈጥሮአችን አሁንም አቋሙ ከማይታዘዙት ወገን እንደሆነ መዘንጋት የለብንም። ሃዋርያው ጳውሎስ ስለ አሮጌው ተፈጥሮአችን ሲጽፍ «እኛም ሁላችን በእነርሱ መካከል የሥጋችንን ፈቃድና የአዕምሮአችንን አሳብ እየተከተልን ከዚህ

በፊት በሥጋችን ምኞት እንኖር ነበር፤ እንደሌሎቹም በተፈጥሮአችን በእግዚአብሔር ቁጣ ሥር ነበርን» ይላል (ኤፌ. 2:3)። ሰይጣን ሊዳስሰውና እንዲሁም እሳቱን ሊጭር የሚያስችለው ብዙ ነገር በውስጣችን አለ። ይሄ ሁኔታ አስገርሞን «አሮጌው ሥጋችን ከክርስቶስ ጋር በመስቀሉ ተሰቅሉ የለም ወይ?» ብለን መጠየቃችን አይቀርም። የሚያስደንቀው፥ ከዚህ በፊት የሰማናቸው ማንኛቸውንም ዓይነት መጥፎ ቃልዶችና ወሬዎች፥ እንዲሁም ወደ አዕምሮአችን የመጡት መጥፎ ሀሳቦች ሁሉ «ወቅታዊ ያልሆኑትን ነገሮች ከምናጠራቅምበት የአዕምሮ ክፍላችን» የተቀመጡ መሆናቸው ነው። እንዲሁም ከዚህ በፊት በሕይወታችን ተቀብለን ሥፍራ የሰጠናቸው ቅናት፥ ምቀኝነትና የሥጋ ፍትወት ሁሉ እዚያ ውስጥ ይጠራቀማሉ።

በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እጅግ ብርቱ ናቸው ተብለው የሚገመቱት አማኞች እንኳን ያለማቋረጥ መጥፎ ትዝታዎችና ሀሳቦች ወደ አዕምሮአቸው እንደሚመጡ ይመሰክራሉ። ሰይጣን እያንዳንዱን ሀሳብ በሚገባ ይጠቀምባታል። እንደ ጭስ በኖ ወይንም እንዳልነበረ ሆኖ የሚጠፋ ሀሳብ የለም። በአዕምሮአችን አስበናቸው ያለፉት መጥፎ ሀሳቦች ሁሉ ከላይ በገለጽነው የአዕምሮአችን ክፍል ውስጥ ተጠራቅመው ይቀመጣሉ። ሰይጣን ወደዚያ በቀላሉ ለመድረስ ችሎታ ስላለው በእነርሱ በጣም ይጠቀማል። ሌላው ቀርቶ ተንበርክከን በጸሎት ላይ ባለንበት ጊዜ እንኳን እነዚህ ሀሳቦች ወደ አዕምሮአችን ብቅ እያሉ እንደሚያስቸግሩን ሁላችንም በሕይወታችን ተለማምደን አይተነዋል። ሰይጣን ያንን መጠቀም ያልቻለው በክርስቶስ ሕይወት ውስጥ ብቻ ነው። ምክንያቱም ክርስቶስ ኃጢአት የሌለበት፥ ፍጹም ሰው በመሆኑ፥ ሰይጣን እጁን የሚያስገባበት ቀዳዳ ስለማያገኝ ነው። ይሁን እንጂ ኢየሱስ በሁሉም አቅጣጫ ልክ እንደ ሰው ተፈትኖአል፤ ኃጢአት ግን ፈጽሞ አልሠራም። በእኛና በእርሱ መካከል ካለው ልዩነት አንደኛው ይሄ ነው።

## 3ኛ ሰይጣን ራስን ከፍ በማድረግ መንፈስ ውስጥ ይኖራል።

አዳም እግዚአብሔርን አለመታዘዝ በመረጠበት ጊዜ፥ ሰይጣን የነበረውን ዓይነት ባህሪ፥ ያም «ራስን ከፍ በማድረግ መንፈስ» የተሞላ ሆነ። ሰይጣን የወደቀው ራሱን ከእግዚአብሔር እኩል ለማድረግ በፈለገበት ወቅት ሲሆን፥ አሁንም ሰይጣን በሰዎች ሕይወት ውስጥ መኖሩ የሚታወቅበት፥ በዚያ ሰው ሕይወት ውስጥ «ራስን ከፍ የማድረግ መንፈስ» እንዳለበት ስናይ ነው።

ቀደም ሲል እንዳየነው የሰይጣን መንፈስ አንደኛው «እኔ!» የሚል መንፈስ ሲሆን፥ በዚህ መንፈስ የተሞላ ሰው፥ ራሱን ከሚገባው በላይ

ሲያሳድግ (ሲያተልቅ) በቀላሉ ይታያል። ሰው «ለራሱ» ፍላጎት ብቻ መኖር ሲጀምር ያ ሰው ምን ያህል በሰይጣን ሀሳብ (መንፈስ) የተሞላ እንደሆን ማየት እንችላለን። የክርስቶስን ፈቃድና ፍላጎት ይዞ የሚኖረው ሰው ደግሞ፣ ምን ያህል በክርስቶስ መንፈስ የተሞላ እንደሆን መገመት እንችላለን። ብዙ ጊዜ ሰውን «በሰይጣን መንፈስ የተሞላ ነው» ስንል፣ ያንን ሰው ሰይጣን ቃል በቃል የሚያነጋግረው ከፉ ሰው ይመስለናል። በክርስቶስ መንፈስ የተሞላ ሰው፣ በሄደበት ሁሉ ክርስቶስን ከፍ ከፍ እያደረገ ሲናገር ይሰማል። በሰይጣን መንፈስ የተሞላ ሰው ግን ሰይጣንን እያሞጋገሰና እያተለቀ ሲናገር አይሰማም። ይሄ ቢሆን ኖሮ ሰይጣን ሥራው በቀላሉ ይታወቅና የማጥቃት ዓላማው ፍጹም ይበላሽበት ነበር። ሰይጣን «ሁሉን ቻይ» ከሆነው አምላክ ጋር መወዳደር እንደማይችል ያውቃል። ስለዚህ በግልጽ «እመለካለሁ» ብሎ አይገምትም። በግልጽ እንደማይመለክ ስለሚያውቅ፣ በተዘዋዋሪ መንገድ ወይንም በስውር ክብሩን ለማግኘት ይሞክራል። ሰው «ራሱን ማተለቅና ራሱን ማምለክ» ሲጀምር፣ ክርስቶስ ሊይዘው የሚሻውን ከፍተኛ ሥፍራ መከልከሉ እንደሆን ስለሚያውቅ፣ ሰይጣን በዚያ ይጠቀማል።

ሰይጣን በክርስቶስ ላይ ከፍተኛ ጥላቻ አለው። በክርስቶስ ላይ ያለው ጥላቻ ጠንካራ የሆነበትም አንደኛው ምክንያት፣ መንግሥቱ ለዘለዓለም እንዳይሆን ስላጨናገፈበት ነው። በዚህ ምክንያት የሰይጣን ዋና ዓላማውና ፍላጎቱ ኢየሱስን ማሳዘን ነው። ይሁን እንጂ ክርስቶስ ዘንድ መድረስ ፈጽሞ ስለማይችል፣ ሊያበሳጨው የሚሞክረው እንደ ዓይኑ ብሌን የሚያያቸውን ልጆቹን በመጉዳት ነው። ኢየሱስ የራሱ ለሆኑት ልጆቹ ምን ያህል ከፍተኛ ፍቅር እንዳለው፣ እንዲሁም ልጆቹን ሲነካ እርሱን እንደሚነካ ስለሚያውቅ፣ እያንዳንዱን ክርስቲያን ሕይወት ለማበላሸት ሰይጣን ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። ሰይጣን በእግዚአብሔር ልጆች ላይ ትልቅ ጉዳት ማድረስ ከሚችልበት መንገድ አንደኛው፣ ክርስቲያኖች በክርስቶስ ፈንታ «እኔ ብቻ» የሚል ሕይወት እንዲኖራቸው ያደረገ እንደሆነ ነው። ይህን ዓይነት መንፈስ በውስጣቸው እንዲኖር የሚያደርገውም፣ ክርስቶስን በጣም እንደሚያሳዝነው ስለሚያውቅ ነው። ሰይጣን ደህንነትን ያላገኙ አንድ ሚሊዮን ነፍሳትን ከመማረክ ይልቅ፣ አንድ ደህንነትን ያገኘውን ክርስቲያን በሕይወቱ ቢያደናቅፈውና ቢያጠፋው የበለጠ ደስ ይለዋል። ሰይጣን በቁጥጥሩ ሥር ያዋላቸው በቢሊዮን የሚቆጠሩ ያልዳኑ ነፍሳት ቢኖሩትም፣ መንግሥቱ ፈጥኖ ስለሚያከትምና እንዲሁም ክርስቶስን ለመተናኮል ያለው ዕድል አሁን ብቻ እንደሆነ ስለሚያውቅ፣ በተለይ በመጨረሻው ዘመን ብርቱ እንቅስቃሴ ሲያደርግ ይታያል።

ሰይጣን ትልቁ ዓላማውና ጥረቱ ክርስቲያኖችን አደናቅፎ ለመጣል ነው። በግልጽ «አለመመለኩን» የመረጠውም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማሳሳትና ማደናቀፍ እንዲያስችለው ነው። ለማይታዘዙት ሰዎች ገዢ ወይንም ንጉሥ አድርጎ በግልጽ ራሱን አያቀርብም፤ ምክንያቱም ራሱን

ግልጽ አድርጎ ቢያቀርብ ክርስቲያኑ ሁሉ እንደሚቃወመው ስለሚያውቅ ነው። እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስን በመምሰል ማደግ የሚችልበት አንድ ሕይወት ብቻ እንዳለውና እንዲሁም ወደ ፊት በመንግሥት ሰማይ ለሚኖረው ሕይወት ወሳኙ አሁን በምድር የሚኖረው የሕይወት አቅጣጫ እንደሆነ ሰይጣን ያውቃል። ስለዚህ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዳያድግና ዋጋ ቢስ እንዲሆን በየቀኑ ትግሉን ያፋፍምበታል።

ሰይጣን በመጨረሻ ማንነቱ ለሰው በሚገለጽበት ወቅት እንኳን፥ ራሱን ለመደበቅ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። ጳውሎስ «ይህ የዐመፅ ሰው፥ አምላክ ከተባለውና ከሚመለከው ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ በማድረግ የሚቃወም ነው፤ «እግዚአብሔር ነኝ» እያለም በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንኳ ለመቀመጥ ይደፍራል» ይለዋል (2 ተሰ. 2:4)። ሰይጣን ሁልጊዜ «እኔ» በሚል መንፈስ ውስጥ ይገኛል። ይሄ ዋና መደበቂያ ሥፍራው ነው። ክርስቲያን በሰይጣን መንፈስ ይሞላል ብለን ጨርሶ አናምንም። ይሁን እንጂ ሰይጣን በረቀቀ ሁኔታ አማኝን ለመጣል ከመታገል ወደ ኋላ አይልም። የሰይጣንን ተፈጥሯዊ ባህሪውን ብናውቅ፥ የተንኮል ሥራውን መለየት አያዳግተንም። ክርስቲያኑን «ለራሱ ብቻ» እንዲኖር ያባብለዋል። «በራስ ወዳድነት» መንፈስ ውስጥ መኖርና እንዲሁም «አለመታዘዝ» እግዚአብሔርን የሚያሳዝነው፥ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረንን አንድነት የሚያሻክር መሆኑን ስለሚያውቅ፥ «እምቢተኞች» ወይንም የማንታዘዝ ልጆች እንድንሆን የሚያደርግበትን ብልሃት በየጊዜው ይፈጥራል። ብልሃቱም ውስጥ «ፍላጎታችን» ወይንም ምኞታችን ምን እንደሆነ ካወቀ በኋላ፥ እነዚያን ፍላጎቶች ልናሟላ የምንችልባቸውን ሀሳቦች በየጊዜው ወደ አዕምሮአችን በማቅረብ በራሳችን ፈቃድ ሥር እንድንኖር ማድረግ ነው። «ራሳችንን ለምኞታችን» ማስገዛት ማለት፥ በእርሱ ፈቃድ ሥር መኖር መሆኑን ሰይጣን ስለሚያውቅ፥ «ለራሳችን» ብቻ እንድንኖር ሁኔታዎችን አመቻችቶ ያቀርብልናል።

የእግዚአብሔርን ቃል በአግባቡ ካልመረመርንና የሰይጣንን አሠራሩንና እንቅስቃሴውን በደንብ ካላጠናን፥ በቀላሉ ተንኮሉን መረዳት አንችልም። ሰይጣን የሚታገለን፥ ከመስመር የወጣ ነገር እንድናደርግ ሀሳብ በመስጠት ብቻ ሳይሆን፥ ለማድረግ የምንፈልገውን ጥሩ ነገር እንዳናደርግ በመከልከልም ጭምር ነው። ለምሳሌ ወደ ጸሎት ፕሮግራም ለመሄድ ስንነሳ፥ ሰይጣን ለእኛ የሚያስብ መስሎ ወደ ሀሳባችን ብቅ ይልና «ዛሬ ደክሞሃል፥ ለሥጋህም ዕረፍት ያስፈልገዋል» ይለናል። ይሄ ሀሳብ ከራሳችን የመጣ እንጂ የሰይጣን ሀሳብ ነው ብለን ፈጽሞ አንጠራጠርም። ሰይጣን ሀሳብ በማቅረብ ብቻ ተወስኖ ሳይቀር፥ የሚያስፈልገንን ነገር ፈልገን እንዳናገኝ፥ ትጉሆች በመሆን ፈንታ ሰነፎች እንድንሆንም ጥረት ያደርጋል። እንዲሁም ሰዎች ያላሉትን «አሉ» በማለት፥ ወይንም ለተናገሩት ነገር ልዩ ትርጉም ሰጥቶ

በሌላ አቅጣጫ እንድንረዳ በማድረግ፥ ከሰው ጋር በሰላም እንዳንኖር ሰይጣን የማጋጨትና የማጣላት ከፍተኛ ችሎታ አለው። እንዲሁም ያልሆንነውን እንደሆንን መስሎ እንዲሰማን፥ ራሳችንን ከፍ፥ ሌሎችን ዝቅ አድርገን እንድንመለከት ሊያደርገን ይችላል። ራሳችንን ማዳመጥ እስከቀጠልንና እንዲሁም አስፈላጊውን ጥንቃቄ እስካላደረግን ድረስ፥ ሰይጣን «ሀሳብ በማቅረብ» ብቻ እርሱ የፈለገውን እንድንሆን ማድረግ ይችላል። ይህን ሁሉ ሲያደርግ ግን «የግል ፈቃዳችንን» ሳይጥስ እንደሆነ ማወቅ ይገባናል። ከዚህ በፊት ያደረግናቸው ነገሮች ሁሉ ፈቅደን እንጂ ማንም አስገድዶን ያደረግናቸው ነገሮች አይደሉም። ሰይጣን ያቀረበልን ሀሳብ በውስጣችን ተቀባይነት ማግኘቱን አይቶና ጊዜ ጠብቆ ፈቃዳችንን ለእርሱ ፈቃድ እንድናስገዛ፥ ፈተናውን በመንገዳችን ላይ ይዘረጋል። እኛም ተንኮሉን በደንብ ካልተረዳን «ተቆርቋሪ» መስሎ የሚያቀርብልንን ሀሳብ ተቀብለን በተግባር ላይ እናውለዋለን።

## ሰይጣን ራሱን በሰዎች ውስጥ ሸፍኖ ያቀርባል

ሰይጣን ወደ እኛ ለመድረስ ብዙ ጊዜ በሰዎች የሚጠቀምበት ጊዜ አለ። ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ መከራ እንደሚደርስበት ሲናገር፥ ጴጥሮስ «ይሄ ባንተ ላይ አይድረስ» ሲል፥ በጴጥሮስ ውስጥ ሰይጣን ለመጠቀም እንደፈለገ ኢየሱስ በግልጽ አወቀ። ለዚህ ነው ኢየሱስ «አንተ ሰይጣን ወዲያ ሂድ» ያለው። ሰይጣን ከክርስቶስ ጋር የሚኖረንንን የተቀራረበ ሕይወት ለማጨናገፍ ሁልጊዜ ቅርባችን ከመሆኑም በላይ፥ የምንወዳቸውንም ሰዎች ይጠቀምባቸዋል። ለምሳሌ በአትግሚ መኖር የማትችል ብኩን ሚስት፥ ባሏን ከአቅሙ በላይ እንዲኖር በማድረግ ዕዳ ውስጥ በመክተት የመከራ ጽዋ እንዲጠጣ ማድረግ ትችላለች። እንዲሁም ልጆች ለወላጆቻቸው የልብ ስብራት ሊሆኑ ይችላሉ። የሚቀረቀሩልንና የሚወዱን ወዳጆቻችን እንኳን ለእኛ ያሰቡልን መስሏቸው ለክርስቶስ የሰጠነውን ሕይወታችንን ፍሬ እንዳናፈራበት በመንገዳችን ላይ ሊቆሙ ይችላሉ። የሰይጣን ዓላማ የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወታችን እንዳይፈጸም ለማድረግ ስለሆነ፥ ይህንን አውቀን በመንገዳችን ላይ በሚያኖራቸው ልዩ ልዩ እንቅፋቶች ተሰናክለን እንዳንወድቅ መጠንቀቅ ይገባናል።

## ሰይጣን በልዩ ልዩ "ሁኔታዎች" ውስጥ ራሱን ይሸፍናል።

ሰይጣን አንዳንድ በጎ ያልሆኑ ሁኔታዎችን ወደ ሰው ሕይወት ማምጣት ይችላል። የጎርፍ መጥለቅለቅ፣ የእሳት ቃጠሎ፣ ረሃብና ችጋር፥ እንዲሁም ልዩ ልዩ አደጋዎችን ማምጣትና መቀስቀስ ይችላል።

ከላይ ያየናቸው ነገሮች ክፉ ቢሆኑም፥ ሁኔታዎቹን እግዚአብሔር
ለደግ የሚጠቀምበት ጊዜ አለ። በቅርቡ ሰሜን አሜሪካ ውስጥ፥ በኦ
ክላሆማ ከተማ የፈነዳው ቦምብ የብዙ ሰዎችን ሕይወት ያጠፋ ቢሆንም፥
በዚህ አደጋ ውስጥ የእግዚአብሔር ክንድ፥ የክርስቲያኖች እንድነትና
ፍቅር በተለያየ መንገድ እንደታየ አንጠራጠርም። በዚህ ዓለም ለሚ
ፈጠሩት ልዩ ልዩ አደጋዎችና ጥፋቶች ምንጩ ሰይጣን ነው። ሰይ
ጣን መፍጠር አይቻል እንጂ ማጥፋትን ያውቅበታል። አማኝ «ይሄ
በሕይወቴ እንዲሆን (እንዲደርስ) እግዚአብሔር ለምን ፈቀደ?» ብሎ
በእግዚአብሔር ላይ አኩርፎ ከእርሱ እንዲሸሸ ያለውን ሀብትና ንብ
ረት በተለያየ ምክንያት እንዲጠፋበት የሚያደርግበት ጊዜ አለ። ሰይጣን
ይህን መንገድ ተጠቅሞ ሊያሸንፋቸው ካልቻላቸው ሰዎች መካከል
አንደኛው ኢዮብ ነው። ኢዮብ «እግዚአብሔር ሰጠ፥ እግዚአብሔር
ነሳ፤ ስሙ ይባረክ» በማለት በማጣቱ እንኳን እግዚአብሔርን አመሰ
ገነ። በሌላ በኩል ደግሞ ሀብት፥ ብልጽግና የክርስትያኑን ሕይወት
ሊያቆሽሽ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት ሊያቀዘቅዝ፤ እንደ
ሚችል ሰይጣን ስለሚያውቅ፥ አማኝ የሚበለጽግበትን አንዳንድ ጤናማ
ያልሆኑ ሁኔታዎችን አመቻችቶ የሚያቀርብበት፥ እንዲሁም አቋራጭ
መንገዶችን የሚዘረጋበት ጊዜ ስላለ፥ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ
እንዳንወጣ መጠንቀቅ ይገባናል።

# 4

# የአማኝ ጠላቶችና የሚያደርሱበት ጥቃት

## ሀ) ሥጋና ደም

ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ፥ ክርስቲያኖች ስለሚኖርባቸው ትግል ሲዘረዝር፥ «...ትግላችን ከሥጋና ከደም ጋር አይደለም...» ይላል (ኤፌ. 6:12)። «ሥጋና ደም» የሚለው ሀሳብ ሁለት ዓይነት ትርጉም ይዞአል።

**1ኛ** ሥጋና ደም የሆነው ተፈጥሮአችን በኃጢአት ያደፈ (የተበላሸ) ነው። ያም ተፈጥሮ ከመጀመሪያው ሰው፥ ከአዳም የወረስነው ነው። አዳም ልክ እርሱን የሚመስል ኃጢአተኛ የሆነ ልጅ ወለደ። ቃየል ወንድሙን አቤልን መግደል የቻለው፥ በተፈጥሮው ኃጢአት የመሥራት ዝንባሌ ስለነበረው ነው። «ቅዱስ» የተባለው ሰው እንኳን በውስጡ የኃጢአተኛነት ተፈጥሮ አለው። ለምሳሌ የተገረዘ ሰው ያልተገረዘ ሕጻን እንደሚወልድ ሁሉ፥ ቅዱስ የሚባለው ሰውም፥ ቅዱስ ያልሆነ ወይንም ኃጢአተኛ የሆነ ልጅ እንደሚወልድ የታወቀ ነው።

«ሥጋ» ብለን የምንጠራው ውስጣዊ የሆነውን፥ እንደገና ያልተወለደውን፥ በተፈጥሮ ያገኘነውን «እኛነታችን» እንጂ ከላይ የሚታየውን ቆዳው ሥጋ አይደለም። ባልተቀደሰ፥ ወይንም በተበላሸ «አዕምሮ»፥ ሰው ስለ እግዚአብሔር ፈጽሞ ማሰብ አይችልም። ሥጋዊው ሰው ፍላጎቱ፥ ደስታውና ምኞቱ ሁሉ

በዚህ ዓለም ሀሳብ ላይ ብቻ ያተኮረ ነው። ጸሀይ በምድር ላለው ነገር ብርሃን በመስጠት እንዲታይ እንደምታደርግ፣ በላይ ወይንም በሰማይ ያለውን ግን እንደምትሸፍን ሁሉ፣ ሥጋዊ አስተሳሰብም መንፈሳዊ የሆነውን ነገር ያጨልምና፣ ምድራዊ በሆነው ነገር ላይ ብቻ ልዩ የሆነ ብርሃኑን ይፈነጥቃል።

ጳውሎስ ትግላችን «ከሥጋና ከደም ጋር አይደለም» ሲል፣ እውነተኛው ትግላችን በአሮጌው ሥጋችንና በአዲሱ ተፈጥሮአችን መካከል የሚደረገው ጦርነት ብቻ አይደለም ማለቱ ነው። ብዙ ጊዜ «መንፈስ» የሥጋ ምኞትን፣ የሥጋ ምኞትም መንፈስን ሲቃወም እናያለን። ሰይጣን በአካባቢው ባይኖር እንኳን ከአሮጌው ሥጋችን ጋር ከፍተኛ ጦርነት (ትግል) ይኖረናል። ጳውሎስ እንድናየው የሚፈልገው ነገር ቢኖር፣ አሮጌው ተፈጥሮአችን፣ አዲሱን ተፈጥሮአችንን ለመቃወም የጦርነቱ ተሳታፊ እንደሚሆን ነው። ሰይጣን እዚህ ላይ «አሮጌውን ሥጋችንን» ለማገዝ (ለመደገፍ) ጦርነቱ ውስጥ ዘሎ ይገባል። የጦሩ አዛዥ (ጄኔራል) ሆኖ ኃጢአት ለመሥራት ዝንባሌ ያለውን ተፈጥሮአችንን በመጠቀም የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወታችን እንዳይፈጸም በብርቱ ይዋጋናል። ክርስቲያኖች በውስጣችን ካለው ኃይል ጋር ስንታገል፣ ሰይጣን «አሮጌውን ተፈጥሮአችንን» በማገዝ፣ የሕይወታችን ዋና አዛዥና ተቆጣጣሪ በመሆን ትግሉን ያፋፍማል። በዚህ ዓይነት ኃጢአተኛው ተፈጥሮአችን «ሞተሩ» ሲሆን፣ «ሰይጣን» ደግሞ ሞተሩን የሚያንቀሳቅሰው ሾፌሩ ነው። የሥጋ ፍላጎታችንን (ምኞታችንን) መስመር ካላስያዝን ወይንም ካልጠበቅን፣ ሰይጣን እኛን ለመጣል ሲል ከአሮጌው ሥጋችን ጋር እንደሚተባበር ማወቅ ያስፈልገናል። እኛ ብቻችንን ከላይ ከጠቀስናቸው «ከሁለት ተባባሪ ኃይሎች» ጋር ገጥመን ማሸነፍ ስለማንችል፣ ጉልበትና ጥበብን ለማግኘት የግድ ከእግዚአብሔር ጋር መጣበቅ ይገባናል።

2ኛ ☛ ጳውሎስ «ውጊያችን ከሥጋና ከደም ጋር አይደለም» ሲል፣ ሌላው ትርጉም «ትግላችን ከሥጋ ለባሽ ሰዎች ጋር አይደለም፣ ትግላችን «ሥጋና ደም» ካልሆነውና ከማይታየው መንፈስ ጋር ነው» ማለቱ ነው። ስለዚህ በሚበሰብሰው «ሥጋችን» መታመን እንደሌለብን ብቻ ሳይሆን መፍራትም እንደማይገባን እንወቅ። ዳዊት በመዝሙሩ «...በእግዚአብሔር ስለምታመን፣ ከቶ ሰው ምን ሊያደርገኝ ይችላል?» ይላል (መዝ. 56:4)። ሕይወታችንን ለጌታ አንዴ ከሰጠነው፣ ሌላ ኃይል ነጥቆ ይወስድብናል ብለን መፍራት አይገባንም። ሥጋና ደምን አንፍራ እንጂ፣ የምንንቀው ወይንም ችላ

የምንለው ጠላት አይደለም። ክርስቲያኖች ጥሩ ከሚባሉትና እንዲሁም ክፉ ከሚባሉት ሰዎች ጋር ውጊያ ሊያጋጥማቸው ይችላል። ከተሳካለት በሁለቱም በኩል ሰይጣን መጠቀም ይፈልጋል።

ሌላው ቀርቶ በቅዱሳኖች መካከልም ከፍተኛ ግጭትና አለመግባባት ሊፈጠር ይችላል። የግጭታቸው ምክንያት ብዙ ጊዜ እውነቱን በትክክል ካለማወቅ የተነሳ ይሆናል። አብርሃም ከሎጥ ጋር፣ አሮንና ማርያም ከሙሴ ጋር፣ እንዲሁም ክር ስቶስ በምድር በነበረበት ዘመን በደቀ መዛሙርቱ መካከልም አለመግባባትና ግጭት ይታይ ነበር። በቅዱሳን መካከል ለሚ ፈጠረው ግጭት ዋናው እሳት ለኳሹ ሰይጣን መሆኑን መር ሳት የለብንም። ራሱን ሸፋፍኖ አንዴ ከአንዱ ወገን፥ ሌላ ጊዜ ከሌላው ወገን በመሆን ግጭቱን ያፋፍማል። ንዴት፥ ቁጣና በቀልን እያጠናከረ ቅዱሳን እርስ በርሳቸው እንዲጎ ዳዱ ያደርጋል። በዚህ ምክንያት ነው ሐዋርያው ጳውሎስ «ለዲያብሎስም ስፍራ አትስጡት» (ኤፌሶን 4:27) ያለው። ጦርነት ወይንም ጠብ ባለበት ሥፍራ ሁሉ ሰይጣን ቶሎ ብሎ እጁን ማስገባት ይወዳል። ሰይጣን ያለ እሳት መሥራት ስለማይችል፥ ሁልጊዜ «እሳት» የሚጭርበትን መንገድ ይፈ ልጋል። ጥቂት እሳት ካገኘ፥ ያንን እያራገበ ትልቅ እሳት እንዲወጣው ያደርጋል። ቅዱሳን እርስ በርሳቸው ሲነካከሱ ሲያይ ሰይጣን ደስ ስለሚለው፥ ያንን ዕድል ላለመስጠት መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ሰይጣን በቅዱሳን መካከል ጠብን መጫር ብቻ አይበቃ ውም። ክፉዎችን በቅዱሳን ላይ እንዲነሱ ማድረግ ደግሞ ሌላው ትልቁ ተግባሩ ነው። ኢየሱስ ራሱ «የዓለም ብትሆኑ ዓለም የራሱ የሆነውን በወደደ ነበር፥ ነገር ግን የዓለም ስላልሆናችሁና እኔ ከዓለም ለይቼ ስለመረጥኋችሁ ዓለም ይጠላችኋል» ይላል (ዮሐ. 15:19)። እሳትና ውሃ፥ ሲኦልና መንግሥተ ሰማይ አብረው መሄድ ስለማይችሉ ሁልጊዜ በመካከላቸው ጦርነትና ግጭት ይኖራል። በአሳዳጆች ልብ የሚቃጠለው የጥላቻ እሳት ምንጊዜም አይጠፋም። ክፉዎች በቅዱሳን ላይ ለሚያስነሱት ጦርነት መሪውና የበላይ አዛዡ ሰይጣን ነው። ኢዮብን በንግግራቸው ያቆሰሉት ጓደኞቹ፥ ክፎዎች በቅዱሳን ላይ ለመነሳታቸው ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ። አሳዳጆች በምላሳቸውም ሆነ በእጃቸው ተጠቅመው ቅዱሳንን የሚጎዱት፥ የሰይጣን መሣሪያ በመሆናቸው ነው። ይህ መሆ ኑንም መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል። «ወደፊት የሚደ ርስብህን መከራ አትፍራ፤ እነሆ እንድትፈተኑ ከእናንተ

አንዳንዶቹን ዲያብሎስ ወደ እስር ቤት ያገባችኋል፤ አሥር ቀንም መከራ ትቀበላላችሁ» ይላል (ራእይ 2፡10)።

«እውነትን» ወይንም ቅዱሳንን የሚዋጉ ሰዎች ስናይ ልናዝንላቸው እንጂ፣ ልንፈራቸውና ችሎታቸውን ልናደንቅላቸው አይገባም። እነርሱ የሰይጣን ቅጥር አርበኛ ናቸው። ጥንት ሰማዕት ሆነው ሕይወታቸውን ያሳለፉ ሰዎች፣ ያሳድዷቸው የነበሩትን ሰዎች «ለሰይጣን የቆሙ ገዳዮች» ይሏቸው ነበር። አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ጥሩ አዕምር ለበጎ በመጠቀም ፈንታ እግዚአብሔርን ለመዋጋት ሲጠቀሙበት ስናይ፣ ከልባችን ልንጸልይላቸውና ልናለቅስላቸው ይገባል። በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር የሰጣቸውን የአዕምሮ ችሎታ ለሰይጣን መገልገያ ከሚያውሉት፣ ሞኞች ተብለው እግዚአብሔርን አገልግለው ቢሞቱ ይሻላቸው ነበር። በክፉዎች ሰዎች አማካኝነት ክፉ ነገር ሲደርስብን ስናይ፣ በእነርሱ ልብ ክፋትን የሚዘራው ሰይጣን መሆኑን አንርሳ። ስለዚህ ዋና ጠላታችን «ሰይጣን» ስለሆነ ትኩረታችን በእርሱ ላይ መሆን ይገባዋል።

## ለ ሰይጣን ዋናው ጠላታችን ነው።

ውጊያችን ከሥጋና ከደም ጋር ብቻ ቢሆን ኖሮ፣ አንዳንዶቻችን ብቻችንን ተዋግተን ማሸነፍ እንችል ነበር። ነገር ግን ትልቁ ትግላችን ከሰይጣን ጋር በመሆኑ ብቻችንን ተዋግተን ማሸነፍ እንደማንችል ሐዋርያው ጳውሎስ ይናገራል። ሰይጣን ከሰማይ ወደ ምድር ከተወረወረበት ጊዜ ጀምሮ እርሱና ተከታዮቹ በምድር መንግሥታቸውን ለማስፋፋት ያለመታከት ከፍተኛ ተጋድሎ አድርገዋል።

### 1. የሰይጣን የመንግሥቱ ተቋም

ደጋግመን እንደተመለከትነው ሰይጣን ትልቅ ኃይልና ሥልጣን ያለው ፍጡር ነው። «...ከባለሥልጣናት...» የሚለው ቃል «አርከስ» ከሚለው የግሪክ ቃል የወጣ ነው። ትክክለኛ ትርጉሙም የተለያየ ደረጃና ሹመት፣ እንዲሁም ሥልጣን ያላቸውን የባለሥልጣናት ማዕረግ የሚገልጽ ነው። ይህ ቃል ሰይጣን «ግዛቴ ነው» ብሎ የሚለውን ድንበርና ግዛቱን የሚያመለክት ነው። ሰይጣን በዚህ በክፉ ዓለም ውስጥ ያለውን ከፍተኛ ደረጃና ኃይል ዝቅ አድርጎ መመልከት፣ እግዚአብሔር ራሱ የተናገረውን መቃረን ይሆናል። ኢየሱስም ሰይጣን በዚህ ዓለም ውስጥ ያለውን ኃይል ሲገልጽ «የዚህ ዓለም ገዢ» ይለዋል

(ዮሐ. 14:30)። የዚህ ዓለም የአገር መሪዎች፥ ከበታቻቸው ሥልጣን የሚሰጡአቸው ሰዎችና እንዲሁም የሙት ድንበር እንዳላቸው ሁሉ፥ ሰይጣንም የራሱ ሹማምንቶችና እንዲሁም ሚኒስትሮች አለው።

በዚህ ዓለም ያሉ ንጉሦች ከልብ የሚያምኗቸው በጣት የሚቆጠሩ የቅርብ ሰዎች ይኑሯቸው እንጂ፥ ሰፊውን ሕዝብ ሁልጊዜ የሚገዙት ያላቸውን ኃይልና ሥልጣን ተጠቅመው ነው። እነዚህ ምድራዊ የአገር መሪዎች ተጠራጥረው ነቅተው ካልጠበቁና እንዲሁም በኃይልና በሥል ጣን ካልገዙ፥ ዙፋናቸውን ብቻ ሳይሆን፥ ሕይወታቸውንም ማጣት እንደሚችሉ የታወቀ ነው። ሰይጣን ግን «መፈንቅለ መንግሥት (ኩዴታ) ያካሂድብኛል» ብሎ የሚፈራው ኃይል የለውም። «ባለሟሎቼ አም ጸው፥ ከሥልጣኔ ፈንቅለው ያወርዱኛል» ብሎ ፈጽሞ አይፈራም። በሥሩ ያሉት ሁሉ ፍጹም ታዛዦችና ተገዢዎች ናቸው (ራዕይ 13፥4)።

ሰይጣን ጨካኝ ገዢ ነው፤ ሕጉንም የሚሰጠው በኃይልና በማስ ነቅ ስለሆነ «የኃጢአት ሕግ» ተብሎ ይጠራል (ሮሜ 8፥2)። የሚያሳዝነው፥ ያ ሕግ በራሱ ደም የተጻፈ ሲሆን፥ ፈቃድና ምኞቱን ለሚፈጽሙት፥ ከኩነኔ (ከሞት) በስተቀር ሌላ የሚሰጣቸው የተለይ ተስፋ የሌለው መሆኑ ነው። ሰይጣን መንግሥቱን ለማስፋፋት የባለ ሟሎቹ ትብብር ያስፈልገዋል፤ በተለይ በጣም በረከሱትና በከፉት፥ የበለጠ ይጠቀማል። የምድር ነገሥታት ፍላጎታቸውን በምትካቸው ሆነው የሚያስፈጽሙ ሚኒስትሮችና መልዕክተኞች እንዳሏቸው ሁሉ፥ ሰይጣንም ዓላማውን የሚያስፈጽሙለት የራሱ የሆኑ ባለሟሎች አሉት። ጳውሎስ ሰይጣንን ሲገልጽ «አንተ የዲያብሎስ ልጅ የእውነት ሁሉ ጠላት፥ ማታለልና ክፋት ሁሉ የሞላብህ፥ ቀጥተኛውን የእግዚአብሔር መንገድ ማጣመም አትተውምን?» (የሐዋ. 13፥10) ይለዋል። እነዚህ ምርጥ የሆኑ አገልጋዮቹ እንኳን፥ የልቡ ሀሳብ ምን እንደሆነ ሙሉ በሙሉ አይገልጽላቸውም። በዓለም ላይ ያለው ኃጢአተኛ ያለው ጊዜ፥ ኃይልና የአዕምሮ ችሎታ ሁሉ ሰይጣን የሚጠቀምበት መሣሪያው ነው።

ለመሆኑ እንዲህ ዓይነቱ ጨካኝ ሰይጣን፥ ይህን የመሰለ ታላቅ ኃይልና ሥልጣን ማግኘት የቻለው እንዴት ነው? ሰይጣን ሥልጣኑና ኃይሉን ያገኘው በትክክለኛው መንገድ እንዳልሆነ ለሁላችንም ግልጽ ነው። ሥልጣኑን ያገኘው ዓለምን አሸንፎ እንደሆነ ይናገር እንጂ፥ በመ ሠረቱ ሥልጣኑንና ኃይሉን ያገኘው የተጣመመ ፖለቲካውን ተጠቅሞ ነው። ሌባ ከሰው ኪስ ገብቶ የሌላውን ሰው የገንዘብ ቦርሳ ለመውሰድ መብት ስለሌለው፥ እጁን ሰዶ በኃይልና በማጭበርበር ነጥቆ የራሱ እንደሚያደርግ እናውቃለን። ሌባው ሌብነቱ ባይታወቅበትም፥ የሌላውን ሀብት በመንጠቁ ብቻ ሌባ ከመሆን ነጻ አይሆንም። ሰይጣንም ከዚህ የተለየ አይደለም። የአዳምን ልብ ከእግዚአብሔር ነጥቆ የራሱ በማድ ረግ ለረጅም ጊዜ የቆየ ነጣቂ ሌባ እንደሆነ እናውቃለን።

ሰይጣን ኃይልን ያገኘው የሰውን ደካማ ተፈጥሮ በመጠቀም ነው። ክርስቶስ በሰይጣን የተወሰደውን ነፍሳችንን ከእጁ ፈልቅቆ ለማውጣት በመስቀል ላይ ሆኖ ተዋጋልን። ያም ለእኛ ደህንነት ሲባል የተደረገ ቅዱስ ጦርነት (ውጊያ) ነው። ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣው የእርሱ የነበረውን መልሶ ለመውሰድ ነው። ሰይጣን ግን ነጥቆ ከመውሰዱ በስተቀር "የእኔ ነው" የሚለው አንዳችም ነፍስ የለውም። ሰይጣን «ሥልጣኑን የያዝኩት በምርጫ ነው» ይበል እንጂ፥ በኃጢአት የበለዘውን የሰውን ተፈጥሮ ተጠቅሞ እንደሆነ እናውቃለን። አዳም የመጀመሪያው ሰው ተሸንፈለትI የአዳም ልጆችም የአባታቸውን መንገድ ስለተከተሉ ሰይጣንን ተዋግተው ማሸነፈያ ኃይል አልነበራቸውም። «እናንተ የአባታችሁ የዲያብሎስ ልጆች ናችሁI ፍላጎታችሁም የአባታችሁን ፍላጎት መፈጸም ነው...» (ዮሐ. 8:44) ይላል። ሰው እግዚአብሔርን እንዲያገለግል የተፈጠረ በመሆኑ፥ ዘለዓለማዊውን ንጉሥ ከሥልጣኑ ለማስወገድ ሥልጣንም ሆነ ኃይል የለውም። ግንም የእግዚአብሔርን አምላክነት (ኃያልነት) ችላ ማለት ይችላልI ኃይሉንና ሥልጣኑን መግፈፍ ግን አይችልም።

ሰይጣን፥ «ምድር የእኔ ናት» በማለት ዘላቂነት ወይንም ዕድሜ የሌላቸውን ስጦታዎችን ማበርከት ይችላል። ምንም ዓይነት እፍረት ሳይሰማው «የዚህ ዓለም ገዢ» እንደሆነና ሙሉ ሥልጣን እንዳለው አድርጎ ራሱን ያቀርባል። ለዚህ ነው ኢየሱስን ሲፈትነው ዓለምን ሁሉ ካሳየው በኋላ «ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ» ያለው (ሉቃስ 4:6)። በመጠኑም ቢሆን ይሄ ሀሳብ እውነትነት አለው። እግዚአብሔር ይህን ዓለም ለሰይጣን ሰጥቶታልI ይሁን እንጂ የሰጠው የፈለገውን ሁሉ እንዲያደርግበት አይደለም። ያንን ደግሞ እግዚአብሔር በፈቀደው ቀን መሰረዝና መለወጥ ይችላል።

## 2 ☛ እግዚአብሔር ለሰይጣን ይህን ያህል ኃይልና ሥልጣን ለምን ሰጠው?

በተወሰነው የአዕምሮ ችሎታችን ለዚህ ክፉ ለሆነው ፍጡር ይህን የመሰለ ሥልጣን እንዲኖረው እግዚአብሔር ለምን እንደፈቀደ በመደነቅ መጠየቃችን አይቀርም። ይሄ አመጸኛ ሰይጣን በሰዎችና በመላእክት ፊት ተንኮለኛ ልምምዱን እንዲያደርግ እግዚአብሔር ለምን ፈቀደለት?

ሀ. አመጸኛውን ሰው እግዚአብሔር የሚቀጣበት አንደኛው መንገድ፥ በዚያ በማይታዘዘውና በእግዚአብሔር ላይ በሚያምጸው ሰው ላይ ሰይጣን የፈቀደውን እንዲፈጽምበት በማድረግ ነው። ስለዚህ ሰይጣን የእግዚአብሔርን ቁጣ አስፈጻሚ ወይንም ገላጭ ነው። ሰይጣን የእግዚአብሔር ባሪያ (አገልጋይ) ሲሆን፥ ሰው ደግሞ በምርጫው የሰይጣን አገልጋይ መሆን ይችላል።

ለ. ሰይጣን ይህን ዓይነት ታላቅ ኃይል እንዲኖረው እግዚአብሔር የፈቀደው፥ የእግዚአብሔር ኃይል ከሰይጣን እንደሚበልጥ ለማሳየት ነው። ታላቁን ድራጎን (እባብ) ወደ መሬት እያምዘገዘገ ሲጥልና ወደ ሲኦል ሲያወርድ የሚያይ ሁሉ፥ የእግዚአብሔር ኃይልና ሥልጣን ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ይጠራጠራል ብለን መገመት ያስቸግረናል።

ሐ. ሰይጣን ጊዜያዊም ቢሆን የዚህ ዓለም ገዢ እንዲሆን እግዚአብሔር የፈቀደለት፥ ኃይልንም የሰጠው፥ የቅዱሳንን ደስታ ለመጨመር ነው። ይሄ ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን በአዕምሮአችን ውስጥ አንዳንድ ጥያቄዎችን መፍጠሩ አይቀርም። የግል ሕይወታችንን ስንመለከት፥ በመከራ ውስጥ ካለፍን በኋላ የምናገኘው ደስታ ትልቅ እንደሆነ እናውቃለን።

## ሐ ርኩሳን መናፍስት

### ሐ-1. ርኩሳን መናፍስትና ተፈጥሮአቸው

#### ❶ ርኩሳን መናፍስት መንፈስ ናቸው።

በመጽሐፍ ቅዱስ «መንፈስ» የሚለው ቃል የተለያየ ትርጉም እንደያዘ እናያለን። ከፉም፥ ደግም የሆኑትን ነገሮች ለመግለጽ «መንፈስ» የሚለውን ቃል እንጠቀማለን። መላእክት መንፈስ እንደሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። «መላእክት የሚድኑትን ለማገልገል የሚላኩ የእግዚአብሔር አገልጋዮች የሆኑ "መንፈሶች" አይደሉምን?» ይላል (ዕብ. 1:14)። ሰይጣን ራሱ የሚታወቀው ርኩስ መንፈስ፣ ክፉ መንፈስ፣ አሳሳች መንፈስ፣ ወዘተ... በመባል ነው። «አንድ መንፈስ ወደ እግዚአብሔር ፊት ቀርቦ እኔ ላሳስተው እችላለሁ አለ» (1 ነገሥት 22:21)። ሉሲፈር መጀመሪያም ቢሆን፥ ተፈጥሮው መንፈስ እንጂ ሥጋ የለበሰ አልነበረም። በእግዚአብሔር ላይ አምጾ ሰይጣን ከሆነም በኋላ መንፈስ ከመሆን አልተለወጠም። ርኩሳን መናፍስት መንፈስ ባይሆኑ ኖሮ፥ ወደ ሰው ሕይወት መግባት አይችሉም ነበር (ሉቃስ 8:30)።

ርኩሳን መናፍስት መንፈስ ይሁኑ እንጂ ሕያውነት የሌላቸው ናቸው ማለት አይደለም። አንዳንድ ሰዎች ርኩሳን መናፍስት ተጨባጭነት የሌላቸው «ስሜቶች» ብቻ ናቸው ብለው በማሰብ ከስህተት ላይ ራሳቸውን ይጥላሉ። ክፉም ሆኑ ጥሩ መንፈሶች «ምድብ ህልውና» (personal being) ያላቸው ናቸው። ይሁን እንጂ በኃጢአት የወደቀው

ሰው፣ በሥጋዊ ህልውና ውስጥ በመታሠሩ፣ በሥጋዊ ዐይኑ ማየት የማይችለውን ሁሉ «አለ» ብሎ ማመንና መቀበል ያቅተዋል። ለሰው ቀርቶ እግዚአብሔርን ራሱን በሥጋዊ ዓይን ማየት ስለማይችል ብቻ «እግዚአብሔር አለ» ብሎ ማመን አይሆንለትም።

ሰይጣንም የብዙዎቹን አዕምሮ እንዳያስብ ስለሚቀልፍ «በዐይናችን የማናየውን ነገር «አለ» ብለን መቀበል የለብንም» እንዲሉ ያደርጋቸዋል። ኃጢአተኛ ሰይጣንን በውስጡ ይዞ ቢኖርም፣ ህያውነቱን ግን መገንዘብ አይሆንለትም። ሕይወቱን በምኞትና በራስ ወዳድነት ሞልቶ እየኖረ ሲወስደው፣ በሥጋዊ ዐይኑ ማየት አይችልም።

## ● ርኩሳን መናፍስት በአዕምሮ የላቁ ናቸው።

እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረቶች ሁሉ ርኩሳን መናፍስት የበለጠ ብልሆችና አዋቂዎች ናቸው። በረጅም ጊዜ ጥናትና ትጋት ሰው ብዙ ዕውቀትን ሊያገኝ ይችላል። ይሁን እንጂ አዋቂ የተባለ አንድ ሰው ከክፉ መናፍስት ጋር ሲወዳደር ዕውቀቱ ሰማይ ከምድር የሚርቀውን ያህል ይራራቃል። እርግጥ ነው እነዚህ «የወደቁ መላእክት» (ርኩሳን መናፍስት) ወደ መሬት ሲጣሉ ቀድሞ የነበራቸውን ጥበብ እንደያዙ አልቀሩም። ስለ እግዚአብሔር የነበራቸው መረዳት ሁሉ የተበረዘ ከመሆኑም በላይ፣ ዕውቀታቸውን ለራሳቸው ጥቅም ማዋል አይችሉም። ይሁዳ በመልእክቱ ስለ ክፉዎች ሲናገር «እነዚህ ሰዎች ግን ለማስተዋል ያቃታቸውን ነገር ሁሉ ይሳደባሉ፤ አዕምሮ እንደሌላቸው እንስሶች በተፈጥሮ ስሜት የሚያውቁት ነገር ቢኖር እንኳ በእርሱ ይጠፋሉ» (ይሁዳ ቁ. 10) ሲል የጠቀሰው፣ ርኩሳን መናፍስትንም ይመለከታል። የእግዚአብሔርን ቅድስና ያውቃሉ፤ ይሁን እንጂ አይወዱትም።

ርኩሳን መናፍስት እውቀታቸው ሁሉ ከራሳቸው የመነጨ አይደለም። ሰይጣን ጥሩውን ነገር በማበላሸት መለወጥ ይችላል እንጂ፣ ክፉን እንኳን የመፍጠር ችሎታ የለውም። ነገር ግን ችሎታው ከራሱ የመነጨ ባለመሆኑ ብቻ ዕውቀቱንና ያለውን ኃይል አቃለን አናየውም። በጥበቡና በተንኮሉ የመጀመሪያውን ሰው አዳምን እንደጣለ አይተናል፤ ኢየሱስን ደግሞ ለመጣል ምን ያህል ጥበብንና ዘዴን እንደተጠቀመ አንብበናል። ጳውሎስም «ይህንንም የማደርገው የሰይጣን የተንኮል ሥራ ስለምናውቅ እንዳያታልለን ብዬ ነው» (2 ቆር. 2:11) በማለት ስለ ሰይጣን ተንኮለኛነት ይናገራል። ርኩሳን መናፍስት በዕውቀታቸው በምድር ካሉ ቅዱሳን ሁሉ ይበልጣሉ።

## ❸ ርኩሳን መናፍስት የማይሞቱ ናቸው።

ሰው ጠላት ቢኖሳበት፣ ከዚያ ጠላቱ በሞት ሊለያይ ይችላል። ኢየሱስን በህጻንነቱ ለመግደል የተነሳው ሄሮድስ ሲሞት፣ የእግዚአብሔር መልአክ ዮሴፍን «ሕጻኑን ለመግደል የሚፈልጉት ሰዎች ስለሞቱ ተነሳና ሕፃኑን ከእናቱ ጋር ይዘህ ወደ እሥራኤል አገር ሂድ አለው» (ማቴ. 2:20)። ሰይጣን ግን ስለማይሞት እስከ መቃብራችን ድረስ ይከተለናል። ጌታን የማያውቁትን ደግሞ በሲኦል እንደገና ያገኛቸውና መከሰሱንና ማሰቃየቱን ይቀጥላል። ርኩሳን መናፍስት የማይሞቱ፣ ጡርሶ የማይደክሙና ተስፋ የማይቆርጡ ናቸው። አንዳንድ ሰዎች ምንም ያህል ብርቱና ጠንካራ ቢሆኑም፣ ጉልበታቸው የተወሰነ ስለሆነ ከአንድ ጦርነት በኋላ ለጥቂት ጊዜ ማረፍ አለባቸው። ሰዎች የሚፈልጉትን ዓይነት ድል በሚፈልጉት ሰዓት ካላገኙ ተስፋ ቆርጠው የተነሱበትን ዓላማ ከግቡ ሳያደርሱ በመካከል ይተውታል። ሰይጣን ግን ተስፋ አይቆርጥም፤ በሰዎችም ላይ ተንኮል ለመፈጸም ፈጽሞ አይ ደክምም። ጊዜው ደርሶ እግዚአብሔር ራሱ ካላሰረው ማቆሚያ የለውም።

## ● ርኩሳን መናፍስት በጭካኔ የተሞሉ ናቸው።

እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፤ በቅድስናውም ተወዳዳሪ የለውም። ሰይጣንም ጨካኝ ስለሆነ በእርኩሰቱ የሚወዳደረው የለም። የሰዎችን ኃጢአትና ክፋት የምንለካው በእርሱ ክፉነት ነው። እግዚአብሔርን በመሰልን ቁጥር ቅዱሳን እንሆናለን፤ ሰይጣንንም እየመሰልን ስንሄድ ደግሞ ክፉዎች እንሆናለን። እነዚህ «የወደቁ መላእክት» (ርኩሳን መና ፍስት) ኃጢአት አመንጪዎች ናቸው፤ በፈጣሪያቸው ላይ የአመጽ ኛነት ድምጻቸውን ያሰሙት የመጀመሪያዎቹ እነርሱ ናቸው። ርኩሳን መናፍስት ተንኮለኛነታቸው አንዳንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜ ነው። በተንኮለኛነታቸው ሰዎችን ያለማቋረጥ ማስጨነቅ ባህሪያቸው ነው። በኃጢአት ውስጥ ደስታ፣ ሰላም፣ ዕረፍት እንደሌለበት ቢያውቁም ሰዎችን ወደዚያ ገፍቶ መጣል፣ ወይንም ኃጢአት እንዲሠሩ ማባበል ደስ ይላቸዋል። ርኩሳን መናፍስት እንደ አበደች ውሻ ደም የተጠሙ ናቸው፤ ከአበደች ውሻ የሚለዩበት ውሻዋ ሲደክማት ትቆማለች፣ ርኩሳን መናፍስት ግን ማቆሚያ የላቸውም።

ርኩሳን መናፍስት ጥረታቸው በምድር ያለውን ነፍስ ያለውን ፍጡር ሁሉ ወደ ዘለዓለማዊ ሞት ለማድረስ ነው። ሰይጣን በእግዚአ ብሔር ላይ ያለውን ጥላቻ ለመግለጽ የሚሞክረው «ቅዱሳንን» በመ ዋጋት ነው። የሚቻለው ቢሆን ጥረቱ ከክርስቶስ መንጋ ውስጥ አንድም ሰው በሕይወት እንዳይኖር ለማድረግ ነበር። የተንኮሉ ስፋት ይህን ያክላል ብሎ መናገር ያስቸግራል። እግዚአብሔርን በቀጥታ መዋጋት ስለማይችል፣ በተዘዋዋሪ የሚዋጋው የእርሱ የሆኑትን ቅዱሳንን በመተናኮል

ነው። ከሰመለመው የእግዚአብሔር መስክ የምንውል፣ ከጠራው የውሃ ምንጭ የምንጠጣ ከሆነ፣ የሰይጣን ጦር በእኛ ላይ የሚወረወር መሆኑን በመረዳት በጥንቃቄ ሁልጊዜ ንቅተን መጠበቅ ይገባናል። እግዚአብሔር ምህረቱን በሰፊው በሚያሳይበት ሥፍራ ሁሉ ምን ያህል እንደሚከብር ሰይጣን ስለሚያውቅ፣ የእግዚአብሔር ምህረት ወደ ሕዝቡ እንዳይፈስ ግድቡን ይሠራል።

## ❺ ርኩሳን መናፍስት ጸብ ጫሪ ናቸው።

ርኩሳን መናፍስት ጥላቻ፣ መራራነት፣ ጦርነትና በቀል ደስ ያሰኛቸዋል። ሰዎች በአጋንንት መሞላታቸውን በግልጽ የምናይበት አንደኛው መንገድ በውስጣቸው ይህን የመሰለውን ተጻራሪ ኃይል ስናይ ነው። ርኩሳን መናፍስት ሰውን ከሰው ጋር መንግሥትን ከመንግሥት ጋር ማጋጨት፣ ጦርነት መፍጠር ተፈጥሮአቸው ነው። የሰው ደም እንደ ውሃ ሲፈስ ልዩ ደስታ ይሰጣቸዋል።

## ❻ ርኩሳን መናፍስት ውሸታሞች ናቸው።

ኢየሱስ ስለ ሰይጣን ውሸታምነት ሲናገር፣ «እውነት በእርሱ ስለሌለ ከእውነት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፤ እርሱ ሐሰተኛና የሐሰት አባት ስለሆነ ሐሰት በሚናገርበት ጊዜ ከገዛ ራሱ አውጥቶ ይናገራል» ይለናል (ዮሐ. 8:44)። ውሸቱ በግልጽ የታየው አዳምንና ሄዋንን «ከዚህ ፍሬ በበላችሁ ጊዜ ሞትን አትሞቱም» ባላቸው ጊዜ ነው። ነገርን አጣሞ በማቅረብና በማሳየት የተካነ ነው። መንግሥቱን ለማስፋፋት የግድ መዋሸት አለበት፤ አለበለዚያ ኃጢአት መሥራት ጥሩ ነው በማለት የኃጢአትን መንገድ የሚመርጥ ማንም አይኖርም ነበር። ሰዎችን ማታለል የቻለባቸው ሁለት ውሸቶች አሉት። አንደኛው ሰዎች «ሰይጣን የለም» ብለው እንዲያምኑ ማድረግ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ሰው «ነጻ» መሆን የሚችለው ራሱን በነጻነት መግለጽ የቻለ እንደሆነ ነው በማለት የሚዋሸው ውሸት ነው። ሌላው ሰውን ዋሽቶ የሚያታልልበት መንገድ እውነት ያልሆነ ትንቢት የሚናገሩትን፣ እውነት ያልሆነ ተአምርና ፈውስ የሚያሳዩትን ሰዎች በማስነሳት ነው። ጳውሎስ ስለነዚህ ሰዎች ሲናገር «ይህም የሚያስደንቅ ነገር አይደለም፤ ምክንያቱም ሰይጣን እንኳ የብርሃን መልአክ ለመምሰል ራሱን ይለውጣል። ስለዚህ የሰይጣንም አገልጋዮች የጽድቅ አገልጋዮችን ለመምሰል ራሳቸውን ቢለውጡ አያስደንቅም፤ በመጨረሻ የሥራቸውን ዋጋ ያገኛሉ» ይላል (2 ቆሮ. 11:14-15)። ኢየሱስም ስለ ሀሰተኞች መሲሆችና ነቢያት ሲያስጠነቅቀን «...ሀሰተኞች መሲሆችና ሀሰተኞች ነቢያት ይነሳሉ፤ እነርሱ ቢቻላቸውስ የእግዚአብሔርን ምርጦች እንኳ ለማሳሳት ታላላቅ ተአምራትንና ድንቅ ነገሮችን ያሳያሉ» ይላል (የማቴ. 24:24)።

## ❼ ርኩሳን መናፍስት ወደ ሰው ሕይወት መግባት ይችላሉ።

በይሁዳ አስቆሮቱ ሕይወት ውስጥ ሰይጣን እንደገባበት ሉቃስና ዮሐንስ በግልጽ ይናገራሉ። «በዚያን ጊዜ ከአሥራ ሁለቱ አንዱ በሆነው በአስቆሮታዊው ይሁዳ ሰይጣን ገባበት» (ሉቃስ 22:3)፤ «...ይሁዳ ጉርሻውን ከተቀበለ በኋላ ወዲያውኑ ሰይጣን ገባበት...» (ዮሐ. 13:27)። ይሁን እንጂ ያለሰው ፈቃድ ሰይጣን ወደ ሰው ሕይወት በግድ የመግባት ችሎታ የለውም። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ «... ለዲያብሎስ ሥፍራ አትስጡት..» ሲል የሚመክረን (ኤፌ. 4፡27)። ሰው ሆን ብሎ ኃጢአት ሲሠራ ለሰይጣን የልቡን በር ከፍቶ ማስገባቱ ነው። በይሁዳ አስቆሮቱ ልብ ሰይጣን መግባት የቻለው ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት ወስኖ በመነሳቱ ነው። ያኔ ሰይጣን ወደ ልቡ ለመግባት የሚያስችለው የተከፈተ በር አገኘ። ጴጥሮስም ሀናንያን «...ሰይጣን ስለምን ወደ ልብህ ገባ?» (የሐዋ. 5:3) ሲለው፥ ለምን የልብህን በር ለሰይጣን ከፈትክለት ብሎ መጠየቁ ነበር። ወደ ልቡ ሰይጣንን ፈቅዶ የሚያስገባ ሰው የዲያብሎስ ልጅ፥ የእውነት ሁሉ ጠላት፥ ማታለልና ክፋት የሞላበት፥ ቀጥተኛውን የእግዚአብሔርን መንገድ የሚያጣምም...» ይሆናል (የሐዋ. 3:11)።

## ❽ ርኩሳን መናፍስት ችክ ያሉ ናቸው።

ሰይጣን በቀላሉ ተስፋ እንደማይቆርጥ ያየነው ኢየሱስን ለመፈተን ወደ ምድረ በዳ ይዞት ሲወጣ ነው። በዚረጋው ወጥመድ ኢየሱስን መጣል እንደማይችል በመጀመሪያው ሙከራው ቢያውቅም፥ ተስፋ ቆርጦ በመተው ፈንታ ሦስት ጊዜ በተለያየ መንገድ እንደሞከረ፥ እስከ መስቀል ድረስም ኢየሱስን ከመፈተን ወደ ኋላ እንዳላለ እናውቃለን። መስቀል ላይ ሆኖም አልተወውም። «አምላክ ከሆንክ እስቲ ከመስቀል ውረድ» አለው (የማር. 15:30)። ይህን ያለው ክርስቶስ በሞቱ የሚያገኘውን ድል ስላወቀ ነው። ሰይጣን በችክነቱ ተወዳዳሪ የሌለው ፍጡር ነው። አማኝን አንድ ጊዜ ብቻ ፈትኖት ባይሸነፍለት «አቃተኝ» በማለት ትቶት አይሄድም። ትንሽ አረፍ ብሎ በሌላ መንገድና ዘዴ እንደገና ሊያጠምደው ይሞክራል።

## ❾ ርኩሳን መናፍስት ፈሪዎች ናቸው።

ያዕቆብ «ሰይጣንን ተቃወሙት ከእናንተ ይሸሻል» (ያዕ. 4:7) ሲል ፈሪነቱን በደንብ ተገንዝቦ ነው። ሰይጣን በመስቀል ላይ ድል የመታውን ኢየሱስን በጣም ይፈራል፤ እንዲሁም በኢየሱስ ስም ደፍረው የሚመጡበትንም ይፈራል። ሰይጣን እንዲፈራና እንዲሸሽ ለማድረግ በክርስቶስ መታመንና መታዘዝን ይጠይቃል። ሰይጣን የተሸነፈ ጠላት

ነው። በክርስቶስ ስም ደፍረው በሚቋቋሙት አማኞች ፊት መቆም አይችልም። ሰው ብቻውን በዕውቀቱ፥ በጥበቡና በተንኮሉ ተወዳዳሪ የሌለውን ሰይጣን መቋቋም አይችልም። ማንንም ማታለልና ማሳሳት፥ ወደ ሰው ሕይወት መግባት፣ ማሸነፍና መግደል ይችላል። ይህን ዓይነቱን ኃይለኛ ጠላት ለብቻው ለመቋቋም ኃይልና ችሎታ ያለው ሰው የለም። ስለዚህ ነው በራሳችን ጉልበት እንዳንታመን የእግዚአብሔር ቃል የሚመክረንና የሚያስጠነቅቀን። ማሸነፋችን የተመሠረተው በኃልኃታው ድል ብቻ ነው፤ እርሱን ሳንይዝ ብቻችንን ካገኘን ሰይጣን ያዋርደናል።

## ሐ-2. ርኩሳን መናፍስትና ኃይላቸው

ጳውሎስ ክርስቲያኖች የሚኖርባቸውን ብርቱ ትግል ለማስረዳት፥ አስቀድሞ ክፉ መናፍስት ስላላቸው ብርቱ «ኃይል» ይናገራል። ሰይ ጣንም ኃያልነቱን የሚናገረው፥ በእርግጥም ባለው ኃይል ተመክቶ ነው። ኃይል የሌለውና ደካማ ቢሆን ኖሮ፥ ሰይጣን ራሱን ከፍ ሲያደርግ እውነት አይደለም ብለን ንቀን ችላ እንለው ነበር። ይሁን እንጂ ከእ ጋንንት ሠራዊት ጋር ሆኖ የሚፈጽማቸውን እያየን፥ ኀያል መሆኑን መካድ አንችልም። ሰይጣን ያለውን ኃይል ለማወቅ፥ ኃይሉን የሚያሳ ይበት ስሙን፣ ተፈጥሮውን፣ በሥሩ ያሉትን ሠራዊቱንና ከክፉ መናፍ ስት ጋር ተባብረው የሚያደርሱትን ጥፋት ማወቅ ያስፈልገናል።

«የክፉ መናፍስት»፥ በስማቸው ብቻ ያላቸውን ኃይል ምን ዓይነት እንደሆነ መገንዘብ እንችላለን። የአዳምን ልጆች በማርከስ (በማሳሳት) ሕይወታቸውን በቁጥጥር ሥር ያደርጋሉ። ከግል ልምምዳችን እንደምን ረዳው ሥጋና ደም ከክፉ መናፍስት ጋር ፍጹም ሊወዳደሩ እንደማይ ችሉ እናውቃለን። ክርስቶስ ክፉ መናፍስትን ለመደምሰስ ባይመጣ ኖሮ ሁላችንም በኃጢአታችን ሞተን በጠፋን ነበር። የክፉ መናፍስት መሪ የሆነውን ሰይጣንን መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጸው «ኃይለኛው» ይለዋል (ሉቃስ 11:22)። ጴጥሮስ ደግሞ «የሚያገሳ አንበሳ» ይለዋል (1 ጴጥ. 5:8)። የአራዊት ሁሉ ንጉሥ የሆነው አንበሳ ሲያገሳ፥ ሊበላቸው ያሰባ ቸውን ሁሉ በድምጹ ብቻ አስደንግጦ በቀላሉ ያለአንዳች ተቃውሞ በቁጥጥሩ ሥር ያውላቸዋል። የሰይጣንም ኃይል ይህንን ይመስላል። የዓለምን ሰዎች ያለአንዳች ትግል በቀላሉ በቁጥጥሩ ሥር ማድረግ ይች ላል። ይህንን ጠላት ሊቋቋሙት የሚችሉት የኃያሉ የእግዚአብሔር ልጆች ብቻ ናቸው።

❶ ክፉ መናፍስት ኃይለኛነታቸው በስም ብቻ ሳይሆን፥ በተፈጥሮአ ቸውም ጭምር ነው። መገንዘብ ያለብን እነዚህ ክፉ መናፍስት ቀደም ሲል መላእክት የነበሩ ሲሆኑ፥ ቀደም ሲል ይዘውት የነበ ረውን ኃይል ያልተገፈፉ መሆናቸውን ነው። መላእክት ስላላቸው

ኃይል ዳዊት በመዝሙሩ፥ «...እናንተ ኃያላንና ብርቱዎች መላእክቱ፡ እግዚአብሔርን አመስግኑ...» (መዝ. 103፡20) በማለት ይናገራል። መላእክት እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ የበለጠ ኃይል ያላቸው ናቸው። ሰው ግን ከመላእክት ትንሽ ያነሰ እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል (ዕብ. 2፡7)። መላእክት ከሰው የበለጡ የሆኑት መንፈስ በመሆናቸውና ሰው ደግሞ ሥጋዊ በመሆኑ ነው። ሰው ሥጋዊ ተፈጥሮው ያለው በመሆኑ ነፍሱ ወደ ላይ ከፍ እንዳይል ወደታች ተጭኖ ይከለክለዋል። ክፉ መናፍስት ግን መጀመሪያ አፈጣጠራቸው «መልአክ» በመሆኑና እንደ ሰው ወደ ታች የሚጫናቸው ሥጋ ስለሌላቸው፥ ኃይላቸው ከሰው ኃይል የበለጠ ነው። ፍጥነታቸውም በነፋስ እንደሚፈናጠር የእሳት ነበልባል ነው። መንፈስ በመሆናቸው በሰው ጉልበትና ኃይል ሊገፉ አይችሉም። እሳትም ሆነ የሰው ጦር ሊጎዳቸው አይችልም። ከእግዚአብሔር ኃይል በስተቀር እነርሱን ማሠር የሚችል ኃይል የለም። ሰይጣን በመውደቁ ምክንያት ወደ ተቀደሰ ሕይወት የሚያቀርበውን ኃይሉን ይጣ እንጂ የተፈጥሮ ኃይሉን አላጣም። አሁንም መልአክ በነበረበት ጊዜ የነበረውን ኃይሉን እንደያዘ ነው።

❷ የክፉ መናፍስት ሌላው ኃይላቸው በቁጥር መብዛታቸው ነው። አንበጣዎች ትናንሽ ፍጥረቶች ሲሆኑ፥ በብዛታቸው ግን በሰው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረስ ይችላሉ። በተፈጥሮአቸው ኃይለኞች የሆኑ ርኩሳን መናፍስት ብዛት ሲኖራቸው ምን ያህል ከፍተኛ ጥቃት በሰው ላይ ማድረስ እንደሚችሉ መገመት አያስቸግርም። ሰይጣን ዓለምን ለማስጨነቅ የሚችሉ በቂ ርኩሳን መናፍስት አሉት። ሠራዊቱን በተጠንቀቅ ያላሰለፈበት ከሰማይ በታች አንድም ሥፍራ የለም። በማንኛውም ሥፍራ ርኩሳን መናፍስት የማይከተሉት አንድም ሰው የለም። የተለየ ከፍተኛ ጥፋት ለመፈጸም ሰይጣን በሚፈልግበት ወቅት የርኩሳን መናፍስት ሠራዊትን ይልካል (የማር. 5፡9)። አንዱን ሰው ለመዋጋት ሰይጣን ይህን ያህል ከፍተኛ የርኩሳን መናፍስት ሠራዊት የሚልከው፥ በጠሩ ውስጥ ምን ያህል ብዙ አገልጋዮች ቢኖሩት ነው? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ያመጹትን መልአክት ከሰማይ አሽቀንጥሮ ወደ መሬት ሲጥል የወደቁት አንድ ሦስተኛ የሚሆኑ እርኩሳን መናፍስት በመሆናቸው ወደ ምድር ከተጣሉበት ጊዜ አንስቶ የሰዎችን ልጆች ለመተናኮል በተለይ በሰማያዊ ጉዞ ላይ ያሉትን ከመስመር ለማስወጣት ቁጥራቸው በቂ ነው።

❸ ርኩሳን መናፍስት ከቁጥራቸው መብዛት ሌላ የበለጠ ኃይለኛና አደገኛ የሚያደርጋቸው ለጥፋት ያላቸው ህብረትና አንድነታቸው ነው። ይሁን እንጂ በመካከላቸው «ፍቅር» አለ ማለት አይደለም። ምክንያ

ቱም ይህን ዓይነት መልካም ባህሪ በርኩሳን መናፍስት መካከል ሊገኝ ስለማይችል ነው። ነገር ግን አንድ ዓይነት የሆነ ዓላማና ግብ አላቸው፤ ያም እግዚአብሔርንና ሰውን ለመዋጋትና ለማሸነፍ ነው። የሚያስተሳስራቸው ፍቅር ሳይሆን፣ ጥላቻና ክፋት የሞላበት ዓላማቸው ሲሆን፣ እንዲሁም ለክፉ ተግባራቸው ካልተባበሩ ከሚሰማቸው ተስፋ ቢስነት ማምለጥ ስለማይችሉም ጭምር ነው።

ይሄ ክፉ የሆነው የክፉ መናፍስት ህብረት የጸና ነው። ኢየሱስ ራሱ ሲናገር «ሰይጣንም ሰይጣንን የሚያወጣ ከሆነ፣ እርስ በርሱ ከተለያየ፣ መንግሥቱ እንዴት ትቆማለች?...» አለ (የማቴ. 12:26)። እንዲሁም ከርኩሳን መናፍስት መካከል ለሰይጣን «አንታዘዝም» በማለት የሚያምጽ የለም። ርኩሳን መናፍስት ቁጥራቸው ብዙ ይሁን እንጂ በሁሉም ውስጥ ያለው አንድ ዓይነት የሆነ የክፋት መንፈስ ነው። ኢየሱስ ለጠየቀው ጥያቄ ርኩስ መንፈሱ «ብዙዎች ስለሆንን ስሜ ሠራዊት ነው» ሲል መለሰለት (ማር. 5:9)። እዚህ ላይ የሰጠው መልስ «ስማችን» ሳይሆን «ስሜ» የሚል ነው። እነዚህ ርኩሳን መናፍስት የተንኮል ሥራቸውን የሚያካሂዱት አንድ ዓላማ ይዘው በህብረት ሲሆን፣ ከተቻላቸው የሰውንም መተባበር ለማግኘት ጥረት ያደርጋሉ።

❶ ርኩሳን መናፍስት ኃይለኛ የሚያደርጋቸው ሌላው ነገር አጥፊ የሆነው ተግባራቸው ነው። የዚህ ዓለም ገዢ በዓለም ላይ የሚያደርሰው ጥፋት እጅግ ከፍተኛ ነው። እርግጥ ነው ተፈጣሪ ስለሆነ የሌለ ነገር መፍጠር አይችልም። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር የፈጠረውን በጎ ነገር በመጥፎ በመጠቀም በዓለም ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዲደርስ ያደርጋል። በባህር ማዕበልን፣ በምድር ነፋስን፣ በሰማይ መብረቅን በማስነሳት ከፍተኛ እልቂት ሊያደርስ ይችላል። ይህን የበለጠ ለመረዳት ብንፈልግ፣ በኢዮብ ሕይወት ላይ ያደረሰውን መአት (ተደራራቢ አደጋ) መመልከቱ በቂ ነው (ኢዮብ 1:19)።

ሰይጣን በሰው አካል ላይ ጉዳት ለማምጣት የተወሰነ ኃይል ከእግዚአብሔር ተሰጥቶታል፤ ለዚህም የኢዮብ ታሪክ መረጃችን ነው፤ «ከዚህ በኋላ ሰይጣን ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ ኢዮብን ከራስ ጠጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ ድረስ በክፉ ቁስል እንዲሰቃይ አደረገው» ይላል (ኢዮብ 2:7)። ሰይጣን ትልቁ ዓላማው የሰውን ነፍስ ማወክ ነው፤ ያንን ለማድረግ የሚጠቀመው የሰውን ሥጋ በማወክ ነው። ሰው ሥጋው ሲነካ ሰላምና ዕረፍት ስለሚያጣ በቀላሉ በውስጡ ማጉረምረም እንደሚፈጠር ሰይጣን ያውቃል። ሥጋችን ለነፍሳችን ተገዢ በመሆን ፈንታ ብዙ ጊዜ ሥጋችን የነፍሳችን ጌታ ሲሆን ይታያል። ስለዚህ ሰይጣን ወደ ነፍሳችን ለመድረስ፣ ሥጋችንን ማወክ ሌላው አቋራጭ መንገዱ ነው። የመጀመሪያው

ሰው በኃጢአት ሲወድቅ፥ ሰይጣን በኃጢአት አማካይነት ሊገባ የሚችልበትን በር ከፍት አድርጎለታል። የክርስቶስ የማዳን ኃይሉ ሰውን ካልጠበቀውና ካልተከላከለው፥ ሰይጣን የሰው ልብ ባዶ ሆኖ ሲያገኘው በተከፈተለት በር ዘው ብሎ መግባቱ የማይቀር ነው።

ሰይጣን የእግዚአብሔርን ጥበብ ቢያደንቅም፥ እርሱም ጥበበኛ በመሆኑ የከፋት ሥራውን የሚያካሂደው በጣም በረቀቀ መንገድ ነው። እግዚአብሔር በቅዱሳን እንደሚገለገለው ሁሉ፥ ሰይጣንም እግዚአብሔርን በማይታዘዙት ሰዎች አማካኝነት ይሠራል። "...እርሱ በማይታዘዙት ሰዎች አሁን የሚሠራ ርኩስ መንፈስ ነው" ይላል (ኤፌ. 2:2)። ክርስቲያኖች ከሆንን ወደ ነፍሳችን ርኩሳን መናፍስት ይገባሉ ብለን መፍራት አይገባንም። ምክንያቱም እግዚአብሔር እንዲገቡ ስለማይፈቅድላቸው ነው። ይሁን እንጂ፥ ሰይጣን የእም ነታችንን ደካማነት በማየት ዙሪያችንን መዞርና በአካባቢያችን አደጋ መጣሉ የማይቀር ነው። በገኘው ዕድል ሁሉ በመጠቀም ይታገለ ናል፤ እኛም እግዚአብሔር በሚሰጠን ኃይልና ጉልበት የምንታ መን ከሆነ፥ ሁልጊዜ እናሸንፈዋለን። ያለ እግዚአብሔር ዕርዳታ ለብቻችን ኃይለኛውን ጠላታችንን ማሸነፍ ግን ጨርሶ አንችልም። በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ጠንካራ ናቸው የሚባሉትን እንኳን ሰይ ጣን አቁስሎአቸው እየተንቀጠቀጡና እየጮሁ ወደ እግዚአብሔር ተመልሰዋል። ይሄን መግለጽ አስፈላጊ ሆኖ ያገኘነው የሰይጣንን ኃይለኛነት ተመልከተን በተስፋ መቁረጥና በፍርሃት እንድንሞላ ለማ ድረግ ሳይሆን፥ ጠላታችን ደካማ ነው ብለን ተዝናንተን እንዳንቀ መጥ ለማስገንዘብ ነው።

## ሐ-3. ርኩሳን መናፍስትን የማንፈራበት ምክንያቶቻችን

ሰይጣን ኃይለኛ ነው፤ በክርስቶስ የምንታመን ከሆንን ግን በድ ንጋጤና በፍርሃት የምንሞላበት ምክንያት አይኖርም። ከእኛ ይልቅ እግዚአብሔርን የማይፈሩት ሰዎች የበለጠ ሊፈሩት ይገባል። እኛ የምና መልከው አምላክ ተራራን ደልዳላ መሬት ለማድረግ የሚችል አምላክ ስለሆነ በእርሱ እንታመናለን። ሰይጣን ማድረግ የሚችለው ነገር ቢኖር በውስጣችን ፍርሃት እንዲፈጠር ማድረግ ብቻ ነው። በጉልበት ከእን በሳ የሚበልጡ አውሬዎች ቢኖሩም፥ አንበሳ በማጓራቱ ብቻ ሌሎች አውሬዎች በፍርሃት ተሞልተው እንዲንቀጠቀጡ ያደርጋል። እኛም በውስጣችን በክርስቶስ አማካኝነት ልዩ ኃይል ቢኖረንም፥ ሰይጣንን በመፍራት ብዙ ጊዜ እንደተንቀጠቀጥን እናስታውሳለን። የሰይጣን ኃይል ከምንገምተው በላይ መስሎ ሲሰማን፥ ልናውቃቸው የሚገባን እውነቶች አሉ። ይኸውም፥

1. እግዚአብሔር ካልፈቀደለት በስተቀር ሰይጣን ኃይሉን በእኛ ላይ መጠቀም አይችልም። በምድርም ሆነ በሲኦል ኃይል ሁሉ የእግዚአብሔር ነው። ይህንን እውነት ካወቅንና አጥብቀን ከያዝን ያለፍርሃት፥ በሙሉ ልብ የትም ቦታ መንቀሳቀስ እንችላለን። እኛ ልጆቹ መቋቋም የማንችለውን ኃይልና መሣሪያ እግዚአብሔር ለጠላታችን ለሰይጣን ስለማይሰጠው፥ በእግዚአብሔር ጥበቃ ውስጥ ያለነው ልጆቹ ሰይጣንን ልንፈራ አይገባም።

2. ሰይጣን ያለው ኃይል «ውስን» ነው። ውስንነቱም አንደኛ የፈለገውን ለማድረግ በቂ ኃይል የሌለው፥ ሁለተኛ ያለውን ኃይል እንኳን ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ለመጠቀም የማይችል በመሆኑ ነው። የሰይጣን ፍላጎቱ በምድር ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም፤ በሰማይ ያለውንም ይመኛል። እግዚአብሔርን ከዙፋኑ አውርዶ ራሱን ማስቀመጥ ይመኛል። እንግዲህ በውስጡ የሚቃጠለው ምኞትና ፍላጎት ይህን ይመስላል። እግዚአብሔር ሰይጣን የሚኖረውን ኃይል ይወስናል እንጂ፥ ሰይጣን እግዚአብሔርን መወሰን አይችልም። «ሕይወታችን በእግዚአብሔር ዘንድ ከክርስቶስ ጋር ስለተሰወረ» (ቆላስ. 3:3) ምንም የሚያስፈራን ነገር የለም» ይላል ሐዋርያው ጳውሎስ።

3. የሚያጽናናንና ደስ የሚለን፥ ሰይጣን ያለፈቃዳችን አስገድዶ ኃጢአት ሊያሠራን የማይችል መሆኑ ነው። ያባብለናል እንጂ የልባችንን ፈቃድ በፈለገው አቅጣጫ ያለፈቃዳችን መጠምዘዝ አይችልም። እግዚአብሔር ሰይጣን ምን ያህል ኃይል እንዲኖረው መወሰን ብቻ ሳይሆን፥ ኃይሉን በአንድ ጊዜ ምን ያህል መጠቀም እንዳለበትም ይቆጣጠራል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ለብቻችን እንድንታገል የተወን የሚመስለን ጊዜ አለ። እግዚአብሔር የሰይጣንን እንቅስቃሴ እያንዳንዱን እየተመለከተ ስለሆነ፥ የመጨረሻውን ድል አይሰጠውም በማለት ተስፋችንን ማጽናት አለብን። ሰይጣን ሰላማችንንና ደስታችንን የሚሰርቅበት ጊዜ አለ፤ ነጥቆ ወደ ራሱ ሊወስደን ግን አይችልም። በፍቅር የተሞላው የእግዚአብሔር ዓይን በእኛ ላይ፥ ክንዱም ሁልጊዜ በሰይጣን ላይ የተዘረጋ መሆኑን ካልተረዳን መጽናናትን አናገኝም።

4. ሰይጣን ምንም ዓይነት የከፋ ነገር ቢጠነስስም፥ መጨረሻው ለቅዱሳን ጥቅም እንዲሆን እግዚአብሔር ሊያደርገው ይችላል። ሰይጣን ዓላማው ሁልጊዜ ሰዎችን ለማጥፋት እንደሆነ ግልጽ ነው። የእግዚአብሔር ፍላጎት ግን፥ ቅዱሳን በዘመናቸው ጥበብንና ዕውቀትን እንዲቀስሙ ነው። ሰይጣን ቅዱሳንን ለማሳደድና ለማጥቃት የሚጠቀምበትን፥ እግዚአብሔር ለበጎ ነገር ያውለዋል፤ «ከጠቢባን አንዳንዶቹ ከባድ መከራ ይደርስባቸዋል፤ ይሁን እንጂ

በዚህ ምክንያት ነጥረውና ጠርተው በመውጣት እንከን የሌለባ ቸው ይሆናሉ፤ ይህም ሁኔታ የሚዘልቀው እግዚአብሔር ያቀደው መጨረሻ ጊዜ እስከሚደርስ ነው» ይላል (ዳንኤል 11:35)። ሰይጣን ቅዱሳንን ለማጥቃት ሀዘንና የተስፋ መቁረጥን መንፈስ ይልክባቸዋል፤ እግዚአብሔር ግን በዚያ ተጠቅሞ እምነታቸውን ያሳድግበታል።

ሰይጣንን በመናቅ ችላ የምንለው ከሆነ እንቅስቃሴያችን በጣም ደካማ ይሆናል። እግዚአብሔርን ከምንታመነው የበለጠ ሰይጣንን የምንፈራው ከሆነ ደግሞ፥ የሌለውን ኃይልና ግርማ ሞገስ መስጠታችን ይሆናል። የክርስቶስ ከሆንን፥ ያለ እርሱ ፈቃድ አንድም ነገር በእኛ ሕይወት አይደርስም። ሕይወትን የሰጠን አምላክ ብቻ ነው የሰጠንን ሕይወት መልሶ መውሰድ የሚች ለው። ስለዚህ የጠላታችንን ኃይለኛነት አይተን አንፈራም።

## ሐ-4. ርኩሳን መናፍስትና ግዛታቸው

ሰይጣን የግዛቱ ክልል የተወሰነ ነው፤ ያም የጨለማው ዓለም ነው። ውሱን የሆነው፥ የሚገዛበት ክልል ወይም ድንበር ብቻ ሳይሆን፥ የሚ ገዛበት ዘመንም የተወሰነ ነው። ገዢነቱ በአሁኑ ዓለም እንጂ ለዘለዓለም አይደለም። የሚገዛውም የጨለማ ልጆችን እንጂ የብርሃን ልጆችን አይደ ለም። ለጊዜው በዚህ ዓለም ሰይጣን የገዢነትን ሥልጣን ይዞ ይታያል። ክርስቶስ ለመጨረሻ ጊዜ ሲመለስ ግን የሰይጣን ሥራ ሁሉ የተጋለጠ ይሆናል፤ ስልጣኑም ከእርሱ ይወሰዳል፤ የሚዋጋበትም ጦር ይሰበራል። ከዚህም ምድር ተዋርዶ ወደ ሲኦል ይወርዳል። ሌላው ቀርቶ ክፋ ችንም እንኳን አይገዛም፤ በቅዱሳንም ላይ ቀድሞ ያደርግ እንደነበረው መከራና ስደትን ማስነሳት አይችልም። በመጨረሻም ከሠራዊቱና ከተ ከታዮቹ ጋር ለዘለዓለም ወደ ሲኦል ይጣላል።

የሰይጣን ዕድሜውና ዘመኑ የተቆጠረ መሆኑ ለተከታዮቹ መጥፎ ዜና ነው። ኃጢአተኞች አሁን የተመቻቸ ሕይወት በመኖራቸው፥ ምቾ ታቸውና ደስታቸው ጊዜያዊ መሆኑን ይረሳሉ። የክርስቶስ ተከታዮች በአሁኑ ዓለምና ዘመን በመከራ በመታሸታቸው ምክንያት ሲያለቅሱ፥ እነርሱ ግን የደስታ ሳቅ ይስቃሉ፤ ቅዱሳን ሲታረዙ፥ እነርሱ ሀር ይለብ ሳሉ። ጊዜያዊም ቢሆን ሰይጣን ለተከታዮቹ ደሞዝ ይከፍላል። በዚህ ሁኔታ እያባበለ ነው ኃጢአተኞችን ጆሮአቸውን ይዞ ወደፈለገበት የሚነ ዳው። ጊዜያዊ ደስታ፥ ምቾትና ክብር በማሳየት ልባቸው በእግዚአብ ሔር ላይ እንዲሸፍት ያደርጋል። የዓለምን ፍርፋሪ በመስጠት ከእግዚ አብሔር መንግሥት ብዙዎችን ያስኮበልላል።

የሰይጣን የግዛቱ ክልልና እንዲሁም የሚገዛቸው ሰዎች የተወሰኑ ናቸው። እነርሱንም መጽሐፍ ቅዱስ «የጨለማ ልጆች» ይላቸዋል። ይህም ማለት በጨለማ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ማለት ነው። ጨለማ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለያየ ትርጉም ይዞአል። ለምሳሌ በችግርና በመከራ ውስጥ ያለውን ሰው ኑሮ፥ «የጨለማ ሕይወት» እንደሆነ ይገልጸዋል (ኢ.ሳ. 50:10)፥ እንዲሁም የኃጢአትን ሕይወት ሲገልጽ፥ «ጨለማ» የሚለውን ቃል ይጠቀማል (ኤፌ. 5:11)I ሌላ ጊዜ ደግሞ «አለማወቅን» ለመግለጽ «ጨለማ» የሚለውን ቃል ይጠቀማል። የጨለማ ልጆች የሚላቸው በኃጢአት ሕይወት ውስጥ የሚኖሩትን እንጂ፥ አንዳንድ ጊዜ ኃጢአት የሚሠሩትንና ባለማወቅ የሚመላለሱትን ሕዝቦች አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያየ ሥፍራ «ኃጢአት» «ጨለማ» ተብሎ ተገልጿል። ለዚህ ዋናው ምክንያት መንፈሳዊ ጨለማ ወደ ኃጢአት ሕይወት ውስጥ ሊከት ስለሚችል ነው። ውጪያዊ የሆነው የኃጢአት ዋና አመንጪ ሰይጣን ሲሆን፥ ከውስጣችን ለኃጢአት ዝንባሌ እንዲኖረን የሆንነው ደግሞ ከአዳም በወረስነው ተፈጥሮአችን ስለምንሳብ ነው። ነፍሳችን በጨለማ ውስጥ ስትሆን፥ ወይም ከእውነት ተደብቃ ስትኖር ኃጢአታችን በግልጽ አይታየንም። መንፈስ ቅዱስ ወደ ነፍሳችን ብርሃኑን ሲፈነጥቅ ግን፥ ያኔ አደገኛው ኃጢአት በውስጣችን መኖሩ በግልጽ ይታየናልI ከዚያ ለማምለጥም ወደ እግዚአብሔር እንጠጋለን።

«ኃጢአት» አጥርተን እንዳናይ መንፈሳዊ ዐይናችንን ያሳውራል። የልባችን ጨለማነት ወደ ኃጢአት ብቻ ሳይሆን፥ አደጋ ወዳለበት ድቅድቅ ጨለማ ውስጥም ይከተናል። ኃጢአት ህሊናችንን ማደንዘዝ ስለሚችል፥ ከዚህ በፊት ጥቃቅን ኃጢአት እንኳን ስንሠራ ያስጨንቀን የነበረው ሁሉ ይቀርና፥ በተደጋጋሚ ኃጢአት ስንሠራ በመጸጸትና በማዘን ፈንታ ደስታ ይሰማናል። ኃጢአት ብርሃንን ይጠላል። «ክፉ ነገር የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልI ክፉ ሥራውም እንዳይገለጥበት ወደ ብርሃን አይመጣም» ይላል (ዮሐ. 3:20)። በኃጢአት ውስጥ የሚኖር ሰው ሥራው የተጋለጠ እንዳይሆን ከብርሃን ይሸሻል። በዚህም ሰይጣን ከጎኑ ሆኖ የእውነት ብርሃን እንዳይፈነጥቅበት በመከላከል ያግዘዋል። በመጨረሻም ከጨለማም ወደ ዘለዓለማዊ ጨለማ፥ የብርሃን ጭላንጭል ወደማይታይበት፥ እሳቱ ወደማይጠፋበት፥ ትሉ ወደማያንቀላፋበት የመከራ ሥፍራ ይጥለዋል።

ሰይጣን «የጨለማው ገዢ» የተባለው፥ እግዚአብሔር በጨለማ ውስጥ ያሉ ሁሉ በእርሱ አስተዳደር ሥር እንዲሆኑ ስለፈቀደ ነው። ኃጢአተኞች መኖሪያቸው ዲያብሎስ በሚኖርበት አካባቢ እንደሚሆን የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል። በጨለማ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሰይጣንን ለመቃወም ኃይል የላቸውም። አስተሳሰባቸውን እያጨለመ፥ በሚፈልገው አቅጣጫ እየመራ ሰይጣን በበላይነት ይገዛቸዋል። እውነትን እያጣመመና እንዲሁም ውሸት እየቀላቀለ በመስጠት «እውነትን» እንዳያዩ ያደርጋቸዋል። እንዲሁም ኃጢአትን እንዳይጠሉ ቀባብቶና አሳምሮ ያቀርብላቸዋል።

# 5

# ርኩሳን መናፍስት በአማኞች ላይ ያላቸው ሥልጣንና ኃይል

## -ሀ-
## ሰው የወደፊቱን የማወቅ ጉጉት አለው

ሰው በተፈጥሮው የወደፊቱን አስቀድሞ የማወቅ ጉጉት አለው። በወቅቱ የሚደሰትበትም ሆነ የሚጨነቅበት በቂ ምክንያት ቢኖረውም፥ በቅርቡ ያለውን በመመልከት ፈንታ ገና ስላልደረሰበት ስለ ወደፊቱ፥ በቅርብ ስለማያየው ነገር ማወቅ ይፈልጋል። በአንዳንድ ክርስቲያኖችም መካከል ይህ ድክመት ጉልህ ሆኖ ይታያል። «በመገለጥ» ስለ ወደፊት ማወቅ ስለሚፈልጉ፥ «የመገለጥ ስጦታ አለው» ብለው የሚያምኑት ሰው ብቻ እጁን ጭኖ እንዲጸልይላቸው ይፈልጋሉ።

አማኞች ባልሆኑ ሰዎች መካከል ይህ ፍላጎት የበለጠ ያይላል። የአሜሪካ ሕዝብ ስለ ወደፊቱ ይነግሩናል ብለው ለሚያምኗቸው «ሳይኪኮች» (ኮከብ ቆጣሪዎች) በዓመት ብዙ ሚሊዮን ብር ወጪ እን ደሚያደርጉ ታውቋል። ስለ ወደፊቱ ለማወቅ ልዩ ጉጉት ያላቸው በአሁኑ ዘመን የሚኖሩ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ፥ በብሉይ ኪዳን ዘመንም ይኖሩ የነበሩት ሰዎች ይህን ዓይነት ፍላጎት እንደነበራቸው በእግዚአ ብሔር ቃል ውስጥ መረዳት እንችላለን።

እግዚአብሔር በፕሮግራሙ ወይንም በዕቅዱ ውስጥ ምን እንዳለ ለልጆቹ የሚያሳውቅበት ልዩ ልዩ መንገድ አለው። ከነዚህ መካከል አን ደኛውና ዋናው «ቃሉ» ነው። ቃሉ እውነተኛ የሆነ ትንቢት የያዘ

ስለሆነ፥ ልጆቼ በጥንቃቄ ያንን እንዲመረምሩ ይፈልጋል። ይሁን እንጂ አማኞች በእግዚአብሔር ቃል ከተጻፈው ውጪ ሌላ መመሪያ በመፈለጋቸው የተነሳ ለሀሰተኛ ትምህርት በጣም የተጋለጡ ሆነው ይገኛሉ። ሰይጣንም ይህንን ጉጉታችንን በመጠቀም በርኩሳን መናፍስቶቹ አማካኝነት እኛን ለማሳሳት ከፍተኛ ጥረት ከማድረግ አይቦዝንም።

የእግዚአብሔር ቃል፥ አማኞች ርኩሳን መናፍስትን እንዳይጠሩ ከእነርሱ ጋርም እንዳይነጋገሩ ይከለክላል። እንዲያውም በብሉይ ኪዳን ውስጥ ርኩሳን መናፍስትን የሚጠሩና የሚያነጋግሩ እንዲገደሉ በግልጽ ያዛል (ዘፀ. 22:18)። በመካከለኛው ክፍለ ዘመን አውሮፓ ውስጥ ጠንቋዮች ርኩሳን መናፍስትን በመጥራት በሌላው ሰው ላይ ጉዳት ያደርሳሉ ተብለው ስለሚታመን፥ በእሳት እያቃጠሉ ይገድሏቸው እንደነበረ ታሪክ ይመሰክራል። በብሉይ ኪዳን፥ ጠንቋይ ማለት የወደፊቱን የሚያውቅ ወይንም የሚጠነቁል ማለት ነው። ጠንቋዮች ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ለርኩሳን መናፍስት የበሙና ያስገዙ በመሆናቸው ስለ ወደፊት መገለጥን ያገኙ ነበር።

እስራኤላውያን እግዚአብሔር በመንፈሱ የሚሰጣቸው ራዕይም ሆነ መገለጥ አልበቃ ብሏቸው በርኩሳን መናፍስት አማካይነት ስለ ወደ ፊቱ ለማወቅ ይጓጉ ነበር። የእግዚአብሔር ቃል ባለው ኃይልና ሥልጣን አለመርካት፥ በቃሉ ውስጥ ባለው መገለጥ በመገልገል ፈንታ፥ ከዚያ ውጪ የርኩሳን መናፍስትን ምክርና ሀሳብ መፈለግ በሞት ያስቀጣ ነበር።

አስማተኞችንና ጠንቋዮችን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ግልጽ መመሪያ ሰጥቶአቸው ነበር። «አምላካችሁ እግዚአብሔር ወደሚሰጣችሁ ምድር በምትገቡበት ጊዜ በዚያ የሚኖሩ አረማውያን የሚፈጽሙትን አጸያፊ ልማድ አትከተሉ» ብሏቸዋል (ዘዳ. 18:9)። እስራኤላውያን ከግብጽ ምድር ወጥተው ወደ ከነአን ሲገቡ፥ ከነአን ውስጥ ይኖሩ የነበሩት ሕዝቦች ልዩ ልዩ አምልኮት የነበራቸው፥ ከጠንቋዮችና ከአስማተኞች መመሪያ የሚቀበሉ ነበሩ። ሌላው ቀርቶ ሰውን ለእርኩሳን መናፍስት መስዋዕት በማድረግ ያመልኩ ነበር። እግዚአብሔር የራሱን መገለጥ ሰጥቶ እየመራ ያመጣቸው እስራኤላውያን፥ ጣኦት በሚመለክበት በከነአን ምድር ሲኖሩ በአንዳንድ አምልኮዎች እንዳይሳቡና እንዳይታለሉ ያስጠነቅቃቸው ነበር። እግዚአብሔር እንዲህ አለ «ልጆቻችሁን በመሠዊያችሁ ላይ የእሳት መስዋዕት አድርጋችሁ አታሳልፉ፤ ከወገናችሁ ማንም የሚርትን ጥራ በመግለጥ ዕድልን የማመልከት ልምድና እንዲሁም የአስማተኝነትንና የመተተኛነትን ልምድ እንዲከተል አትፍቀዱለት» ዘዳግም 18:10)። መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ መንገድ ከርኩሳን መናፍስት ጋር የሚደረገውን ማንኛውንም ዓይነት ግንኙነት ይከለክላል። ልዩ ልዩ አስማት በመጠቀም ስለ ወደፊቱ የሚናገሩ፥ ኮከብ በመቁጠር የሰውን የወደፊት

ዕድል «ይሆን ይመስላል» የሚሉ ነበሩ። በዘመናችንም ኮከብ በማስ ቆጠርና በሌላ ዘዴ የወደፊት ዕድላቸውን ለማወቅ የሚፈልጉ ሰዎች ቁጥር ምን ያህል ብዙ እንደሆነ እናውቃለን።

ልዩ ልዩ ዓይነት ድግምት በመድገም ሌላው ሰው በርኩሳን መና ፍስት ቁጥጥር ሥር እንዲውል የሚያደርጉ፣ ጠንቋይ ሳይጠይቁ ምንም ዓይነት ውሳኔ ግድረግ የማይችሉ፣ አጋንንት በመጥራት ከአጋንንት ጋር በግልጽ የሚነጋገሩም ነበሩ፤ አሁንም አሉ። ሰይጣን ሰውን ያለ ፈቃዱ በማስገደድ ሙሉ በሙሉ መግዛትና መቆጣጠር ስለማይችል፣ አጋንንት ጠሪ የሆነው ሰው በፈቃዱ ራሱን ለሰይጣን የሰጠ ነው። ራሱን ከሰጠ ርኩሳን መናፍስት ለዚያ ሰው የወደፊቱን ይገልጹለታል፣ ያም ሰው መካከለኛ በመሆን መልዕክቱን ከርኩሳን መናፍስት ተቀብሎ ለሌላው ሰው ያስተላልፋል።

## -ለ-
## በርኩሳን መናፍስት አማካኝነት መገለጥን ማግኘት ይቻላል?

ብዙ አማኞችን ግራ ያጋባና ጥያቄ በአዕምሮአቸው እንዲፈጠር ያደረገ ታሪክ ቢኖር፣ በ1ኛ ሳሙኤል 28:1-6 የተጠቀሰው ታሪክ ነው። በዚህ ታሪክ ውስጥ የእስራኤል ንጉሥ የነበረው ሳኦል ፍልስጥኤማውያን ሊወጉት እንደተነሱበት እናያለን። ቀደም ሲል መመሪያና ምክርን ከነብዩ ከሳሙኤል ያገኝ ነበር፤ አሁን ግን ሳሙኤል ስለሞተ ሌላ መመሪያ የሚሰጠው ሰው በማጣቱ ከፍተኛ ግራ መጋባት ደርሶበት ነበር። ንጉሥ ሳኦል እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት የሰጠው ቃል ምሪትን ሊሰጠው ይችል ነበር። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በቃሉ የሰጠውን ራዕይ (መመሪያ) ችላ በማለት ሌላ ምሪትን ስለ ፈለገ «ሙታን ጠሪ የሆነች አንዲት ሴት ፈልጉልኝ፤ እኔም ሄጄ ምክር እጠይቃታለሁ ሲል ባለሟሎቹን አዘዘ» (1ኛ ሳሙ. 28:7)። ሳኦል ይህ ንን ልምምድ እግዚአብሔር እንደማይቀበለው በደንብ ያውቅ ነበር። ምክንያቱም ሳኦል ቀደም ሲል «ጠንቋዮችንና ሙታን ጠሪዎችን ከእሥ ራኤል ምድር እንዲባረሩ አስገድዶአቸው ነበር» ይላል (1 ሳሙ. 28:3)።

ሳኦል ይህ ነገር እግዚአብሔርን የሚያሳዝነው መሆኑን ቢያውቅም ያቺን ሴት ከመጠየቅ ወደ ኋላ አላለም። እርሷም «ማንን አስነስቼ ላቅርብልህ?» ስትል ጠየቀችው፤ ሳኦልም «ነብዩ ሳሙኤልን» ብሎ መለሰላት። ንጉሥ ሳኦል የእግዚአብሔር ሰው የነበረውን ነብዩን ሳሙ ኤልን ለማነጋገር የፈለገው ስለ ወደፊቱ እግዚአብሔር ምን እንዳቀደ ለትና እንዳዘጋጀለት ለማወቅ ፈልጎ ነበር። «ያቺም ሴት ሳሙኤልን ባየች ጊዜ በኃይል ጮኸች» (1 ሳሙ. 28:12)። የጠበቀችው መጀመሪያ እርኩሱ መንፈስ ተገልጾላት በእርሱ በኩል ከሳሙኤል ጋር እንደምት

ገናኝ ነበር። ነገር ግን የተገለጸላት የተለማመደችው ዓይነት መንፈስ ባለመሆኑና ያየቸውም ከዚህ በፊት ያላየችውን የሳሙኤልን ፊት በመ ሆኑ ደነገጠች። ሳኦልም ሴቲቱን ሳሙኤልን «ምን ይመስላል?» ብሎ ጠየቃትI እርሷም በሰጠችው ገለጻ መሠረት «ሳሙኤል ሳይሆን አይቀ ርም» አለ። ሴትየዋ እንጂ ሳኦል ሳሙኤልን እንዳላየው አንዘንጋ። ሳሙኤል መቅረብ የቻለው እርኩሳን መናፍስት ስለጠሩት ሳይሆን፥ እግዚአብሔር በሳኦል ላይ ሊያደርስ ያሰበውን ፍርድ ማለትም የሳኦልን መንግሥት እንደሚደመስስ እንዲነግር በእግዚአብሔር ስለተላከ ብቻ ነው።

በአዲስ ኪዳንም ተመሳሳይ ሁኔታ እንደተፈጸመ እናነባለን (የሐዋ. 8:9)። ወንጌላዊው ፊልጶስ በሰማርያ ክርስቶስ አዳኝ እንደሆነና እንዲ ሁም ከኃጢአትና ከእርኩሳን መናፍስት ነጻ እንደሚያደርግ ይሰብክ ነበር። በዚሁ ከተማ ውስጥ ስምዖን የተባለ በእርኩሳን መናፍስት ኃይል መገለጥን አግኝቶ ስለ ወደፊቱ በመናገር በሕዝቡ ዘንድ ተደናቂነትን ያተረፈ ሰው ነበር። እውነትን ባለማወቃቸው ብዙዎች «ተታልለው የእግ ዚአብሔር ሰው ነው» ይሉ ነበር። በእግዚአብሔር ኃይልና እንዲሁም በእርኩሳን መናፍስት የሚፈጸሙትን ተዓምራት ሕዝቡ ለይቶ ማወቅ አይችልም ነበር። እንደምናውቀው የሰይጣን ዋና ጥረት እግዚአብሔርን በመምሰል ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን ክብርና አምልኮት ለእርሱ እንዲ ሰጠው ነው። እግዚአብሔር ልዩ ልዩ ተዓምራትን በመሥራት፥ በትን ቢት ስለ ወደፊቱ በመናገር አምላክነቱን በግልጽ ያሳይ ነበር። ሰይጣ ንም በበኩሉ በእርኩሳን መናፍስቶቹ አማካይነት ተዓምራትን በመሥ ራትና የወደፊቱን በመግለጽ የራሱን ታላቅነት ለማሳየት ሞክሯል። በሰማርያ ያሉት ሕዝቦች የሰይጣንን አምላክነት እንዲቀበሉ ለማድረግ ሰይጣን በሲሞን ይጠቀም ነበር።

ከዚህ እርኩስ መንፈስ ነፃ መሆን የሚቻለው በክርስቶስ ወንጌል አማካኝነት ብቻ ነው። «ፊልጶስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥትና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም የተናገረውን መልካም ዜና በሰሙ ጊዜ ወንዶ ችም ሴቶችም አምነው ተጠመቁ» ይላል (የሐዋ. 8፡12)። የሰማርያ ሰዎች ከሰይጣን ኃይል መላቀቅ የቻሉት የክርስቶስን ወንጌል ካመኑ በኋላ ነው። ነጻነታቸውን ያገኙት ሕዝቡ ብቻ ሳይሆኑ፥ ራሱ ሲሞንም ከእርኩሳን መናፍስት ነጻ ሆነ። ሐዋርያት በክርስቶስ ስም ተዓምራትን በማሳየት የሚሰብኩት ወንጌል እውነት መሆኑን ማስመስከር ቻሉ። ፊልጶስ እርኩሳን መናፍስትን ለሚያመልኩት የሰማርያ ሰዎች እግዚአ ብሔር እውነተኛ አምላክ፥ ሰይጣንም አወናባጅ መሆኑን ትክክለኛ መረጃ በማሳየት ማሳመን ቻለ።

ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ እስከ ዛርው ዘመን ድረስ ሰይጣን ተንኮ ሉና ዕቅዱ በመጠኑም ቢሆን ተሳክቶለታል። ሰዎች እውነቱን ማየት እንዳይችሉ በእርኩሳን መናፍስቱ አማካኝነት የብዙዎች አዕምሮ እንዲ

# - ሰ -
# አማኝ በርኩሳን መናፍስት መያዝ ይችላል?

ሳኦል በእስራኤል ሕዝብ ላይ የመጀመሪያው ንጉሥ እንዲሆን የተመረጠና የተቀባ፣ (1 ሳሙ. 10:1)፣ በመንፈስ ቅዱስም ተሞልቶ ትንቢት የተነበየ ሰው ነበር (1 ሳሙ. 10:9-13)። ይሁን እንጂ ሳኦል ኃጢአት እየሠራና ከእግዚአብሔር እየሸሸ ሲሄድ፣ በእርኩስ መንፈስ ተሞልቶ ይጨነቅ ነበር፤ «የእግዚአብሔር መንፈስ ከሳኦል ስለተለየ ከእግዚአብሔር የተላከ ክፉ መንፈስ ያሰቃየው ነበር» ይላል (1 ሳሙ. 16:14)። በእርኩስ መንፈስ መቼ እንደተሞላ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ስለማይናገር ማወቅ አስቸጋሪ ነው። በእግዚአብሔር ላይ በማመጹ፣ ለእርኩሳን መናፍስት መግቢያ ቀዳዳ ሰጥቷቸው ይሆናል (1 ሳሙ. 15:23)። በወቅቱ ለነበረበት ጭንቀትና ስቃይ ጊዜያዊ መፍትሄ የሚያገኘው ዳዊት በፊቱ ቀርቦ በገናውን በሚጫወትበት ጊዜ ነበር፤ «...ከእግዚአብሔር የተላከ ክፉ መንፈስ በሳኦል ላይ በሚመጣበት ጊዜ ሁሉ ዳዊት በገናውን አንስቶ ይደረድራል፤ ክፉውም መንፈስ ለቅቆት ስለሚሄድ ሳኦል እየ ተሻለው እንደገና ጤናማ ይሆናል» ይላል (1 ሳሙ. 16:23)።

እርኩሳን መናፍስት ክርስቲያኑን መያዝ የሚችሉት እስከምን ደረጃ ድረስ ነው? በውስጡ ገብተው ሙሉ በሙሉ ሊቆጣጠሩት ይችላሉ? በአጋንንት መያዝ ምን እንደሆነ ዶክተር መርልኸንገር፣ «እርኩሳን መናፍስት በዛሬው ዓለም» (Demons in the World Today) በሚለው መጽሐፋቸው ሲገልጹ፣ «በአጋንንት መያዝ ማለት ሰው አንድም ሆነ ብዙ መናፍስት ወደ ውስጡ ገብተው ሙሉ በሙሉ ሲቆጣጠሩትና ሰውየው የራሱ ፈቃድ ሳይኖረው ሲቀር ማለት ነው። ለጊዜውም ቢሆን ህሊናውን ጨርሶ በማጥፋት በሰውየው አማካኝነት የፈለጉትን መናገርና መሥራት ሲችሉ ነው። ያ ሰው ለእነርሱ መሣሪያ ወይም ፍጹም ታዛዥ አገልጋይ ይሆናል። እርኩሳን መናፍስት ወደ ሕይወቱ እንደ ፈለጋቸው፣ ያለአንዳች ከልካይ መግባትና መውጣት ይችላሉ። በእር ኩሳን መናፍስት የተያዘው ሰው ጤናማ የሆነ ሰው የሚኖረውን ዓይነት ሕይወት መኖር አይችልም..» አሉ። ንጉሥ ሳኦል ላይ ይታይ የነበረው ሁኔታም ከላይ የተገለጸውን ዓይነት ይመስል ነበር።

እርኩሳን መናፍስት ሰውን የሚዋጉት ሁልጊዜ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራቸው ውስጥ በማድረግ ብቻ ሳይሆን በተለያየ ደረጃና ዘዴ ነው። አንዳንድ ጊዜ እርኩሳን መናፍስት ሰዎች በኃጢአት እንዲወድቁ በማባበልና በማታለል የሚቀርቡ ሲሆን፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ የአዕምሮ ጭንቀትና የሥጋ ደዌን በማምጣት ጥቃት ያደርሳሉ። በዚህ ዓይነት አልፎ አልፎ በሰው አካል ላይ ከፍተኛ ጉዳትን ሲያደርሱ ይታያሉ። «ከአሥራ ስምንት ዓመት ጀምሮ እርኩስ መንፈስ ያጎበጣት አንዲት ሴት ነበረች፤ እርስዋ ወገብዋ በመጉብጡ ቀና ለማለት አትችልም

ጨልም አድርጓል። ብዙዎች «የወደፊቱን ገልጾ ማሳየት ከቻለ፥ እውነትም
እምላክ መሆን አለበት» በማለት አምነው ተቀብለዋል። የመጨረሻው
ዘመን እየተቃረበ ሲመጣ የሰይጣን እንቅስቃሴ ከምንጊዜውም በበለጠ
ሁኔታ ጎልቶ ይታያል። «...ምድርና ባህር ግን ወዮላችሁ! ምክንያ
ቱም ጥቂት ጊዜ እንደቀረው ስላወቀ ዲያብሎስ በታላቅ ቁጣ ወደ
እናንተ ወርዶአል» ይላል (ራዕይ 12፡12)።

ሰይጣን ከእግዚአብሔር ጋር ጦርነት የሚፈጥረው የሰውን አዕምሮ
(አንጎል) ለመያዝ ነው። አዕምሮውን መያዝ ከቻለ፥ የሰውን «ፈቃድ»
በቀላሉ በቁጥጥሩ ሥር ማድረግ እንደሚችል ያውቃል። ሰይጣን የሰ
ውን ፈቃድ ካገኘ በኋላ ሰው ሥልጣንና ኃይል ያለውን የእግዚአብ
ሔርን ቃል ችላ ብሎ ለሕይወቱ ሌላ መመሪያ እንዲፈልግ ያደርጋል።
ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞ. 4:1 «በኋለኛው ዘመን አንዳንድ
ሰዎች መናፍስትንና የአጋንንትን ትምህርት በመከተል ሃይማኖትን
ይክዳሉ» ያለው ለዚህ ነው። ሰዎች ከስህተት ሁሉ ነጻ የሆነውንና
እንዲሁም ሥልጣን ያለውን የእግዚአብሔርን ቃል ችላ ብለው ራሳቸ
ውን ለሰው ጥበብና ዕውቀት ማስገዛት ሲጀምሩ፥ ያኔ አዕምሮአቸውን
ሰይጣን እንዲቆጣጠረውና እንዲያሳስተው ለሰይጣን አጋልጠው መስጠ
ታቸው ይሆናል። በዘመናችን በጣም የሚያሳዝነው አንዳንድ ሰዎች
በእግዚአብሔር ቃል ላይ የመፍረድ ኃይል ወይንም ሥልጣን ያላቸው
ስለሚመስላቸው ደስ ያላቸውን ብቻ ተቀብለው ደስ ያላላቸውን ችላ
ሲሉት ይታያሉ። ይሄ የሚሆነው በተራ ምዕመናች መካከል ብቻ
ሳይሆን በመሪዎችና እንዲሁም ወንጌልን እንሰብካለን በሚሉትም መካ
ከል ነው። ሰባኪዎች ሕያው የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ችላ
ሲሉ፥ ያኔ እርኩሳን መናፍስት በጥበባቸው አዕምሮአቸውን ይቆጣጠርና
እነርሱ የሰጡአቸውን እውነት መሳይ ትምህርቶችን ማስተማር ይጀም
ራሉ። ትምህርታቸው የረቀቀ ስለሚመስል «ተምረናል፥ አውቀናል»
የሚሉትን በቀላሉ የመሳብ ኃይል አለው። የእግዚአብሔርን ሙሉ
ሥልጣንና ኃይል የሚጻረርም ቢሆን ችግሩ (ድክመቱ) ለምዕመኑ ግልጽ
ሆና አይታየውም።

ክርስቶስን እንደ ግል መድኃኒታቸው አድርገው ያልተቀበሉ ወይ
ንም አማኞች ያልሆኑ በጥንቆላ ተግባር ቢሳተፉ፥ ስለ ወደፊቱ ለማ
ወቅ ኮከብ ቆጠራ ቢለማመዱ፥ መናፍስትን ቢጠሩ፥ ራሳቸውን በፈቃ
ዳቸው ለሰይጣን እንደሰጡ ግልጽ ነው። የብዙዎቻችን ጥያቄ ግን
አማኞች ከላይ የዘረዘርናቸውን ልምምዶች መለማመድ ይችላሉ ወይ?
ቢሳተፉስ በአጋንንት መንፈስ ሊሞሉ ወይንም ሌላ ጉዳት ሊደርስባቸው
ይችላል ወይ? የሚል ነው።

ነበር። ኢየሱስ ባያት ጊዜ ጠራትና አንቺ ሴት ከበሽታሽ ተፈውሰሻል አላት። በእጁም ዳሰሳት፤ ወዲያውም ቀጥ ብላ ቆመች፤ እግዚአብሔርንም አመሰገነች» ይላል (ሉቃስ 13:11-13)። ይህች ሴት በእርኩስ መንፈስ መታሠሯን እንጠራጠርም። ምክንያቱም ኢየሱስ ራሱ ሲናገር «ይህች ሴት አሥራ ስምንት ዓመት በሰይጣን ታሥራ ስትሰቃይ ኖራለች...» አለ (ሉቃስ 13:16)። ይህቺ ሴት አማኝ መሆን አለመሆኗ ግን አይታወቅም። አንዳንዶች ኢየሱስ ይህችን ሴት «የአብርሃም ልጅ የሆነች» ስላላት ደህንነትን ያገኘች ነች የሚሉም አሉ። ያም ሆነ ይህ ሰይጣን የሰዎችን ሥጋ መዋጋት እንደሚችል የዚህች ሴት ታሪክ ይመሰክርልናል።

## - ፴ -
## እርኩሳን መናፍስት የአማኞችን አዕምሮ ማፈሊስም ይችላሉ?

ኢየሱስ በአሳዳጆቹ ለመጨረሻ ጊዜ ከመያዙ በፊት ጴጥሮስን «ስምኦን! ስምኦን! እነሆ ገበሬው ስንዴውን ከገለባ አበጥሮ እንደሚለይ እንዲሁም ሰይጣን እናንተን ሊያበጥራችሁ ወይንም ሊፈትናችሁ ተመኘ። ነገር ግን የአንተ እምነት እንዳይጠፋ እኔ እጸልያለሁ...» አለው (ሉቃስ 22:31-32)። በኢዮብ 1:6 ላይ እንዳየነው ሰይጣን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ሳያገኝ እምነታችንን መፈተን ስለማይችል፥ በአዲስ ኪዳን «ሰይጣን ሊያበጥርና ሊፈትን ተመኘ» የሚለው አባባል እንግዳ አይሆንብንም። «ማበጠር» ሲል ሰይጣን ወደ ሕይወታችን ለመግባት ደካማ ጎናችንን ወይንም ለመግባት የሚችልበትን ቀዳዳ መፈለጉን ያሳያል። የጴጥሮስን ደካማ ጎን ሲፈልግ ያገኘው «ትዕቢት» ወይንም «የራስ ትምክህትን» ነበር። «...ጌታ ሆይ! ለእስራትም ሆነ ለሞት ከአንተ ጋር አብሬ ለመሄድ ዝግጁ ነኝ! አለ» (ሉቃስ 22፥33)። ያንን ቀዳዳ በመጠቀም ጴጥሮስ ጌታውን እንዲክዳ አደረገው (ሉቃስ 22፥54-66)።

ኢየሱስ ስለሚደርስበት መከራና እንዲሁም የመስቀል ሞት ለደቀ መዛሙርቱ ሲናገር፥ ጴጥሮስ ኢየሱስን ወደ ጎን ወስዶ «እንዲህ አትበል» አለው። ኢየሱስ ግን ጴጥሮስን «አንተ ሰይጣን ከእኔ ወዲያ ሂድ፤ አንተ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን ነገር አታስብም» ሲል ገሰጸው» (የማር. 8:3)። «ገሰጸው» የሚለው ቃል ተራ ቃል አልነበረም። ኢየሱስ «ጴጥሮስን ገሰጸው» የሚለው ቃል እርኩሳን መንፈስ ሲያስወጣ «ገሰጸው» ከሚለው ቃል ጋር አንድ ዓይነት ነው። ሰውን «መገሰጽና» እርኩሱን መናፍስትን መገሰጽ አንድ ዓይነት አይደለም። ስለዚህ ኢየሱስ የገሰጸው ጴጥሮስን ሳይሆን ያንን ዓይነት

ንግግር እንዲናገር ያደረገውን እርኩስ መንፈስ ነበር። የብዙዎቻችን ጥያቄ ቀደም ሲል በልዩ መገለጥ «አንተ መሲህ ነህ» ሲል «ሥጋና ደም ሳይሆን የአባቴ መንፈስ ነው የገለጸልህ» የተባለው ጴጥሮስ እንዴት «አንተ ሰይጣን ከእኔ ወዲያ ሂድ» ሊለው ይችላል? የሚል ነው። ጴጥሮስ ያንን ዓይነት ንግግር ሲያደርግ ምንጩ ከየት እንደሆነ ኢየሱስ ስላወቀ ነው የገለጸው። ጴጥሮስ በአጭር ጊዜ ውስጥ በእርኩሳን መናፍስት ተከቦ ስለነበረ፥ ከሰይጣን የሚገኘውን ዓይነት ጥበብ ተጠቀመ። ሃዋርያው ያዕቆብ «እንዲህ ዓይነት ጥበብ የሚገኘው ከዓለም፥ ከሥጋና፥ ከሰይጣን ነው እንጂ ከእግዚአብሔር አይደለም» ይላል (ያዕቆብ 3:15)። በያዕቆብ አነጋገር መሠረት ሰው ጥበብ ከሚያገኝበት ከሦስት ምንጮች መካከል አንደኛው «ከሰይጣን» እንደሆነ እንረዳለን። ስለዚህ የጴጥሮስም አነጋገር ምንጩ ከሰይጣን የመጣ ጥበብ ስለነበረ፥ ኢየሱስ ያንን መንፈስ ገሰጸ። ይሁን እንጂ ጴጥሮስ በእርኩስ መንፈስ ተሞልቶ፥ ህሊናውን መናፍስቱ አጨልመውብት፥ ሙሉ በሙሉ በእነርሱ ቁጥጥር ሥር በመዋል ቅን አገልጋያቸውና ዕቃቸው ሆነ ማለት አይደለም። እርኩሳን መናፍስት የሰዎችን አስተሳሰብ ለጊዜውም ቢሆን ሊያጨልሙና ሊያሳስቱ እንደሚችሉ ግን አን ጠራጠርም።

ከጴጥሮስ የተለየ ታሪክ ያላቸው ሌሎች አማኞች አሉ። በሐዋርያት ሥራ ታሪካቸው የተጻፈው ሐናንያና ሰጲራ አማኞች እንደነበሩ እናውቃለን። ሐናንያ ሰይጣን ወደ ልቡ እንዲገባ እንደፈቀደ እናያለን። ለዚህ ነው ጴጥሮስ እግዚአብሔር በሰጠው የመገለጥ ስጦታ ተጠቅሞ «...ሐናንያ ሆይ!... ሰይጣን ወደ ልብህ ለምን ገባ?» ብሎ የጠየቀው (የሐዋ. 5:3)። እርኩሳን መናፍስት የሐናንያን አስተሳሰብ ያጨለሙብት፥ የጴጥሮስን አስተሳሰብ ባጨለሙበት መንገድ አይደለም። ሐናንያ ልቡን ከፍቶ ስላስገባቸው ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራቸው ውስጥ አስገብተውት ነበር። ይህ በመሆኑ ነው ወዲያው ወድቆ የሞተው። የሚስቱም የሰጲራ ታሪክ እንደ ባሏ ተመሳሳይ ነበር።

## — ሠ —
## እርኩሳን መናፍስት በአማኞች ላይ ምን ያህል ኃይል አላቸው?

እርኩሳን መናፍስት ሁልጊዜ በአማኞች ዙሪያ ይገኛሉ። ጴጥሮስ «...ጠላታችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን በመፈለግ እንደሚያገሳ አንበሳ በዙሪያችሁ ያደባል» በማለት ያስጠነቅቀናል። ጴጥሮስ ይህን የሚናገረው አማኞች ላልሆኑት ሳይሆን አማኝ ለሆኑት ነው። ዲያብሎስ ቀደም ሲል ተሳክቶለት የቀጣቸው አሉ፤ አንዳንዶችም ለመቀጥ የተቃረቡ ስላሉ ለእነርሱ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል። እዚህ ላይ ማወቅ የሚያስፈልገን

ነገር ቢኖር፥ በራቸውን ከፍተው የሚያስገቡት ሁሉ አማኞችም ሆኑ የማያምኑት በእርኩሳን መናፍስት መዋጥ የሚችሉ መሆናቸውን ነው።

እርኩሳን መናፍስት አማኞችን ለማጥቃት የሰውን ደካማ ተፈጥሮ ይጠቀማሉ። የተፈጥሮ በራችንን በመጠቀም ሁኔታዎችንና አንዳንድ ነገሮችን አመቻችተውና አሳምረው ማቅረብ ይችላሉ። ለምሳሌ፥ በዓይናችን መስኮት በመጠቀም የማያምረው እንደሚያምር አድርገው በማቅረብ «ፍትወት» በውስጣችን እንዲፈጠር ያደርጋሉ። የስሜት ሕዋሳቶቻችንን በመጠቀም የማይጣፍጠው እንዲጣፍጠን በማድረግ ሰካራሞችና የሀሺሽ ሱሰኞች ሊያደርጉን ይሞክራሉ። በዚህ ዓይነት እምስቱንም ሕዋሳቶቻችንን (ስሜቶቻችንን) በመጠቀም ያለማቋረጥ ሊያጠምዱን ሙከራ ያደርጋሉ። ይህንን ከመሰለው ከእርኩሳን መናፍስት ትግል ፍጹም ነፃ የሆነ አንድም አማኝ የለም።

እርኩሳን መናፍስት ያለመታከት ከታገሉ በኋላ አንዳንድ ቀዳዳ ወይንም ደካማ ጎናችንን ያገኛሉ። ለምሳሌ አንዳንዶቻችንን ቁጠኞች ሆነን ያገኙናል፤ ያንን ጥሩ አድርገው ስለሚጠቀሙበት በዚህ ድካም ብቻ የብዙዎችን ትዳር አፍርሰዋል። ለዚህ ነው ሃዋርያው ጳውሎስ «ምንም ያህል ብትቆጡ ኃጢአት አትሥሩ» (ኤፌ. 5:26) በማለት የሚመክረን። አንዳንዶቻችን «ይቅር» ማለት ችግር ይሆንብናል፤ ጳውሎስ ለሰይጣን ቀዳዳ ሊሆኑ የሚችሉትን ድካሞች ይዘረዝራል፤ «ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣኦትን ማምለክ፣ ሟርት፣ ጠላትነት፣ ንትርክ፣ ቅንአት፣ ቁጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ መለያየት፣ አድመኛነት፣ ምቀኝነት፣ ስካር፣ ዘፋኝነት...» ይላል (ገላትያ 5:19-21)። እነዚህ ሁሉ ደካማ በሆነው ሥጋችን ምክንያት በውስጣችን ሊኖሩ የሚችሉ ናቸው።

እርኩሳን መናፍስት ከላይ ያየናቸውን ድካሞች በመጠቀም አንድን አማኝ ካዳከሙት በኋላ፥ በራሱ ፈቃድና ምርጫ ተደጋጋሚ ኃጢአት እንዲሠራ ያባብሉታል። በዚህ ዓይነት የእግዚአብሔር መንፈስ ከሕይወቱ ሲወጣ፥ ያኔ ልቡ ለእርኩሳን መናፍስት ክፍት ስለሚሆን በቀላሉ በቁጥጥራቸው ሥር ያውሉታል። የእኛን ፈቃድ ሳይጠይቁ እርኩሳን መናፍስት በብርቱ የልባችንን በር ማንኳኳት ይችላሉ። አማኞች በደንብ ማወቅ የሚገባን ግን እኛ ከፍተን «ግቡ» ካላልናቸው ፈጽሞ መግባት እንደማይችሉ ነው። ስለዚህ «ድንገት እርኩሳን መናፍስት እኔ ሳላውቀው ይገቡ ይሆን?» ብለን መፍራት አይገባንም።

## - ረ -

## ኃጢአትን በመገሰጽ ብቻ ከሰው ሕይወት ውስጥ ማስወጣት ይቻላል!

በዚህ ሀሳብ ላይ ብዙ አማኞች ያልተረዱት አንድ ነገር አለ። ይኸውም «በፍትወት፣ በቁጣ፣ በስግብግብነት» ምክንያት የሚደርሱትን ፈተናዎች፥ ኢጋንንትን ገስጸን እንደምናስወጣው፥ ገስጸን ማስወጣት የማንችል መሆናችንን ነው። በምንዝር የተያዘችው ሴት ኢየሱስ ፊት በቀረበች ጊዜ ኢየሱስ «የምንዝር መንፈስ ውጣ!» ብሎ ገስጾ አላስወጣትም (ዮሐ. 8)፥ ያላት «ሁለተኛ ተመልሰሽ ኃጢአት አትሥሪ» ነው። በቆሮንቶስ ምዕመናን መካከል አባቱ የዝሙት ሥራ በመኖሩ ጳውሎስ «የዝሙትን መንፈስ» ገስጾ አላስወጣም፣ ጴጥሮስ ጌታውን ከካደ በኋላ «የክህደት መንፈስ ውጣ!» በማለት እንዲወጣለት አል ሆነም። በእያንዳንዱ ሁኔታ ግለሰቡ በእግዚአብሔር እርዳታ ራሱን ለመለወጥ እንዲሞክር፥ እንዲታገል ምክር ወይንም ትዕዛዝ ተሰጠው እንጂ፥ አቋራጭ መንገድ አልተሰጠውም። አንዳንድ ፈተናዎች በእር ኩሳን መናፍስት የቀረቡ ቢሆኑም አማኞች እርኩሳን መናፍስትን ለማስ ወጣት በመሞከር ፈንታ ሰይጣንን እንዲቃወሙ የእግዚአብሔር ቃል ይመክራቸዋል።

አማኝ የሚቀርብለትን ፈተና መታገልና መቃወም ሲገባው፥ «የፍ ትወት መንፈስ...፣ የቁጣ መንፈስ...፣ የስርቆት መንፈስ...፣ ወዘተ» እያለ እርኩሱን መንፈስ ለማስወጣት ሲሞክር የሚሳሳታቸው ሦስት ነገሮች አሉ፣ ይኸውም፥

1ኛ. «እርኩሳን መናፍስት ኃጢአት እንድሠራ አደረጉኝ» በማለት በሰይጣን ላይ ስለሚያሳብብ ራሱን ያለአግባብ ከኃላፊነት ነፃ ያደርጋል። «...እግዚአብሔር ታማኝ ነው፣ ምክንያቱም ከአ ቅማችሁ በላይ የሆነ ፈተና እንዲደርስባችሁ አይፈቅድም» (1ቆሮ. 10:13) የሚለው ቃል ለድክመታችን ተጠያቂ መሆና ችንን ወይንም ኃላፊነት እንዳለብን ያሳያል። «ሰይጣን አሳሳ ተኝ» ብቻ ማለቱ ከተጠያቂነት ነፃ አያደርገንም።

2ኛ. «አንዳንድ ሁኔታዎች ከእኔ ቁጥጥር ውጪ ናቸው» በማለት በሕይወቱ መሻሻል የሚገባቸውን ነገሮች እንዳያስተካከል እን ቅፋት ይሆንበታል።

3ኛ. ድካሙን አውቆ እነዚያን ለማሸነፍ በመታገል ፈንታ፥ «ም ክንያቱ ሰይጣን ነው» በማለት ጤናማ ያልሆነ የሕይወት አቋም እንዲይዝ ይሆናል። በዚህም ምክንያት በሁሉም አቅጣጫ የክርስቶስወብት እንዳይታይበት ይሆናል። አማኝ ያለማቋረጥ

እርኩሳን መናፍስትን የሚቋቋምበት መመሪያ ተሰጥቶታል። ይኸውም፥

(ሀ) በአዕምሮ መታደስ፥

(ለ) መከላከያው ምን እንደሆነ ተገንዝቦ ራሱን መከላከል ነው። እነዚህን መከላከያዎችና መሣሪያዎች ወደፊት በሰፊው እንመረምራለን።

# 6

# የሰው አዕምሮ ግዕዛዊ የጦር ግዳ ነው

«ሰው የሀሳቡ ውጤት ወይንም ምርት ነው» ይባላል። ስለሆነም፥ ሰውን ለመያዝ ወይንም በቁጥጥር ሥር ለማድረግ ከተፈለገ በእግር ብረት አስር ማስቀመጥ ሳይሆን፥ «አዕምሮውን» መያዝ ብቻ ነው። ሰይጣንም ይህንን ስለሚያውቅ የሰውን አዕምሮ ለመያዝ ከፍተኛ ተጋድሎ ያደርጋል። የኮሚኒስት ፍልስፍናና እንዲሁም ልዩ ልዩ እምነት መሳይ ሃይማኖቶች በትምህርታቸው የሰውን አዕምሮ በተቻላቸው መጠን ለመያዝ ከፍተኛ ጥረት የሚያደርጉት ለዚህ ነው። አንደኛው መንገዳቸው በሥጋ ጽሁፋቸው የሰውን አዕምሮ ማግበብ ነው። ጳውሎስም የሰይጣንን ተንኮልና ፍላጎት በመገንዘብ አማኞች ሀሳባቸውን (አዕምሮአቸውን) መጠበቅ እንዳለባቸው ያሳስባል፤ «እባብ ሔዋንን በተንኮል እንዳታለላት ምናልባት የእናንተም «አሳብ» ተበላሽቶ ለክርስቶስ ያላችሁን ቅንነትና ንጽህና ትተዋላችሁ ብዬ እፈራለሁ» ይላል (2 ቆሮ. 11:3)።

እርኩሳን መናፍስት ብልሹ የሆነውን ሀሳባቸውን በአዕምሮአችን ውስጥ በመሙላት ፈቃዳችን ለእነርሱ ፈቃድና ፍላጎት እንዲታዘዝ ይጥራሉ። ይህንን ዘዴያቸውን በመጀመሪያዋ ሴት፥ በሔዋን ላይ ሞከረውት ሲሠራ ስላዩት፥ ሁልጊዜ ጦርነታቸውን በሰው «አዕምሮ» ውስጥ በማካሄድ በዙ ጊዜ የእግዚአብሔርን ሕዝብ አዕምሮ በቀላሉ መጠምዘዝ ችለዋል። አንዳንድ ክርስቲያኖች «ክፉ ሀሳብ አይለቀኝም፤ ለመጸለይ ተንበርክኬ የማስበው ከፉ ወይንም ሌላ ነገር ሆኖ አገኘዋለሁ፤ ለምን ይሄ ይሆናል?» ብለው ሲጠይቁ ይሰማሉ። ሰይጣን አዕምሮአችንን ለመያዝ ምን ያህል ከፍተኛ ጦርነት እንደሚያካሂድ ያሳየናል።

ሰው በአዕምሮው ውስጥ የሚያልፈውን ሀሳብ ሁሉ መመዘንና መመርመር ካልቻለ፣ በቀላሉ ሰይጣን በራሱ ሀሳብና ፍልስፍና ሊሞላው ይችላል። ብዙ ጊዜ ሰይጣን የሰውን አዕምሮ በራሱ ሀሳብ የሚሞላው በረቀቀ ዘዴ በመሆኑ፣ ሀሳቡ ከሰይጣን የመጣ ሳይሆን ከራሱ የመነጨ ይመስለዋል። በአስተሳሰባቸው ግዴለሾች የሆኑ ሰዎች፣ ብዙ ጊዜ ለጥቃት የተጋለጡ ናቸው። ሰይጣን ትንሽ መግቢያ ቀዳዳ በአዕምሮአቸው ውስጥ ካገኘ፣ በቀላሉ በቁጥጥሩ ሥር ሊያደርጋቸው ይችላል። ጳውሎስ «ምንም እንኳ በዓለም ብንኖር፣ የምንዋጋው እንደ ዓለም ሰዎች አይደለም። የጦር መሣሪያዎቻችንም ምሽግ ለማፍረስ የሚያስችል መለኮታዊ ኃይል ያላቸው ናቸው እንጂ እንደ ዓለም የጦር መሣሪያዎች አይደሉም። በእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ በትዕቢት የሚነሣውን ክርክርና ከንቱ አሳብ እናፈርሳለን፤ አዕምሮን ሁሉ እየማረክንም ለክርስቶስ እንዲታዘዝ እናደርጋለን» ይላል (2 ቆር. 10:3-5)። የክርስቶስ መንፈስ ዋና ዓላማ የሰው አዕምሮ ሰማያዊውን፣ ወይንም የክርስቶስ የሆነውን ነገር እንዲያስብ ማድረግ ነው። ጳውሎስም ይህን ስለተረዳ ነው «ዘወትር በላይ በሰማይ ስላሉት ነገሮች አስቡ እንጂ በምድር ላይ ስላሉት ነገሮች አታስቡ» (ቆላስይስ 3፡2) በማለት አማኞችን የሚመክረው።

መንፈሳዊ ጦርነት ተጨባጭ የሆነ እውነት ነው። ጦርነቱ የሚካሄድበትም የጦር ሜዳ የሰው አዕምሮ ነው። ለዚህ ነው ሃዋርያው ጳውሎስ አማኝ በአዕምሮው ብርቱና ዝግጁ እንዲሆን የሚመክረው። ሰይጣን ድል ማግኘቱ የሚታወቀው የሰውን አዕምሮ በቁጥጥሩ ሥር በማዋል እንደሆነ ከታወቀ፣ አማኞች አዕምሮአቸውን ሁልጊዜ መጠበቅ ይገባቸዋል። የሰው አዕምሮ የሰይጣን እንቅስቃሴ የሚታይበት መድረክ ነው። ሰይጣን ሰውን ምን ያህል እንደያዘ የሚታወቀው፣ በሰው አዕምሮ ውስጥ ምን ያህል ሥፍራ እንዳገኘ በመተመን ነው። ሰይጣን የሰውን ውጪአዊ ሥጋ ወይንም አካል የሚመታና የሚያሰቃይ ቢሆንም፣ በሰው አዕምሮ ላይ ከሚያደርሰው ጥቃት ጋር ሲወዳደር ግን እጅግ በጣም አነስተኛ ነው። ሰይጣን የሰውን አዕምሮ መያዝ ከቻለ፣ የተቀረውን ሥጋውን መያዝ ይህን ያህል ከባድ እንደማይሆንበት በደንብ ያውቃል።

## ሀ ሰይጣን የሰውን አዕምሮ ለመያዝ የተለያየ ብልሀት አለው።

ሰይጣን በአንድ ጊዜ በሁሉ ሥፍራ መገኘት ስለማይችል፣ በእርኩሳን መናፍስቱ አማካኝነት እያንዳንዱን ሰው ይዋጋል። የሚዋጋውም በአጠቃላይ ሳይሆን በነፍስ ወከፍ ግለሰቡን ነው። የሰይጣን ጦር ሜዳ የሰው አዕምሮ እንደሆነ ቀደም ሲል አይተናል። የሰውን አዕምሮ ለመያዝ የተለያየ ዘዴና ብልሀት አለው። ይኸውም፣

1. የእግዚአብሔርን ቃል ከአዕምሮው ይሠርቃል። ሰው በአዕምሮው ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል በቅሉ ፍሬ እንዳያፈራ ጠላት ከአዕ ምሮው ውስጥ ቃሉን ሊወስድ እንደሚችል የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል፤ «...ሰይጣን መጥቶ በልቡ የተዘራውን ቃል ይወስድበ ታል...» ይላል (የማቴ. 13:19)። ሰይጣን ይህን ለማድረግ ከተሳካለት፣ አማኝ ከጠላቱ ጋር በሚያደርገው ጦርነት፣ ጠላቱን የሚወጋበት ዋነኛውን መሣሪያ አስጣለው ማለት ነው።

2. ሰይጣንን አደገኛ የሚያደርገው የእግዚአብሔርን ቃል ከሰው አዕምሮ መስረቁ ብቻ ሳይሆን፣ በራሱ ሀሳብ መሙላቱም ጭምር ነው። ሰው አዕምሮው የዘመኑን ውጥንቅጥና እንዲሁም ፍሬ የሌለውን ሀሳብ ብቻ የሚያጠራቅም ከሆነ፣ መንፈስ ቅዱስ በዚያ ሰው ሕይወት መሥራት አይሆንለትም። ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ በበኩሉ ሥራ ውን የሚያከናውነው በሰው አዕምሮ ውስጥ በመሆኑ ነው። በማይረባ ሀሳብ ከተሞላ፣ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በሰውየው ሕይወት እንዳይ ታይ መንገዱን ይዘጋል። ሰይጣን የማያምኑትን (ያልዳኑትን) አዕምሮ በማሳወር፣ ሕያው እግዚአብሔርን እንዳያዩ በማድረግ የራሳቸውን አምላክ እንዲፈጥሩ ያደርጋል። አማኞችን ደግሞ አዕምሮአቸውን በጊዜያዊና በቁሳቁሳዊ ነገር በመሙላት ለክርስቶስ ሥፍራና ጊዜ እንዳይኖራቸው ያደርጋል። ሀሳባቸው በዓለም ነገር ተወስዶ ለክርስ ቶስ ወንጌል ትኩረት እንዳይሰጡ፣ የሚጠብቃቸውንም ዘለዓለማዊ ሽልማት ችላ እንዲሉና እንዲያጡ ያደርጋል።

3. ሰይጣን በቁጥጥሩ ሥር ስላሉት ይህን ያህል ግድ የለውም። ከሥሩ አምልጠው በመውጣት በክርስቶስ አዲስ ፍጡር በሆኑት ላይ ግን፣ የጦርነት አዋጅ ያውጅባቸዋል። ከሰይጣን ተላቀው ሲወጡ፣ «አመለጥኩ» ብለው ደስ ሲላቸው፣ ወዲያው ሌላ ትግል ሲያጋ ጥማቸው ይደነግጣሉ። ወደ ክርስቶስ መምጣት ማለት የክርስቶስ የጦር ሠራዊት አባል በመሆን ለጦርነት መዘጋጀት እንደሆነ የሚ ረዱት ቆየት ብለው ነው። አንድ ሰው ወደ ክርስቶስ ገና እንደ መጣ፣ ጦርነቱ ሲፋፋምበት ይደነግጣል። ይሁን እንጂ የጦርነቱ ዋና ምክንያት ሰይጣን አዕምሮውን ለመያዝ የሚያደርገው ጥረት እንደሆነ እንዲያውቅና እንዲሁም አዕምሮውን እንዲጠብቅ ማስተማር ይገባል። ጳውሎስ አማኞችን «አዕምሮአችሁ በመንፈስ ይታደስ» (ኤፌ. 4:23) በማለት ሲመክር፣ ሰይጣን ግን ያ እንዳይሆን አጥብቆ ይዋጋል።

4. የሰው አዕምሮ በአንድ ሥፍራ ተተክሉ በነፋስ እንደሚሠራ ወፍጮ ነው። የነፋስ ወፍጮ፣ የሚፈጨው ነገር ባይኖርም በነፋሱ ኃይል ሁልጊዜ እንደሚዞር ሁሉ፣ የሰው አዕምሮም ያለዕረፍት ያስባል። ስለ ኢየሱስ የሚያስብ (የሚፈጭ) ከሆነ፣ የክርስቶስ መልክና

ውብት ያለው ሆኖ ይወጣል። የእግዚአብሔርን ቃል ያለማቋረጥ ካሰበና ካሰላሰለ፥ ሁልጊዜ አዲስ ሰው፥ የተለወጠ ሰው ይሆናል። የአማኝ አዕምሮ በክርስቶስ ሀሳብ ከተሞላ፥ በየጊዜው የተለወጠና የታደሰ ሕይወት ይኖረዋል። አዕምሮው ቀንና ማታ በምድራዊ ሀሳብ ከተሞላ ግን፥ ፍጹም የሆነ ዓለማዊ ሰው እንደሚወጣው ስለሚያውቅ፥ አዕምሮ መንፈሳዊ የሆነውን ነገር እንዳያስብ ሰይጣን ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል።

❺ ያለማቋረጥ በተግባር ላይ የሆነውን አዕምሮውን መጠበቅ የማይችል አማኝ፥ በጠላቱ ለመመታት ራሱን አመቻችቶ የሰጠ ሰው ነው። ሰይጣን ለሰው አዕምሮ ዕረፍት ሳይሰጥ ልዩ ልዩ ሀሳብን በማቀበል ይተጋል። በሰው ላይም ያለውን ሥልጣን መለማመድ የሚሞክረው በዚህ ነው። «ፈቃዱን» በፍጹም መንካት ወይንም «አስገድዶ ኃጢአት ማሠራት» እንደማይችል ስለሚያውቅ፥ ፈቃዱን ሊያስለውጥ የሚችለውን ክፍል ለማለስለስ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። የሰው የግል «ፈቃድ» የሚወሰነው ባለው የአስተሳሰብ ዝንባሌ ነው። ለዚህ ነው «ሰው የሃሳቡ ውጤት ነው» (Man is the product of his thingking) የሚባለው። ሰይጣን በአማኝ «የሀሳብ ወፍጮ» (አዕምሮ) ላይ ሥልጣን እስከገኘ ድረስ፥ በዚያ ሰው ሕይወት ውስጥ እንዳየለ ይቆያል።

## ለ የሰይጣን ግዛት የሆነ የሰው አዕምሮ፥

«የሰይጣን ግዛት መሆን» ስንል አማኙ ሁልጊዜ በኃጢአት ውስጥ ይኖራል ማለት አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ይሄዳል፤ ግብረገብ የጎደለው ሕይወት አይታይበትም፤ ጥሩ የቤተሰብ አቋም ያለው፥ ሕብረተሰቡ የተቀበለውና ያከበረው ሰው ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በእርሱ ሕይወት ውስጥ ምን ማድረግ እንዳሰበና ምን ማድረግ እንደሚፈልግ ለማወቅ ፍላጎት የለውም። ሕይወቱን ለክርስቶስ መንግሥት አገልግሎት ያልሰጠ፥ እንዲሁም ፍጹም ባዶና የባከነ ሕይወት ያለው ነው። ክርስቲያንም ቢሆን አዕምሮውን በሰይጣን ቁጥጥር ሥር እንዲውል ከፈቀደ፥ «የተለወጠ ሕይወት» አይታይበትም። በየቀኑ የሚያስበው «ክርስቶስን እንዴት ላከብረው?» የሚል ሳይሆን ለራሱ ተመችቶትና ተዝናንቶ መኖር የሚችልበትን መንገድ ብቻ ነው።

ሰይጣን በራሱ ሀሳብ የአማኙን አዕምሮ ያለማቋረጥ ሲሞላ፥ መንፈሳዊ ሕይወቱ እንዳያድግና እንዲቀረጭጭ ያደርገዋል። ሰው «ደህንነትን» ሲያገኝ ወዲያው ድልን በሰይጣን ላይ ያገኛል ማለት አይደለም። እግዚአብሔር አማኝ እንዲያደርጋቸው ከሚፈልጋቸው ነገሮች መካከል አንደኛው ከሰይጣን ጋር ውጊያ እንዲጀምር ነው። ያለ ትግል እንዲሁ የሚገኝ ድል እንደሌለ ማወቅ ይገባዋል። በማመኑ ብቻ ከሰይጣን ጦር (ውጊያ) ነፃ ይሆናል ማለት አይደለም፤ እንዲያውም

ጦርነቱ የሚያይለው፥ ለጠላት ጦር ፍጹም የተጋለጠ የሚሆነው ያኔ ነው። ይኼ ባይሆን ኖሮ ጌታችን «ነቅታችሁ ጠብቁ!» በማለት ባላስጠነቀቀንም ነበር። ወይንም ሃዋርያው ጳውሎስ ሰይጣንን የምንዋጋበትን «ዕቃ ጦር» መዘርዘር ባላስፈለገውም ነበር። አማኝ የሚኖረው ሁልጊዜ በከባድ ጦርነት ውስጥ ነው። ሁልጊዜ ጦርነት እንዳለበት እንጂ፥ በጦርነቱ አሸናፊ መሆን እንደሚችል ግን ይዘነጋል። ሰይጣንን አለመቃወምም፥ የበለጠ ሰይጣንን ይጋብዛል።

## ሰይጣን የሰውን ፈቃድ መጣስ ይችላልን?

ሰይጣን ወደ ሰው አዕምሮ መቅረብ ከቻለ፥ ለመሆኑ ሰውን በቁጥጥሩ ሥር ማድረግ የሚችለው በምን ዓይነት መንገድና ዘዴ ነው? የሰውን አስተሳሰብ ጠምዝዞ ከእርሱ ሀሳብ ጋር አንድ እንዲሆን ማድረግ ይችላል? በሚያስበው ሀሳብ ላይ ሰው የራሱን ምርጫ ወይንም ውሳኔ እንዳያደርግ ጣልቃ መግባት ይችላል? ሰው ሳይፈቅድ ሰይጣን የራሱን ሀሳብ ወደ ውስጡ መክተት ይችላል? መልሱ ፈጽሞ አይችልም የሚል ነው። ለሰው ጠቅላላ የሕይወቱ አቋም ወሳኙ፥ የራሱ ፈቃድ ወይንም ምርጫ ነው። እግዚአብሔር ራሱ የሰውን «ፈቃድ» የማይጥስ ከሆነ፥ ሰይጣን የሰውን ፈቃድ ጥሶ ይገባል ብለን መጠራጠር አይገባንም። ይህን ስለሚያውቅ ሰይጣንም የሰውን አዕምሮ ጥሶ ለመግባት ሙከራ አያደርግም። ያለ ሰው ፈቃድ ሰይጣን ወደ ሰው ሕይወት መግባት ቢችል ኖሮ፥ ሰው ከኃላፊነት ወይንም ከተጠያቂነት ነጻ በሆነ ነበር። ሰይጣን ማድረግ የሚችለው ፈቃዱን እንዲያደርግ ማባበል ብቻ ነው። እንደ ፈቃዱ ማድረግ ሲጀምር ደግሞ መለስ ብሎ ፈታኝ ብቻ መሆኑ ይቀርና ከሳሽም መሆን ይጀምራል። እግዚአብሔርም ሆነ ሰይጣን፥ ሰው የመምረጥ ነጻነት እንዲኖረው ይፈልጋሉ። ይሁን እንጂ ሰይጣን እንዲፈርድበት የእርሱን ክፉ መንገድ እንዲመርጥ የሚፈልግ ሲሆን፥ እግዚአብሔር ግን የጽድቅን መንገድ መርጦ ሽልማቱን እንዲቀበል ይፈልጋል።

እግዚአብሔርም ሆነ ሰይጣን ለሰው ሀሳብ አቅራቢዎች ብቻ ናቸው። ከሰው ፍላጎት ውጪ የራሳቸውን ዓላማ ለማስፈጸም ሰውን አያስገድዱትም። ሰይጣን ኃይሉ ያለው «ሀሳብ በማቅረብ» ችሎታው ላይ ነው። በዚህ አቅጣጫ ከፍተኛ ችሎታና ጥበቡ እንዳለው የሚታወቀው፥ የሰውን ድካምና የመሸነፍ ዝንባሌን እየተከተለ የሚያጓጓና ስሜቱን የሚቀሰቅስ ሀሳብ ማቅረብ በመቻሉ ነው። ሰይጣን ለሰው ሀሳብ የሚያቀርበው በደከመበት አቅጣጫና እንዲሁም ድካም ተሰምቶት ዕርዳታ በሚፈልግበት ወቅት ስለሆነ፥ ብዙ ጊዜ በቀላሉ ሰውን ማታለል ችሏል።

## መ ሰይጣን የሰውን አዕምሮ ለመበረዝ ምን ያህል ይችላል?

ሰይጣን ውደ ሰው አዕምሮ በመቅረብ «አስተሳሰቡን» ለመበረዝ ከፍተኛ ኃይል አለው። ወደ እያንዳንዱ ሰው አዕምሮ ለመቅረብ ፈጣን የሆነ ችሎታ አለው፣ የእያንዳንዱን ሰው ብርታትና ድካም ያውቃል፣ በተለይ የመከላከል አቅሙ የተዳከመበትንና እንዲሁም ለጥቃት የተጋለጠውን ክፍሉን ለይቶ ያውቃል፣ ሀሳቡን፣ ግምቱን፣ ውስጣዊ ዓላማውንና እንዲሁም ምን ለማድረግ እንዳሰበና እንዳቀደ፣ ምኞቱንና ፍላጎቱን የማየት ችሎታ አለው፣ በግዴለሽነትም ሆነ በግል ፈቃዱ ለሰይጣን ዕድል ከሰጠው በጎ የሆነው አሳቡን ከውስጡ አስወጥቶ ክፉ የሆነውን የራሱን አስተሳሰብ መትከል ይችላል።

ሰው ራሱን ከሚያውቀው የበለጠ ሰይጣን ያውቀዋል። ብዙ ጊዜ ስህተቱን ረስቶ ወደ ፊት መቀጠል ይፈልጋል፣ ሰይጣን ግን የሰውን ስህተት አይረሳም። እያንዳንዷ የሰው ድካምና ውድቀት በሰይጣን መዝገብ ውስጥ ተመዝግባ ትቀመጣለች። አስደናቂ የሆነው የአዕምሮ ችሎታውና እንዲሁም በረጅም ዘመን ያገኘው ልምምድ፣ ሰው በደካማው ሥጋዊ ተፈጥሮው ምክንያት የሚሰተውን ሁሉ እንዲያስታውስ አስችሎታል።

## ሠ ሰይጣን ለሰው ሀሳብ የሚያቀርብበት ብልሀቱ ምንድነው?

እግዚአብሔር ለሰው የሚሰጠው ወይንም የሚያቀርበው ሀሳብ ከሰይጣን የሚለይበት፣ የሀሳቡ ፍሬ ወይንም ውጤት በቅርብ የማይታይ በመሆኑ ነው። ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር ሀሳብ ጊዜያዊ የሆኑ የሥጋ ምቾቶችን የማይሰጡና እንዲሁም ስደትን የሚያስከትሉ ናቸው። በዚህ ዓይነት ሰዎች የእግዚአብሔርን ድምፅ ከመስማት ይልቅ የሰይጣንን ድምጽ ሰምተው መታዘዝ ይቀላቸዋል። ብዙ ሰው ወቅታዊ ወይንም ጊዜያዊ የሆነውን ደስታ ይፈልጋል እንጂ፣ «እርሱነቱን» ገድሎ፣ የሥጋ ፍላጎቱንና አዕምሮውን መስዋዕት አድርጎ በዓይን የማይታየውን የወደ ፊቱን፣ ገና ያላየውንና ያልጨበጠውን አይመርጥም።

1. ሰይጣን ሁልጊዜ ሀሳብ የሚያቀርበው ሰው በደከመበት አቅጣጫ ነው። በዚህ ብልሀቱ በብዙዎች ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ድልን እያገኘ ነው። በሰው ደካማ ጎን ተጠቅሞ ቀስ ብሎ ከገባ በኋላ፣ የራሱን ሀሳብ በሰው አዕምሮ ውስጥ መርጨት ይጀምራል። ተወዳዳሪ የሌለውን ጥበቡንና ተንኮሉን በመጠቀም፣ ሰው ደካማ በሆነበት አቅጣጫ ወጥመዱን በመዘርጋት የሰውን ሕይወት ማዳከም ከፍተኛ ተግባሩ ነው። ለሰዎች የሚያቀርበው ሀሳብ፣ ብዙ ጊዜ

ድካማቸውን ለማገዝ አስቦ የተነሳ ይመስላል። ቀባብቶና አሰማምሮ ስለሚያቀርበው፥ በሰዎች አዕምሮ ውስጥ፥ ትክክል መስሎ እንዲታያቸው ይሆናል። ሰይጣን ለመሆኑ ይህን ያህል ኃይል አለው እንዴ? ብለን በመደነቅ መጠየቃችን አይቀርም። ይህንን ዘዴውን ሰይጣን በኢየሱስም ላይ ለመጠቀም ሞክሯል። ኢየሱስ በራብውና እንዲሁም ሥጋው በደከመበት ወቅት እውነት መሳይ ሀሳብ እንዳቀረበለት እናውቃለን። ምኞታችን በምን ላይ እንዳተኮረና የሚያጓጓን ምን እንደሆነ በደንብ አድርጎ ያውቃል። አስመስሎ ስለሚቀርብ መጥፎው፥ በጣም ጥሩ ሆኖ እንዲታየን የማድረግ ችሎታ አለው። ከእርሱ ሀሳብ ጋር የምንስማማበትን ምክንያት መፈለግ ያውቅበታል።

2. ሰይጣን ሀሳብ ሲያቀርብልን ብዙ ጊዜ የስሜታችንን አቅጣጫ እየተመለከተ ነው። ድካማችንን ስለሚያውቅ፥ ለማግኘት የምንፈልገውን (የምንናፍቀውን) ነገር አመቻችቶ ያቀርብልናል። ሰይጣን እኛ ሰዎች እርሱ እንደሚያስበው እንድናስብ ይፈልጋል። ይህን ማለት በግልጽ እንደ እርሱ አጥፊዎች ይሆናሉ ማለት አይደለም። ሰይጣን ጥሩ የሆነውን ስሜታችንን እንኳን ቀልብሶ ለእርሱ ጥቅም እንዲውል ለማድረግ ከፍተኛ ችሎታ እንዳለው እንወቅ። ሰይጣን «ስሜታችንን» በማወቅና በመጠቀም ተንኮለኛ (ተናካሽ) ሊያደርገን ይችላል። ሰይጣን ብልህ ስለሆነ፥ «የተንኮል» ሀሳቡን ለእኛ ለአማኞች ፊት ለፊት ያቀርብልናል ማለት አይደለም፤ ይህን ቢያደርግ እንደማንቀበለው ያውቃል። ደካማው ተፈጥሮአችን፥ ትክክል ላልሆነ ነገር የመሸነፍ ዝንባሌ እንዳለን ሰይጣን ስለሚያውቅ፥ ያንን ተደግፎ በሕይወታችን ክፉ ነገር እንዲረጭ ያደርጋል።

3. እግዚአብሔር ይናገራል? ከተናገረስ በሥጋ ጆሮአችን ለመሆኑ ሰምተነው እናውቃለን? ፈቃዱ ምን እንደሆነ ሲገልጽ በጆሮው የሰማው ሰው አለ? አይመስለኝም። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር አይናገርም ማለት አይደለም። ሰይጣንም እንደዚሁ ነው፤ ከፍ ባለ ድምፅ ሲናገር በጆሮአችን አንሰማውም። እግዚአብሔርም ሆነ ሰይጣን እንደሰው ሥጋ የለበሱ ሳይሆኑ መንፈስ በመሆናቸው ሰው እንደሚናገረው አይናገሩም። መንፈስ ለሆነው ውስጣዊው እኛነታችን ከእግዚአብሔርና ወይንም ከሰይጣን ጋር ለመነጋገር ጆሮና አፍ አያስፈልገንም። ለአዕምሮአችን ሀሳብ ሲያቀርቡ ግን የመስማት ችሎታ አለን። ውስጣዊውን ድምፅ እንደምንሰማ መፅሐፍ ቅዱስ ሲገልጽ፥ «የእግዚአብሔር መንፈስ ከእኛ መንፈስ ጋር ሆኖ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ይመሰክራል» ይላል (ሮሜ 8:16)። መንፈስ ቅዱስም ሆነ እርኩሳን መናፍስት ወደ እኛ የሚቀርቡት ከአዕምሮአችን ጋር በሚያደርጉት ንግግር ነው።

የእግዚአብሔር መንፈስ ከመንፈሳችን ጋር እንደሚገናኘው ሁሉ+ እርኩሳን መናፍስትም ከመንፈሳችን ጋር መገናኘት ይች ላሉ። እግዚአብሔርን በሥጋዊ ዓይናችን ማየትና እንዲሁም በሥጋዊ ጆሮአችን መስማት እንደማንችለው ሁሉ+ እርኩሳን መናፍስትንም በሥጋዊ ዓይናችን ማየትና እንዲሁም በሥጋዊ ጆሮአችን መስማት አንችልም። ሰይጣን ምድራዊው ነገር አምሮ እንዲታየን በማድረግ ፍላጎታችንን መቀስቀስ ይችላል። ወደ እግዚአብሔር ልባችንን እንዳናቀና ሰይጣን ዓይናችንን በመማ ረክ በምድራዊ ነገር ሀሳባችንን መሙላት ይችላል። ያኔ ለክ ርስቶስ ሙሉ በሙሉ እንዳንኖር ውስጣችንን ባዶ ያደርጋልI ወይንም በመንገዳችን እንቅፋት ይፈጥራል። አንድ ሀሳብ ወደ አዕምሮአችን ብቅ ሲል ወዲያው ላንቀበለው እንችላለን። እዚ ሀም ላይ የመምረጥ መብታችን የተጠበቀ ነው። ከውስጣችን ሲፈልቅ ግን+ ሀሳቡ በሌላ ዘዴ ከውጪ የመጣ ነው ብለን ፈጽሞ አንጠራጠርም። ስለማንጠራጥር ሀሳቡ የራሳችን ወይንም ከውስጣችን የመጣ መስሎ ይሰማናል። ስለዚህ ሀሳቡን ተቀብ ለነው በውስጣችን ማስተናገድ እንጀምራለን። ረጅም ጊዜም በውስጣችን እንዲቆይ ዕድል እንሰጠዋለን። አንድ ሀሳብ ወደ አዕምሮአችን ብቅ ሲል አለመቀበል ከፍተኛ ጉልበትን ይጠይ ቃል። ይሄን ዓይነቱን የውሳኔ ኃይል ለማግኘት የሚቻለው ስለ ጠላታችን ስለ ሰይጣን በቂ እውቀት ሲኖረን ብቻ ነው።

ለምሳሌ የዘመድ ናፍቆትና ብቸኝነት ባንገላታን ጊዜ ሰይጣን ስለ እኛ የሚቆረቆርና የሚያዝንልን ይመስል ወደ እኛ በሀሳባችን አማካኝነት ጠጋ ይልና «ስልክ እንኳን ደውለህ ብታነ ጋግራቸው ናፍቆትህ ይቃለል ነበር» በማለት ከጠረጴዛው ላይ ያለውን ስልክ ያሳየናል። ሌላ ድምፅ ከውስጣችን «ስልኩ የአ ንተ አይደለምI የመሥሪያ ቤቱ ነውና ተው አታድርግ» ይለናል። በዚህ ጊዜ የሰይጣን መንፈስ «እውነት ነው» በማ ለት ቀትን አይሄድም። «የመሥሪያ ቤቱስ ቢሆን+ ለዚህ ትልቅ መሥሪያ ቤት አንተ አሥር ደቂቃ ኢትዮጵያ ደውለህ ብታነጋግር ምን ጉዳት ይደርስበታል? ከናፍቆትህ ብትላቀቅ ሥራህንም በተቀላጠፈ መንገድ ልትሠራና መሥሪያ ቤትህን የበለጠ ልትጠቅም ትችላለህ» ይለናል። ከሁለቱ አንደኛውን ድምፅ መርጠን የሚያዘንን እናደርጋለን። «አላደርግም! ይሄ ሌብነት ነው» ብለን «እምቢ» ብንል ሰይጣን በኃይል ትትቶ+ እኛችንን ይዞ በማስገደድ እንደማያስደውለን ግልጽ ነው። ድካ ማችንን በደንብ ስለሚያውቅ በዚያ በኩል ሊያባብለን ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል።

## 2 በሰይጣን ላለመሸነፍ አዕምሮአችንን እንጠብቅ

የሰውን አዕምሮ በሁለት መደብ ከፍለን እናየዋለን። አንደኛው «ንቁ ሀሊና» (conscious) ሲሆን፣ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ «ንቁ ያልሆነ ሀሊና» (unconscious) የሚባለው ነው። «ንቁ ሀሊና» የምን ለው በወቅቱ በአካባቢያችንና በአጠገባችን ያለውን ለይተን የምናውቅበት ነው። ለምሳሌ በአሁን ጊዜ ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ወረቀትና ብዕር መያዜን፣ እናንተም ተጽፎ ያለቀውን መጽሐፍ እያነበባችሁ መሆናች ሁን፣ ጊዜው ቀን ወይንም ማታ መሆኑን ለይታችሁ የምታውቁበትና የምትረዱበት «በንቁ ሀሊናችሁ» ነው። «ንቁ ያልሆነው» የአዕምሮ ክፍላችን ደግሞ በወቅቱ አስፈላጊ ያልሆኑ ሀሳቦች የሚጠራቀሙበት ክፍል እንደሆነ የታወቀው የሥነ አዕምሮ ሊቅ የነበረው ሲግመንድ ፍሮይድ ይገልጻል። ሰው «ንቁ ሀሊናውን» እስኪተወሰነ ድረስ መሸፈን ይችላል። ሰው ይሄ ችሎታ ባይኖረው፣ ከሰው ጋር መኖር ያስቸግረው ነበር። ከላይ ተስማሚ ባህሪ ያለው ይምሰል እንጂ፣ እውነተኛው ውስጣዊ ባህሪው፣ ከውጪ ከሚታየው የተለየ ነው። እጅግ በጣም ተግባቢ፣ ትሁት ከሚመስለው ሰው እንኳን፣ ያልታየ (ያልታወቀ) ክፉት ሊኖርበት ይች ላል። በዚህኛው የሰው አዕምሮ ክፍል ውስጥ ሰይጣን የሚፈልገውን ሁሉ ያገኛል።

በሰው ሕይወት ውስጥ ተቀብሮ የተቀመጠ፣ የተደበቀ ፍላጎትና ድካም መኖሩን ሰይጣን በደንብ ያውቃል። አዕምሮአችንን ከመንፈሳዊ ነገር ገለል ለማድረግ ምን ዓይነት ሀሳብ መወርወር የተሻለ እንደሆነ የማወቅ ችሎታ አለው። ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ የረከሰውን ሀሳቡን በአዕምሮአችን ውስጥ ይሞላል። ሰይጣን በሰው አዕምሮ የራሱን ሀሳብ መትከል ከጀመረ «የእግዚአብሔር ሰው» የሚባለው እንኳን ተግባሩ እንደ ሰይጣን ሊሆን ይችላል። ስለዚህ በሰይጣን ላለመሸነፍ አዕምሮ አችንን መጠበቅ ይገባናል።

1. በክርስትና ሕይወታችን አሸናፊ ለመሆን ከፈለግን፣ ሰይጣንን አቃ ለንና አሳንሰን ማየት የለብንም። አሠራሩንና ጥበቡን በደንብ ካልተ ረዳንና ካልተጠነቀቅን፣ ጠቃሚ በሚመስል ሀሳቡ ሕይወታችንን መያዝና መቆጣጠር ይችላል። በክርስቶስ ውስጥ የሚገኘው ድል በግላችን ሳንታገል የምናገኘው ድል አይደለም። ወይንም ክርስቶስ በውስጣችን በመኖሩ ብቻ ሰይጣን እኛ ባለንበት አካባቢ ድርሽ አይልም ማለት አይደለም። ሰይጣን ክርስቶስ ያሸነፈው ጠላት ቢሆንም፣ ጠላትነቱ ያላከተመ መሆኑን አንዘንጋ።

2. ሰይጣንን እርግጥ ነው ኢየሱስ አሸንፎታል። እኛ ካልተቃወምነ ውና ካልተዋጋነው በኢየሱስ ማሸነፍ ብቻ ድልን አናገኝም። ክርስቶስ የደህንነትን መንገድ አበጅቶልናል I በእምነት ካልተቀ በልነው ግን የደህንነት መንገድ በመዘርጋቱ ብቻ እንድናለን

ማለት አይደለም። እንዲሁም ኢየሱስ በሰይጣን ላይ ድል በማግ ኘቱ፡ ብቻ ያለ እኛ ተቃውሞ በሰይጣን ላይ ድልን እንቀዳጃለን ማለት አይደለም።

3. ወደ አማኞች አዕምሮ የሚመጣው ሀሳብ ሁሉ ከሰይጣን የመጣ ነው ማለት አይደለም። ይሁን እንጂ ሰይጣን አዕምሮአችንን ለመ ቆጣጠር ምን ያህል ከፍተኛ ኃይል እንዳለው መዘንጋት የለብንም። እውነተኛውም መንፈሳዊ ጦርነት የሚካሄደው በዚሁ በአዕምሮአ ችን ውስጥ ነው።

4. መንፈስ ቅዱስም ሆነ እርኩሳን መናፍስት ሁለቱም «ወቅታዊ ያልሆነውን ሀሳብ የምናጠራቅምበት የአዕምሮ (unconscious) ክፍላችንን መንካት ይችላሉ። ከዚህኛው ክፍል እያወጡ ወቅታዊ የሆነውን ሀሳብ ወደምናስብበት ክፍል ያስተላልፋሉ። ሀሳብ ከውስ ጣችን ስለሚመነጭ፥ ሁሉም ሀሳብ የራሳችን መስሎ ይሰማናል። ከውጪ ያለ ኃይል ያንን ሀሳብ እንዳመነጨ የሚያሳየን ምንም ነገር የለም። ስለዚህ አማኞች አስተሳሰባቸውን ሥርዓት ማስያዝና በጥን ቃቄ መመርመር ያስፈልጋቸዋል። በክርስቶስ ውስጥ እውነተኛ ድልን ማግኘት የምንችለው፥ ሀሳባችንን በጌታ አገዛዝ ሥር ያደ ረግን እንደሆነ ብቻ ነው።

5. ሰይጣን የእኛን ፈቃድ እንዲጥስ ኃይልና ሥልጣን አልተሰጠ ውም። ለእኛ ሀሳብ ከማቅረብና ከማባበል በቀር የማስገደድ ኃይል የለውም። ይሁን እንጂ «ሀሳብ በማቅረብ» ውስጥ ከፍ ተኛ ኃይል መኖሩን አንዘንጋ። ሰይጣን ደግሞ ሀሳብ በማቅረብ ጥበበኛ ነው። የእያንዳንዱን ሰው ድካም ስለሚያውቅ፥ እንደየሰው ፍላጎትና ድካም የተለያየ ሀሳብ ማቅረብ ያውቅበታል። የሚያቀ ርብልን ሀሳብ ድካማችንን እያየ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ በሰጠንም ሀሳብ እርካታ እንደምናገኝ ተስፋ ይገባልናል። ብዙዎቻችን የሚያ ቀርብልን አንዳንድ ሀሳብ በጣም እውነት ስለሚመስለን «እምቢ» ማለት ያስቸግረናል።

# 7

# ሰይጣንን የምናሸንፍበትን ዘዴ እንወቅ

ሰውም ሆነ እንስሳት፣ አራዊትም ጭምር የራሳቸው የሆነ የግል ጠላት አላቸው። ከአውሬዎች መኖሪያ ጫካ ሄደን አካባቢውን በዓይናችን ብንቃኝ፣ አንዳንድ አውሬዎች ለመጠጣት ጎንበስ ከማለታቸው በፊት የጠላቶቻቸውን መኖርና አለመኖር ለማወቅ አስቀድመው ዙሪያቸውን በዓይናቸው እንዴት እንደሚቃኙ እናያለን። አንዳንዶቹ ጠላታቸው ገና ከሩቁ ሲመጣ የሚያውቁበት የተፈጥሮ ችሎታ አላቸው። የጠላታቸውን መቃረብ እያወቁ በግዴለሽነት ለአንድ ደቂቃ ቢዘገዩ፣ ፈጣን በሆነው ጠላታቸው እንደሚበሉ ስለሚያውቁ፣ የጠላታቸውን መምጣት ገና ከሩቁ ሲያዩ ከዚያ አካባቢ በፍጥነት ይጠፋሉ።

ክርስቲያኖችም የግል ጠላት አላቸው፤ እርሱም ከብርሃን የበለጠ ፍጥነት ያለው ሰይጣን ነው። ሀሳባቸው ሊበር ከሚችለው ፍጥነት በላይ መብረር ይችላል። በዚህ ዓለም እስካሉበት ጊዜ ድረስ የማይለያቸው ጠላት በመሆኑ፣ ሁልጊዜ ነቅተው መጠበቅ አለባቸው። የሚኖሩበት ዓለም የጠላት መንደር ስለሆነ፣ ያለስጋት ተዝናንተው ምን ጊዜም ቢሆን መኖር አይችሉም። ስለዚህም በጠላታቸው ላለመጠቃት ሁልጊዜ ነቅተው መጠበቅ አለባቸው። ሌላው ቀርቶ ሲሠሩ፣ ሲዝናኑና ሲጫወቱም ቢሆን፣ ይህንን አደገኛ የሆነውን ጠላታቸውን ችላ ሊሉት አይገባም።

እጅግ በጣም ፈጣን ስለሆነ አስቀድመው ተዘጋጅተው ካልጠበቁት፥ በሕይወታቸው ከፍተኛ ጥፋት ሊያደርስ ይችላል።

ይሄ የአማኞች ሁሉ ጠላት ፈጣን ከመሆኑም ሌላ አደገኛና አጥ ፊም ነው። ወደ አማኞች ዘንድ ፈጽሞ እንዳይደርስ ሊገታው የሚችል ሥጋ የለበሰ ኃይል የለም። አንዳንድ እንስሳትና አውሬዎች ጠላቶቻ ቸውን የሚያሳስቱበት የተፈጥሮ ችሎታ ሲኖራቸው፥ አማኝ ግን ሰይጣንን የሚያታልልበት ምንም ዓይነት መንገድና ብልሃት የለውም። ከሰይጣን ሊጠብቀው የሚችል የተፈጥሮ መከላከያ ስለሌለው፥ ሁልጊዜ በሰይጣን ለመጠቃት ፍጹም የተጋለጠ ነው። ይሄ ጠላት የሰውን የተ ፈጥሮ ድካም በመጠቀም በሰው ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚያስችለው ኃይልና ጥበብ አለው። አልፎ አልፎ ወደ አዕምሮአችን የሚመጡትን አንዳንድ የሰይጣን ሀሳቦች የራሳችን መስሎን ሳናውቀው በእርሱ ሀሳብ ልንጠቀምና ልንመራ እንችላለንና ሁልጊዜ አዕምሮአችንን መጠበቅ ያስፈ ልገናል። ወደ አዕምሮአችን የሚመጡትን ሀሳቦች ምንጫቸውን ካላወ ቅን፥ የሰይጣንን ዓላማና ፈቃድ በመፈጸም ላይ ብንሆንም የእግዚአብ ሔርን ፈቃድ እየፈጸምን እንደሆነ መስሎ እንዲሰማን የማድረግ ጥበብና ችሎታ አለው።

## ሀ ☛ <u>ሰይጣን የሰውን የተፈጥሮ ዝንባሌ ያውቃል</u>

ከሰው የተፈጥሮ ዝንባሌዎች መካከል፥

- ➤ በዚህ ዓለም ሁሉም አንዱ ከሌላው መብለጥ ይፈልጋል።
- ➤ ሁሉም ለመብቱ ይከራከራል።
- ➤ ጥሩ ዕድል ሲያጋጥመው በዕድሉ ለመጠቀም ይፈልጋል።
- ➤ የራሱ የሆነውን አጥብቆ ይይዛል።

ሰይጣን ከላይ የጠቀስናቸውን የሰውን የተፈጥሮ ዝንባሌዎችን በደንብ ያውቃል። ማወቅ ብቻ ሳይሆን፥ እነርሱን በመጠቀም የራሱን ፍላጎት እንዲፈጽም አማኝን በልዩ ጥበቡ ያባብለዋል። ለምሳሌ፥ «ጥሩ ዕድል ሲያጋጥመው፥ በዕድሉ መጠቀም» እንደሚፈልግ የሚያውቀው ሰይጣን፥ ለአማኝ አንዳንድ ሁኔታዎችን አመቻችቶ ያቀርብለታል። ለም ሳሌ በገንዘብ እጥረት ምክንያት ያለ እንቅልፍ ሲጨነቅ ማደሩን ሲያውቅ፥ አንድ ሰው የገንዘብ ቦርሳው ከኪሱ ሲወድቅበት ያሳየውና «የገንዘብ እጦትህን እግዚአብሔር አይቶ ዕድሉን አመቻችቶ ሰጥቶሃልና ያውልህ በዕድሉ ተጠቀምበት» ይለዋል። ይሄ ሀሳብ በቀጥታ ከራሱ የወጣ ስለ ሚመስለው፥«ጥሩ ሀሳብ ነው» ብሎ ማመን ይጀምራል። ሌላው በውስጡ ያለው ድምጽ ወይንም ህሊናው ደግሞ በበኩሉ፥ «የለም! ያ ገንዘብ ያንተ አይደለምI ከሰውየው ኪስ ሲወድቅ አይተሃልና አንስተህ ስጠውI ባትሰጠው ግን ሌብነት ነው» ይለዋል። ሰይጣንም «እውነት ነውI ለባለ ቤቱ ልትመልስለት ይገባል» በማለት በቀላሉ ተሸንፎና በሀሳቡ ተስማ

ምቶ ያገኘ ሰው ቀሉ አይተወውም። ክርክሩን በመቀጠል «አንተ ኪሱ ገብተህ አልበረቅህም፤ የወደቀ አንሱ፤ የሞተ ቅበሩ እንደሚባለው፣ አንተ የወደቀ በማንሳትህ ኃጢአተኛ አያሰኝህም፤ እሱቴ በርሳውን ከፈትና እየው... አንድ ሺ ብር አለበት። ዕዳዬን ምን ልክፈል እያልክ ስትጨነቅ ያደርክበትን የትላንትናውን ሌሊት አታስታውሰም? ይሄ ገንዘብ ያለብህን ችግር በቀላሉ ያቃልልልህ ነበር! እግዚአብሔር በመንገድህ ያኖረልህን ዕድል ባትጠቀምበት፣ ጥፋቱ የራስህ ነው» በማለት ሊያ ግባባው ይሞክራል። በዚህ ዘዴው ካልተሳካለት፣ «ገንዘቡን ወስደህ ችግርህን አቃልልበት! ኃጢአት መስሎ ከተሰማህ ደግሞ ንስሀ ትገባ ለህ» በማለት የመጨረሻውን ሀሳብ ያቀርብለታል። የሰይጣንን ውሸት አምኖ ከተቀበለና ፍላጎቱን ካሟላ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙ ነትና አንድነት የሚያበላሽበትን ኃጢአት በውስጡ መዝራት ይጀምራል። በዚህ ዓይነት መንገድ የሰይጣንን ፈቃድ ቢፈጽምና ኃጢአት ቢሠራ፣ ሰይጣን አባበለው እንጂ እጁን ጠምዝዞ እንዲወስድ እንዳላደረገው ግልጽ ነው። ድርጊቱን የፈጸመው በራሱ ፍላጎትና ምርጫ ስለሆነ ከኃላፊነት ወይንም ከተጠያቂነት ነጻ መሆን አይችልም።

ከላይ እንደተመለከትነው ሰው የሚስተው ከራሱ ፍላጎት የተነሳ ነው። የራሱን ፍላጎት ከሌላው ፍላጎት ማስቀደም ተፈጥሮው ስለሆነ፣ ከላይ የጠቀስነው የገንዘቡ ባለቤት በዚያ ገንዘብ መጥፋት ምክንያት ምን ያህል ጉዳት ሊደርስበት እንደሚችል እንዳይረዳ የማስተዋል አዕም ሮውን ይዘጋበታል። ቢያውቅም «የእኔ ችግር ከእርሱ ችግር ይበልጣል፤ የእኔን ችግር ሳቃልል እንጂ ሌላው የራሱ ጉዳይ ነው፤ እኔ ችግሬን የማቃልልበት ዕድሉ አጋጥሞኛልና በዕድሉ መጠቀም አለብኝ» ይላል። ሰይጣን ሰው በራሱ ፍላጎት ላይ ብቻ እንዲያተኩር፣ ሌላው ሰው ስለሚ ደርስበት ጉዳት እንዳይጨነቅና እንዳያስብ አዕምሮውን መዝጋት በደንብ ያውቅበታል።

## ለ. ሰይጣን ሲዋጋ አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ አይሰጥም

የአሜሪካ መንግሥት ዲ.ኢ.ደብልዩ (D.E.W.) እየተባለ የሚጠራ፣ እስከ አርክቲክ የሚደርስ የተዘረጋ የራዳር መስመር አለው። ይሄ ከጠ ላት ወገን ሚሳይል ሲተኮስ ለአሜሪካ ጦር ኃይል፣ ከጠላት ወገን ሚሳይል መተኮሱን ምልክት የሚሰጥ (የሚያስጠነቅቅ) መሣሪያ ነው። ይህ መሣሪያ ሚሳይሉ ከታሰበበት ሥፍራ ለመድረስ አሥር ደቂቃ እንደ ቀረው ሲገልጽ፣ የአሜሪካ የጦር ኃይል በአሥር ደቂቃ ውስጥ የተተኮሰውን ሚሳይል የሚያከሽፍ ወይንም ከታሰበበት ሥፍራ እንዳይ ደርስ የሚያደርግ መሣሪያ (anti-missile) አለው።

ሰይጣን ሚሳይሉን በክርስቲያኖች ላይ ሲተኩስ ግን፣ የአሥር ደቂቃ ጊዜ አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ አይሰጥም። ሌላው ቀርቶ የአንድ ሰኮንድ ስንጣሪ ጊዜ ያህል እንኳን ማስጠንቀቂያ አይሰጥም። የራሱን

ሀሳብ በሰው ሕይወት (አዕምሮ) ውስጥ ሲተከል፣ ከመብረቅና ከብር ሃን በበለጠ ፍጥነት ነው። እንዲሁም ሰይጣን ምንም ዓይነት ማስጠንቀ ቂያ ስለማይሰጥ፣ አማኝ ሁልጊዜ በተጠንቀቅ ሆኖ መጠበቅ አለበት። በተጨማሪ አማኝ ከሰይጣን ወጥመድ ሥር እንዳይወድቅ ከፈለገ፣

- ስለ ጠላቱ ማንነት እግዚአብሔር የነገረውን አምኖ መቀበል፣
- ስለ ጠላቱ አሠራር ማወቅ፣
- የጠላቱን ድካምና ብርታት ለይቶ ማወቅ፣
- የሚቃወምበትን ተጨባጭ የሆነ ብልሀት መፈለግ፣
- ሀሳቡ ከሰይጣን የተወረወረ መሆኑን እንዳወቀ፣ መቃወም ያስፈልገዋል።

ብዙ ጊዜ የሰይጣንን ብልሃትና ዘዴ በቀላሉ ማወቅና መለየት ያስቸግራል። ምክንያቱም ሰይጣን አሠራሩ እንዳይታወቅበት ስለሚፈልግ ሁልጊዜ የሚሠራው በጨለማ ውስጥ ስለሆነ ነው። ስለ ሰይጣን የተጻፈ ውን አንብቦ ማወቅና ከእርሱ ጋር ፊት ለፊት ተገናኝቶ ማንነቱንና አሠራሩን ማወቅ በጣም ይለያያል። ሰይጣንን መቃወም ስንጀምር፣ ከእርሱ ጋር ያለን ግጭት ከባድ እየሆነ ይመጣል፤ የግጭቱም ኃይል በደንብ ይሰማናል። ጦርነቱ የቃላት ልውውጥ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ግብግብና ትግል ያለበት ይሆናል። ሩቅ ለሩቅ ሆነን የምናካሂደው ጦር ነት ሳይሆን፣ «የጨበጣ ውጊያ» ይሆናል። «የኢየሱስ ስም» ሲጠ ራበት ሰይጣን ሲሸሽ ስለምናይ፣ ከምንጊዜውም የበለጠ «የኢየሱስ ስም» ምን ዓይነት ትልቅ ኃይል እንዳለው እንረዳለን።

## ሐ. ሰይጣን ወደ ሰው አዕምሮ ዘልቆ መግባት ይችላል

ኢየሱስ ህያው እንደሆነው ሁሉ ሰይጣንም ህያው ነው። «ሀሳብ» ወይንም «ፍልስፍና» ብቻ ሳይሆን ህይወት ያለው ተጨባጭ ፍጥረት ነው። ወደ አዕምሮአችን ዘልቆ ለመግባትና ዓላማውን ለማስ ፈጸም ያለማቋረጥ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። ለእኛ ያሰበና የተቀረቀረ ይምሰል እንጂ፣ ሰይጣን ሁልጊዜ ዓላማው እኛን ለመጥቀም ሳይሆን እኛን ለመጉዳት ነው። ትንሽ ቀዳዳ ሲያገኝ ሰይጣን ሀሳቡን ወደ አዕ ምሮአችን ለመወርወር዗ዝግጁ መሆኑን እንወቅ። ይህንን ከሚመስል ጠላት አዕምሮአችንን የምንጠብቅበትና የምንከላከልበት ብልሃት ሊኖረን ይገባል። ሌባ ጨለማን ተገን አድርጎ ቤታችንን ሰብሮ በመግባት ጥቃት እንዳያደርስብን የምንከላከልበት ልዩ ልዩ ብልሃትና ዘዴ ሊኖረን ይገባል። ይኸውም፣

1 ሰይጣን ብርሃንን ስለሚጠላ በብርሃን እናጋልጠው። ይሄ የእኔ
ጽሁፍ የሰይጣንን ማንነትና ባህሪ ስለሚያሳይ በመጠኑም ቢሆን
መብራቱን እያበራሁበት ነው። ይህን ሳደርግ የበለጠ እንደሚጠላ
ኝና በተለያየ መንገድ እንዲዋጉኝ የርኩሳን መናፍስት ሠራዊቱን
እንደሚልክብኝ አውቃለሁ። ጨለማ ብዙ ጊዜ ሌባን ይጠራል (ይጋ
ብዛል) ይባላል። ሰይጣን ብርሃንን ስለሚጠላ የሚሠራው በጨለማ
ውስጥ ነው። ሰዎች እያዩት መሥራት የማይችላቸው ብዙ ነገሮች
አሉ። ዘዴውና ብልሃቱ በሰዎች ዘንድ ከታወቀበት፣ አሠራሩ ይከሽ
ፋብታል። ስለዚህ የሁላችንም ጥረት ፍላጎቱን በሰው ላይ እንዳይፈ
ጽም ማክሸፍ ነው። የሰይጣንን አደገኛነት የማያስብ፣ ወይንም
የማያውቅ ክርስቲያን፣ ሰይጣን የሚፈልገውን ሁሉ እንዲያደርግ
ነጻነት እየሰጠው መሆኑን ማወቅ አለበት። ስለ እርሱ ምንም ካልተና
ገርን፣ ለሰይጣን መደበቂያ የሆነለትን ጨለማ እያሰፋንለት ነው።
የእግዚአብሔር ሕዝብ ሰይጣንን አቃሎ ችላ ሲለው፣ ሳይታወቅበት
ብዙ ነገሮችን ማጥፋትና ማበላሸት ይችላል። አሠራሩን ሲመረ
ምር ግን፣ ጨለማው ውስጥ ያለውን ሰይጣንን በብርሃን ማጋለጡ
ይሆናል። ስለ ሰይጣን ያለንን ዕውቀት ለሌሎች ስናካፍል፣ ብር
ሃንን በሚጠላው ሰይጣን ላይ በኃይል ብርሃንን መፈንጠቃችን
ይሆናል። «ሰይጣንን ተቃወሙት ከእናንተ ይሸሻል» የሚለውን
ሀሳብ ስንሰብክና ስናስተምር፣ በሰይጣን ላይ አሁንም የሚጠላውን
ብርሃን አብርተን ማጋለጣችን ይሆናል። ቤተ ክርስቲያን ምዕመ
ናኗን ስታስተምርና ስታስጠነቅቅ፣ ሰይጣንን እያጋለጠችው ነው።
እንግዲህ ሰይጣንን ለመቋቋም የመጀመሪያ እርምጃችን፣ አሠራሩን
ተረድተን ለሚሰማን ሁሉ ማንነቱን መግለጽ ነው።

2 ሰይጣን የሚደበቅበትን ሥፍራ እንወቅ። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን
«ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ» አላቸው (የማቴ. 26:
41)። የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ከላይ ያየነውን ጥቅስ «እየጠ
በቃችሁ ጸልዩ...» (Watch and pray...) ይለዋል። ከጸሎት
በፊት «መጠበቅ» እንደሚቀድም እናያለን። አንዴ ከሰይጣን ወጥ
መድ ውስጥ ከገባን በኋላ «መጠበቁ» አይጠቅምም። «መጠበቅ»
ሰይጣንን ከምንከላከልበት መንገድ አንደኛው ነው። ከጠላት የተ
ወረወረው ሚሳይል፣ ኒው ዮርክ ወይንም ዋሽንግተን ዲ.ሲ.
ከደረሰ በኋላ የሚሳይልን መቃረብ የሚያመለክተው መሣሪያ
(DEW) ምልክት ቢሰጥ፣ ምንም ጥቅም የለውም። ሰይጣንም
የራሱን ሀሳብ በአዕምሮአችን ከተከለ በኋላ መጠበቁ ምንም
አይጠቅምም።

ዲያብሎስን «መጠበቅ» ማለት ዓይኖቻችንን ከፍተን ወደ
ሰማይ መመልከት ማለት አይደለም። ቀደም ሲል እንደተመለከ
ትነው ዲያብሎስ መንፈስ ስለሆነና እንዲሁም አሠራሩ በድብቅና

በጨለማ ውስጥ ስለሆነ፣ በሥጋዊ ዓይናችን ልናየው አንችልም። በምንነት ራሱን ገላልጦ ስለማያሳየን፣ የሚደበቅበትን ሥፍራ በቀላሉ ማወቅ ያስቸግራል።

ሁላችንም የራሳችን የሆነ ድካም ስለ አለን፣ ሰይጣን የሚደበቀውና ጥቃቱን የሚያካሂደው እዚያ ውስጥ ተደብቆ ነው። ሰይጣን ያንን ደካማ ጎናችንን ሲጫን፣ የተለያዩ ችግሮች በውስጣችን መታየት ይጀምራሉ። እነዚህ ድካሞቻችን ምን ዓይነት እንደሆኑ ሃዋርያው ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ ላይ ዘርዝሮ ጽፎታል፤ «የሥጋ ሥራዎች የታወቁ ናቸው፤ እነርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ንትርክ፣ ቅንአት፣ ቁጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ መለያየት፣ አድመኝነት፣ ምቀኝነት፣ ስካር፣ ዘፋኝነትና እነዚህን የመሳሰሉ ናቸው» (ገላትያ 5:19-21) ይላል።

ሰይጣን ራሱን የሚደብቀው ከላይ የእግዚአብሔር ቃል በዘረዘራቸው በሰው ድክመት ውስጥ ነው። የሰይጣንን አሠራር ለማየት ወደ ሰማይ ማንጋጠጥ አያስፈልገንም፤ ከዚያ ይልቅ የግል ሕይወታችንን በመስታወት (የእግዚአብሔር ቃል) መመልከት ያስፈልገናል። ያኔ በቀላሉ ሰይጣን የተደበቀበትን ሥፍራ ማየት እንችላለን። እስቲ ከላይ ከተዘረዘሩት ድክመቶች መካከል ሁለቱን ብቻ ለምሳሌ ያህል እንመልከት፣

### ① በመዳራት (ፍትወት)

ሰይጣን ብዙ ጊዜ በዚህ ድካማችን በመጠቀም ከፍተኛ ጥቃት ያደርስብናል። አዕምሮአችንን «በሚቀሰቅስ ነገር» (stimuli) በቀላሉ ያነሳሳል። ሰይጣን ይህን በደንብ ስለሚያውቅ ብዙ ጊዜ ስሜታችንን የሚቀሰቅስ ነገር አመቻችቶ ያቀርብልናል። ለዳዊት የሚደክምበትን አቅጣጫ አውቆ ያቀረበለት «የሚቀሰቅስ ነገር»፣ ቤርሳቤ ገላዋን ስትታጠብ እንዲያይ በማድረግ ነበር። ዳዊት ይሄ የሰይጣን ተንኮል መሆኑን ስላላወቀ፣ በቀላሉ ዘሎ ወጥመዱ ውስጥ ገባ።

የሰው አዕምሮ ንጹህ ያልሆነ ሀሳብ የማሰብ ዝንባሌ እንዳለው ሰይጣን በደንብ ስለሚያውቅ፣ ወደ አዕምሮአችን ብዙ ሀሳቦችን ይወረውራል። ሌሎች የሰውነት ክፍሎቻችን የሰይጣንን ሀሳብ በተግባር ለማዋል የሚተባበሩት፣ ከአዕምሮአችን በሚተላለፍላቸው ትዕዛዝ መሠረት ነው። ለምሳሌ፣ እጃችን ወደ ስርቆት የሚዘረጋው ትዕዛዙ ከአዕምሮአችን ሲመጣ ብቻ ነው። ይህን መጽሐፍ ስጽፍ እጄ ብዕሩን ይዞ ፊደሎችን እየቀጣጠለ የሚጽፈው፣ አንጎሌ የሚነግረውን ብቻ ነው። ሰውን የሚያንቀሳቅሰው ሞተር የሰው አንጎል እንደሆነ ስለሚያውቅ ነው ሰይጣን አዕምሮአችንን በቁጥጥሩ ሥር ለማዋል ከፍተኛ ተጋድሎ የሚያደርገው።

## ② በራስ ወዳድነት

ከማንኛቸውም ድክመቶች የበለጠ ሰይጣን ራሱን የሚደብቅበት ሥፍራ ቢኖር፣ በሰው «ራስ ወዳድነት» ባህሪ ውስጥ ነው። በመሠረቱ «ራስን መውደድ» ተገቢ ነው፤ መጽሐፍ ቅዱስም ይደግፈዋል። ሰይጣን ግን ይህንን በመጠቀም ያሰፋውና «ከመጠን በላይ ራስን መውደድ» (selfishness) ያደርገዋል። ራሱን በጣም የሚወድ ሰው፣ ከራሱ ፍላጎት በቀር የሌላው ሰው ፍላጎት አይታየውም። እርሱን እስከተመቸው ድረስ ሌላው ቢረገጥ፣ ቢጨፈለቅ ግድ የለውም። ራሱን ከመጠን በላይ የሚወድ ሰው ስስታም ነው። ሌላው ቀርቶ ለኢየሱስ የሚገባውን ድርሻ እንኳን መስጠት አይሆንለትም።

ሰይጣን የሚጠቀምባቸው የሰው ድክመቶች እነዚህ ብቻ አይደሉም፤ በጣም ብዙዎች ናቸው። ፊታችንን ወደ ሌሎች ሰዎች አዙረን የእነርሱን ድካም ከመቆፈር ይልቅ፣ ወደ ግል ሕይወታችን በመመልከት የራሳችንን ድካም መመርመር የበለጠ ይረዳናል። «እነዚህ ድክመቶች ሰይጣን የፈጠራቸው ናቸው» በማለት በሰይጣን አናመካኝ። ይልቁንስ ራሳችንን እንውቀስ። በሰይጣን ማመካኘት ራሳችንን ከኃላፊነት ነጻ ለማድረግ የምንጠቀምበት ምክንያት አናድርገው። ራሳችንን ከኃላፊነት ነጻ ማድረጋችንን ሰይጣን አይጠላውም። ምክንያቱም በዚህ ውስጥ በቀላሉ ራሱን መደበቅ ስለሚያስችለው ነው።

## መ ሰይጣን በማጥፋት ተግባር ላይ እንዳለ መያዝ ይቻላል

መጠኑና ብዛቱ ይለያይ እንጂ አብዛኞዎቹ ጳውሎስ የዘረዘራቸው ድካሞች፣ በብዙዎቻችን ሕይወት ውስጥ የሚታዩ ናቸው። ድክመታችንን ካወቅን በኋላ ቀጥሎ ምን ማድረግ ይገባናል? ሰይጣን ጥቃቱን ሲፈጽም «እጅ ከፍንጅ» ለመያዝ እንሞክር። «እጅ ከፍንጅ» ለመያዝም፣

1. «በደከምንበት አቅጣጫ» ብቅ ማለቱ አይቀርምና፣ በዚያ በኩል ነቅተን እንጠብቀው። ይህን ማድረግ ለመጀመሪያ ጊዜ ቀላል ላይሆንልን ይችላል። ይሄም በቀላሉና በአጭር ጊዜ ውስጥ ይሳካልናል ብለን አናስብ። ሰይጣን እየተጠባበቅነው መሆናችንን ስለሚያውቅ፣ ራሱን መሸፈንና መደበቅ ይጀምራል። ይሄ ዋና ዘዴው ነው። እርሱን እንዳንጠብቅ ሰይጣን አዕምሮአችን ወደ ሌላ በቀላሉ እንዲሳብ የማድረግ ችሎታ አለው። አዕምሮአችን እርሱን በመጠበቅ ፈንታ ባጋጠመን ችግር ላይ ብቻ እንዲያተኩር ለማድረግ፣ መሰናክል በመንገዳችን ላይ መፍጠርንም ያውቅበታል።

ሰይጣንን በተግባር ላይ እያለ «እጅ ከፍንጅ» መያዝ እንዴት እንችላለን? ለምሳሌ ድካማችን «የሥጋ ፍትወት»

ነው እንበል። ይህን ድክማችንን በመጠቀም ሰይጣን በሕይወታችን ላይ የሚያደርሰው ጥቃት ቀላል እንዳልሆነ እናውቃለን። በዚህ አቅጣጫ መጠበቃችንን ስለሚያውቅ ሰይጣን ራሱን ገላልጦና ገልጾ አድርጎ እንደማይቀርብ ቀደም ሲል ገልጸናል። አረሳስቶና «ሰይጣን ይመጣል» ብለን በማንጠብቀው ጊዜና ሥፍራ የመጣል። እርጉ የሀሳብ ፋይሎችን ከምናጠራቅምበት የአዕምሮ ክፍላችን ውስጥ (unconscious) ገብቶ አንዳንድ ነገሮችን ይፈልግና፣ ክርስቲያን ከመሆናችን በፊት ወይንም ክርስቲያን ከሆንን በኋላ ካየነው ብዙ ጊዜ የሆነውን ነገር ወደ አዕምሮአችን እንደ ፊልም ብቅ ያደርግልናል። ይህን የሚያደርገው ምናልባት ተገቢር ከከን በመጸለይ ላይ ሳለን ሊሆን ይችላል። ሰይጣን በዚያ አካባቢና በጸሎት መንፈስ ውስጥ እያለን ይመጣል ብለን ፈጽሞ ስለማንገምት፣ ወደ አዕምሮአችን ብቅ ያለውን ሀሳብ ቶሎ በማስወጣት ፈንታ፣ ይበልጥ ራሳችንን በዚያ ሀሳብ ማዝናናትና ማስደሰት እንጀምራለን። ሰይጣን ሀሳቡን ማመንጨት ብቻ ሳይሆን ያየነውን በተግባር ላይ እንድናውለው በረቀቀ ጥበቡ ሀሳብ ያቀርብልናል።

2 የምናስታውሰውን የእግዚአብሔርን ቃል እንጥቀስበት። ሰይጣንን በተግባር ላይ እያለ «እጅ ከፍንጅ» ለመያዝ በመጠበቅ ላይ ከሆንን፣ ቆሻሻ የሀሳብ ፋይል አውጥቶ ወደ አዕምሮአችን አስማምሮ ሲያቀርብልን፣ እኛም በውስጣችን ያጠራቀምነውን የእግዚአብሔርን ቃል አንድ በአንድ እያስታወስን እንወርውርበት። ለምሳሌ፣

- «...ሴሰኞችንና አመንዝሮችን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል» (ዕብ. 13:14)፣
- «...የምንዝር ተግባር የሚፈጽም ሰው ግን ማስተዋል የጎደለው ነው፤ ሕይወቱንም በከንቱ ያጠፋል። ውርደትና ድብደባ ይደርስበታል፤ ሁልጊዜም እንደተዋረደ ይኖራል» (ምሳሌ 6፡32)፣
- «...ከዝሙት ራቁ» (የሐዋ. 15፡29)፣
- «...ከዝሙት ራቁ፤ ሰው የሚያደርገው ሌላው ኃጢአት ሁሉ ከሰውነቱ ውጪ የሚደረግ ነው፤ ዝሙትን የሚፈጽም ሰው ግን በገዛ ሰውነቱ ላይ ኃጢአትን ያደርጋል» (1 ቆሮ. 6፡18)፣
- «ነገር ግን በዝሙት ኃጢአት ላለመውደቅ እያንዳንዱ ወንድ የራሱ ሚስት ትኑረው፤ እያንዳንዷም ሴት የራሷ ባል ይኑራት» (1 ቆሮ. 7፡2)፤

• «የእግዚአብሔር ፈቃድ እናንተ እንድትቀደሱና ከዝሙት እንድትርቁ ነው፤ ከእናንተ እያንዳንዱ የገዛ ሰውነቱን በቅድስናና በክብር ጠብቆ መያዝን ይወቅ። እግዚአብሔርን እንደማያውቁ አረማውያን የፍትወት ምኞት አይኑረው» (1 ተሰ. 4:3-5)፣

እነዚህንና ሌሎች ጥቅሶችን እያወጣን እንምታው። በቃላችን የማናስታውሰው ከሆነ፣ በትናንሽ ካርድ ጽፈን ኪሳችን እናስቀምጠውና ሰይጣን መቆስቆስ ሲጀምር አውጥተን እንጥቀስበት። ጌታ ኢየሱስም በሰይጣን ሲፈተን «ተጽፏል» በማለት ተጠቅሞበታል።

3 ሰይጣን «አንዴ ታውቀብኛልና ተመልሼ አልመጣም» አይልም። ትንሽ ቆይቶና አረሳስቶ፣ እንዲሁም መልኩን ቀይሮ ብቅ ይላል። በተለይ በውጪ አገር የምንኖር ኢትዮጵያውያን የዕለቱን ዜና ለማዳመጥ ቴሌቪዥናችንን ስናይ፣ በወሬው መካከል ማስታወቂያ ስለሚኖር በከፊል ሰውነቷ የተጋለጠ ሴት የመኪና ማስታወቂያ ስትናገር ብቅ አድርጎ ወንዶች ለሆንነው ማጥመጃና ማባበያውን ያሳየናል። መስኮት በሆነው ዓይናችን ይጠቀምና በአዕምሮአችን መጫወት ይጀምራል። በመጠበቅ ላይ ካለን፣ ያ የሰይጣን ወጥመድ መሆኑን ወዲያው ለይተን እናውቀዋለን። በዚህ ዓይነት ሰይጣንን እጅ ከፍንጅ ያዝነው ማለት ነው። ከዚህ በኋላ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስለሚያግዘን ትግላችን ቀላል ይሆንልናል። ሰይጣንን ለመዋጋት ትልቁና አስቸጋሪው ክፍል ሰይጣንና አሠራሩን ለይቶ ማወቁ ላይ ነው።

4 የሰይጣንን አመጣጥ ለማወቅ በመንፈስ ቅዱስ ላይ እንታመን። ሰይጣንን «እጅ ከፍንጅ» መያዝ ቀላል አይደለም። የተሳካ ውጤት ወዲያው እናገኛለን ብለን መጠበቅ አይገባንም። በክርስትና ሕይወት ስናድግና በቂ ልምምድ እያገኘን ስንመጣ፣ ማንነቱንና አሠራሩን እያወቅን እንመጣለን። ሰይጣንን «እጅ ከፍንጅ» በያዝነው ቁጥር መረዳት ያለብን፣ መንፈስ ቅዱስ እየጠቀመን መሆኑን መርሳት የለብንም። ይሄ የእርሱ የሥራ ድርሻ ነውና በእርሱ ልንታመን ይገባል። ይሁን እንጂ የሰይጣንን አሠራር ለማወቅ የራሳችንም ድርሻ እንዲኖርበት ያስፈልጋል። ችግሩ ግን የብዙዎቻችን «ደካሞች» በጣም ብርቱዎች ስለሆኑ፣ ዓይኖቻችን የሰይጣንን ተንኮል እንዳንመለከት የታወሩ ናቸው። ለምሳሌ «ቅናት» ደካማ የሆነ ሰው፣ ቅናቱ ሲቀሰቀስ፣ ያ ከሰይጣን የመጣ ነው ብሎ ማመንና መቀበል ያቅተዋል። ስሜቱ ኃይለኛ ስለሚሆን፣ ምንጩን እንዳያይ ዓይኑን ያሳውረዋል። እዚህ ላይ

የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ የግድ ያስፈልገዋል። ያለመንፈስ ቅዱስ ድጋፍና ዕርዳታ አዕምሮአችን በጠላታችን በሰይጣን ላይ ማተኮር አይችልም።

መንፈስ ቅዱስ በዚህ ሁኔታ ላይ የሚያግዘን መቼ ነው? ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ፣ ማለትም ሰይጣን ሀሳቡን ወደ አዕምሮአችን መወርወር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ነው። ይሄ ሀሳብ «ከሰይጣን የመጣ ነው» በማለት የማስጠንቀቂያ መልዕክቱን ወደ አዕምሮአችን ይልካል። ድምጹ ለስላሳ በመሆኑ ከሩቅ እንጂ ከቅርብ የመጣ አይመስለንም። ጆሮአችንን የሚያደነቁር ድምጽ ባይሆንም፣ እኛን ለማስጠንቀቅ ግን በቂ ነው። መንፈስ ቅዱስ ሲናገር የመስማት ልምምድ ስለሌለን ምናልባት አንለየው ይሆናል፤ ነገር ግን ቀስ በቀስ ድምጹን ለመስማትና ለይተን ለማወቅ ራሳችንን ማለማመድ ይገባናል።

5 ሰይጣንን «እጅ ከፍንጅ» ለመያዝ ድምጻችንን እናሰማው። ሌባ ጨለማን ተገን አድርጎ ወደ ግቢያችን ሲገባ «ማነህ አንተ? መጣሁብህ!» ብለን ድምጻችንን ስናሰማው ፈርጦ ይጠፋል። ሰይጣንም ሥራውን በጨለማ ውስጥ ስለሚሠራ፣ ራሱን ደብቆ ብቅ ሲል «አንተ ሰይጣን!» ስንለው ማንነቱን እንዳወቅንበት ስለሚረዳ ያኔ ብርክ ይይዘዋል። ከሰይጣን ጋር ንግግር መያዝ ይገባናል እንዴ? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ኢየሱስ ራሱ ካነጋገረው፣ እኛም ልናነጋግረው ይገባል፤ የምናነጋግረውም ኢየሱስን እንደምናነጋግረው ነው። ኢየሱስን በጸሎት፣ ሰይጣንንም በመቃወምና በመገሰጽ እናነጋግራቸዋለን። የሰይጣንን አጥፊነትና ያለውን ኃይል እያወቅን ለእርሱ ትዕዛዝ መስጠትና መቃወም ያስፈራን ይሆናል። ይሁን እንጂ ሰይጣን ፊት ለፊት ስሙን እየጠራን ብንቃወመው ይጎዳን ይሆናል ብለን መፍራትና ማሰብ የለብንም።

እንዴት ለሰይጣን መልስ መስጠት እንደሚገባን ኢየሱስ ከግል ሕይወቱ ምሳሌ ትቶልናል። ኢየሱስ በዲያብሎስ ሲፈተን፣ ለእያንዳንዱ ሀሳብ «እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል» እያለ መልስ ሰጠው። *«ሰው የሚኖረው እግዚአብሔር በሚናገረው ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይደለም ተብሎ ተጽፏል...»* (የማቴ. 4:4)፣ *«..እግዚአብሔር አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ተጽፏል...»* (4:7)፣ *«...ወግድ ሂድ አንተ ሰይጣን ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ስገድ፣ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏል አለው»* (4:10)። ከዚህ በኋላ *«ዲያብሎስ ኢየሱስን ትቶት ሄደ»* ይላል።

ሰይጣን ድል የተመታ ጠላት መሆኑን መረዳት ትልቅ ነገር ነው። ይኼ ሀሳብ ግን ብዙዎችን አሳስቷል። ሰይጣንን ኢየሱስ ድል ያደረገው ጠላት በመሆኑ «ምንም ዓይነት ኃይል የለውም» ብለው የሚያስቡ አሉ። ኢየሱስ ሰይጣንን ስላሸነፈው ሰይጣን እኛን አይዋጋንም ብሎ ማሰብና መገመት ትልቅ ስህተት ነው። ሰይጣን ይሸነፍ እንጂ ጨርሶ የሞተ አይደለም። የነበረውም ኃይል አልተቀነሰም። መጀመሪያ እንደ ነበረው ኃይለኛና አደገኛ ነው። ጠብ ለመጫርም ሁልጊዜ በተጠንቀቅ የቆመ ነው። ሰይጣን ማንኛውንም ሰው ፈጽሞ አይፈራም። እንደ ቃሉና ፈቃዱ በቅድስና ሕይወት ካልፀናን፥ ሰይጣን የፈለገውን ጥቃት በእኛ ላይ ማድረስ መብቱ ነው። እርሱን የምንቋቋምበት የራሳችን የሆነ ኃይልና ጉልበት ስለ ሌለን፥ ለብቻችን ሰይጣንን እንዋጋለን ብንል ይሰቅብናል።

ኢየሱስ ሰይጣንን ድል ስለመታው በእርግጥ እርሱን ይፈራዋል። ስሙም ሲጠራ ይንቀጠቀጣል። እኛም የምንዋጋው በራሳችን ስም ሳይሆን፥ በኢየሱስ ስም በመሆኑ ያንን ስም ሲሰማ ይንቀጠቀጣል። ሰይጣን የኢየሱስ ስም ሲጠራበት አይወድም፤ ይፈራል። ስሙ ሲጠራ የተሸነፈበትን ወቅት ስለሚያስታውሰው፥ ያ ስም እንደ ጦር ይወጋዋል። ስለዚህ የእኛ ኃይልና ሥልጣን የተመሠረተው በኢየሱስ ስም ላይ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ደጋግሞ በዚህ ስም በመ ጠቀም ማድረግና ጠይቀን ማግኘት የምንችለውን ነግሮናል። «በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት» ይለናል (ቆላስይስ 3፥17)። ስለዚህ ሰይጣንን ስንቃወም በዚህ ስም መጠቀም አለብን። «አንተ ሰይጣን በኢየሱስ ስም እመግብሃለሁ...» በማለት በድፍረትና በሥልጣን ልንገስጸው ይገባል። ርኩሳን መናፍ ስት የኢየሱስ ስም ሲጠራባቸው ይንቀጠቀጣሉ። ማወቅ ያለብን የኢየሱስን ስም ጠርተን ሰይጣንን የምንቃወመው ኢየሱስን ከሕይወታችን ውጪ አድርገን ሳይሆን፥ እንደ ልብስ ለብሰነው ነው። ሰይጣን የኢየሱስን ስም ስንጠራ መስማት ብቻ ሳይሆን፥ እርሱን በሕይወታችን መልበሳችንን ጭምር ያያል። አለበለዚያ ይንቀናል። እዚህ ላይ በኤፌሶን ከተማ በሰባቱ የአስቄዋ (የካህናት አለቃ) ወንዶች ልጆች ላይ የደረሰውን ታሪክ መመልከቱ ይጠቅማል (የሐዋ. 19:11-17)።

## ሠ. ሰይጣንን ነቅተን መጠበቅ እንዳለብን እንወቅ

ዘብ የቆመ ወታደር በተጠንቀቅ መጠበቅ ከፍተኛ ኃላፊነቱ ነው። በጥበቃ ላይ ዘብ የሚቆሙ ወታደሮች አንዳንድ ጊዜ በእንቅልፍ

የሚሸነፉበት ጊዜ አለ። አንድ በዘብ ላይ ያለ ወታደር ዕንቅልፉን ተኝቶ ቢገኝ በሮማውያን ሕግ መሠረት በሞት ይቀጣል። ሌሎች ወታደሮች ያለስጋት መተኛት እንዲችሉ፣ እርሱ ሳያንቀላፋ ጠላትን መጠበቅ አበት። ሲያንቀላፋ የተገኘ ወታደር በሞት የሚቀጣበት ምክንያት፣ የተቀሩትን ወታደሮች በጠላት ያስፈጃል ተብሎ ስለሚገመት ነው።

ነቅቶ መጠበቅ ለምድራዊ ወታደር ከሚያስፈልገው የበለጠ ለክርስቶስ ወታደሮች ያስፈልጋቸዋል። በምድራዊ ውጊያ የተሰማሩ ወታደሮች የሚዋጉት እንደ እነርሱ በእንቅልፍ ሊሸነፉ ከሚችሉ ሰዎች ጋር ነው። የክርስትያኖች ጠላት ግን ሃያ አራት ሰዓት የማያንቀላፋ፣ ሁል ጊዜ ንቁ የሆነ ነው። ስለዚህ ክርስቲያን ካንቀላፋ ራሱን ለአደጋ አጋልጦ መስጠቱ ግልጽ ነው። ከተዝናናና ተደላድሎ ከተኛ፣ እንዲሁም ግዴለሽ ከሆነ፣ በሰይጣን ይጠቃል። ሰይጣን ውጊያውን ይበልጥ የሚያፋፍመው ክርስትያኑ ከተኛበት መንፈሳዊ እንቅልፉ ነቅቶ ሰይፉን እስከሚመዝበት ድረስ፣ ሰይጣን ቀደም ብሎ ከፍተኛ ጥቃት እንደሚያደርስበት ስለሚያውቅ ነው።

የተኛን አንበሳ ሌላው ቀርቶ ዝንቦች እንኳን ሳይፈሩ ፊቱን ይወሩታል። ልክ እንደዚሁ በእንቅልፍ ላይ ያለውን ክርስቲያንንም በጣም ቀላል የሚባለው ፈተና እንኳን አሸንፎ ሊጥለው ይችላል። ሳምሶን በተኛበት ወቅት በቀላሉ ደሊላ «የኃይሉ ምክንያት የሆነውን ጸጉሩን» መቁረጥ ቻለች። ንጉሥ ሳኦል ተኝቶ ጦሩ ከአጠገቡ ተወሰደ፤ እንዲሁም ኖህ በተኛበት ወቅት ራቁትነቱ ታየ፤ ክርስቲያኑም በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሲያንቀላፋ ለጠላት ጦር ያኔ ከምንጊዜውም ይበልጥ የተጋለጠ ይሆናል። ስለዚህ ክርስቲያን ሁልጊዜ ነቅቶ መጠበቅ እንዳለበት መርሳት የለበትም።

ክርስቲያን ነቅቶ ከጠበቀ፣ ሰይጣን ዓላማውን መፈጸም አይችልም። ሌባ ቤታችንን ሰብሮ እንዳይገባ መጠበቅ ምን ያህል ከጉዳት እንደሚያድነን መረዳት ይህን ያህል ከባድ አይደለም። ቤታችንን ከሌባ ከመጠበቅ ይልቅ፣ ሰይጣን ወደ ሕይወታችን ገብቶ ጥቃት እንዳያደርስብን መጠበቅ የበለጠ ጥቅም አለው። ለዚህ ነው ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ነቅተው እንዲጠብቁ ያሳሰባቸው (የማቴ. 26:41)። ለእንቅልፍ ስንል ብቻ አንገታችንን በወንበዴ ማስቆረጥ ትልቅ ዋጋ መክፈል ይሆናል። ያ እንኳን ምናልባት ከሞት ልናመልጥ፣ እንዲሁም ቁስላችንም ሊድን ይችል ይሆናል። ባይድንም እንኳን የምንሞተው ሞት ጊዜያዊ ሞት ብቻ ነው። ሰይጣን የሚያደርሰው ጉዳት ግን ከዚያ የበለጠ፣ ወይንም ዘለዓለማዊ ነው። ዳዊት በሰገነቱ ሆኖ ዓይኑ በቤርሳቤህ ላይ ያረፈው፣ መንፈሳዊ እንቅልፍ ውስጥ በነበረበት ጊዜ ነበር። ስለሆነም በቀላሉ ከሰይጣን ወጥመድ ውስጥ መግባት ቻለ። በኃጢአቱ ምክንያት ዳዊት ያለእንቅልፍ ያደረባቸው ሌሊቶች ምን ያህል እንደነበሩ መገመት አያቅተንም። ስለዚህ ሳንናቀላፋ ነቅተን መጠበቅ ከቻልን፣ ሰይጣን ዓላማውን እንዳይፈጽም እናደርገዋለን።

በማንቀላፋት ውስጥ ያለውን አደጋ የምናውቀው ነቅተን በንጠብቅ ብቻ ነው። የተኛ ሰው የራሱን «ማንኮራፋት» መስማት አይችልም፤ ሌላውን ግን እንቅልፍ በመንሳት ያበሳጫል። ያንቀላፋ ሰው በአካባቢው የሚሆነውን ያውቃል፤ ይሰማል። በመንፈሳዊ ሕይወታችን ንቁዎች ከሆንን ደግሞ፣ በስም ክርስቲያን ነን የሚሉት ልባቸውን ካለመጠበቃቸው የተነሳ የሚፈጽሙትን ኃጢአት ማየት እንችላለን። ታዲያ የሌላውን ሰው ኃጢአት ማየትና ማወቅ እኛን ምን ይጠቅመናል? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። እርግጥ ነው የሌላውን ሰው ሕይወት የምናየው ለመፍረድ ሳይሆን፣ ልባችንን ካልጠበቅን በእኛ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ነገር ስለሚያሳየን፣ ምሳሌና ማስጠንቀቂያ እንዲሆነን ብቻ ነው። እንቅልፍ ሁሉንም ሰው እኩል ያደርጋል። ደካማውም ሆነ ኃይለኛው ካንቀላፉ ሁለቱም እኩል ናቸው። ሞኙም ሆነ ጥበበኛው በእንቅልፍ ላይ ከሆኑ፣ ሁለቱም ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው። በመንፈሳዊ ሕይወቱ ብዙ የቆየውና እንዲሁም ገና ወደ ክርስቶስ የመጣውም በመንፈሳዊ የእንቅልፍ ሰመመን ውስጥ ከሆኑ፣ ሁለቱም ለሰይጣን የተጋለጡ ናቸው።

ማንም ሰው በእንቅልፍ ሰመመን ውስጥ ካለ ሰው ጋር ቁጭ ብሎ ተዝናንቶ መጫወት የሚወድ የለም። ሌላው ቀርቶ ስናወራላቸው እንቅልፋቸው የመጣ ከመሰለን፣ «ይረፉ» ብለን ትተናቸው እንሄዳለን እንጂ ቁጭ ብለን ከነርሱ ጋር ደስ ብሎን መጫወት አይሆንልንም። ለምሳሌ በእንቅልፍ ላይ ያለውን ሰው እንዲያስቀምጡልን በአደራ የሰጠነውን ዕቃ በማግሥቱ መልሶ እንዲሰጠን ብንጠይቀው፣ ከእጃችን መቀበሉን ፈጽሞ አያስታውስም።

ክርስቶስም በመንፈሳዊ እንቅልፍ ውስጥ ካለ ክርስቲያን ጋር ሕብረት ማድረግን አይመርጥም። ስለ አባቱ መንግሥት ራእይን (መገለጥን) የሚሰጠው ነቅተው ለሚጠብቁት ክርስቲያኖች እንጂ መቀበላቸውን ለማያስታውሱ፣ በእንቅልፍ ሰመመን ውስጥ ላሉት ክርስቲያኖች አይደለም።

አንዳንድ ክርስቲያኖች በኃጢአት ወድቀው በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ከቆሰሉና ከተሳሳቱ በኋላ የት መሄድ እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው፣ ከማን ጋር መተባበር እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው ያኔ መመርመርና እርምጃቸውን መጠበቅ ይጀምራሉ። ቁስሉ ሲድንላቸውና አገግመው ሲነሱ፣ ከዚህ በፊት የደረሰባቸውን ጉዳት ፈጽሞ ይረሱና ከቀድሞው ባሳነሰ ሁኔታ «የግድየለሽ ክርስትና ሕይወት» መኖር ይጀምራሉ። አንድ ጊዜ በሌባ የተዘረፈ ሰው፣ ተመሳሳይ ጉዳት ለሁለተኛ ጊዜ እንዳይደርስበት በሩን በጥንቃቄ ይዘጋል። እንዲያውም አንዳንዴ እንቅልፉን መስዋዕት በማድረግ ነቅቶ የሚጠብቅበት ጊዜ አለ። እውነተኛ የክርስቶስ ወታደር ለመሆን ከፈለግን፣ ሁልጊዜ ነቅተን መጠበቅ አለብን። እንደ ሰነፍ መንገደኛ በየመንገዱ ዳር ማንቀላፋት የለብንም። እግዚአብሔር ያረፈው ሥራውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ ነው፤ እኛም

የደህንነታችንን ጉዞ እስክንፈጽም ድረስ ንቅተን መጠበቅና መሥራት አለብን። ማረፍ የምንችለው፥ ምንም ዓይነት አደጋ ከሌለበት ከዘለዓ ማዊ ቤታችን ስንደርስ ብቻ ነው።

የሆኑ የከተማ ወይንም የመንደር ዘብ ጠባቂዎች፥ እየዞሩ የሚጠ ብቁት ሁለት ወይንም ሦስት ቤቶችን ብቻ ሳይሆን መላውን መንደር ወይንም ከተማ ነው። ልክ እንደዚሁ አማኝም የሚጠብቀው የተወሰነውን የሕይወት ክፍሉን ብቻ ሳይሆን ሁለንተናውን መሆን አለበት። አንዳ ንዱ ሌላውን በንግግሩ እንዳይጎዳ «ምላሱን ይጠብቅና» በሌላ በኩል ግን ወደ ዝሙት ሊጥለው የሚችለውን አዕምሮውን አይጠብቅም። ሌላው ደግሞ እጁን ከሌላው ሰው ኪስ ከመከተት ይቆጥብና፥ ልቡን ግን ከትናትና ከምቀኝነት መጠበቅን ችላ ይላል። ስለዚህ እውነተኛ ክርስቲያን ሕይወቱን መጠበቅ ያለበት በአንዳንድ አቅጣጫ ብቻ ሳይ ሆን በሁሉም አቅጣጭ ሊሆን ይገባል። ምክንያቱም ሰይጣን ትንሽ ቀዳዳ ካገኘ ያንን በመጠቀም ከፍተኛ መንፈሳዊ ጉዳት ሊያደርስብን ስለሚችል ነው።

ብዙዎቻችን በጥቃቅኑ ነገር ጠንቃቃዎች እንሆንና፥ ጎልቶ የሚ ታየውን ትላልቁን ነገር ግን ችላ እንላለን። ኢየሱስ ፈሪሳውያንን «ከአዝ ሙድ፥ ከእንስላል፥ ከከሙን ዐሥራት ትሰጣላችሁ፤ ነገር ግን በሕግ ውስጥ የሚገኙትን ዋና ነገሮች ትተዋላችሁ» (የማቴ. 23:23) እንዳላ ቸው እናስታውሳለን። አንዳንድ ክርስቲያኖችም በጥቃቅን ነገሮች ላይ ትኩረት ይሰጡና ትላልቁን ነገር ችላ ይሉታል። ቅድስናን፥ ራስን የመካድ ሕይወት፥ ለሌላው ፍቅርና ርህራሄን ማሳየትን ችላ ይሉና «በአምልኮ ሥርዓት» ላይ ንቃት ያሳያሉ። እንዲያውም የበለጠ ንቅተን መጠበቅ የሚገባን ደካማ በሆንንበት አቅጣጫ ላይ መሆን አለበት። ሰይጣን በደከምንበት አቅጣጫ በመጠቀም ዓላማውን ለመፈጸም ስለ ሚችል፥ በዚያ አቅጣጭ እንዳያጠቃን የበለጠ በማስተዋል መጠበቅ ይገባናል።

ሰይጣን የሚያጠቃው ማሸነፍ የሚችልበትን ጊዜና ሁኔታ እየጠበቀ ነው።

**1** ሰይጣን በተለይ አዲስ የሆነውን አማኝ መፈተን ይወዳል። ከሰይ ጣን መንጋጋ አምልጦ ወደ ኢየሱስ የመጣ አዲስ አማኝ ሰይጣን የፈተና ቀስቱን ሲወረውርበት በሲኦል ያሉት የርኩሳን መናፍስት በሙሉ በእርሱ ላይ እንደተለቀቁበት መስሎ ይሰማውና ጩኸቱን ያሰማል። የክርስቶስ ደቀ መዛሙርትንም ቢሆን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ገና ህጻን በሆኑበት ጊዜ ከመፈተን ሰይጣን ወደ ኋላ አላለም። ተስፋ የተሰጣቸው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ገና እንዳልወረደላቸው ያውቅ ነበር። ሰይጣን ማንም ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ አድጎ ትልቅ እስኪ ሆን ድረስ አይጠብቅም። ገና በጨቅላነቱ ወግቶ ለመጣል ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። እነዚያ በእምነታቸው ህጻን ሆነው ያልወደቁት፥

የእግዚአብሔር ጸጋ ደግፎ ስለያዛቸው ብቻ ነው። ሰይጣን «ይኼ ሰው በእምነቱ ገና ህጻን ነውና እርሱን አሁን አልነካውም» አይልም። ሰይጣን የሚፈትነን በራሱ ጊዜ እንጂ እኛ በምንመርጠው ሰዓትና ቀን አይደለም።

**2** ሰይጣን ክርስቲያንን ለመፈተን የሚመርጥበት ሌላው ጊዜ፣ በችግርና በመከራ ውስጥ በሚያልፍበት ጊዜ ነው። ኢዮብ ትዕግሥት እንዲያጣና በመከራው ጊዜ በእግዚአብሔር እንዳይታመን ለማድረግ ፈተናውን የበለጠ ያፋፋመው ሰውነቱን በቁስል መትቶ ካዳከመው በኋላ ነው። ኢየሱስን የፈተነው አርባ ቀን ጾሞ በደከመበት ጊዜ ነው። በመከራና በችግር ጊዜ ጸንተን ለመቆም ብንፈልግ፣ አንድ ነገር መረዳት ያስፈልገናል። ያም ሰይጣን በዘረጋልን ፈተና ከምንጎዳው ይልቅ፣ እንድናደርግ የሚያባብለንን ኃጢአት ሠርተን የሚደርስብን ጉዳት (ጠባሳ) የበለጠ እንደሚያመዝን ነው። በገንዘብ እጦት ምክንያት እኛና ቤተሰባችን ስንሰቃይ፣ ሰይጣን ይህን አጋጣሚ ይጠቀምና «አሁን ምን ልታደርግ ነው? ልጆችህ በረሀብ እንዲያልቁ እግዚአብሔር እንደማይፈልግ ታውቃለህ። ከጠገበና ከተረፈው ወስደህ ልጆችህን ብትመግብ ምን አለበት?» በማለት የራሳችን ያልሆነውን ገንዘብ እንድንወስድ ያግባባናል።

**3** ሰይጣን ሊፈትነን የሚመርጥበት ጊዜ እግዚአብሔርን በሚያከብር አገልግሎት ውስጥ ለመግባት ስንዘጋጅ ነው። «ጊዜው ገና ነው! የጌታን ቀን ጠብቅ» በማለት ሊያዳክመን ይሞክራል። በአገልግሎታችን ውጤት ማምጣት ስንጀምርና የብዙዎች ዓይን በእኛ ላይ መሆን ሲጀምርም፣ በረቀቀ ጥበቡ የምንጠፋበትን መርዝ እየቀመመልን መሆኑን አንርሳ። ይህን ማለት ሰይጣን ጎልቶ የሚታይ አገልግሎት እስኪኖረን ድረስ አይፈትነንም ማለት አይደለም። ባጋጠመው ዕድል ሁሉ ከአገልግሎታችን ለማደናቀፍ የተቻለውን መንገድ ሁሉ ይጠቀማል። የምንፈተንበትን ወይንም ደካማ የሆንበትን ነገር ማወቁ፣ ሥራውን በጣም ቀላል ያደርግለታል። ሰይጣን የሔዋን ልብ በፍሬው ውበት ልቧ መያዙን ስላወቀ፣ በቀላሉ የሚጥልበት መሣሪያ (ምክንያት) አገኘ። ሔዋን ከፍሬው ለመብላት እንደ ጎመጀች አይቶ፣ ሰይጣን ያንን ዕድል በመጠቀም የበለጠ ሁኔታው እንዲመስል አድርጎ አቀረበላት። ያኔ የራሷን ፍላጎት መግታት ስላልቻለች ቀጥፋ በላች። ለኃጢአት እጃችንን ላለመስጠት ከፈለግን፣ እግራችን ኃጢአት ወዳለበት ሥፍራ እንዲወስደን አንፍቀድለት። ለኃጢአት ላለመሸነፍ ከፈለግን፣ ሰይጣን የዘረጋልንን ፈተና በመደነቅ ዓይን አተኩረን አንመልከተው፤ ወይንም አዕምሮአችንንና ልባችንን ሙሉ በሙሉ አንስጠው።

**4** ሰይጣን ሊፈትነን የሚመርጥበት ሌላው ጊዜ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር ከምንጊዜውም የበለጠ በሚገለጥልን ጊዜ ነው። እግዚአብሔር ፈገግ ብሎ ልቡን ሲከፍትልን፣ ትዕቢት ወደ ውስጣችን ይገባና በራሳችን መመካት እንጀምራለን። በሌላ በኩል ደግሞ ድምፁ ሲርቅብን

«ስብርብር» እንላለን። እርሻ ጥሩ ዓየር፣ ተመጣጣኝ የጸሀይ ሙቀት አግኝቶ እህሉ ሲያብብ፣ አረሙም በዚያው መጠን ማደግና ማበብ ይጀምራል። ውርጭና ብርድ ሲመታው ደግሞ እርሻው መሞት ይጀምራል። ልክ እንደዚሁ ሰይጣን መጥፎውንም ሆነ ጥሩውን ሁኔታ መጠቀም ስለሚችል ነቅተን ልንጠብቀው ይገባል።

ሰይጣን መቼ እንደሚፈትነን ብቻ ሳይሆን እንዴት እንደሚፈትነንንም አይነግረንም። ወሳኙ እርሱ እንጂ እኛ አይደለንም። መጀመሪያ እንደ ቅርብ ወዳጅና ጓደኛ ሆኖ ይቀርበናል። ማንነቱን እስከምናውቅ ድረስ በራችን ለእርሱ የተከፈተ ነው። ጳውሎስ ሰይጣን «የብርሃን መልአክ ለመምሰል ራሱን ይለውጣል» ይለናል (2 ቆር. 11:14)። ከሁሉም የበለጠ ይሄኛው ዘዴ አደገኛ ነው። ምላሱን አለስልሶና የነብይ ካባ (ልብስ) ለብሶ ሲመጣ ብዙ ቅዱሳንን ያሳስታል። የወንጌል ተቆርቋሪ በመምሰል እውነትን እያጣመመ ይቀርባል።

አማኞች ሁሉ በዚህ እንደማይሞኙለት ስለሚያውቅ፣ ሌሎች ብልሃቶችና ዘዴዎችን ይፈጥራል። በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ውስጥ አልፎ አልፎ የሚኖረውን ድክመት አጋንኖና አተልቆ በማሳየት አንዳንድ የዋህና ደካማ ክርስቲያኖች «መንፈሳዊ መሪዎች እንዲህ ከሆኑ፣ ክርስትናን አልፈልግም» ብለው ከቤተ ክርስቲያን እንዲሸሹ ያደርጋል። «ለጌታ ሥራ» የሚቆረቆሩትን በመጠቀም፣ ልባቸውን በቁጣና በንዴት በመሙላት፣ በእግዚአብሔር ቤት ስተዋል ብለው የሚያስቧቸውን በይቅርታ በመቀበል ፈንታ፣ እንዲያጠቋቸው ይገፋፋቸዋል። የክርስቶስ ደቀ መዛሙርትም ለእግዚአብሔር መንግሥት ቅናት ስለነበራቸው፣ መልእክታቸውን ባልተቀበሉ ሰዎች ላይ እግዚአብሔር እሳት አውርዶ እንዲያጠፋቸው ጸለዩ (ሉቃስ 9:54-55)። በዚህ ዓይነት በመቆርቆር መንፈስ ሳናውቅ ጠላታችን የሆነውን ሰይጣንን ወደ ሕይወታችን አስገብተን እንዳናስተናግደው እንጠንቀቅ።

ሰይጣን የአማኞችን የዕለት እንቅስቃሴ መሰለል ከዘዴዎቹ አንደኛው ነው። በመሰለል ተግባሩ ሰይጣንን የሚስተካከለው አገርም ሆነ የስለላ ድርጅት የለም። ያለንን ዝንባሌ፣ ሀሳብ፣ ዕቅድና እንዲሁም ልባችንን የጣልንባቸው ነገሮች ምን እንደሆኑ ለማወቅ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። ልባችን ያዘነበለበትን አቅጣጫ ካወቀ በኋላ፣ የፈተና ወጥመዱን ይዘረጋል። ሰይጣን መጨረሻ ላይ የት ለመድረስ እንዳሰብን ሳያውቅ የምንፈልገውን ነገር ማድረግ ፈጽሞ አንችልም። በዚህ ጊዜ ደካማ የሆነው ክፍላችን ለነፍሳችን ታማኝነቱን አጉድሎ አቅጣጫችንን ወይንም ምስጢራችንን ለሰይጣን ሊገልጽብን ይችላል።

ሰይጣን «ዕድገት የመፈለግ» ምኞታችንን (ambition) በጣም ይወደዋል። ምክንያቱም ነፍሳችንን ለፈተና አጋልጦ የሚሰጠው ይኸው «ምኞት» እንደሆነ ስለሚያውቅ ነው። ሰይጣን በቀላሉ በማይሆን

ተስፋ ልባችንን ካሳበጠው (ከሞላው) በኋላ፣ ይህንን ፍላጎታችንን በመጠቀም ወደጠለቀ ኃጢአት ውስጥ ይከተናል። ነፍሳችንን ለመንካት ሁልጊዜ የረቀቀ ተንኮሉን ይጠቀማል። ለመፈተን ጠጋ ሲል እጅግ በጣም ተለሳልሶና ለእኛ የሚቆረቆር መስሎ ነው። ለማወቅ የሚፈልገውን በአንድ ጊዜ ለማግኘት ቢሞክር ተንኮሉ ስለሚታወቅበት፣ አቀራረቡ በዝግታ ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ሔዋንን ለመጣል የተጠቀመበት ጥበብና ዘዴ ነው። ሔዋንን «ቀጥፈሽ ብዪ» በማለት አልነገራትም፤ በዚህ ዓይነት መልክ ቢቀርባት፣ ተንኮሉ ገብቷት እንደምታባርረው ያውቃል። ስለዚህ ከሄዋን ጋር የሀሳብ ልውውጥ ለማድረግ በር ከፋች የሆነ ጥያቄ አቀረበላት። «በአትክልቱ ቦታ ካሉት ዛፎች ሁሉ ፍሬ እንዳትበሉ በእርግጥ እግዚአብሔር አዟችኋልን?» ሲል ጠየቃት (ዘፍ. 3:1)። የሚቀጥለው የተንኮል ጥያቄው «እርግጠኛ ነሽ? እግዚአብሔር ቸር አምላክ እንደሆነ ታውቂያለሽ፤ በአትክልቱ ቦታ ካሉት ዛፎች ሁሉ እንዳትበሉ ሳይከለክላችሁ ይህኛውን እንዳትነኩ ማለቱ ለምን ይሆን?» በማለት በእግዚአብሔር ላይ ጥርጥር ወይንም ጥያቄ እንዲኖራት አደረገ። ከዚህ በኋላ ሔዋንን ለመጣል አስቸጋሪ አልሆነበትም።

ከሰይጣን ጋር ውይይት መጀመር በጣም አደገኛ ነው። ብዙዎች ሳያውቁት አንድ እርምጃ፣ ከዚያም ሁለት እያሉ ከሰይጣን ጋር የሚጓዙ አሉ። አንዴ ከእርሱ ጋር መራመድ ከጀመሩ ሳያውቁት ብዙ ርቀው ይሄዱና መመለስ ፈጽሞ ያቅታቸዋል። ለሰይጣን አንዴም ቢሆን «በጅ» ማለት፣ እርሱን ለመቃወም የምንችልበትን ኃይል ማጣት ማለት ነው። በዚህ ዓይነት ሰይጣን ያጠመደውን ሰው ቀስ በቀስ እየመራ ሊወጣበት ከማይችለው የኃጢአት ማጥ ውስጥ ይከተዋል። እግዚአብሔር ሲጠራቸውና ማስጠንቀቂያ ሲሰጣቸው ሰምተው የማይመለሱ ለዘለዓለም ይጠፋሉ።

ምናልባት አንዳንዶች አንዳንድ ፈተና ሰይጣን ሲያቀርብላቸው «እምቢ» ለማለት ኃይልና ጉልበት ይኖራቸው ይሆናል። ይሁን እንጂ ጥበቃቸውን ምንጊዜም ማላላት የለባቸውም። ምክንያቱም ሰይጣን በአንድ ጊዜ ሙከራ ብቻ ትቷቸው ስለማይሄድ ነው። ጥቂት ቆይቶ ሌሎች አዳዲስ እርኩሳን መናፍስት ጨምሮ ተመልሶ ይመጣል። ሰይጣን ለሥራው የሚመለምላቸው ተጠባባቂ ሠራተኞች ምንጊዜም አያጡም። በአንድ ዓይነት ፈተና መጣል ካቃተውና ከተሸነፈ፣ ሌላ ዓይነት ፈተና በምትኩ ይዘረጋል። አልፎ አልፎ ሰይጣን ወደ ኋላ የማፈግፈግን ዘዴ ይጠቀማል። ክርስቲያኑ በሕይወቱ መዝናናት እስኪጀምር ድረስ አድፍጦ ይጠብቀዋል፤ ሰይጣን ለጊዜው «ተሸንፌአለሁ!» ብሎ ቢያምን ጦርነቱ አልቋል ወይንም አብቅቷል ማለት አይደለም። «መሸሹ» እምነታችንን የሚያጠነክርልን ይሁን እንጂ ጥበቃችንን የሚያላላብንና እንዲሁም መንፈሳዊ ሕይወታችንን የሚያዳክምብን እንዳይሆን እንጠንቀቅ።

ሰይጣን መቼና እንዴት እንደሚፈትነን ብቻ ሳይሆን፥ ሥራውን ለማስፋፋት እነማንን እንደሚጠቀም ያውቃል። እንደ ብልህ አናጢ፥ ሰይጣን ለእያንዳንዳችን የሚስማማውን ፈተና ቅርጾ፥ መልክ ሰጥቶ የማቅረብ ከፍተኛ ችሎታ አለው። ያንን ያቀደውን ፈተና እነማን ጥሩ አድርገው ሊያስፈጽሙለት እንደሚችሉና እንዲሁም ለሥራው ተስማሚ የሆኑትን ሰዎች የመመልመል ዕውቀትና ችሎታ አለው። ሰይጣን ምልመላውን የሚያካሂደው በብርቱ ጥንቃቄ ነው። እግዚአብሔር ዓላማውን ለመፈጸም የማንንም ሰው እርዳታ አይፈልግም። ሰይጣን ግን ያለሰው ዕርዳታ ዓላማውን ማስፈጸም አይችልም። የዚህ ዋናው ምክንያት ሰይጣን በኃይሉና በችሎታው «ውስን» በመሆኑ ነው። ሰይጣን ለዓላማው የሚጠቀምባቸው ተራ ሰዎችን ብቻ አይደለም። የሚመርጣቸው ሰዎች ብዙ ጊዜ ከፍተኛ የአዕምሮ ችሎታ ያላቸውን (superior intellect)፥ ቅዱሳች ናቸው ተብለው የሚታዩትን፥ ዝነኞችን፥ በሌሎች ዘንድ ተቀባይነትና ከበሬታ ያላቸውን ሰዎች ነው።

ሰይጣን ኃይልና ሥልጣን ያላቸውን፥ እንዲሁም የታወቁ ሰዎችን ይጠቀማል። እነዚህ በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በአገር ደረጃ የታወቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ከተሳካለት በሁለቱም መስክ እንዲሆንለት ይጥራል። የቤተ ክርስቲያኑን መድረክና እንዲሁም የአገሪቱን አመራር መቆጣጠር ከቻለ፥ ሰይጣን የሚፈልገውን ዓላማ ለማስፈጸም በጣም ቀላል ይሆን ለታል። ስለዚህም የአገር መሪዎች ከጎኑ እንዲሰለፉ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። ምክንያቱም ባላቸው ኃይልና ሥልጣን ምክንያት ብዙዎችን የመሳብ ኃይል እንዳላቸው ስለሚያውቅ ነው። የአንድን የጦር አዛዥ ልብ በማሸፈት፥ በእርሱ ሥር ያሉትን ወታደሮች በሙሉ መቆጣጠር እንደሚቻል ግልጽ ነው። የእስራኤል ንጉሥ የነበረው ኢዮርብአም ወደ ጣኦት አምልኮ በማዘንበሉ ምክንያት የእስራኤልን ሕዝብ በሙሉ ወደ ኃጢአት አዘቅት ውስጥ እንደከተታቸው እናውቃለን። ዳዊት የእስራኤልን ሕዝብ እንዲቆጥር በሰይጣን ለቀረበለት ፈተና እጁን ሰጥቶ ሲሸነፍ፥ በእስራኤል ሕዝብ ላይ ትልቅ መቅሰፍትን አመጣ።

ሰይጣን እጁን ማስገባት የሚፈልገው በአገር አስተዳደር ውስጥ ያሉትን ባለስልጣናት ብቻ ሳይሆን፥ ቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን ያላቸውን ለማያዝና በእነርሱ ለመጠቀምም ይፈልጋል። የቤተ ክርስቲያን መሪውን መንፈስ በኃጢአቱ ከበከለ፥ የተቀሩትን ምዕመናንን ለመበከል በጣም ቀላል ይሆንለታል። ሰይጣን የሚጠቀምበት ለተንኮል ይሁን እንጂ፥ ጥሩ የአስተዳደር ችሎታ አለው። እያንዳንዱን ተራ ምዕመን ለመንካት ከመድከም ይልቅ፥ ከላይ ያለውን መሪ በመጠቀም ብቻ የተቀረውን ሰፊ ሕዝብ ለመድረስ ይፈልጋል፤ ይሞክራልም።

ሰይጣን በአዕምሮ የላቁትን ሰዎች ይጠቀማል። በችሎታቸው ዓለም ባደነቃቸው ሰዎች ቢጠቀም፥ የሚያገኘውን ከፍተኛ ውጤት አስቀድሞ ያውቃል። በአዕምሮአቸው ተደናቂ የሆኑ ሰዎች ብዙዎችን

ማሳሳት እንደሚችሉ ያምናል። ኢየሱስም ይህን ስለሚያውቅ ነው አማኞችን «ሐሰተኞች መሲሆችና ሐሰተኞች ነብያት ይነሳሉ፤ እነርሱ ቢቻላቸውስ የእግዚአብሔር ምርጦችን እንኳ ለማሳሳት ተአምራትንና ድንቅ ነገሮችን ያሳያሉ» (የማቴ. 24፡24) በማለት ያስጠነቀቀው። ሰይጣን ሁልጊዜ ርካሽ የሆነ ዕቃውን «ጥሩ ዕቃ ነው» ብለው ሊያሻሽጡለት የሚችሉትን በአዕምሮአቸው የላቁትን ሰዎች ይመለምላል። ጳውሉስ ሰይጣን የሰውን አዕምሮ በመጠቀም ሊያደርስ የሚችለውን ጥፋት ስለሚያውቅ፥ ለቆሮንቶስ ምዕመናን «...የእናንተም አሳብ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ያላችሁን ቅንነትና ንጽሕና ትተዋላችሁ ብዬ እፈራለሁ» (2 ቆሮ. 11:3) በማለት ያስጠነቅቃቸዋል። እግዚአብሔር የላቀ አዕምሮ ሰጥቶን እንደሆነ እናመስግነው፤ ይሁን እንጂ ሰይጣን የራሱን ዓላማ መፈጸሚያ እንዳያደርገው በጣም እንጠንቀቅ።

ዓለም በአዕምሮአቸው የላቁትን ሰዎች ያመልካል። በዚህ ምክንያት ነው ብዙ ጊዜ አሳሳች ትምህርቶችና ልምምዶች ከእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች የሚፈልቁት፥ ተከታዮችንም የሚያገኙት። ከትዕቢታቸው የተነሳ ብዙዎቹ የራሳቸው አምላክ መሆን ይፈልጋሉ። ይሁን እንጂ አወዳደቃቸው ታላቅ ነው። ሰዎች ከማንኛውም ነገር ይበልጥ «ነጻነታቸውን» ይፈልጋሉ፤ ሰይጣንም ይህንን ፍላጎታቸውን አውቆ ያንን የሚያገኙበትንና እንደልባቸው መሆን የሚችሉብትን መንገድ ያመቻችላቸዋል። እውነተኛ አስተማሪዎች ክርስትና መስዋዕትነት የሚጠይቅ እንጂ «ልቅ» ሕይወት የሚኖርበት አለመሆኑን አጥብቀው ያስተምራሉ። ሰይጣን ይህን አይቶ «ለምን ቀንበር ተሸካሚዎች ያደርጓችኋል? ይህን አድርጉ፤ ያንን አታድርጉ እያሉ ለምን ሕግ ያበዛባችኋል?» ይላል። በዚህ ሳይበቃው ራስን የመካድ ሕይወት የሌለበት፥ እንደልባቸው መሆን የሚችሉብትን የሃይማኖት ዓይነት አሳይቶ ወደዚያ ይከታቸዋል። ርካሽ ዕቃ የያዘ ነጋዴ ብዙ ገዢዎች እንደሚኖሩት፥ ራስን መካድ የሌለበት፥ እንደልብ መሆን የሚቻልበት ሃይማኖትም ብዙ ተከታዮች ይኖሩታል። ለጊዜው ሥጋቸውን ደስ ማሰኘት ይቻል እንጂ መጨረሻ ላይ «እውነት» ያሸንፋል።

ሰይጣን በልዩ የአገልግሎት መስክ የተሰማሩትን ሰዎች መገልገልን ይወዳል፤ እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ብዙዎችን መሳብ እንደሚችሉ ሰይጣን ያውቃል። በብሉይ ኪዳን አንድ ከቤቴል የመጣ ነብይ ሌላውን እንዴት በመዋሸት እንዳታለለውና እግዚአብሔር አታድርግ ያለውን ነገር በማድረጉ ያ ሰው እንዴት እንደሞተ እናስታውሳለን (1 ነገሥት 13:18)። እግዚአብሔር አሳድጎን ከፍ ከፍ ሲያደርገንና ሰዎች ጆሮአቸውንና ልባቸውን ሲከፍቱልን፥ ብዙዎችን ልናሳስታቸው እንችላለንና በጣም እንጠንቀቅ።

ሰይጣን ሌሎችን ለመማረክ (ለማሳመን) ችሎታ ያላቸው የሚላቸውን ሰዎች፥ ፈተናውን ሲዘረጋ እንዲያግዙት ይጠቀምባቸዋል።

ብዙ ጊዜ በጣም ቅርባችን በሆኑ፣ ሊያባብሉን በሚችሉ ሰዎች ይጠ
ቀማል። የኢዮብን ሚስት ቀደም ሲል ሰይጣን ያልገደላት ወደ ኢዮብ
ለመጠጋት በእርሷ መጠቀም እንደሚችል ስላወቀ ነበር። «እግዚአብ
ሔርን ስደብና ሙት» አለችው። የተከለከለውን ፍሬ ለአዳም ያቀረበ
ለት ደግሞ በጣም ቅርቡ በሆነችው በሚስቱ፣ በሔዋን በኩል ነበር።
ይህን ያደረገው፣ በአዳም ሕይወት ውስጥ ሔዋን ያላትን ቅርበትና
የማግባባት ችሎታዋን ስለተረዳ ነው። ኢየሱስ የተነሳበትን ዓላማ
ከፍጻሜ እንዳያደርስ ለማደናቀፍ ሰይጣን የተጠቀመው ሩቅ የሆነውን
ሰው ሳይሆን፣ ከደቀ መዛሙርቱ መካከል በጣም ቅርቡ የነበረውን
ጴጥሮስን ነበር።

ሃዋርያው ጳውሎስ «ይህንንም የማደርገው የሰይጣንን የተንኮል
ሥራ ስለምናውቅ፣ ሰይጣን እንዳያታልለን ብዬ ነው» ይላል (2 ቆሮ.
2:11)። እኛስ የሰይጣንን የተንኮል አሠራሩንና እንዲሁም ዘዴውን
ምን ያህል እናውቅ ይሆን? ሰይጣን ጠጋ ይልና እርሱ በሚመርጥልን
አቅጣጫ ብንሄድ በሕይወታችን የሚኖረንን ምቾት፣ ነጻነትና ቁሳቁሳዊ
ነገር ምን እንደሆነ ይዘረዝርልናል። መጀመሪያ ላይ የሚያሳየን ከህግ
ውጪ ያልሆነውንና ትክክለኛውን ነው። ይሁን እንጂ ትንሽ ቆየት
ይልና ቀደም ሲል የነገረንን ሀሳብ በመለወጥ «ይህንን ደንብ ተከት
ላችሁ ብትሠሩ፣ ውጤታችሁ ያማረ ይሆናል» ይለናል። ያ ግን የእግ
ዚአብሔርን ሕግ የሚቃረን እንደሆነ እናውቃለን። «የእግዚአብሔርን
ሕግ ተከትላችሁ ማደግና መበልጸግ ካልቻላችሁ፣ እኔ በምሰጣችሁ
መመሪያ ሥሩ፣ ያኔ ታድጋላችሁ» ይለንና የእግዚአብሔርን ህግ
የሚቃረን ተግባር እንድንፈጽም ያባብለናል። ለጊዜው በሰይጣን መን
ገድ ያተረፍን ይምሰለን እንጂ፣ መጨረሻ ላይ ውጤታችን ኪሳራ
ብቻ ነው። ሰይጣን በሚሰጠን ሽልማት ብቻ ተታልለን ኃጢአት
እንድንሠራ ከተገደድን፣ መጨረሻችን እጅግ የከፋ ይሆናል። ከእርሱ
ጎን መቆማችንን ሰይጣን ካወቀና ካረጋገጠ፣ አሠራሩ እንዴት እንደ
ሆነ በማሳየት ሊያሰለጥነን ይሞክራል። ኃጢአታችንን ግንም እንዳያ
ውቅብን፣ ሌላው ቀርቶ እግዚአብሔርም እንዳያይብን እንዴት መደበቅ
እንደምንችል ያሳየናል። አዳምን ከእግዚአብሔር ሸሽቶ በዛፍ ሥር
እንዲደበቅ ነገረው። ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር መደበቅ አልቻለም።
እኛም ከእግዚአብሔር መደበቅ አያዋጣንምና አሸናፊ ሊያደርገን ወደ
ሚችለው ጌታ ተጠግተን እንኑር።

# 8

# ሰይጣንን ፊት ለፊት እንቃወመው እንጂ አንሸሸው

ቀደም ሲል እንደገለጽነው ከትግል ወይንም ከጦርነት ነጻ የሆነ እንስሳም ሆነ አውሬ አይገኝም። ሁሉም የራሱ ጠላት ስላለው፣ ሁልጊዜ በተጠንቀቅ ላይ ይገኛል። አንዳንዶቹ የጠላታቸውን አመጣጥ ከሩቅ ማሽተት፣ ማየትና ድምጻቸውን ለይተው ማወቅ ይችላሉ። አብዛኛዎቹ ከጠላቶቻቸው ጋር ፊት ለፊት ገጥመው የመታገል አቅም ስለሌላቸው፣ መከላከያቸው «ሮጦ ማምለጥ» ብቻ ነው።

ክርስቲያኖችም የራሳቸው ጠላት አላቸው። ሲበሉም፣ ሲሠሩም፣ ሲዝናኑም፣ በአጠቃላይ ሁልጊዜ ከአካባቢያቸው የማይጠፋ ጠላት አላቸው። እንደ አንዳንድ እንስሳትና አውሬ ሁልጊዜ በፍጥነት ሮጠው ማምለጥ ወይንም መሸሽ አይችሉም። ምክንያቱም ጠላታቸው ሰይጣን ከመብረቅ የበለጠ ፍጥነት ያለው እጅግ በጣም አደገኛ የሆነ ጠላት ነው። ወይንም ከጠላታቸው የሚደበቁበት የተፈጥሮ ከለል የላቸውም። ስለዚህ ክርስቲያኖች ያላቸው ምርጫ ሰይጣንን ከመሸሽ ይልቅ ፊት ለፊት መቃወም ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስም «ሰይጣንን ተቃወሙት፣ ከእናንተ ይሸሻል» በማለት ይመክረናል። ጥያቄያችን ግን "ይህንን ጠላታችንን የምንቃወመው በምን ዓይነት ሁኔታ ነው?" የሚል ነው።

## ሀ ሰይጣንን ለመቃወም የምንወስዳቸው እርምጃዎች፣

1. ሰይጣንን ለመቃወም፣ «እየጠበቅን መጸለይ» መጀመሪያ መውሰድ ያለብን እርምጃ ነው። ኢየሱስ «ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ፤ የሰው መንፈስ ሁልጊዜ ዝግጁ ነው፤ ሥጋ ግን ደካማ ነው» በማለት መመሪያ ሰጥቶናል። የሰጠንን መመሪያ «እየጠበቅን እንድንጸልይ» እንጂ፣ «እየጸለይን እንድንጠብቅ» አይደለም። ምክንያቱም ሰይጣን ወጥመድ ውስጥ ከገባን በኋላ መጠበቁ ይህን ያህል ጥቅም የለውምና ነው።

2. ብዙ አማኞች ሰይጣን «የተሸነፈ» ጠላት መሆኑን ስለሚዘነጉ፣ ሁልጊዜ በፍርሃት ውስጥ ይኖራሉ። ያዕቆብ «ሰይጣንን ተቃወሙት ከእናንተ ይሸሻል» ይላል (ያዕ.4:7)። «ተቃወሙት» ሲለን፣ ጉዳት በሌለበት ሁኔታ እንድንቃወም፣ ወይንም ራሳችንን የምንከላከልበት ዘዴ እንድንፈጥር ማለቱ አይደለም። «ጠላታችሁን ፊት ለፊት ገጥማችሁ ተዋጉት እንጂ ወደ ምሽጋችሁ ሸሽታችሁ አትግቡ» ማለቱ ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስም «..በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት» (1 ጴጥ. 5:9) ይላል። «ፊት ለፊት ግጠሙት፤ ተቃወሙት፣ በኃይል ስትቃወሙት ይሸሻል፤ አሳዳጁ ተሰዳጅ ይሆናል» ይለናል። «እምነት» ሲል በእግዚአብሔር ቃል የተገለጸውን መለኮታዊ እውነት ማለቱ አይደለም። ያ ለአማኞች ሁሉ የተሰጠ ነው። «በእምነት ጸንታችሁ» ሲል በመጽሐፍ ቅዱስ ካለው ጠቅላላ እውነት መካከል፣ በተለይ ከጠላታችን ከሰይጣን ጋር ስለምናደርገው ውጊያ መጽሐፍ ቅዱስ የሚገልጸውን «እውነትን» ማለቱ ነው። ይሄ «እውነት» ምንድነው?

**2-1.** አማኞች በሰይጣን ላይ ሙሉ ሥልጣን እንዳላቸው የሚገልጸው፣ አንደኛው «እውነት» ነው። እግዚአብሔር ለአማኞች በክርስቶስ በኩል ከጠላታቸው የበለጠ ሥልጣንና ኃይልን እንደሰጣቸው ማመን ይገባቸዋል። እግዚአብሔር ለአማኞች በክርስቶስ በኩል ከጠላታቸው የበለጠ ሥልጣንን ሰጥቷቸዋል። የይሁዳ መልዕክት ቁጥር 8-9 «እንዲሁም እነዚህ ሰዎች በሕልም እየተመሩ ሥጋቸውን ያረክሳሉ፤ የእግዚአብሔርንም ሥልጣን ይንቃሉ፤ በሰማይ ክብር ያላቸውንም ይነቅፋሉ። የመላእክት አለቃ ሚካኤል እንኳ ስለ ሙሴ አስከሬን ከዲያብሎስ ጋር በብርቱ በተከራከረ ጊዜ «እግዚአብሔር ይገሥጽህ!» አለው እንጂ የስድብ ቃል በመናገር ሊፈርድበት አልደፈረም» ይላል። የሙሴን ሬሳ ለመውሰድ በሰይጣንና በሚካኤል መካከል ከፍተኛ ግጭት በተፈጠረበት ወቅት፣

ሚካኤል ሰይጣን ያለውን ከፍተኛ ኃይል ስለሚያውቅ ብቻውን ይህንን ኃይለኛ ጠላት መቋቋም እንዳልፈለገ እናያለን። ሚካኤል በእግዚአብሔር ፊት ያልወደቀ መልአክ በመሆኑ እግዚአብሔርን በመጥራት «እግዚአብሔር ይገሥጽሕ!» አለው። ሃዋርያው ጳውሎስ «ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በመተባበራችን ከእርሱ ጋር ከሞት አስነሳን፤ ከክርስቶስም ጋር በሰማይ አስቀምጦናል» (ኤፌ. 2:6) ይላል። ጳውሎስ እዚህ ላይ ሊገልጽልን የሞከረው፥ በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ ከተቀመጠው ኢየሱስ ጋር በመሆናችን፥ በጠላታችን በዲያብሎስ ላይ ሥልጣን እንደተሰጠን ነው። መልአኩ ሚካኤል እንኳን ከሰይጣን ጋር ለነበረበት ውጊያ ያለ እግዚአብሔር እርዳታ ብቻውን መግጠም ካልደፈረ፥ እኛም ያለእግዚአብሔር እርዳታ ብቻችንን ይህንን ብርቱ ጠላታችንን መግጠም እንደማያዋጣን ማወቅ ይገባናል።

**2-2.** አማኞች ሰይጣንን እንዲያሸንፉ ከእግዚአብሔር ሥልጣንን እንደተቀበሉ የእግዚአብሔር ቃል ስለሚያረጋግጥላቸው፥ ያንን «ተስፋ» በእምነት መቀበል ይገባቸዋል። በጠላታችን በሰይጣን ላይ ድልን ለመቀዳጀት፥ እግዚአብሔርንና ቃሉን በእምነት መቀበል ይገባናል። በሰይጣን ላይ ሥልጣን እንደተሰጠን ካላመንን፥ ሰይጣንን ፈጽሞ «መቃወም» አንችልም።

**2-3.** አማኞች ሊላው በእምነት መቀበል ያለባቸው እውነት፥ ሰይጣን የተሸነፈ ጠላት እንደሆነ ነው። በ2ኛ ቆር. 2፥14 «ነገር ግን እኛን ዘወትር በክርስቶስ ድል አድራጊዎች አድርጎ ለሚመራንና መልካም መዓዛ እንዳለው ሽቶ ስለ ክርስቶስ ያለንን ዕውቀት በየሥፍራው ሁሉ እንድናዳርስ ለሚያደርገን አምላክ ምስጋና ይሁን» በማለት ጳውሎስ በክርስቶስ ውስጥ ያገኘውን ድል ይናገራል። ክርስቶስ በሞቱና በትንሣኤው ሰይጣንን ድል ስላደረገው፥ በእርሱ የሚያምኑትን አማኞች ሁሉ ድል ነሺዎች እንዳደረጋቸው የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል።

## ለ ሰይጣንን ሁልጊዜ «መቃወም» የአማኞች ተግባር ነው

ከሰይጣን ጋር የሚኖረን ጦርነት፥ ማንም በእኛ ምትክ ሆኖ ሊዋጋልን የማይችለው የራሳችን ጦርነት ነው። ስለዚህ ሰይጣንን በሙሉ ልብና በቆራጥነት ልንቃወመው ይገባል። ጳውሎስ ስለምንዋጋበት መሣሪያ

ሲገልጽ፣ «ምንም እንኳ በዓለም ብንኖር የምንዋጋው እንደ ዓለም ሰዎች አይደለም። የጦር መሣሪያዎቻችንም ምሽግ ለማፍረስ የሚያስ ችል መለኮታዊ ኃይል ያላቸው ናቸው እንጂ እንደ ዓለም የጦር መሣሪያዎች አይደሉም» ይላል (2 ቆሮ. 10:3-4)።

እግዚአብሔር ሰይጣንን «ተቃወሙ» ሲለን «ተዋጉ» ማለቱ ይሆን? ምድራዊ ጦር በጠላት ጦር ሲጠቃ፣ አዛዡ «ተቃወሙ» (resist) የሚል ትዕዛዝ ለወታደሮቹ ሲሰጥ፣ «ባላችሁ መሣሪያ ሁሉ በመጠቀም የመጣውን የጠላት ጦር በኃይልና በቆራጥነት በመዋጋት ወደ መጣበት መልሱት» ማለቱ ነው። እዚህ ላይ ሰይጣን እንዳያሳስተን እኔና እናንተ በጣም እንጠንቀቅ። «ተቃወሙት» ሲል «ተዋጉት» ማለት አይደለም በማለት እጅና እግራችንን አጣምረን ሲያጠቃን ቁጭ ብለን እንዳናየው። ጳውሎስ ውጊያችን (ትግላችን) ከማን ጋር እንደሆነ በግልጽ ይናገራል (ኤፌ. 6:12)። አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ «መጋደላችን» የሚለውን ቃል፣ የግሪኩ ትርጉም «ፔሌ» ይለዋል። ቀጥተኛ ትርጉ ሙም «መታገል» ወይንም «ትግል» ማለት ነው። «ትግል» የሚ ለውን ትርጉም ከተጠቀምን፣ ከሰይጣን ጋር የሚኖረን ጦርነት ምን ዓይነት እንደሆነ የበለጠ መረዳት እንችላለን።

**ለ 1** ከሰይጣን ጋር ያለን ትግል የከረረ ነው። «ትግል» በአውሮፓና በአሜሪካ ብዙ ስፖርተኞች የሚካፈሉበት የስፖርት ዓይነት ነው። ጳውሎስ ከሰይጣን ጋር ስለሚኖረን ትግል ሲገልጽ «የስፖርት ዓይነቱን» ትግል ማለቱ ሳይሆን፣ ክርስቲያኖች ከጠላታቸው ከሰ ይጣን ጋር የሚያደርጉትን ማቆሚያ የሌለውና ብዙ ደም መፋሰስ ያለበትን ጦርነት ማለቱ ነው። ይህን ትግል የከረረና አስፈሪ እንዲሆን የሚያደርገው፣ ትግሉ ከሰይጣን ጋር በነፍስ ወከፍ (በግል) የሚደረግ ትግል በመሆኑ ነው። «ትግል» እንደ ሌሎች የስፖርት ዓይነቶች፣ ለምሳሌ እንደ እግር ኳስ፣ የቅርጫት ኳስ በብዙ ሰዎች ወይንም በቡድን-በቡድን ተከፋፍሎ የሚደረግ ሳይሆን፣ በነጠላ ማለትም በሁለት ሰዎች መካከል የሚ ደረግ የስፖርት ውድድር ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን በእስራ ኤላውያንና በፍልስጤማውያን መካከል በነበረው ጦርነት፣ ዳዊትና ጎልያድ ሁለቱ ብቻ ፊት ለፊት እንደተጋጠሙ፣ ታጋዮችም ሁለት ሆነው ወደ መድረኩ ወጥተው የሚያደርጉት የትግል ውድ ድር ነው። ታጋዮቹ ዋና ጥረታቸው አንዱ ሌላውን በኃይልና በጥበብ ተጭኖ ወደ መሬት ለመጣል ነው። ይሄን ዓይነቱ መጋደል፣ ከሩቅ ሆነው እንደሚታኮሱት ወታደሮች ሳይሆን፣ የከረረና ረጅም ጊዜ የሚፈጅ የፊት ለፊት ጦርነት ነው። ሩቅ በሩቅ ሆነው በጦር መሣሪያ የሚታኮሱ ወታደሮች ያለማ ቋረጥ አይታኮሱም። ጦርነቱ በረድ የሚልበትና ዕረፍት የሚያ ገኙበት ጊዜ አለ። በዚህ ዓይነት ጦርነት ተሳታፊ የሚሆኑ

ወታደሮች ዓላማቸው ጠቅላላ ጦሩን ለማሸነፍ እንጂ የሚያነጣጥሩት አንዱ ወታደር ላይ ብቻ ስላልሆነ፣ አልፎ አልፎ ወታደሮቹ ምንም ዓይነት ጉዳት ሳይደርስባቸው ጦርነቱ ሊያልቅ ይችላል። «ትግል» ግን እንዲህ ዓይነት አይደለም። በሁለት ሰዎች መካከል የከረረ ጦርነት ሲሆን፣ ከሁለቱ አንዳቸው አሸናፊ ሆነው ካልወጡ ትግሉ አያበቃም።

ወደድንም ጠላንም አማኞች እያንዳንዳችን ሰይጣንን ለመታገል ወደ ትግል መድረኩ የግድ መውጣት አለብን። ሰይጣን በቅዱሳን ሠራዊት ላይ በአጠቃላይ አደጋ ለመጣል የሚወድ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ በነፍስ ወከፍ፣ እያንዳንዱን አማኝ ይዋጋል። እግዚአብሔር በግል ከእያንዳንዱ ቅዱሳን ልጆቹ ጋር መገናኘት እንደሚፈልገው ሁሉ፣ ሰይጣንም እያንዳንዱን አማኝ ለብቻው መግጠም ይፈልጋል። «ሰይጣን የሚዋጋው በአጠቃላይ ቅዱሳን ሠራዊትን እንጂ እኔን በግሌ አይነካኝም» ብለን ካሰብን፣ ሰይጣን በእኛ ላይ ድል እንዲያገኝ ዕድል መስጠታችን መሆኑን መርሳት የለብንም። «ሰይጣን እኔን በግሌ ይጠላኛል፣ ይከሰኛል፣ ይፈትነኛል» ካላለን፣ እግዚአብሔር እንደ አስፈላጊነቱ ሊሰጠን ያዘጋጀውን ኃይልና መጽናናት እንዳንቀበል ራሳችንን እንነፍጋለን። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር እንደሚወደን፣ ይቅርታን እንደሚሰጠንና እንደሚጠነቀቅልን ማየት አንችልም። ስለዚህ ያለን መንፈሳዊ ትግል ከሰይጣን ጋር በተናጠል የምናደርገው ትግል መሆኑን አንርሳ።

ለ ፪ ትግላችን በሩቅ የሚሆን ሳይሆን የተቀራረበ ውጊያ ያለበት ነው። ምድራዊ ወታደሮች ከጠላታቸው ጋር ተራርቀው በመቆም ወይንም በመደበቅ ይታኮሳሉ። ከሰይጣን ጋር የሚኖረን ጦርነት ግን በሩቁ የምናካሂደው ሳይሆን፣ ተቀራርበን የምንዋጋው ነው። ሰይጣን ወደ እኛ በጣም ተጠግቶ፣ ደካማውንና ኃጢአት ለመሥራት ዝንባሌ ያለውን ሥጋችንን በመያዝ ሊጥለን ይታገለናል። ይህ ትግል የጥቂቶች ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፍ ነው። ጳውሎስ «ትግላችን» ሲል፣ ትግሉ ራሱንም የሚጨምር መሆኑን ሲገልጽ ነው። የሰይጣን «ትግል» ከተወሰኑ አማኞች ጋር ብቻ አይደለም። ሰይጣን ማንንም «ተራ አማኝ ነው»፣ ብሎ አይንቀውም። ብዙ ዘመን በክርስትና ሕይወት ውስጥ የቆየውንም «ብርቱ ክርስቲያን ነው፧ እኔ አልችለውም» በማለት አይፈራም፧ ሁሉንም ሳይሰለችና ተስፋ ሳይቆርጥ ይዋጋል። ስለዚህ «እኔ ከትግል ነጻ ነኝ» ብሎ ተዝናንቶ የሚቀመጥ እውነተኛ የሆነ አማኝ ሊኖር አይችልም።

**ለ 3** ከሰይጣን ጋር የምንታገለው ትግል፣ በሕይወት እስካለን ድረስ የማያቋርጥ (የማይቆም) ትግል ነው። አማኝ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እያደገ ሲመጣ፣ በዚያው መጠን ከሰይጣን ጋር የሚኖረውም ትግል እየከረረ ይመጣል። አማኝ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንደገና ከተወለደበት፣ ዓይኑን ወደ ሰማያዊ ቤቱ ማቅናት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የምድር ዘመኑን እስከሚጨርስበት ጊዜ ድረስ ከሰይጣን፣ ከኃጢአትና ከሥጋ ጋር ያለው ትግሉ ይቀጥላል። አንዳንድ አማኞች «እንዲህ ዓይነት አካባቢ ብኖር ኖሮ፣ ወይንም ይህን የመሰለ አገልግሎት ቢኖረኝ ኖሮ ሰይጣን አይዋጋኝም (አይታገለኝም) ነበር» ብለው ያስባሉ። ቦታ መለወጣችን፣ ሰይጣን የሚፈትንበትን መንገድና ብልሃት እንዲለውጥ ያደርገዋል እንጂ፣ እኛን ከትግል ፍጹም ነጻ አያደርገንም። ከሰይጣን ማንም ሸሽቶ ማምለጥ አይችልም። በሄድንበት ሥፍራ ሁሉ ይከተለናል። ሁኔታው ሲለወጥ፣ ሰይጣንም በዚያው መጠን የመፈተኛ ዘዴውን ይለውጣል እንጂ ትግሉን ያቆማል ማለት አይደለም። አሮጌው ተፈጥሮአችን እስካለ ድረስ የሕይወት በራችንን ከማንኳኳት ወደ ኋላ አይልም። ባጋጠመው ዕድል ሁሉ ይዋጋናል። ተንበርክከን ስንጸልይ እንኳን አይተወንም፤ ሀሳባችን እንዳይሰበሰብ ብዙ ሁካታን በውጪና በውስጥ ለማስነሳት ይጥራል። ሙሉ በሙሉ ከመጸለይ ሊያግደን (ሊከለክለን) ባይችልም፣ ለጊዜውም ቢሆን ለማደናቀፍ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል።

**ለ 1** በትግላችን ጉዳት (ጥቃት) የሚደርስብን እኛ ደካማውን ሥጋችንን ይዘን ስለምንዋጋ ነው። ታዲያ ሥጋችን ኃይል ካገኘ፣ ለምሳሌ ፍትወት በሕይወታችን ሙሉ ሥልጣን ካገኘ፣ በምናካሂደው መንፈሳዊ ትግል ውስጥ ደካማ ስለሚያደርገን፣ ጥቃት እንዲደርስብን እንሆናለን። ሰይጣንን ለመዋጋት ደካማ የሚያደርገን የምንዋጋው በደካማ ሥጋችን በመሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ኃጢአተኛ በሆነው ተፈጥሮአችን በመሆኑ ጭምር ነው። በዚህ ምክንያት አማኝ መሆን የሚፈልገውን መሆን ስለሚቸገር፣ ከትግልና ከመንፈሳዊ አገልግሎቱ ለጊዜውም ቢሆን ገለል እንዲል ይሆናል። ለዚህ ነው ሃዋርያው ጳውሎስ «ወደ እናንተ ለመምጣት እስቤ ሰይጣን ከለከለኝ» ብሎ ያለው።

## ትክክል ያልሆነ «ትግል» አንታገል

ከሰይጣን ጋር ስንታገል፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት መታገላችን ነው። ሰይጣንን አንታገልም ስንል በተዘዋዋሪ መንገድ እግዚአብሔርን መታገላችን ይሆናል። በሌላ ጊዜ ፊት ለፊት ከእግዚአብሔር ጋር በግልጽ

የምንታገልበት ጊዜ አለ። ኢሳያስ «ከሠሪው ጋር ለሚከራከር (ለሚታገል) ወዮለት!» (ኢሳ. 45:9) በማለት ከእግዚአብሔር ጋር እንዳንታገል ያስጠነቅቀናል። ደካማው ተፈጥሮአችን ታግለን ማሸነፍ ከማንችለው ኃይል ጋር እንድንታገል ስለሚገፋን ትክክል ያልሆነ ትግል እንዳንገጥም በብርቱ እንጠንቀቅ።

**ሐ 1** ወደ ጥፋት እየተጣደፍን ስንሄድ እግዚአብሔር ሊመልሰን ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። ሰዎችን ወደ ሞት እየነዳ ከሚወስዱቸው ምክንያቶች መካከል አንደኛውና ትልቁ የሥጋ ፍትወት ነው። መንፈስ ቅዱስም ያንን ከሕይወታችን አውጥቶ ለመጣልና በምትኩ በክርስቶስ ጸጋና በዘለዓለማዊ ሕይወት ሊሞላን ይታገላል። ይሁን እንጂ ለመንፈስ ቅዱስ አንታዘዝም ስንል፣ መንፈስ ቅዱስን መታገላችን መሆኑን ብዙዎቻችን የተገነዘብነው አይመስለኝም። እስጢፋኖስ የእግዚአብሔርን መንፈስ ይታገሉ የነበሩትን እስራኤላውያንን «እናንተ አንገታችሁ የደነደነ፣ እልኸኞች! ልባችሁ የተደፈነ፣ ጆሮ አችሁም የማይሰማ! እናንተም ልክ እንደ አባቶቻችሁ ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ» (የሐዋ. 7፡51) አላቸው።

**ሐ 2** የእግዚአብሔርን ሕግ ችላ ብለን በራሳችን ሕግ ስንመራ፣ እግዚአብሔርን መታገላችን ይሆናል። በጎ የሚያስብልንን እግዚአብሔርን በመታገል ፈንታ፣ «ኃጢአትን» እንታገል። የምንታገለውም እርሱ በሚሰጠን ሕግና ደንብ መሠረት እንዲሆን ይፈልጋል። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈለት ደብዳቤ ውስጥ «በሩጫ የሚወዳደር ሰው በደንቡ መሠረት ካልተወዳደረ፣ የአሸናፊነት ሽልማት አያገኝም» (2 ጢሞ. 2:5) ይላል። የክርስቶስን የጦር ሠራዊት ትተን የራሳችንን ጦርነት እያካያሄድን እንደሆን ራሳችንን መመርመር ይገባናል። አንዳንዶቻችን ከአንዱ «ኃጢአት» ጋር ብንታገልም፣ በሌላ በኩል ግን ሌላውን የምንወደውን «ኃጢአት» የምናቅፍ እንሆናለን። ለምሳሌ ያስቀየመንን ሰው የመበቀል ስሜት በውስጣችን ሲሰማን፣ ሰይጣን ሁኔታውን ተጠቅሞ «ቁጣህን አታሳይ! ይሁን እንጂ ይቅርታን አትስጥ» ይለናል። ኃጢአትን ሁሉ ተቃውሞ፣ አንዲትም ኃጢአት ብትሆን በውስጡ የሚሸሽግ አማኝ፣ በትግሉ አሸናፊ መሆን አይችልም። አንዳንዶች «የሥጋ ፍትወት ባሪያ እንሆናለን» ብለው በመፍራት ብቻ ለጊዜው ከሥጋዊ ፍትወት ይቆጠባሉ። «ኃጢአትን» በከፊል ይታገሉ እንጂ፣ ሙሉ በሙሉ አይጠሉትም። ስለሆነም በሙሉ ልባቸው አይታገሉትም። በውስጣቸው ለኃጢአት ያላቸው ፍቅር ካልቆመ፣ እሳቱ ፈጽሞ አይጠፋም። ጥያቄው ይሄ የኃጢአት ፍቅር እንዴት ሊጠፋ ይችላል? የሚለው ነው። መልሱ «በሌላ ፍቅር የተተካ እንደሆን» ብቻ ነው። ለክርስቶስ ፍቅር ሲኖረን፣ ኃጢአትን እንድንጠላ ያደርገናል። ይህ ካልሆነ፣ በኃጢአት ላይ አሸናፊዎች መሆን አንችልም።

## ሠ ሰይጣንን እንዴት እንታገል?

**ሠ.1** እግዚአብሔር ጠላታችንን ለማጥቃትም ሆነ ለመከላከል የምንችልበትን ኃይል ለመስጠት ዝግጁ ነው። ይሁን እንጂ እስከንጠራው ድረስ ይጠብቃል። ንጉሥ ሳኦል የእስራኤልን ጦር ያለእግዚአብሔር ዕርዳታ ይዞ በመውጣት ታላቅ መሸነፍ እንደደረሰበት፣ እኛም እግዚአብሔርን ሳንይዝ ከሰይጣን ጋር ለመግጠም ብንሞክር ታላቅ መሸነፍ እንደሚደርስብን እንርሳ። ያዕቆብ በእርሱ ላይ የተቆጣውን ወንድሙን ፊት ለፊት ከመገናኘቱ በፊት እግዚአብሔር እንዲረዳው መጮሁ ትልቅ ጥበብ ነው። እግዚአብሔርን ከጎናችን ስናሰልፍ፣ በራችን ለጠላት የተዘጋ ስለሚሆን፣ የትኛውም ዓይነት ጠላት ተደብቆ ሊያጠቃን አይችልም። እንዲያውም እስኪ ደንቀን ድረስ በእግራችን ሥር ይወድቃል። ዳዊት ልጁ አቤሴሎም ባመጸበትና አኪጦፌል ከአቤሴሎም ጋር በአመጽ በተባበረ ጊዜ፣ «እግዚአብሔር ሆይ! የአኪጦፌልን ምክር ወደ ከንቱነት እንድትለውጥበት እለምንሃለሁ» (2 ሳሙ. 15:31) ሲል ጸለየ። እግዚአብሔርም የዳዊትን ጸሎት ሰምቶ ጠላቱን ተበቀለለት። እኛም ሰይጣንን ከመታገላችን በፊት ሁልጊዜ በጸሎት ጌታን ከጎናችን እንዲሰለፍ እንጠይቀው።

**ሠ.2** ሐዋርያው ያዕቆብ «ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙት» (ያዕቆብ 4:7) ሲለን፣ ዲያብሎስን ከመቃወማችን በፊት በቅድሚያ ራሳችንን ለእግዚአብሔር ማስገዛት እንዳለብን ይነግረናል። ክርስቲያኖች ሰይጣንን የሚቃወሙት በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ ነው። በሥጋው ሰይጣንን ማባረር የሚችል አንድም ሰው የለም። ሰይጣን የሥጋችንን ደካማነት ስለሚያውቅ፣ በሥጋችን ልንዋጋው ብንሄድበት በመፍራት ፈንታ ይስቅብናል። ሰይጣን ሥጋን አይፈራም፤ እንዲያውም ይወደዋል፤ ይጠቀምበታል፤ ውስጡም ይኖራል። ሰይጣን በሥጋ ያለውን እኛነታችንን ምንጊዜም ቢሆን አይፈራም። እንዲያውም የሥጋ ድካማችንን ተጠቅሞ ወደፈለገው አቅጣጫ ሊመራን ይችላል። ክርስቶስን ሳንይዝ ልንዋጋው ስንሞክር ሁልጊዜ ደስ ይለዋል። ያለ ክርስቶስ ሰይጣንን ለመታገል መሞከር ማለት «ጉንዳን» በኃይል የሚበረውን ባቡር ገልብጣ ለመጣል እንደምትሞክረው ዓይነት ይሆናል።

**ሠ.3** ራስን ለእግዚአብሔር ማስገዛት ትህትናን ይጠይቃል። አማኝ ራሱን በህያው እግዚአብሔር ፊት ሲያኖር፣ ስለ ኃጢአቱ ሲል እግዚአብሔር ከፍተኛ ዋጋ የከፈለለት መሆኑን በመረዳት የተሰበረ ልብ ይዞ መሆን አለበት። ራስን ለእግዚአብሔር ማስገዛት ማለት ራስን በእርሱ ቁጥጥር ሥር ማድረግ ማለት ነው። በዚህ ዓይነት ሰይጣንን የምንዋጋው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንጂ በራሳችን ኃይል

አይደለም። ያለ እግዚአብሔር ምንም ኃይልና ጉልበት እንደሌለን አውቀን ራሳችንን ለእርሱ ሳናስገዛ ሰይጣንን እንቃወማለን (እንታገላለን) ማለት፥ መሸነፍን ወደ ህይወታችን መጋበዝ ይሆናል። ይሁን እንጂ አንዳንዶች ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ያስገዙ ቢሆኑም፥ ሰይጣንን ግን የማይቃወሙ አሉ። ስለ ጠላታቸው ስለ ሰይጣን በቂ ዕውቀት ስለሌላቸው፥ ጠላታቸው መሆኑን አያምኑም፤ ከእርሱም ጋር ምንም ዓይነት ጉዳይ ያላቸው አይመስላቸውም። በዚህ ክፉ ዓለም ውስጥ ስለ ሰይጣን አለማወቅ፥ ራስን አደጋ ላይ መጣል ይሆናል። «ሰይጣንን ተቃወሙት ከእናንተ ይሸሻል» ስለሚል፥ በግል ካልተቃወምነው ለእግዚአብሔር ራሳችንን ማስገዛታችን ብቻ ሰይጣንን እንዲሸሽ አያደርገውም። በሌላ በኩል ደግሞ ራሳችንን ለእግዚአብሔር ሳናስገዛ ሰይጣንን ብንቃወም፥ አሸናፊዎች መሆን አንችልም።

ክርስቶስ በሰይጣን ላይ ስለተቀዳጀው ድል ጳውሎስ ሲናገር «ይከሰንና ይቃወመን የነበረውን የዕዳ ጽሁፍ ደመሰሰ፤ በመስቀል ላይ ቸንከሮም ከእኛ ወዲያ አስወገደው። አለቆችንና ባለሥልጣኖችን በመስቀሉ ላይ ቸንከሮም ከእኛ ወዲያ አስወገደው። አለቆችንና ባለሥልጣኖችን በመስቀሉ ድል ነስቶ ትጥቃቸውን ካስፈታ በኋላ ምርኮኞች ሆነው በይፋ እንዲታዩ አደረጋቸው» (ቆላስይስ 2:14-15) ይላል። ይህ ጥቅስ «ኃይልና ሥልጣን አለኝ» ይል የነበረውን ሰይጣንን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ድል ነስቶ «ኃይሉንና ሥልጣኑን» እንደወሰደበት ያሳያል።

አማኞች ከክርስቶስ ጋር በመተባበራቸው፥ ለክርስቶስ የተሰጠው ኃይልና ሥልጣን ለእነርሱም እንደተሰጠ ማወቅ ይገባቸዋል። አማኞች በግላቸው (ለብቻቸው) ሰይጣንን ማሸነፍ አይችሉም። ሰው በአፈጣጠሩ ከመላእክት ጥቂት ዝቅ ያለ በመሆኑ፥ በመላእክት ላይ ሥልጣንና ኃይል የለውም፤ በመላእክት ላይ ብቻ ሳይሆን፥ በወደቁት መላእክት፥ ማለትም በእርኩሳን መናፍስትም ላይ በራሱ ኃይልና ሥልጣን የለውም። በእርኩሳን መናፍስት ላይ ሥልጣን ሊኖረው የሚችለው፥ ከፈጣሪው ማለትም ከእግዚአብሔር ጋር በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የተቀራረበ አንድነት ያለው እንደሆነ ብቻ ነው። አማኝ በራሱ ኃይል ብቻ ከታመነ፥ በሰይጣን መሸነፍ እንጂ ማሸነፍ እንደማይችል ግልጽ ነው።

**መ 1** ሰይጣንን የምናሸንፍበት መንገድ «ከእርሱ ሸሽቶ ማምለጥ ነው» ብሎ እግዚአብሔር መመሪያ አልሰጠንም። ምክንያቱም መንፈስ የሆነውንና እንዲሁም በፍጥነቱ ተወዳዳሪ የሌለውን ሰይጣንን ሮጦ መቅደም ወይንም ማምለጥ ማንም እንደማይችል ስለሚያውቅ ነው። እግዚአብሔር የሰጠን መመሪያ ግን «ሰይጣንን ተቃወሙት» የሚለውን ነው። ኢየሱስ በሰይጣን በተፈተነ ጊዜ

ጫካ ውስጥ ወይንም ጉድጓድ ውስጥ አልተደበቀም፣ ነገር ግን ፊት
ለፊት ቆሞ ጠበቀው፣ በኃይልም ተሞልቶ ገሰጸው። እኛም «በእም
ነት ጸንቶ ከመቋቋም» በስተቀር ሰይጣንን የምናሸንፍበት ሌላ
መንገድ የለንም። ሰይጣን «እንደሚያገሳ አንበሳ በዙሪያችሁ ያደባል»
የሚለውን ቃል ስንሰማ፣ ሰይጣን ፈጽሞ የማይፈራ ይመስለናል።
ይሁን እንጂ ሰይጣን በተፈጥሮው በጣም ፈሪ ነው። የአውሬዎች
ሁሉ ንጉሥ የሚባለው አንበሳም በተፈጥሮው ፍጹም ፍርሃት የሌ
ለበት ይምሰል እንጂ፣ ከፍርሃት ነጻ አይደለም። አንበሳ አደኖ
ያገኘውን እንስሳም ሆነ አውሬ ከገደለ በኋላ በጣም እንደሚያጓራ
የታወቀ ነው። ይህን የሚያደርገው እርሱ አደኖ ያገኘውን ሌላው
መጥቶ ይነጥቀኛል ብሎ ስለሚፈራ ነው። ስለዚህ «የራሳችሁን ፈልጉ
እንጂ ከእኔ ለመንጠቅ አትሞክሩ» የሚለውን መልዕክቱን ለሌሎች
በማጓራት ያስተላልፋል። ሰይጣንም ማጓራቱ የድፍረት ሳይሆን የፍር
ሃት ምልክት መሆኑን እናያለን። በዚህ ዓይነት ሰይጣን ፈጽሞ
ፍርሃት የሌለበት መስሎ እንዲገባን በማድረግ ብዙዎቻችንን ያሞ
ኘናል። ያዕቆብ ግን «በእምነት ጸንተን ከተቃወምነው ፈርቶ እንደ
ሚሸሽ» ይነግረናል። ሰይጣንን የምንቃወምበትም ኃይል ከክርስቶስ
የተቀበልነው እንጂ ከራሳችን በመነጨ ኃይል እንዳልሆነ መዘንጋት
የለብንም።

ከሰይጣን ጋር በሚኖረን መንፈሳዊ ትግል ላይ እግዚአብሔር
በሚሰጠን ኃይል ካልተደገፍን፣ ሕይወታችን በፍርሃት የተሞላ እንደ
ሚሆን ግልጽ ነው። በመንገዳችን ላይ ሰይጣን የፈተና ወጥመዱን
በመዘርጋት ሲዋጋን፣ እግዚአብሔር በሰጠን ተስፋ ላይ ጸንተን
በመቆም፣ የሚያዋጋንን ሰይጣን «ኃይልና ሥልጣን ባለው በክርስ
ቶስ ስም እቃወምሃለሁ» እንበለው እንጂ ለመሸሽ አንሞክር። ከሰ
ይጣን እየሸሸን የራሳችንን የሩጫ ድምጽ ከመስማት ይልቅ፣ ፊት
ለፊት ተቃውመነው ሰይጣን በፍርሃት ደንብሮ ሲሸሽ የሚያሰማውን
የመርበድበድ ድምጽ እንስማ። አማኞች ኃይልና ሥልጣን የተሰጠን
የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆንን፣ በእምነት ጸንተን በመቆም ሰይጣ
ንን እንድናባርር ይጠበቅብናል። የማይሠራ መሣሪያ አስይዞ እን
ድንሸነፍ ወደ ጠላት ክልል ይወስደናል ብለን እግዚአብሔርን አን
ጠራጠረው። «ሰይጣንን ተቃወሙት ከእናንተ ይሸሻል» ሲለን
ውሸት ሳይሆን እውነት ነው። በዚህ ዓይነት «አድርጉ» የሚለንን
ማድረግ ብንችል፣ ማሸነፍ እንጂ መሸነፍ አይደርስብንም።

# 9

# የጦር መሣሪያ ሳንለብስ ሰይጣንን መዋጋት አንችልም

ለእውነተኛው መንፈሳዊ ጦርነት ብቁ የሚያደርገን የእኛ ውስን የሆነው ጉልበታችን ሳይሆን፥ ሁሉን ማድረግ በሚችለው እግዚአብሔር ላይ መታመናችን ብቻ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ «የዲያብሎስን የተንኮል ሥራ መቃወም እንድትችሉ የእግዚአብሐርን የጦር መሣሪያ በሙሉ ልበሱ» (ኤፌ. 6:1) በማለት ይመክረናል። «የእግዚአብሔርን የጦር መሣሪያ መልበስ» ማለት ኃይሉን በግል ሕይወታችን መለማመድ ማለት ሲሆን፥ ለዚህም መጀመሪያ በእውነተኛ የልብ መለወጥ ክርስቶስን ወደ ግል ሕይወታችን ማስገባት ይኖርብናል። እውነተኛ የልብ መለወጥ ሳይኖረን «በእግዚአብሐር ላይ ሙሉ እምነትና ትምክህት አለኝ» ማለት አንችልም። የልብ መለወጥ ከሌለን ደግሞ የእግዚአብ ሔርን የጦር መሣሪያ መልበስ አንችልም። የእግዚአብሔርን የጦር መሣሪያ በሙሉ ካልለበስን ደግሞ ወደ ጦር ሜዳ ገብተን ሰይጣንን በቀላሉ ማሸነፍ አንችልም። ጠላታችን ራቁታችንን መሆናችንና፥ እን ዲሁም ምንም ዓይነት የጦር መሣሪያ በእጃችን አለመያዛችንን አይቶ ፉከራችን ሳያስደነግጠው በቀላሉ ተዋግቶ ያሸንፈናል።

ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ በሚመለከት ሀሳብ ላይ ሁለት ነገር እንድናደርግ ይመክረናል። አንደኛው፥ «የእ ግዚአብሐርን የጦር መሣሪያ» እንድንለብስ ሲሆን፥ ሁለተኛው፥ ሰይጣንን

«እንድንቃወመው» ነው። ለጦርነት ከመሄዳችን በፊት እንደሚገባ መልበስ ያለብን የጦር መሣሪያ ምን ዓይነት እንደሆነ ከዚህ ቀጥሎ በጥንቃቄ እንመረምራለን። ቀደም ሲል ግን ይህን «የጦር መሣሪያ» የማይልብሱ ሰዎች ምን ዓይነት የሕይወት አቋም እንደሚኖራቸው እንመለከታለን።

ክርስቶስን ያልለበሰ ሰው ፀጋ የራቀውና ፍጹም የተራቆተ ሰው ነው። እግዚአብሔር አዳምን ፈጥሮ በምድር ላይ ሲያኖረው፥ ሙሉ የፀጋ ልብሱን አልብሶት ነው። ይሁን እንጂ አዳምና ሄዋን «አታድርጉ» የተባሉትን ካደረጉ በኋላ፥ ሰይጣን የለበሱትን የጸጋ ልብስ ሙሉ በሙሉ ስለገፈፈ «ራቁታቸውን መሆናቸውን አወቁ» (ዘፍ. 3:7)። ሰይጣን የለበሱትን የጸጋ ልብስ ከላያቸው ላይ ገፎ ስለወሰደባቸው፥ ለኃጢአት ፍጹም የተጋለጡና ደካማ ፍጥረቶች ሆኑ። ልባቸውም በኃጢአት ምክንያት የደነደነ በመሆኑ እግዚአብሔርን መበደላቸውን ተገንዝበው ምህረቱንና ይቅርታውን በመለመን ፈንታ እርስ በርሳቸው ይካሰሱ ነበር። እግዚአብሔር እንደገና በልጁ ደም እስከገዛው ድረስ፥ ሰይጣን የሰውን ልጅ ራቁትነቱን በመጠቀም፥ ወደ ሕይወቱ ዘልቆ በመግባት የግል ባሪያው ማድረጉን ቀጠለ። አሁንም ቢሆን ሰው የልቡን በር ከፍቶ ሰይጣንን በፈቃዱ ወደ ሕይወቱ ካስገባው፥ ሰይጣን በተከፈተለት በር በመግባት የዚያ ሰው «ንጉሥ ነኝ» ብሎ ዘፋኑን ዘርግቶ ይቀመጣል። ከእግዚአብሔር ጋር የሚያጋጩትንና እንዲሁም ዘለዓለማዊ ሞት ላይ ሊጥሉት የሚችሉትን አደገኛ የሆኑ ኃጢአቶችንም በዚያ ሰው ሕይወት ውስጥ መዝራት ይጀምራል። ስለዚህ ከሰይጣን ጥቃት ለመዳን ክርስቶስን ወደ ሕይወታችን ማስገባትና እንዲሁም የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ መልበስ ይገባናል።

ዕቃ ጦር አለመልበስ ማለት፥ ያለእግዚአብሔር መኖር ማለት ነው። ያለእግዚአብሔር ከሆንን፥ የእግዚአብሔር ልጆች አይደለንም ማለት ነው። የእርሱ ካልሆንን፥ «በዓየር ያሉትን የመናፍስት ኃይሎች የሚገዛውን የምንከተል» (ኤፌ. 2:2) መሆናችን ነው። ያለእግዚአብሔር ከሆንን፥ በሕይወታችን የሚያጋጥመንን ትግል ሁሉ ለብቻችን ተዋግተን ማሸነፍ አለብን። ያ ደግሞ ከእኛ አቅም በላይ ነው። የእርሱ ከሆንን ግን በማንኛውም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ብንሆን፥ ጠላታችንን የምናሸንፍበትን እግዚአብሔር ኃይሉን ይሰጠናል። ሰይጣንም ያለእግዚአብሔር ፈቃድ ሊነካን አይችልም።

ያለእግዚአብሔር እርዳታ፥ በርኩሳን ሠራዊትና እንዲሁም ነፍስንና መንፈስን በሚዋጉ ኃጢአቶች መከበብ ምን ያህል የሚያስፈራ ነው? እንዲህ ዓይነቱ ሰው የሚረዳውና እንዲሁም የሚጠራው አምላክ ስለሌለው፥ ሰይጣን በቀላሉ ቦጫጭቆ ይጥለዋል። ምንም ዓይነት ጠንካራና ደፋር ሰው ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ከተወው ወይንም ከሌለው፥ የነበረውን ጉልበትና ድፍረት ሁሉ ያጣል። «ደካማ ወይንም ጥቃትን

ናቸው» የሚባሉት ነገሮች እንኳን ከተደላደለበት ሥፍራ ፈንቅለው ሊጥ ሉት ይችላሉ። ኢያሱና ካሌብ «...እዚያም የሚኖሩትን ሕዝቦች አትፍ ሯቸው፤ እኛ በቀላሉ በጦርነት ድል እንነሣቸዋለን፤ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው፤ እነርሱን ይጠብቁ የነበሩትንም አማልክት ድል ነሥቷቸዋል፤ ስለዚህ ፈጽሞ አትፍሯቸው» (ዘሁ. 14:9) በማለት እሲኪያረጋግጥቸው ድረስ፥ እስራኤላውያን በከነአ ናውያን ፊት በፍርሃት ተሞልተው ነበር። ልክ እንደዚህ እግዚአብሔርን ተገኑ ያላደረገ ሰው ፥ ሕይወቱ በፍርሃት የተሞላ ይሆናል።

በጦርነት ወቅት «የጦር ዕቃ» ሳይለብስ ወደ ጦር ሜዳ የሚ ሄድ፥ በጦርነት ውስጥ ያለው አደጋ ምን እንደሆነ ያልተረዳ ሞኝ ሰው ነው። «ክርስቲያን ነኝ» ብሉ ክርስቶስን ሳይለብስ ለጦርነት የሚወጣ ሰው፥ በብርሃን ሳይሆን በጨለማ ውስጥ ሆኖ የሚዋጋ መሆኑን ማወቅ አለበት። ጳውሎስ «ቀደም ሲል በጨለማ ትመላለሱ ነበር፤ አሁን ግን በጌታ ውስጥ ብርሃንን አግኝታችኋል» ይላል (ኤፌ. 5:8)። ክርስቲያኖች እንደ ብርሃን ልጆች እግዚአብሔር የሰጠን አንዳ ንድ ተስፋዎችና እውነቶች በግልጽ የማይታዩን ጊዜ ይኑር እንጂ፥ ክርስቶስን የማያውቁ ሰዎች የሌላቸው መንፈሳዊ ዓይን፥ እኛ አለን። በክርስቶስ ያልተለወጠ ሰው ሰይጣንን መቃወም አይችልም፤ ክርስቲ ያን ግን በፈተና ምርኮኛ ሆኖ በሰይጣን ቢወሰድ እንኳን፥ ሰይጣንን ታግሎ ነፍሱን ከጠላት እጅ ማስለቀቅ እንደሚችል ያውቃል።

የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ያልለበሰ ሰው፥ ሰይጣን በሕይወቱ ላይ የሚጭነውን ቀንበር ማንሳት አይችልም። ሰይጣን የሰውን ነፍስ እስር መያዝ የሚችል ብርቱ ኃይል እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገ ራል (ሉቃስ 11:21)። ሰማያዊ ኃይል ካልገታው፥ ሰይጣን ሁሉንም በቁጥጥሩ ሥር ማዋል ይችላል። መንፈስ ቅዱስ ለቅዱሳን የራሱ የሆ ነውን መልካም ነገር ይኸውም፥ ልባቸውን በፍቅር፥ በደስታና በተቀ ደሰው ፍላጎቱ ሲሞላ፥ ሰይጣን ደግሞ ለኃጢአተኞች የራሱን ባሕሪ የሚያሳየውንና እንዲሁም የእርሱ በሆኑት ክፉ ነገሮች፥ ይኸውም በትዕቢት፥ በፍትወት፥ በውሸትና እነዚህን በመሳሰሉ ኃጢአቶች ልባቸ ውን ይሞላዋል።

«ክርስቶስን አልለብስም» የሚል ሰው፥ የእግዚአብሔር ጠላት መሆኑን ማወጁ ነው። የእግዚአብሔር ጠላት የሆነ ሁሉ የሰይጣን ወዳጅ እንደሆነ የታወቀ ነው። የሰይጣን ወዳጅ ከሆነ ደግሞ ሰው ወዳጁን ስለማይዋጋ ሰይጣንንም አይዋጋም ማለት ነው። በንስሀ ያልተ ለወጠ ልብ ያለው ሰው፥ በመልካም ምግባሩ ሰይጣንንና ኃጢአትን የሚዋጋ ይምሰል እንጂ፥ ብዙም ሳይቆይ የማብገዝነት ጨዋታ የሚጫ ወት መሆኑ ይታወቃል።

## 1. "የጦር ዕቃችንን" የሠራው እግዚአብሔር ነው

ማንኛውም ዓይነት «የጦር ዕቃ» በጦርነት ወቅት ጠላትን ለማጥቃትም ሆነ ለመከላከል ይረዳል ማለት አይደለም። የአንድ አገር ወታደር ወደ ጦር ግዳ ሲዘምት፥ የፈለገውንና ደስ ያለውን መሣሪያ ይዞ አይሄድም፤ ነገር ግን የጦር አዛዡ ይዞ እንዲሄድ የነገረውን መሣሪያ ብቻ ይዞ ይሄዳል። የፈለገውንና እርሱ የመረጠውን ዓይነት መሣሪያ ብቻ ይዞ ቢሄድ በራሱ ላይ ብቻ ሳይሆን በመላው ሠራዊት ላይ ትልቅ መሸነፍን ያስከትል ነበር። ክርስቲያን ወታደርም ወደ መንፈሳዊ ጦር ግዳ ሲሄድ፥ እግዚአብሔር «ሰይጣንን የምትዋጋበት መሣሪያህ ይሄ ነው፤ የምትዋጋውም በዚህ ዓይነት ነው» በማለት መመሪያና ትዕዛዝ ይሰጠዋል። እግዚአብሔር ከሰጠው መሣሪያ ሌላ ለመጠቀም የሚሞክር ቢኖር፥ የተሳካ ውጤት በኃጢአትና በሰይጣን ላይ እንደማያገኝ የታወቀ ነው።

የእግዚአብሔር ሀሳብ እንደ ሰው ሀሳብ አይደለም። ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ በራሱ መንገድና ጥበብ ከግብጽ ለማውጣት ቢሞክር ኖሮ፥ የግብጽን ምድር ለቀው ከመውጣታቸው በፊት የግብጻውያንን ፈረሶችና መሣሪያዎቻቸውን ይዘው እንዲወጡ ያደርግ ነበር። እግዚአብሔር ግን ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ እንዲወጡ የነገራቸው ምንም ዓይነት የጦር መሣሪያ በእጃቸው ሳይዙ፥ በእግራቸው ተጉዘው እንዲወጡ ነበር። እንዲሁም የሚዋጉት ጦርነት የእግዚአብሔር ስለነበረ፥ ያጋጠማቸውን ጦርነት ሁሉ የተዋጉት ልክ እርሱ ባዘዛቸው መሠረት ነበር። መሣሪያቸውም ሆነ የጦርነት ታክቲካቸው (ስልታቸው) ከእግዚአብሔር የተቀበሉት ነበር። እኛስ ከእስራኤላውያን ሕይወት ምን እንማራለን? ወደ ሰማያዊው ቤታችን በምናደርገው ጉዞ እግዚአብሔር የሰጠንን ህግና መመሪያ ተከትለን እንጓዝ ይሆን?

ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ጦር ዕቃ ከመታመን ይልቅ የጦር ዕቃውን በሠራው በእግዚአብሔር መታመን ይገባናል። መሣሪያችን ጠንካራና ኃይለኛ ሊሆን የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድ የተሠራ መሆኑን ማመን የቻልን እንደሆን ብቻ ነው። የእስርኤል ሕዝብ የቃል ኪዳኑ ታቦት በጉዞአቸው ላይ ከፊታቸው እየቀደመ ሲሄድ፥ ለእስራኤል ሕዝብ ተገን ነበር፤ ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር ይልቅ የቃል ኪዳኑን ታቦት የሚያከብሩና የሚያመልኩ ከሆን ግን፥ ያ ለእነርሱ መጥፊያቸው ይሆናል። ክርስቲያኖችም እግዚአብሔር መከላከያ እንዲሆነንና እንዲሁም እርሱን እንድናከብርበት የሚሰጠንን ስጦታዎች በአግባቡ እንድንጠቀምባቸው እንጂ፥ ስጦታውን ከሰጠን አምላክ የበለጠ እንድናከብራቸውና እንድናመልካቸው አይደለም።

የጦር ዕቃውን የሚሰጠን እግዚአብሔር ከሆነ፥ አጠቃቀሙንም የሚያስተምረን እግዚአብሔር ነው። ከጠላት የሚከላከልልን የእግዚአብሔር ጦር ዕቃ እንጂ ማንኛውም ዓይነት ዕቃ ጦር እንዳልሆነ ተመ

ልክተናል። ጸሎት፣ እምነት፣ ተስፋና ቅድስና የጦር ዕቃዎች ናቸ
ውን? የጦር ዕቃ መሆን የሚችሉት እግዚአብሔር ራሱ የደነገጋቸው
ከሆኑ ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ዓለምን ማሸነፍ የሚችለው ከእግዚ
አብሔር የተወለደ ብቻ እንደሆነ ይናገራል። ሰይጣን ራቁታችንን፣
ወይንም ያለጦር ዕቃ ማስቀረት ካልቻለ፣ ሌላ ዘዴው፣ እውነት መሳይ
የሆኑና ፈጽሞ ሊከላከሉልን የማይችሉ ደካማ ዕቃ ጦሮች እንድንታጠቅ
ማድርግ ነው። ከነዚህ እውነት መሳይ ዕቃ ጦሮች መካከል አንደኛው፣
«የራሳችን የጽድቅ ሥራ» ነው። በዚህ የጽድቅ ሥራችን እግዚአብ
ሔርንና ሰዎችን ለመማረክ እንድንሞክር ያደርገናል። ትክክለኛ የጦር
ዕቃ የማይለብሱ ለመሆኑ በእግዚአብሔር የሚያምኑ ናቸው ማለት
ይሆን? አይደለም። ቢያምኑም የታጠቁት ዕቃ ጦር በክፉ ቀን ተዋግ
ተው ሰይጣንን ሊያሸንፉበት የሚችሉ ለመሆናቸው ግን በጣም አጠ
ያያቂና አጠራጣሪ ነው። ከሰይጣን፣ ከሞትና በመጨረሻም ከፍርድ
ፊት ሲቀርቡ፣ እርቃናቸውን ሆነው ይገኛሉ። «ዕቃ ጦር» ታጥቀናል
ብለው ቢያውጁም፣ ሕይወታቸው የተጋለጠ በመሆኑ ምንጊዜም በሰይጣን
ከመጠቃት ነጻ አይሆኑም።

አንዳንድ እውነት የሚመስል «ዕቃ ጦር» ትክክለኛውን የጦር
ዕቃ ስለሚመስል፣ ብዙዎቻችን በቀላሉ እንሞኛለን። ጌታችን ሲገለጥ
የትኛው ትክክለኛና እውነተኛ እንደሆነ ይለየዋል። የሚያብለጨልጭ
ሰይፍ በእጄ መያዝ እችላለሁ። እንደ ምላጭ ስለት ባለው ምላሴ
ለረጅም ጊዜ እየጮሁኩ መስበክ እችላለሁ። ታዲያ ይህን የሚያዩና
የሚሰሙ እኔ «ቅዱስ» ወይንም ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው አለመሆኔን
መንገስ ቅዱብ ካልገለጸለት የሚጠራጠር ማን ነው? የማልጠብቀው ወይ
ንም ችላ የምለው የእግዚአብሔር ሕግ አንድም አይኖርም። ከውጪ
በማሳየው ሁኔታ ልቡ የማይሳብና የማይነካ አይኖርም። ያለሁብትን
ሁኔታ ማጋለጥ የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። ያም ሆኖ ሰይ
ጣን ልቤን አደንድኖታልና በቀላሉ መቀበልና መለወጥ አይሆንልምኝም።
እንግዲህ የእግዚአብሔርን እውነተኛውንም የጦር ዕቃ ለመልበስ ከፈለ
ግሁ፣ በአሮጌ ዕቃ ጦር ላይ ደርቤ መልበስ ስለማልችል፣ አስቀድሜ
እንደ መርገም ጨርቅ የረከሰውን የጽድቅ ሸማዬን አውልቄ መጣል
አለብኝ። ራሱን አዋርዶና ገላልጦ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆም፣
ትክክለኛ ዕርዳታ እንደሚያስፈልገው የተገነዘበ ሰው ነው። እንዲህ
ዓይነቱን ሰው እግዚአብሔር አሮጌውን አስወግዶ አዲስ የዕቃ ጦር
ያለብሰዋል።

## 2. የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ በከፊል ሳይሆን በሙሉ እንልበስ

ጳውሎስ የእግዚአብሔርን የጦር መሣሪያ «በሙሉ ልበሱ» (ኤፌ.
6:11) በማለት ይመክረናል። «በሙሉ» ሲል፣ «ሳይለበስ የቀረ» ክፍል
እንድይኖር ማለቱ ነው። ካልሆነ ተንኮለኛው ዲያብሎስ የሚወረውረው

ጦር ቀዳዳ አግኝቶ ወግቶ ሊጥለን ይችላል። ሰው ከላይ እስከታች ለብሶ ዓይኑን ሳይሸፍን ቢቀር፣ ሰይጣን በዓይኑ አማካኝነት በፍትወት ጦሩ ይወጋዋል። ሔዋን «ፍሬዋ የምታመር» መሆኗን ስትመለከት፣ መርዘኛ የሆነው ጦር ልቧን ወጋው። ዓይናችንን ሸፍነን ጆሯችን የተጋለጠ ከሆነ ደግሞ በምንሰማው ክፉ ወሬ ሕይወታችንን ወግቶ ለመጣል ይሞክራል።

ጠላታችን በአንድ አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን፣ ሁልጊዜ በዙሪያችን ይገኛል። ፈተናውንም እየከፋፈለና ሥፍራ እየለዋወጠ ያቀርብልናል። አንዴ እዚህ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ እዚያ እያለ ግዕበሉን ያስነሳብናል። በአንድ በኩል ስናቆመው፣ በሌላ በር ወይንም አቅጣጫ ብቅ ይላል። የእግዚአብሔር የጦር መሣሪያ፣ እያንዳንዱ ክፍል የተለየ ሥራና አገልግሎት አለው። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ክፍል ዓላማና ጥቅም እንዲኖረው አድርጎ የፈጠረው ስለሆነ፣ «ይሄኛው አያስፈልገኝም» የምንለው ክፍል አይኖርም። እያንዳንዱ ክፍል አስፈላጊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ፍጹምና የተሟላ ነው።

ሰይጣን በክርስቲያኖች ሕይወት ትልቁ ዓላማው ሁልጊዜ ተስፋ ማስቆረጥ፣ ግራ ማጋባትና ረብሻን መፍጠር ነው። ግራ ስንጋባ፣ በምንወስደው እርምጃና በምንኖረው ኑሮ እርግጠኞች መሆን አቅቶን ስንወላውል፣ የመሸንፍና የተስፋ መቁረጥ ስሜት ሲጫነን፣ ሰይጣን በሕይወታችን የሚፈልገውን ዓላማ እየፈጸመ መሆኑን መረዳትና መገንዘብ ይገባናል። የእግዚአብሔር ቃል የሰይጣንን ውጊያና እንዲሁም የውጊያውን ስልት አውቀን የምንቋቋምበትን መመሪያ ይሰጠናል። ጳውሎስ «በጌታና በእርሱም ታላቅ ኃይል በርቱ» (ኤፌ. 6:10) ሲለን፣ የሰይጣንን ኃይል መቋቋም (ማሸነፍ) እንደሚቻል በማመን ነው። ይሄ ቃል እኛን የሚያደፋፍረን ቢሆንም፣ ምን ማድረግ እንደሚገባን ግን በግልጽ አይነግረንም። ጥያቄያችን በጌታ ውስጥ እንዴት ብርቱ መሆን እንችላለን? የሚል ነው። ለዚህ ጥያቄ መልስ እንዲሆነን ጳውሎስ የሰጠን ምክር፣ «የእግዚአብሔርን የጦር መሣሪያ በሙሉ ልበሱ» የሚል ነው። ጳውሎስ በጌታ ኃይል ውስጥ የበረታን እንድንሆን የሰጠን ሀሳብ፣ «እውነትን እንደ ዝናር ታጥቃችሁ ጽድቅን እንደ ጥሩር ለብሳችሁ፣ የሰላምን የምስችራች ቃል እንደ ጫማ በእግሮቻችሁ አጥልቃችሁ በመዘጋጀት ቁሙ» (ኤፌ. 6:14-15) የሚል ነው።

ጳውሎስ እዚህ ላይ ምሳሌ በተሞላበት ቋንቋ ሲገልጽ እናያለን። እነዚህ ምሳሌዎች እንጂ በእርግጥ በዓይን የሚታዩ፣ በእጅ የሚጨበጡ ነገሮች አይደሉም። ሀሳቡን የበለጠ ለመረዳት፣ ምሳሌዎቹ ምን እንደሚያመለክቱ መረዳት ያስፈልገናል። የጦር ዕቃው በጌታ ውስጥ ብርቱ እንድንሆን የሚያግዘን ነው። ይሄ የጦር ዕቃ ሌላ ነገር ሳይሆን፣ ጌታ ኢየሱስ ማንነቱን የሚገልጽ ነው። ጳውሎስ የዕቃ ጦሮችን ክፍል ሲዘረዝር፣ ስለ ክርስቶስ ሲናገርም መሆኑን እንዲሁም ኢየሱስን በምን

ዓይነት ሁኔታ ልናየው እንደሚገባ ሲገልጸው ነው። ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ሲጽፍ፣ «ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት እንጂ፣ የሥጋችሁን ፍላጎት ለማርካት አታስቡ» ይላቸዋል (ሮሜ 13:14)። ይሄም የጦር ዕቃችን ምንጭ ክርስቶስ እንደሆነ ያሳየናል። መከላከያችን ክርስቶስ ብቻ ነው። ስለዚህ የጦር ዕቃዎችን በተናጠል ስናጠና፣ ተጨባጭ በሆነ መንገድ ክርስቶስን እንዴት መያዝና መጠቀም እንዳለብንና እንዲሁም እርሱ የሚዋጉንን የክፉ መናፍስትን ኃይሎች እንዴት እንደሚዋጋልን ያሳውቀናል። ክርስቶስ መከላከያችን እንዲሆን ራሱን የሰጠን መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ እኛም ተቀብለን በጥቅም ላይ ልንገለገልበት ይገባል። "እውነትን" ካልተጠቀምንበት ማወቁ ብቻ በቂ አይደለም። ስለ "ቅድስና" በአጠቃላይ መናገር ቀላል ነው። አንዳንዴ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ቃል ያለቦታው በመሰንጠቅና በመውሰድ እንደ «ድግምት» ተጠቅመን በዚያ አሸናፊ ሕይወት ለመኖር የምንሞክርበት ጊዜ አለ። በክርስትና ሕይወቱ ትግል ለበዛበት አማኝ «ለጥያቄህ ሁሉ መልሱ እግዚአብሔር ነው» እንለዋለን። «ይህን አውቃለሁ፤ ግን መልስ የሚሆነው በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ነው?» ብሎ ሲጠይቀን የምንሰጠው መልስ እንዲኖረን ያስፈልጋል።

እያንዳንዱን ዕቃ ጦር በዝርዝር ከመመልከታችን በፊት ስለነዚህ ዕቃ ጦሮች ሁለት አስፈላጊ የሆኑትን እውነቶች መረዳት ያስፈልገናል። ይኸውም፣

**1** እነዚህ ስድስት ዕቃ ጦሮች በሁለት የተከፈሉ ሲሆኑ፣ <u>የመጀ መሪያዎች ሦስቱ፣</u>

«① እውነትን እንደ ዝናር ታጥቃችሁ...

② ጽድቅን እንደ ጥሩር ለብሳችሁ...

③ የሰላምን የምሥራች ቃል እንደ ጫማ በእግራችሁ አጥልቃችሁ...» – እነዚህን ቀደም ሲል በሕይወታችን ያደረግናቸው ወይንም የፈጸምናቸው መሆናቸውን ነው።

እንዲሁም <u>በሁለተኛው ክፍል ያሉት ሦስቱ</u> ደግሞ

«① ...እምነትን እንደ ጋሻ አንሡ፤

② ...ደህንነትን እንደ ራስ ቁር በራሳችሁ ድፉ፤

③ ...የእግዚአብሔርን ቃል እንደ መንፈስ ቅዱስ ሰይፍ ያዙ...» የሚለው ውጊያ ባጋጠመን ጊዜ ሁሉ እየደጋገምን የምንይዛቸውና የምንጠቀምባቸው መሣሪያዎች መሆናቸው ነው።

**2** ማወቅ የሚያስፈልገን እነዚህ ዕቃ ጦሮች የተዘረዘሩት አስፈላጊ የሆነ ቅደም ተከተል ይዘው ስለሆነ፣ በአጠቃቀማችን ቅደም ተከተላቸውን ማክበት እንደሌለብን ነው። ለምሳሌ፣ ብዙ ክርስቲያኖች «የቃሉን ሰይፍ» በደንብ መጠቀም የማይሆንላቸው ቀደም ሲል «በእውነት መቀነት» ሳይታጠቁ በመቅ

ረታቸው ነው። መጀመሪያ መሆን ያለበትን መጨረሻ፥ መጨ ረሻ መሆን ያለበትን መጀመሪያ አድርገን መጠቀም፥ የምን ጠብቀውን ዓይነት ውጤት አያስጠንም።

በታሪክ የሰው ልጅ በዘመናት ሁሉ ከተለያዩ ጠላቶች ራሱን ለመጠበቅና ለመከላከል ሲል የጦር መሣሪያ ማዳበር ላይ የነበረውን እሽቅድምድም እናውቃለን። ክርስቲያን ከጠላቱ ከሰይጣን የሚገጥመው ጦርነት ስላለበት ራሱን የሚከላከልበት መሣሪያ ያስፈልገዋል። በግድየ ለሽነትና በቸልተኝነት ክርስቲያን ለዚህ ጠላቱ ራሱን ከፋፍቶና አጋ ልጦ መስጠት የለበትም። እግዚአብሔር ክርስቲያኖች ራሳቸውን የሚ ከላከሉብትና የሚዋጉብትን መሣሪያዎች ምን እንደሆኑና እንዴት መጠ ቀም እንዳለባቸው በጳውሎስ አማካኝነት ገልጾልናል። እኛን ሊከላከሉ ልን (ሊሸፍኑን) የሚችሉ የጦር ዕቃዎች የእግዚአብሔር እንጂ እኛ የሠራናቸው እንዳልሆኑ ማወቅ ይገባናል። በክፉ ቀን ሊቋቋሙሉን የሚችሉት የእኛ ቅድስና፥ የእኛ እምነት፥ የእኛ ወንጌል አይደለም። እነዚህን ዕቃ ጦሮች ወደ ጦርነት ውስጥ ከመግባታችን በፊት ልንጠ ቀምባቸው ይገባል። ሰይጣን ፍላጻውን እስኪወረውርብን ድረስ ቁጭ ብለን መጠበቅ አይገባንም።

## 3 የእግዚአብሔር የጦር መሣሪያ ምንድነው?

### ሀ. የእውነትን መቀነት

«...እውነትን እንደ ዝናር ታጥቃችሁ...» ሲል የዕቃ ጦር አለባበ ሳችን የሚጀምረው ከዚህ እንደሆነ እናያለን። ወገባችንን መታጠቃችን ለጦርነት ዝግጁ መሆናችንን ያሳያል። በእውነት ካልታጠቅን ወደ ጦር ሜዳ መሄድ አንችልም። «ወገባችንን በእውነት መታጠቅ» ማለት ምን ማለት ነው? ሰይጣን አንደኛው መዋጊያ መሣሪያው በውሸትና በተሳ ሳተ ትምህርትና ሀሳብ አዕምሮአችንን መሙላት ነው። ሰይጣን ከመ ጀመሪያው ጀምሮ የውሸት ሁሉ ምንጭ ነው። ኢየሱስ ራሱ ስለ ሰይጣን የውሸት ባህሪ ሲናገር፥ «...እውነትም በእርሱ ስለሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፤ ሐሰተኛ፥ የሐሰትም አባት ነው» (ዮሐ. 8:44) ይለዋል። የመጀመሪያውን ሰው ሲወጋው መጀመሪያ የተጠቀመበት የውሸት መሣሪያውን ነው። እግዚአብሔር አዳምን "...ደጉን ከክፉ ለመለየት የሚያስችል ዕውቀት ከሚሰጠው ዛፍ ፍሬ አትብላ፤ ምክንያቱም ከዚህ ዛፍ ፍሬ በበላህበት ቀን በእርግጥ ትሞታለህ" (ዘፍ. 2:17) ብሎት ነበር። ሰይጣን ግን «...በፍጹም አትሞቱም...» በማለት ውሸቱን ነገራት።

ሰይጣን ሁልጊዜ ጥረቱ በአዕምሮአችን ልዩ ልዩ ጥርጣሬዎች መፍጠር ነው። «እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ አይደለም፤ ...እግዚ

እግዚአብሔር ዓለምን ሁሉ አይቆጣጠርም፤ ...እኔ ኃጢአተኛ በመሆኔ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን አልችልም፤ ...እግዚአብሔር እንደ እኔ ዓይነቱን አያደንግም፤ ...ይቅር እንዳለኝ በምን አውቃለሁ? ...ክርስቲያን መሆን አልችልም...» በማለት እንድንጠራጠር ሁልጊዜ የጥርጣሬ እንክርዳድ በውስጣችን ይዘራል። በተስፋ መቁረጥ ልባችን ሲሞላ፥ መንፈሳዊ ሕይወታችን ሲቀዘቅዝና ሲደክም፥ እነዚህን ስሜቶች ጠላታችን ሰይጣን የረጨብን መሆኑን ስለማናውቅ፥ መልሰን ሰይጣንን የምንቋቋመው በምን ዓይነት መንገድ ነው? አንደኛው ወገባችንን በእውነት መቀነት መታጠቅ ነው። ይሄ «እውነት» ምንድነው? ኢየሱስ «እኔ መንገድና እውነት፥ ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» አለ (የዮሐ. 14:6)። ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም የሆነ «እውነት» ነው። በሰይጣንና በሠራዊቱ ድል ተመተን እንዳንወሰድ የሚከላከልልን እርሱ ብቻ ነው። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ «ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት» ብሎ የሚመክረን (ሮሜ 13:14)።

ጌታን በተቀበልንበት ጊዜ ወገባችንን እንዴት በእውነት መቀነት እንደታጠቅን እናስታውሳለን። «በእውነት ወገባችንን መታጠቅ» ስንል ክርስቶስን ልክ ባገኘንበት ወቅት በእርሱ ውስጥ ያለውን እውነት ሁሉ፥ እንዲሁም የሕይወት ቁልፍ የሆነው፥ የዓለም ምስጢራት ገላጭ የሆነውን፥ እርሱ «ፍጹም እውነት» የሆነውን አገኘነው ማለት ነው። እርሱም ኢየሱስ እውነትና «የሕይወት ቁልፍ» ነው። ጳውሎስ ስለ ኢየሱስ ሲጽፍ፥ «...የተሰወረ የጥበብና የዕውቀት መዝገብ ሁሉ በእርሱ ነው...» ይላል (ቆላ. 3:3)። ሰይጣን እምነታችንን ለማናጋት በክርስቶስ ላይ ያለንን ተስፋ ለማጨለምና ተስፋ ለማስቆረጥ፥ «...በኢየሱስ አምናለሁ ትላለህ፤ በሁሉ ነገር ኃይልና ሥልጣን ያለው ነው ብለህ ተቀበልክ እንጂ ምንም ዓይነት መረጃና ማረጋገጫ የለህም፤ ይሄ ደግሞ ዕውር (ጭፍን) የሆነ እምነት ነው» ይለናል። እዚህ ላይ ማወቅ ያለብን፥ «እውነት» ክርስቶስ ሙሉ ሥልጣንና ኃይል እንዳለው ራሱን ገልጦ በመረጃ ገልጾልናል። ይህ ኢየሱስ «እውነት» መሆኑን በሕይወታችንም ቢሆን እስከምንወራረድ ድረስ እርግጠኞች ነን።

ኢየሱስ «እውነት» መሆኑን፥ በዓለም ያሉትን ምስጢራት ከፋች መሆኑን በምን እናረጋግጣለን? ኢየሱስ ራሱ በተናገረው ቃል እናረጋግጣለን። ራሱ የተናገረውን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተናገረውን አንብበን «ይሆናል» ብሎ ከገለጻቸው ነገሮች ጋር አመሳክረን እውነትነቱን ማረጋገጥ እንችላለን። የሰው ሕይወት ምን እንደሆን ሰው በሚገባውና ሊረዳው በሚችለው መንገድ ገልጾ ተናግሯል። ሌላው ቀርቶ ጠላቶቹ እንኳን ይህን አልካዱትም። ማንም ሰው ሁኔታዎችን እርሱ እንዳየው ያየ፥ ወደ ውስጥ ጠለቅ ብሎ ምስጢራትን እንደ ገለጸው የገለጸ የለም። ኢየሱስ በግልጽ የተናገረው ሁሉ «እውነት» ነው።

ኢየሱስ ማንነቱን ያረጋገጠው በተናገረው ቃል ብቻ ሳይሆን፥ በፈጸመው ድርጊትም ጭምር ነው። አዲስ ኪዳን እርሱ ያደረጋቸውን ተአምራቶችና ያሳያቸውን ታሪካዊ እንቅስቃሴዎች የያዘ ነው። ሰው መፍታት ያልቻለውን ወይንም ማሸነፍ የማይሆንለትን «ሞት» ድል የነሳ ነው። ከክርስቶስ በስተቀር ሞትን ያሸነፈ ማንም የለም። ስለዚህ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ «እውነት» ነው ብለን የምናምነውና የምንቀበለው።

ኢየሱስ ማንነቱን የሚያረጋግጥልን በተናገረውና በሠራው አስደናቂ ተአምራት ብቻ ሳይሆን፥ በወቅቱ፥ ማለትም በአሁኑ ጊዜ «በሆነው» እርሱነቱ፡ ነው። በግል ሕይወታችንና እንዲሁም በሌሎች ሕይወት «ነው» የምንለው ምንድነው? የክርስትና ሕይወትን ስንጀምር የነበር ንበትን ወደ ኋላ መለስ ብለን መመልከት እንችላለን። በእርግጥ ነጻ የወጣ ንበት ሁኔታ ነበረን? የታሠርንበትን ሠንሠለቶች በጥሶልናል፤ እውነተኛ የልብ ወዳጅና ጓደኛ ሆኖልናል፤ የተዘበራረቀውም ሕይወታችንን አደብ እንዲይዝና ሚዛናው የሆነ ሕይወት እንድንኖር አድርጎናል፤ «ጌታ ኢየሱስ ሆይ! እባክህን እርዳኝ!» ስንለው፥ ዕርዳታውን ሰጥቶናል፤ «አውጣን!» ስንለው፥ ከወደቅንበት አዘቅት ውስጥ አውጥቶናል። በዚህ ምክንያት ኢየሱስ «እውነት» መሆኑን የምናውቀውና የምናረጋግጠው።

በዓለም ላይ ያሉት ፍልስፍናዎችና እንቅስቃሴዎች በአንድ አቅጣጫ መፈተን ይገባቸዋል። አንዳንድ ፍልስፍናዎች ብዙ ነገር ማድረግ ይችላሉ፤ እንዲሁም አንዳንድ እንቅስቃሴዎችና ሥርዓቶች በብዙ አቅጣጫ ስህተት ቢኖርባቸውም፥ በአንዳንድ መስመር ደግሞ ጥሩ ሆነው ሊገኙ ይችላሉ። አንዳንድ ጥሩ የሆኑ ነገሮችን መፈጸም ይችላሉ። ይሁን እንጂ ይህ «የእውነት» መለኪያ አይደለም። «እውነት» ፍጹም ነው፤ በአንድ በኩል «ልክ»፥ በሌላ በኩል ደግሞ ልክ ላይሆን አይችልም። «እውነት» ተጨባጭ የሆነ ሀልውና ያለው ነው። ስለዚህ የሁሉ ነገር «ገላጭ» ነው። «እውነት» ነው ብለን የተቀበልነው ሁሉን ማቀፍ እንድንችል ጥልቀቱ፥ ስፋቱና ከፍታው ተወዳዳሪ የሌለው መሆን አለበት። ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ዓይነት ነው።

«እውነት» ሌላው ምልክቱ ፍጹም የማይለወጥ መሆኑ ነው። «እውነት» ጊዜውን እንዲመስል የምንለውጠው፥ የምናሻሽለው ነገር አይደለም። ከአሥር ሺ ዓመት በፊት «እውነት» የሆነው ዛሬም «እውነት» ነው። ዛሬም «እውነት» ከሆነ፥ ከመቶ ሺ ዓመት በፊትም «እውነት» ነበረ። ሁለትና ሁለት አራት መሆን እውነት ነው። ከመቶ ዓመት በፊት ሁለትና ሁለት አራት ነበር፥ ዛሬም አራት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስም አይለወጥም፤ «ትናንትናም፥ ዛሬም እንዲሁም ለዘለዓለም ያው ነው»። በሕይወታችን «እውነትን እንደያዝን የምናረጋግጠው በዚህ ነው። ስለዚህ ሰይጣን ሲዋጋን፥ የተሸነፍን ሲመስለን አዕምሮአችን በጥርጣሬ ማዕበል ሲሞላ፥ በእውነት ቀበቶ የታጠቅን መሆናችንን እናስታውስ። እውነተኛ ዓለት የሆነውን ኢየሱስን ያገኘን መሆናችንን እንወቅ።

ሰይጣን ክርስቲያኖችን የሚዋጋበት ዋናውና ትልቁ መንገድ ክሳሻችን በመሆን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣንን «የወንድሞቻችን ከሳሽ» (ራዕይ 12:10) ይለዋል። ሰይጣን እኛን እየከሰሰን ለእግዚአብሔር ቢያሳጣንም፥ እግዚአብሔር «የውሸት አባት» መሆኑን ስለሚያውቅ አያምነውም። እግዚአብሔርን ማሳመን ፈጽሞ አይችልም። ክርስቲያኖች ግን እግዚአብሔር የሚለንን ከመስማት ይልቅ ሰይጣን የሚነግረንን ወይንም የሚከሰንን ክስ እየሰማን ተስፋ የምንቆርጥ ስንቶቻችን እንሆን ይሆን? ሰይጣን በዚህ ዓይነት መልክ ሲዋጋን፥ ሊቋቋምልን የሚችለው «የታጠቅነው የእውነት ቀበቶ» ነው። በውሸት ሰይጣን ሲከሰን የምን ሰጠው መልስ «በክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት አሁን ኩነኔ የለባቸውም» (ሮሜ 8:1) የሚለውን እውነት ነው። እዚህ ላይ መጠንቀቅ ያለብን ነገር ቢኖር የሰይጣን ክስ መሆኑን ወይንም ህሊናችን የሚናገረን መሆኑን ለይተን እንድናውቅ ነው። ንጹህና እውነተኛ ልብ ያስፈልገናል። መንፈስ ቅዱስ እንዲያርመን ልባችንን ለእርሱ ክፍት አድርገን ብንሰጥም፥ በተከፈተው ልባችን ሰይጣን የራሱን ክስ እንዳይወረውርብን መጠንቀቅ ያስፈልገናል።

ሌላው ሰይጣን ክርስቲያኖችን የሚዋጋበት መንገድ የእግዚአብሐርን ባህሪና ማንነት አጨልሞና አበላሽቶ በማሳየት ነው። እግዚአብሔር በእርግጥ የሚወዳቸው መሆኑን የሚጠራጠሩ ብዙ ክርስቲያኖች አሉ። ኢዮብ በልዩ ልዩ መከራዎች ውስጥ እንኳን ቢያልፍ የእግዚአብሔርን ፍቅር ሳላተጠራጠረ፥ «የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን» አለ። እኛም በአንዳንድ መጥፎ ሁኔታዎች ውስጥ ስናልፍ፥ ሰይጣን ያንን ተጠቅሞ የእግዚአብሔርን ንጹህ ባህሪና ማንነት እያበላሸ ሲያቀርብልን ያንን በመቀበል ፈንታ፥ «መከራዎቹን እንደ በረከት» በመቁጠር ደስ ይበለን። ያም ሰይጣንን የምንቃወምበት «የእውነት ቀበቶ» ነው። በዚህ «በእውነት ቀበቶ» ሁልጊዜ እንጠቀምበት።

## ለ. የጽድቅ ጥሩር

"...የጽድቅን ጥሩር ለብሳችሁ..." ሲል ምን ማለት ነው? በእግዚአብሔር ፊት በድፍረት መቆም የሚያስችለንን፥ የጽድቃችን መሠረት የሆነውን ራሱን ክርስቶስን መልበስ ማለት ነው። ክርስቲያኖች አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔርን ያሳዘኑ፥ እግዚአብሔር ያልተቀበላቸውና የተዋቸው ስለሚመስላቸው፥ የበደለኛነትና «የዋጋቢስነት» ስሜት ይሰማቸዋል። በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም እንደጠፉቁት ካላደጉ፥ እግዚአብሔር የራቃቸውና የተቆጣቸው መስሎ ስለሚሰማቸው ደስታ የራቃቸው ይሆናሉ። ይህን ዓይነት ስሜት ሲሰማቸው፥ እግዚአብሔር በሕይወታቸው እየሠራ ያለውን ለማፍረስ ሰይጣን እየተዋጋቸው መሆኑን አይገነዘቡም። ይህን ዓይነቱን የሰይጣንን ክስና ውጊያ ለመሆኑ መቋቋም የሚቻለው በምን

ዓይነት ሁኔታ ነው? «የጽድቅ ጥሩር» የለበስን መሆናችንን በግልጥ ነው? ይህም ማለት በራሳችን ቅድስናና በጎነት በእግዚአብሔር ፊት መቆም እንደማንችል መረዳት ማለት ነው። ለእግዚአብሔር የምንሰጠው ወይም የምናሳየው ከራሳችን የመነጨ ምንም ዓይነት በጎ የሆነ ነገር እንደሌለንና ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ የቻልነው በራሳችን ቅድስና ሳይሆን ክርስቶስ በፈጸመልን ቅድስና ብቻ መሆኑን ያወቅን እንደሆን ነው።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሰይጣንን ፊት ለፊት ከገጠሙት ሰዎች መካከል ታላቁ ካህን ኢያሱ አንደኛው ነው። «እርሱም ታላቁን ካህን ኢያሱን በእግዚአብሔር መልአክ ፊት ቆሞ አሳየኝ፤ ሰይጣንም ይከሰው ዘንድ በስተ ቀኙ ቆሞ ነበር» (ዘካርያስ 3:1)። ይህ ታሪክ ሰይጣን ወደ ሰው ህሊና ዘልቆ በመግባት እንዴት እንደሚከስ ያሳየናል። የሁላችንም ልብ ለአደጋ (ለመሸነፍ) የተጋለጠ እንዲሆን የሚያደርገው አንደኛ ምክንያት ደካማነታችንን፥ ኃጢአተኛነታችንንና መተላለፋችንን ስለምንገነዘብ ነው። «ማድረግ የሌለብንን በማድረግ» ኃጢአት ባንሠራ፥ «ማድረግ ያለብንን ባለማድረጋችንን» ኃጢአተኞች መሆን እንደምን ችል እናውቃለን። ማናችንም ብንሆን እግዚአብሔር እንደሚፈልግብን ያህል በሙሉ ልባችን፤ በፍጹም አዕምሮአችንና ነፍሳችን እርሱን መውደድ እንደማንችል፥ ወይንም ጎረቤቶቻችንን እንደራሳችን አድርገን እንደማንወድ እናውቃለን። እንደ ክርስቲያን ማድረግ የሚገባንና ሳናደርግ ችላ የምንላቸው ብዙ ነገሮች እንዳሉ እናውቃለን። በየቀኑ የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብና በየቀኑ መጸለይ እንዳለብን ብናውቅም ችላ ያልናቸው መሆኑን አንክድም። እነዚህ ሁሉ የእኛን ደካማ ጎን የሚያሳዩ ናቸው።

ታላቁን ካህን ኢያሱን ሰይጣን ለመውጋት ያነጣጠረው እግዚአብሔርን ለማስደሰትና ለማክበር የሚፈልግበትን ውስጣዊ ህሊናው ላይ ነበር። ኢያሱ በእግዚአብሔር መልአክ ፊት በቆመበት ወቅት ሰይጣን በስተቀኝ ቆሞ ይከሰው እንደነበረ አንብበናል (ዘካርያስ 3:1)። ሰይጣን ክርስቲያኖች ወደ እግዚአብሔር በሚቀርቡበት ወቅት የሚዋጋቸው «በመክሰስ» ነው። የክርስቲያኖች ድካም ለሰይጣን በር ይከፍትለታል። ሰይጣን ክርስቲያኖችን ቀንና ሌሊት በእግዚአብሔር ፊት ይከሳቸዋል። «...ቀንና ሌሊት በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልን...» (ራዕይ 12:10)። የሰይጣንን ክሱ መስማት ለብዙዎቻችን አዲስ ነገር አይደለም። በጌታ ፊት ተንበርክከን ልመናችንን ልናቀርብ ስንል፥ ሰይጣን ጠጋ ይልና «እንዴት አንተ ከእግዚአብሔር መልካም ነገር ያደርግልኛል ብለህ ትጠብቃለህ? እስቲ ሕይወትህን ተመልከተው፤ በክርስትና ሕይወት እንዳንተ ደካማ ፈጽሞ የለም። በደልህን እስቲ ቁጠረው፤ ማድረግ ሲገባህ ያላደረግሃቸውን ነገሮች እስቲ አስብ» ይለናል። በዚህ ዓይነት እረፍት በመንሳት ሰይጣን የሚጨቀጭቀን ተስፋ ቆርጠን በእግዚአብሔር ላይ ያለንን መታመን እንድንተውና ከእርሱ

ፊቶቹ ሙሉ እንድንናገር ለማድረግ ነው። ኢያሱ በዚህ ዓይነት ክስ ሲወነጀል እግዚአብሔር አይቶ በፍጥነት ደረሰለትና «እግዚአብሔርም ሰይጣንን፣ ሰይጣን ሆይ! እግዚአብሔር ይገሥጽህ፤ ...» አለው (ዘካ. 3:2)።

«ኢያሱ እድፋም ልብስ ለብሶ በመልአኩ ፊት ቆሞ ነበር» (ዘካ. 3:3)። «እድፋሙ ልብስ» ኢሳይያስ «...ጽድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው...» (ኢሳ. 64:6) ብሎ በሚገልጸው መሠረት፣ የኢያሱን «ጽድቅ» የሚያሳይ ነበር።። ይህን የተመለከተው መልአክ አጠገቡ የቆሙትን «እድፋሙን ልብስ ከእርሱ ላይ አውልቁ» አላቸው (ዘካ. 3:4)። እድፋሙን ልብስ ካወለቁለት በኋላ መልአኩ ኢያሱን «...እነሆ! አበሳህን ከአንተ አርቄአለሁ፤ ጥሩ ልብስም አለብስሃለሁ አለው» (ዘካ. 3:4)። በእግዚአብሔር ፊትም መቆም እንዲችል አዲስና ንጹህ ልብስ አለበሱት።

ይሄ የብሉይ ኪዳን ታሪክ መልበስ ስላለብን «የጽድቅ ጥሩር» ጥሩ ምሳሌ ነው። «የጽድቅ ጥሩር» ሰይጣን የእግዚአብሔርን ልጆች ልብ ወግቶ ለመጣል እንዳይችል የሚከላከል «የእግዚአብሔር የጦር ዕቃ» ነው። የጥንት የሮም ወታደሮች ከሚታጠቁት የጦር ልብስ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው «የደረት ጥሩር» ነበር። በዚህ መጣሪያ የሚሸፈነው የሰውነት ክፍሎች ልብ፣ ሳንባ፣ ጉበትና የመሳሰሉት ናቸው። የጠላት ጦር ተወርውሮ እነዚህ የሰውነት ክፍሎችን ቢወጋ ያ ሰው እንደ ሚሞት የታወቀ ነው። ስለዚህ «የደረት ጥሩሩ» ሁልጊዜ መለበስ ያለበት መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ በጣም ጠንካራም መሆን አለበት።

አማኝ በሚያደርገው መንፈሳዊ ጦርነትም «ቅድስና» ወይንም «ጽድቅ» በጣም አስፈላጊ ነው። ቅድስና ሰይጣንን ሙሉ በሙሉ እንዲሸነፍና እንዲሸሽ ያደርገዋል። ሰይጣን «ቅዱስ» መሆን አይችልም። «ቅድስና» ከእግዚአብሔር ባህሪ አንዱ ነው። ዘማሪው እግዚአብሔርን «አንተ ጻድቅ ነህ፤ ፍርድህም ቅን ነው» (መዝ. 119:137)፣ «...እግዚአብሔር በመንገዱ ሁሉ ጻድቅ ነው፤ በሥራውም ሁሉ ቸር ነው» (መዝ. 145:17) ይለዋል።

«...የጽድቅን ጥሩር ለብሳችሁ...» ሲል ምን ማለቱ ነው? በእግዚአብሔር ፊት በድፍረት መቆም የሚያስችለን የጽድቃችን መሠረት የሆነውን ክርስቶስን መልበስ ማለት ነው። «የጽድቅን ጥሩር ለብሰን» ከሆነ፣ ልባችንና ስሜታችን ከሰይጣን ፍላጻ (ውጊያ) የተጠበቀ መሆኑን ስለምናውቅ ፍጹም የሆነ እረፍት ይሰማናል። ክርስቶስን ተቀብለን በዳንበት ወቅት እግዚአብሔር አብ የልጁን ቅድስና ያለብሰናል። ጳውሎስ ይህን ሲገልጽ «...በሕግ የተመሠረተውን የራሴን ጽድቅ ትቼ፣ በእምነት ላይ የተመሠረተውን የእግዚአብሔርን ጽድቅ በክርስቶስ አማካይነት ለማግኘትና ከእርሱም ጋር ለመሆን ነው...» ይላል (ፊልጵ. 3:9)።

«የጽድቅን ጥሩር» መልበስ ማለት በየቀኑ በዚህ ተጨባጭ በሆነ እምነት፣ ማለትም «የእግዚአብሔርን ጽድቅ» የለበስን መሆናችንን መገንዘብ ማለት ነው። ሰይጣን የእኛን «ኃጢአተኛነት» እያነሳ ሁልጊዜ እንዳይከሰን የሚከላከልልን «የጦር መሣሪያ» ቢኖር «የጽድቅ ጥሩር» ብቻ ነው። «እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም» (ሮሜ 8፡1) በየቀኑ በልባችን የሚመላለስ ቃል ይሁንልን።

«የጽድቅ ጥሩር» ክርስትያናችን በተለያየ መንገድ ይጠቅማል።

1ኛ. ድፍረትና መተማመንን ይሰጣቸዋል። በጦርነት ላይ "ድፍረት" በጣም አስፈላጊ ነው። ሰይጣን ድካማችንን እየጠቀሰ ሲከሰን፣ የለበስነው ቅድስና የራሳችን ሳይሆን «የክርስቶስ ቅድስናን» መሆኑን መንገሩ የበለጠ ድፍረትን ይሰጣል።

2ኛ. የለበስነው የራሳችን ቅድስና ሳይሆን የክርስቶስን ጽድቅ መሆኑን ስለምንገነዘብ «እኔ ቅዱስ ነኝ» ብለን በራሳችን በጎነት እንዳንታመንና እንዳንመካ ያደርገናል። በራሳችን ቅድስና መታመን ደካማነት መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ራሳችንን ለአደጋ የተጋለጥን የሚያደርገን መሆኑ ነው። ከእግዚአብሔር ዕርዳታን የምንፈልገው ደካማነታችንን የተረዳን እንደሆነ ብቻ ነው። ደካማነታችንንም እስከንገነዘብ ድረስ እግዚአብሔር ለክብሩ አይጠቀምብንም።

ሐዋርያው ጳውሎስ ተስፋ እንዲቆርጥና እንዲሸነፍ ግፊት ሲደርስበት ይህን «የጽድቅ ጥሩር» የተጠቀመበት በምን ዓይነት ሁኔታ ነበር? ጳውሎስ ጌታን ከማግኘቱ በፊት የክርስትያኖች ዋና ጠላት ሆኖ ብዙዎችን ያንገላታና ያሰቃየ በመሆኑ፣ ከመጥፎ ትዝታ ምን ጊዜም ቢሆን ራሱን ነጻ ማድረግ እንደማይችል ግልጽ ነው። በጭካኔ ተሞልቶ ቤተ ክርስቲያንን በማሳደድ የታወቀ ነው። እርሱ ባመጣው ስደት ምክንያት ብዙ ሰዎች እንደተሰቃዩ ያውቃል። ሰይጣን የጥንቱን ሕይወቱን እያስታወሰ ሊከሰው ሲሞክር «የጽድቁን ጥሩር» የተጠቀመበት «እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ስላሳደድሁ ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ፤ ለእኔም የተሰጠኝ ጸጋው ከንቱ አልነበረም፤ ከሁላቸው ይልቅ ግን ደከምሁ፤ ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም» (1 ቆሮ. 15:9-10) በማለት ነው። «...በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ...» ሲል፣ «ከዚህ በፊት ስለነበረኝ ሕይወት ግድ የለኝም፤ ራሴን የምከላከልበት ወይንም ንጹህ ነኝ የምልበት ነገር የለኝም። የምለው በእግዚአብሔር ጸጋ አሁን የሆንኩትን ነኝ። አሁን የሆንኩትም ክርስቶስ ስለ ሠራኝ ብቻ ነው። የቆምኩት በራሴ ቅድስና ሳይሆን በእርሱ ቅድስና ብቻ ነው። በጸጋው ላይ ስለቆምኩ የእኔ ሁኔታ ምንም ዓይነት ለውጥ አያመጣም» በማለት ራሱን ከተስፋ መቁረጥ ይጠብቅ ነበር። «የጽድቅን ጥሩር» ጌታን

በተቀበለበት ወቅት ስለለበሰ፥ ጳውሎስ ሁልጊዜ ወደ ክርስቶስ በመመልከቱ፥ ተስፋ ቆርጦ ወደ ኋላ ለመመለስ የታጣው ጊዜ አልነበረም።

## ሐ. የሰላም ወንጌል ጫማ

"...በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው..." (ኤፌሶን 6:15) ሲል፥ ጫማ ማድረግ በጦርነት ወቅት በጣም አስፈላጊ እንደሆነ እናያለን። ባዶ እግሩን ወደ ጦር ሜዳ የሚሄድ ወታደር ተራራውንና ቁልቁለቱን ሲሮጥ ብዙ እንቅፋትና መላላጥ እንደሚደርስበት የታወቀ ነው። ልዩ ልዩ የጦር መሣሪያ በእጁ ቢኖረው እንኳን፥ በእግሩ ጫማ ከሌለው፥ ለጦርነት ብቁ እንዳይሆን ያደርገዋል። ጫማ ማድረግ የወታደሩን ዝግጁ መሆን ያሳያል።

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ «..ሰላምን እተውላችኋለሁ፤ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም...» (ዮሐንስ 14:27) አላቸው። በሕይወታችን ሰላምን ያጣንበት ጊዜ፥ ፍርሃት፤ ድንጋጤና ስጋት ሕይወታችንን የሞላበት ጊዜ ይኖር ይሆን? አማኞች ከፈተና፤ ከችግርና ሰላም ከማጣት ሕይወት ነጻ አይደሉም። ከጭንቀታቸው ብዛት የተነሳ በኃይል ቢጸልዩም፥ ጸሎታቸው ወደ እግዚአብሔር ጆሮ እንዳይደርስ የታገደ የሚመስላቸው ጊዜ፤ የእግዚአብሔርን ቃል በሰፊው ቢያነቡም የተጨነቀውን አዕምሮአቸውንና ስሜታቸውን መፈወስ የማይችል፥ ፍጹም ሕይወት የሌለው ተራ ቃል ብቻ ሆኖ የሚሰማቸው ጊዜ አለ። መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያው ጳውሎስ አማካኝነት በጦርነት ወቅት መንፈሳዊ ወታደር «የሰላም ጫማ» እንደሚያስፈልገው ይገልጻል። ወታደር ከሚያጠልቀው የጦር ዕቃ ሁሉ «ከጫማ» የሚበልጥ ይናራል ብሎ መገመት ያስቸግራል። እግራችን ቢጎዳ ሌላው ሰውነታችን ሁሉ እንደሚጎዳ ያልተገነዘበን ሰዎች የለንም። ከእግር ጣቶቻችን መከከል አንደኛው ቢጎዳ፥ በኃይል የሚያመን መሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ እንኳን መዋጋት ቀርቶ መራመድም አንችልም። በመንፈሳዊ ጦርነትም ውስጥ ሰላማችን ከደፈረሰ፥ ውስጣችን ከተጎዳ እንደሚገባን መዋጋት አንችልም። ስለዚህ ጥሩ ጫማ ማድረግ ሁልጊዜ አስፈላጊ ነው።

የተለያየ ጫማ በተለያየ ጊዜ ማድረግ የሚያስፈልገን ጊዜ አለ። ሯጭ በጥሩ ሁኔታ ለመሮጥ እንዲችል ቀለል ያለ ጫማ፥ የቅርጫት ኳስ የሚጫወት ተጫዋች የተወለወለው ጣውላ እንዳያዳልጠው የማያንሸራትት ጫማ ያስፈልገዋል። አናጢ ደግሞ መዶሻም ሆነ ሌላ መሣሪያ እግሩ ላይ ሲወድቅ እግሩን እንዳይጎዳው ጠንካራና ከባድ ቦት ጫማ ማድረግ ያስፈልገዋል። በመንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ ተሳታፊ የሚሆነው አማኝ ደግሞ የተለየ ጫማ ያስፈልገዋል። ያም «የሰላም ጫማ» ነው።

የመጀመሪያው "ሰላም" ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን ሰላም ነው። ጳውሎስ "...በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን..." ይላል (ሮሜ 5:1)። ይህን ዓይነቱ ሰላም በምርጫ ሳይሆን በግድ ሊኖረን የሚያስፈልግ ሰላም ነው። ይህንን ሰላም ለማግኘት በአዕምሮአችን ተረድተን፥ በእምነት የምንቀበለው ነው። ክርስቶስ በመስቀል ላይ በፈጸመው ተግባር ብቻ ስለቀደስን፥ የእግዚአብሔር ቁጣ በእኛ ላይ አይኖርም። ነገር ግን ከእርሱ ጋር ፍጹም የሆነ ሰላምና እርቅ ይኖረናል። ከእግዚአብሔር ጋር የነበረን ቅራኔና መለያየትም ፈጽሞ ይጠፋል። ይህንንም ስንገነዘብና አምነን ስንቀበል፥ በውስጣችን ፍጹም የሆነ ሰላም ይሰማናል። አንዳንድ አማኞች በሕይወታቸው የማይፈልጉት ነገር ሲደርስባቸው፥ ወይንም በተለያየ ፈተና ውስጥ ሲያልፉ፥ «እግዚአብሔር ተቆጥቶኝ እየቀጣኝ ነው፤ ምን እንዳደረግሁ ግን አልገባኝም» ይላሉ። ይህን ዓይነት አባባል መሥመር የለቀቀ ወይንም የእግዚአብሔርን ባሕሪ በትክክል የሚገልጽ አይደለም። እግዚአብሔር ቁጣውን በልጆቹ ላይ አያፈስም። ሥነ ሥርዓት እንድንይዝ፥ አባት ልጁን በአርጩሜ እንደሚቀጣው ያህል ይቀጣናል እንጂ፥ ሊጎዳንና ሊያጠፋን ክንዱን በእኛ ላይ አይዘረጋም። ባለብን መንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ አሸናፊዎች ለመሆን፥ አዕምሮአችን ይህን እውነት ማወቅ አለበት። «እግዚአብሔር ተቆጥቶኛል» በሚል እምነት ውስጥ መኖር፥ በቆሰለ እግር እንደመራመድ ይቆጠራል።

«በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ፥ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ፥ በአንዲት ነገር አትጨነቁ። አዕምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል» (ፊልጵ. 4:6-7)። ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን ሰላም በአዕምሮአችን የምንረዳው ሲሆን፥ እግዚአብሔር የሚሰጠን ሰላም ደግሞ መንፈሳችንን የሚያረጋጋና የሚጠብቅ "ሰላም" ነው። ስለ እግዚአብሔር በቂ ዕውቀት ቢኖረንም፥ ስሜታችን ዕውቀታችንን ካልተቀበለውና ካልደገፈው የምናውቀውን እውነት በሥራ መተርጎም አንችልም። በውስጣችን ሰላም ሲጠፋ ምን እንደሚሰማን ብዙዎቻችን እናውቃለን። ጥቂት ችግርና እንቅፋት ሲያጋጥመን በቀላሉ እንታወካለን፥ እንጨነቃለን። በዚህ ጊዜ ነው አንዳንድ ሰዎች ማደንዘዣ መድኃኒትና መጠጥ የሚፈልጉት።

አማኝ ይህንን «የሰላም ጫማ» አድርጎ መራመድ የሚችለው እንዴት ነው? ጳውሎስ ለፊልጵስዮስ ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ "በጸሎትና በምሲጋና" እንደሆነ ይጠቅሳል። በአማኝ ሕይወት ውስጥ የሚፈጠረውን ሁከት ጸጥ ለማድረግ ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት ከመገናኘት የሚበልጥ ምንም ነገር የለም። አንዳንድ ጊዜ በውስጣችን ሰላም ስናጣ ምናልባት እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር በጸሎት እንድንገናኝ፥ ጊዜ እንድናሳልፍ እየጠራን ይሆናልና ጥሪውን ችላ አንበለው። የምንኖረው ጠላታችን ሰይጣን ለብቻችን ተዋግተን የምናሸንፈውና የምንች

ሰውም አይደለም። "የእግዚአብሔር ሰላም" ከእኛ ጋር መሆኑን ስና ውቅ፥ ፈጽሞ ፍርሃት አይሰማንም። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ "የሰላም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል" (ሮሜ 16:20) ያለው ለዚህ ነው።

## መ. የእምነት ጋሻ

«...እምነትን እንደ ጋሻ አንሡ...» (ኤፌሶን 6:16) ሲል የእምነት ጋሻ በአማኞች ሕይወት ውስጥ አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል። ዘማሪው እግዚአብሔርን «አንተ ጻድቁን ትባርከዋለህና አቤቱ፥ እንደ ጋሻ በሞገስ ከለልኸን» ይለዋል (መዝ. 5:12)። እግዚአብሔር በጻድቁ ዙሪያ ሆኖ ማለትም በላይም በታችም፥ በግራም በቀኝም ሆኖ እንደሚጠብቀውና እንደሚከላከልለት ዘማሪው ይገልጻል። ሰይጣን ኢዮብን ለመፈተን ፈቃድ ከማግኘቱ በፊት ጻድቅ መሆን የቻለበትን ምክንያት እየጠቀሰ ሲከሰው «በውኑ ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚፈራው በከንቱ ነውን? እርሱንና ቤቱን፥ በዙሪያውም ያሉትን ሁሉ አላጠርህለትምን?» አለ (ኢዮብ 1:10)። በእርግጥም የሰይጣን ቁጣና የሚያመጣው መአት እንዳይነካው ዙሪያውን አጥሮ ይከላከልለት ነበር። በኢዮብ ታሪክ ውስጥ እንደምናየው እግዚአብሔር በእኛም ሕይወት ዙሪያ ሆኖ ባይከላከልልን ኖሮ በሰይጣን ሰይፍ ነፍሳችን ትጨነቅ ነበር።

ለመንፈሳዊ ውጊያችን ጋሻ ጠቃሚ የሚሆንበት ዋና ምክንያት መከላከያ እንዳለን ሙሉ እምነትና መተማመኛ ስለሚሰጠን ነው። በዚህ ዓይነት አንዳንድ ሰዎች ሰይጣን ወደ እኛ ፈጽሞ አይደርስም ብለው የሚያስቡ አሉ። እንዲህ ብሎ ማሰብ ትክክል አይደለም። ኢዮብ ጻድቅ ቢሆንም፥ ወደ እርሱ መቅረብ ችሏል። ኢዮብ የቀመሰውና የተለማመደውን ዓይነት ፈተና እንደማይቀምስ የሚያረጋግጥበት ምንም ነገር የለውም። የእምነት ጋሻ የሰይጣንን ፍላጻ መቋቋም እንደሚችል በምን እናውቃለን? ለዚህ ጥያቄ የምንሰጠው መልስ፥ የኃያሉን እግዚአብሔር መለኮታዊ አሠራር በጥንቃቄ በመመርመር ነው። የሰይጣን ጦር የሚንበለበለው አማኞችን ወግቶ ለመጣል፥ እንዲሁም ለማጥፋት ነው። በጭካኔው ተወዳዳሪ የለውም። ስለሆነም ከእግዚአብሔር ጋሻ ወይንም መከላከያ በስተቀር ምንም ዓይነት ኃይል ሊያቆመውና ሊገታው አይችልም።

አማኝ የእምነትን ጋሻ ቢይዝም፥ እንዲሁም ሙሉ የጦር ዕቃ ቢለብስም፥ የሰይጣን ጦር ጋሻውን ዘልቆ እንዲያጠቃው እግዚአብሔር ሆን ብሎ የሚፈቅድበት ጊዜ አለ። የሰይጣን የሚንበለበለው ፍላጻ ጋሻውን አልፎ ወደ አማኝ ሲደርስ፥ «የሰይጣን ፍላጻ» መሆኑ ይቀርና የአማኙን ሕይወት የሚያጠራና የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚያሳይ መሣሪያ ይሆናል። እሳት «ማጥፋት» ብቻ ሳይሆን «ማጥራትም» ይችላል።

ብረት በእሳት ሲቀልጥ የተፈለገውን ዓይነት ቅርጽ እንዲይዝ ማድረግ ይቻላል። እግዚአብሔርም የሰይጣን ፍላጻ «የእምነታችንን ጋሻ» ዘልቆ እንዲነካን ቢያደርግም ለዓላማው ይጠቀምበታል። እግዚአብሔር ካቀደ ውና ከሚፈልገው በላይ ግን ሰይጣን ገፍቶ እንዲሄድ አይፈቅድለትም። «ወንድሞቼ ሆይ፣ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፣ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት። ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም» (ያዕቆብ 1:2-4)።

ይሄ ጋሻ ምንድነው? የምንጠቀምበትስ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ነው? የእምነት ጋሻ ቀጥተኛ ትርጉሙ፣ የእግዚአብሔር መገኘት ማለት ነው። እግዚአብሔር አብርሃምን «አብራም ሆይ! አትፍራ እኔ ለአንተ ጋሻህ ነኝ፤ ዋጋህም እጅግ ታላቅ ነው» አለው (ዘፍ. 15:1)። በሙሴ አማካኝነት ለእስራኤል ሕዝብም «...እስራኤል ሆይ! ምስጉን ነህ፤ በእግዚአብሔር የዳነ ሕዝብ እንደ አንተ ማን ነው? እርሱ የረድኤትህ ጋሻ የከፍተኛነትህም ሰይፍ ነው። ጠላቶችህም ይገዙልሃል፤ አንተም ከፍታቸውን ትረግጣለህ» ይላቸዋል (ዘዳ. 33:29)። ዳዊትም እግዚአብሔር ከሳኦል እጅና ከጠላቶቹ እጅ ሁሉ ባዳነው ቀን ምስጋናውን በቅኔ ሲገልጽ «...እግዚአብሔር ዓለቴ፣ አምባዬ፣ መድኃኒቴ ነው፤ እግዚአብሔር ጠባቂዬ ነው፤ በእርሱም እታመናለሁ፤ ጋሻዬና የረድኤቴ ቀንድ፣ መጠጊያዬና መሸሸጊያዬ...» ይለዋል (2 ሳሙ. 22:2-3)።

ሰይጣን ተፈጣሪ ስለሆነ የፈጣሪን ኃይልና «መገኘት» መቋቋም አይችልም። የእምነት ጋሻችን ግንም ሊያሸንፈው የማይችለው የራሱ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ መገኘት እንደሆነ ማወቅ ትልቅ ተስፋና መጽናናት ነው። ጌታ ኢየሱስ በእኛና በጠላታችን በሰይጣን መካከል እንዳለ በእምነት እናውቃለን። «...በእምነት የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን...» የሚለው ቃል (ኤፌ. 6፡16)፣ አማኞች የሰይጣንን እሳት ወይንም ተንኮል ማክሸፍ እንደ ምንችል ያሳየናል። ከሰይጣን ጋር በየቀኑ ለሚኖርብን ውጊያ፣ ራሳችንን ለመከላከያ ይሆን «የእምነት ጋሻ» ሁልጊዜ መያዝ አለብን።

## ሠ. የራስ ቁር

ሰይጣን ትልቁ ጥረቱ የሰዎችን አዕምሮ በቁጥጥሩ ሥር ለማዋል ነው። የሚጠቀምበትም መሣሪያ የረቀቀውን «ውሸት» ነው። እውነቱን በደንብ ካላወቅን፣ «ውሸትን» እውነት አድርጎ ማቅረብ ስለሚችል ተንኮሉን መረዳት በጣም ያስቸግራል። አዕምሮአችንን በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ፣ የእግዚአብሔርን እውነት እንዳናውቅ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። ከሰው የሰውነት ክፍል ወይንም አካል ውስጥ ለጉዳት የተጋለጠ

የሚሆነው «ጭንቀላቱ» ወይንም ራሱ ነው። «የራስ ቁር» የሚደፉት ወታደሮች ብቻ ሳይሆኑ፣ ግንበኞች፣ አናጢዎችና የሞተር ብስክሌት አሽከርካሪዎችም ናቸው። ሰው ራሱ ከተጎዳ ሌላው ሰውነቱ እንደፈለገው አይታዘዝለትም። በመንፈሳዊ ሕይወትም ልክ እንደዚሁ ነው። በውሸቱ ተጠቅሞ ሰይጣን አዕምሮአችንን በቁጥጥሩ ሥር ማድረግ ከቻለ ፍጹም ሊያጠፋን ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ሥፍራ አዕምሮአችን በሰይጣን ጦር ለመወጋት የተጋለጠ እንደሆነ ይነግረናል። ያዕቆብ በምዕራፍ 1:8 «...ሁለት አሳብ ላለው፥ በመንገዱም ሁሉ ለሚወላውል ለዚያ ሰው በጌታ ዘንድ አንዳች እንዲያገኝ አይምሰለው..» በማለት ያስጠነቅቀናል። «ሁለት አሳብ» ያለው ሰው አዕምሮው «የሚወላውል» እንደሚሆን ግልጽ ነው። «ሁለት አሳብ» ማለት በአንድ በኩል የሰይጣንን ውሸት፥ በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔርን «እውነት» የሚያምን ማለት ነው። ሁለት አሳብ መያዝ ያለበትን አደጋ የተገነዘበው ዳዊት «ስምህን እንድፈራ ያልተከፋፈለ ልብ ስጠኝ...» ብሎ እንደ ጸለየ እናነባለን (መዝ. 86:11)።

የሰይጣንን ሀሳብ ከአዕምሮአችን ማስወጣት የምንችለው፥ አዕምሮአችንን በክርስቶስ ሀሳብ የሞላን እንደሆን ብቻ ነው። ሰይጣን ልባችንን በእርሱ መንፈስ መሙላት እንደሚችለው ሁሉ፥ ክርስቶስም አዕምሮአችንን በራሱ ሀሳብ ሊሞላን ይችላል። ኢየሱስ ከሰይጣን የሚለይበት ሁኔታ ግን እርሱ ያለእኛ ፈቃድ፥ ሳንጋብዘው ፈቃዳችንን ጥሶ ለመግባት የማይሞክር መሆኑ ነው። አዕምሮአችንን በክርስቶስ ሀሳብ መሙላት የምንችለው ቃሉን በልባችን ውስጥ መሰወር የቻልን እንደሆን ነው። ዳዊት «አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ» ይላል (መዝ. 119:11)። በሰይጣን ፍልጻ አዕምሮአቸው ተመትቶ የሚሰቃዩ ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል ያስፈልጋቸዋል። በ1ኛ ተሰሎንቄ 5፥8–9 ጳውሎስ «...እኛ ግን ከቀን ስለ ሆንን የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር፥ የመዳንንም ተስፋ እንደ ራስ ቁር እየለበስን በመጠን እንኑር፤ እግዚአብሔር ለቁጣ አልመረጠንምና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መዳንን ለማግኘት ነው እንጂ» ይላል። እዚህ ላይ ጳውሎስ «የራስ ቁርን» የተስፋ ቁር ብሎ ይጠራዋል።

ክርስቶስ ደህንነታችንና ተስፋችን ነው። ተመልሶም የሚመጣው እኛን ለመውሰድ ነው። ተመልሶ እንደሚመጣ ፍጹም እርግጠኞች ነን፤ እርግጠኛ የምንሆነው ያኔ ብቻ ሳይሆን አሁንም በአማኞች ልብ ውስጥ እንደሚኖር እናውቃለን። የተረሳንና ፍጹም የጠፋን፥ ጠላታችን ያሸነፈንና እንዲሁም በከባድ ማዕበል የተመታን ሲመስለን፥ የደህንነት ተስፋችን አደጋ ወደ ሌለበት ስፍራ ዞር ያደርገናል። የደህንነት ራስ ቁር አዕምሮአችንን የሚሸፍን፥ ወይንም የሚሞላ ከሆነ፥ ፈጽሞ ተስፋ መቁረጥ አይገባንም። ያለንበትን ሁኔታ ስለሚያውቅ አይተወንም፤ እኛ ወዳለንበት ሥፍራ ይመጣል። «...እርሱ ራሱ አልለቅህም ከቶም አልተውህም፤ ብሎአልና ስለዚህ በድፍረት ጌታ ይረዳኛልና አልፈራም፤ ሰው ምን ያደርገኛል እንላለን..» (ዕብ. 13:5-6)።

## ፈ. የመንፈስ ሰይፍ

የመጨረሻው የጦር ዕቃ «የመንፈስ ሰይፍ» ሲሆን፥ ትርጉሙም የእግዚአብሔር ቃል ማለት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆላስያስ ሰዎች «የክርስቶስ ቃል በሙላት በእናንተ ይኑር...» በማለት ይመክራቸዋል (ቆላስይስ 3:16)። ቃሉና ክርስቶስ ምንጊዜም ስለማይነጣጠሉ፥ የክርስቶስን ኃይልና ሥልጣን ካመንና ከተቀበልን፥ የቃሉንም ኃይልና ሥልጣን መቀበል አለብን። «የመንፈስ ሰይፍ» ሲል መጽሐፍ ቅዱስን በአጠቃላይ ማለቱ ይሆን? «ቃል» የሚለው ሀሳብ በግሪክ ቋንቋ ሁለት ዓይነት ትርጉም አለው። ይኸውም፥ አንደኛው በሰፊው የታወቀው «ሎጎስ» ሲሆን፥ ዮሐንስ በወንጌሉ በመጀመሪያው ምዕራፍና ቁጥር ላይ የጠቀሰው ነው። «መጀመሪያ ቃል (ሎጎስ) ነበር፤ ቃልም (ሎጎስም) ከእግዚአብሔር ጋር ነበር፤ ቃልም (ሎጎስም) እግዚአብሔር ነበር» የሚለው ነው (ዮሐ. 1:1)። ሌላው ትርጉም ደግሞ ብዙ ጊዜ ያልተጠቀሰ «ሬማ» የሚለው ሃሳብ ሲሆን፥ ይህኛው ከሎጎስ የተለየ ትርጉም የያዘ ነው። «ሎጎስ» እግዚአብሔር የተናገረው ጠቅላላ «ቃል»፥ እግዚአብሔር የሰጠው ሙሉ ራዕይን የሚያመለክት ነው። «ሬማ» ግን በአንድ በተለየ ጊዜ፥ ለተለየ ሁኔታ የተናገረው ቃል ነው፤ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ወይንም ጥቅስ ለተለየ ሁኔታና ጊዜ የሚያገለግል ቃል ነው።

«የመንፈስ ሰይፍ» ስንል፥ «ቃሉን» ለአንድ የተለየ ሁኔታ የምንጠቀምበት ማለት ነው። አማኞች በሚያስፈልጋቸው ጊዜ፥ በተለያየ ሁኔታ ውስጥ ሲያልፉ የሚጠቀሙበት ታልቅ መሣሪያ ነው። የሰይጣን ፍላጻ ሲዋጋን፥ በልዩ ፈተና ውስጥ ስናልፍ ካለንበት ሁኔታ በአሸናፊነት ለመውጣት ግራ በተጋባን ወቅት የእግዚአብሔር ቃል፥ ለዚያ ላለንበት ሁኔታ መልስ ሊሰጠን የሚችል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብሩህ ሆኖ ወደ አዕምሮአችን ብቅ ይላል። ይሄ «የእግዚአብሔር ቃል (ሬማ) እንደ ቀስት በወቅቱ የተወረወረ የመንፈስ ሰይፍ ነው። «የመንፈስ ሰይፍ» የተባለበት ምክንያት ምንጩ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን፥ መንፈስ ቅዱስ በአስፈላጊው ወቅት ያመጣውና ፍጹም ብርቱ ያደረገው መልዕክት በመሆኑ ነው። ተስፋ ሊያስቆርጠን ለመጣው ሰይጣን መልስ ይሰጣል።

ለመከላከልና ለማጥቃት የተሰጠን የጦር መሣሪያ «የመንፈስ ሰይፍ» የተባለው ብቻ ነው። መከላከል ብቻ ሳይሆን ጥቃትም በጠላት ላይ ያደርሳል። የሰይጣንን ውሸት ከእኛ ሕይወት ብቻ ሳይሆን ከሌሎችም ሕይወት ያጠፋል። ለክርስቲያን ትክክለኛ የማጥቂያ መሣሪያው «የእግዚአብሔር ቃል» ነው። ለእግዚአብሔር ቃል ማንም ጠበቃ ሊቆምለትና ሊከላከልለት አይገባም፤ አማኝ ያለበት ኃላፊነት ቃሉን ማወጅ ብቻ ነው። የዕብራውያን መልዕክት ጸሐፊ «የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፤

ነፍስንና መንፈስንም፣ ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፤ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል...» ይላል (ዕብ. 4:12)። የእግዚ
አብሔር ቃል ራሱን ችሎ ኃይለኛ በመሆኑ የእኛ እርዳታ አያስፈልገውም። በዘመናት በሰይጣን አነሳሽነትና ቀስቃሽነት ብዙዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥፋት ከፍተኛ ጥረት አድርገው ሳይሳካላቸው ቀርቷል። በዘመና
ችንም ቢሆን በአዕምሮ ችሎታቸው በጣም የላቁትን ሰዎች ሰይጣን በመጠቀም የእግዚአብሔርን ቃል፣ «የሰዎች ተራ ቃል» አድርጎ ለማሳ
የት፣ ያለውን ተቀባይነት ለመቀነስ፣ የረቀቀ ሥራ ሲሠራ እናያለን፤ ይሁን እንጂ አልቻለም።

እውነትን በሚያጣምም ዓለም ውስጥ «የእግዚአብሔር ቃል» እምነታችን እንዳይናጋ የሚጠብቀን ኃይል ነው። «የመንፈስ ሰይፍ» ከሁሉ በላይ ኃይልና ሥልጣን ያለው ሕያው ቃል ጥቃት ሲደርስብን የሚከላከልልን የጦር መሣሪያ ነው። ይሄ «የመንፈስ ጦር» ምን ያህል ጊዜ እውነት ከሚመስል አሳሳች ትምህርትና ፍልስፍና ተከላክሎ እንዳዳነን ብዙዎቻችን በመንፈሳዊ ሕይወት ልምምዳችን ውስጥ አይተ
ነዋል። አንዳንድ ፍልስፍናዎችና የሕይወት ልምምዶች፣ ብዙዎች ስለሚከተሉአቸውና እንዲሁም በጣም እውነት ስለሚመስሉ፣ ተሳስተን ከመስመር ልንወጣ ጥቂት ሲቀረን፣ ይሄ «የመንፈስ ሰይፍ» ምን ያህል እንደጠበቀን ብዙዎቻችን እንመሰክራለን። በዚህ ዓለም ላይ ብዙ እውነት የሚመስሉ አሳሳች ነገሮች ስላሉ፣ ምንም ያህል «በአስተሳሰባችን የበሰልን ነን፤ ነገርን ማጣራትና መመርመር እንችላለን» ብንልም፣ የሰይጣንን ውሸት ለመለየት በአዕምሮ ችሎታችን በጣም ውስን ስለ
ሆንን፣ ያለ ቃሉ በቀላሉ ተሰናክለን እንወድቃለን።

አንዳንድ ጊዜ «የመንፈስ ሰይፍ» መሸነፍ ሊደርስብን ትንሽ ሲቀረን፣ እግዚአብሔር ሰይፉን በእጃችን በአስፈላጊው ወቅት ቶሎ ያስጨብጠናል። ለምሳሌ፣ ንዴታችንን መቆጣጠር አቅቶን ለረጅም ዘመን የምናዝንበትንና የምንጸጸትበትን መጥፎ ድርጊት እንዳንፈጽም፣ «የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሠራም» (ያዕቆብ 1፡20) በማለት ያስቆመናል፤ ምላሳችን ክፉ እንዳይናገር ይገታዋል። የእግዚ
አብሔር መንፈስ ትክክለኛውን ቃል በአስፈላጊው ወቅትና ሁኔታ ላይ ሆነን ወደ አዕምሮአችን ሲያመጣው፣ ወይንም የመንፈስ ሰይፉን በእጃችን ሲያስጨብጠን፣ የእኛ የክርስቲያኖች ድርሻ ምን ይሆን? ድርሻ
ችን እንደ ቃሉ እንደሚነግረን መጠንቀቅ፣ መታዘዝና እንዲሁም «እምቢ» ማለት ለሚገባን ጥያቄ ሁሉ «እምቢ» ማለት ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ ቃሉን ወደ አዕምሮአችን ሲያመጣው ለዓላማ ነውና በቀላሉ ችላ አንበለው። እዚህ ላይ አንድ መጠንቀቅ የሚገባን ነገር አለ። ይኸውም፣ ሰይጣንም በበኩሉ የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅስ ያለአግባብ የሚጠቀስበት ጊዜ አለ። ይህንን ዘዴውን በኢየሱስ ላይም ተጠቅሞበታል። «ይጠበቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል፤ እግርህንም በድንጋይ ከቶ እንዳትሰናከል በእጃቸው ያነሡሃል ተብሎ

ተጽፎአልና» (ሉቃስ 4:11) በማለት ሲጠቅስበት እናያለን። በዚህም ኢየሱስ አልተሞኘለትም። እኛም በዚህ ዓይነት የሰይጣን ተንኮል እንዳንሞኝ፥ አንዱን ጥቅስ ከመቀበላችን በፊት ከሌላው ጥቅስ ጋር እናመሳክረው።

ኢየሱስ ይህን «የመንፈስ ሰይፍ» ጥሩ አድርጎ ሲጠቀምበት እናያለን። «አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ እስቲ እነዚህን ድንጋዮች እንጀራ ሁኑ ብለህ እዘዝ» ሲለው፥ «ሰው በእግዚአብሔር ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል» (ሉቃስ 9:1-13) በማለት እየደጋገመ ቃሉን ሲጠቅስለት እናያለን። ይህንን «የመንፈስ ሰይፍ» ለመጠቀም እንድንችል ቃሉን እንደሚገባ ማወቅ ይገባናል። ቃሉንም ስንጠቅስበት ጠላታችን ሰይጣን በቀላሉ አይሸሽም። የቃሉን እውነተኛነት እንድንጠራጠር በማድረግ ሊዋጋን ይጥራል። ስለዚህ ከክርስቶስ ጋር በመጣበቅ ኃይላችንን ማጠናከር ይገባናል።